

# የአዲስ ኪዳን መክፈቻ

[illegible] BROOKS FOUNDATION, INC.
[illegible]
[illegible] TEXAS [illegible], USA

ለመሠረታዊ ደረጃ

መግቢያ


የወንጌሎች መግቢያ - ትምህርት 1

ማቴዎስ ወንጌል - ትምህርት 2-5

ማርቆስ ወንጌል - ትምህርት 6-11

ሉቃስ ወንጌል - ትምህርት 12-16

ዮሐንስ ወንጌል - ትምህርት 17-22

ሐዋርያት ሥራ - ትምህርት 23-26

ሮሜ - ትምህርት 27-32

1ኛ-2ኛ ቆሮንቶስ - ትምህርት 33-42

ገላትያ - ትምህርት 43-47

ኤፌሶን/ቈላስይስ/ፊልጵዩስ - ትምህርት 48-56

1ኛ-2ኛ ተሰሎንቄ/1ኛ-2ኛ ጢሞቴዎስ/ቲቶስ - ትምህርት 57-66

ፊልሞን/ዕብራውያን - ትምህርት 67-73

ያዕቆብ/1ኛ-2ኛ ጴጥሮስ/1ኛ-2ኛ-3ኛ ዮሕንስ - ትምህርት 74-82

ዮሐንስ ራእይ - ትምህርት 83-88

# የአዲስ ኪዳን መክፈቻ

፩

NEW TESTAMENT INTRODUCTION

SIM PRESS
1984

# አዲስ ኪዳን መክፈቻ

## መቅድም

ይህ የማስተማሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው መምህራን ማድረግ የሚገባቸውን ዝግጅት ለማስቀረት ሳይሆን ለመቀነስ ታስቦ ነው። ስለዚህ ምንም ተጨማሪ ዝግጅት ሳያደርግ ይህንን መጽሐፍ ብቻ ጨብጦ የሚያስተምር መምህር ተማሪዎችን ይበበድላል

አንድ ካርታ የሚያጠና ሰው ተዘዋውሮ ሥፍራዎቹን የመመልከት ዕድል ካላገኘ ጥናቱ አሰልቺ ነው፤ ቁልፍ የያዘ ሰው ቤቱን ከፍቶ መግባት ካልቻለ ምንም አይጠቅመውም፤ እንዲሁም ሥጋ የሌለበት አጥንት እጅግም አይጣፍጥም። የአዲስ ወይም የብሉይ ኪዳን መክፈቻ ትምህርት ከበድ የሚል ስለሆነ ብዙ መምህራን ሊያስተምሩት አይፈልጉም። ብዙ ተማሪዎችም በቀላሉ መረዳት አይችሉም ይሆናል። ነገር ግን በማንኛውም ወቅት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ ከሆነ እጅግ ጣፋጭና ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

መምህሩ የተማሪውን መጽሐፍ፥ የራሱን ማስተማሪያና መጽሐፍ ቅዱስን አቀነባብሮ በማዘጋጀት ትምህርቱን ማቅረብ ይኖርበታል።

## ማሳሰቢያ

1. ተማሪዎች ቀደም ብለው ከትምህርት ክፍለ ጊዜ በፊት የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ አንብበው መምጣት ይገባቸዋል። መምህሩም ወደ ክፍል ከመግባቱ በፊት ሊጠቅሳቸው የሚፈልጋቸውን ጥቅሶች መርጦ ማዘጋጀት ይኖርበታል።
2. ተማሪዎች የመጽሐፉ ጠቅላላ ዓላማ ምን እንደሆነ ካልተረዱ መምህሩ ማስተማር ከመጀመሩ በፊት የሚያስተምረውን መጽሐፍ ለምሳሌ የማቴዎስ ወንጌልን በሙሉ አዘጋጅቶ መቅረብ አለበት።
3. ክለሳ ለተማሪዎች በጣም አስፈላጊ ስለሆነ መምህሩ ከምንባብ ጋር የግድ ተጨማሪ የቤት ሥራ መስጠት አለበት።
4. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ 88 ትምህርቶች ተዘጋጅተው ቀርበዋል። በየሳምንቱ ሦስት ሦስት ትምህርቶች እንድታስተምሩ ታስቦ ለ30 ሳምንታት የታቀደ ነው። ትምህርቶቹ ምንም ከባድ ቢሆኑም እንኳ በደንብ አቀነባብራችሁ ካዘጋጃችሁ ለራሳችሁና ለተማሪዎቻችሁ እጅግ ጣፋጭና ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። እንግዲህ በዚህ መንገድ የምትጠቀሙ ከሆነ ለጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓይነተኛ መሠረት ትጥላላችሁ። ተማሪዎቻችሁም በአገልግሎታቸው ዘመን ሁሉ ያመሰግኑአችኋል።

## የአዲስ ኪዳን አመጣጥ ቅደም ተከተል ሰንጠረዥ

| ወቅት | ቀን | ክንውን | ታሪክ | የጽሑፍ ስርጭት |
|---|---|---|---|---|
| መንደርደሪያ | 6 ዓክልበ | የኢየሱስ መወለድ | | |
| | 4 ዓክልበ | የሄሮድስ መሞት | | |
| 6 ዓክልበ 29 ዓ.ም | | | | |
| | | | ማቴዎስ | |
| | | | ሉቃስ | |
| | 26 ዓ.ም. | ጥምቀት | ማርቆስ | |
| | 29 ዓ.ም. | ስቅለት | ዮሐንስ | |
| <u>ማስፋፊያ</u> | | | | |
| 29-60 ዓ.ም. | 31-33 ዓ.ም. | የጳውሎስ መለወጥ | | |
| | 45 ዓ.ም. | | የሐዋ. | ያዕቆብ |
| | 49 ዓ.ም. | የኢየሩሳሌም ጉባዔ | | ገላትያ /ማርቆስ/ |
| | 52 ዓ.ም. | | | 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ማቴዎስ /?/ |
| | 54 ዓ.ም. | | | 1ኛ ቆሮንቶስ |
| | 55 ዓ.ም. | | የጳውሎስ መልዕክቶች | 2ኛ ቆሮንቶስ |
| | | የመጀመሪያው የጳውሎስ | | ሮሜ |
| | 56 ዓም. | መታሠር | | ቆላስይስ+ ኤፌሶን ፊልሞና |
| | 60 ዓ.ም. | | | ፊልጵስዩስ ሉቃስ-የሐዋ. |
| <u>ማጠናቀሪያ</u> | | ሁለተኛው የጳውሎስ | | 1ኛ ጢሞቴዎስ |
| | 68 ዓ.ም. | መታሠር | | ቲቶ |
| | | | | 1ኛ ጴጥሮስ |
| 60-100 ዓ.ም. | | | | 2ኛ ጢሞቴዎስ |
| | 70 ዓ.ም. | የኢየሩሳሌም መፈራረስ | | 2ኛ ጴጥሮስ |
| | | | | ማርቆስ |
| | | | | ዕብራውያን |
| | | | | ይሁዳ |
| | | | አጠቃላይ መልዕክቶች | |
| | 85 ዓ.ም. | | | 1+2+3ኛ ዮሐ. ዮሐ. |
| | 95 ዓ.ም. | | ራዕይ | ራዕይ |


ጳለስጤና
በክርስቶስ ጊዜ
ሲዶና
ጢሮስ
ፊኒሺያ
የአርሞንኤም
ተራራ
የሜሮም ባሕር
ኮራዚን
ቅፍርናሆም
መቅደላ
ጥብርያዶስ
ቃና
የገሊላ ባሕር
ናዝሬት
ናይን
ገሊላ
ታላቁ ባሕር
ቂሣርያ
የዮርዳኖስ ወንዝ
ዐሥር ከተማ
ሰማርያ
ሰማርያ
ሲካር
ሴኬም
የገሪዚም
ተራራ
ፔሬያ
ኢዮጴ
ቤቴል
ቢታንያ
ይሁዳ
ኤማሁስ
ኢየሩሳሌም
ቢታንያ
የደብረዘይት ተራራ
ቤተልሔም
ጋዛ
ኬብሮን
የጨው ባሕር
የይሁዳ በረሃ
ቤርሳቤ

# አዲስ ኪዳን

# ትምህርት አንድ

## የአዲስ ኪዳን ጠቅላላ መግቢያ

አዲስ ኪዳንን የምናጠናው ለምንድነው? ለዚህ ጥያቄ ሦስት መልሶች ቀርበዋል።

1. የሕያው እግዚአብሔር መገለጥ ስለሆነ ነው። ይህ መሆኑም በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ይታወቃል። እነርሱም:-
   ሀ/ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት፤
   ለ/ ጌታችን በአይሁድ መካከል በፈጸማቸው ድርጊቶች፤
   ሐ/ የእግዚአብሔር ቃል የሰዎችን ሕይወት መለወጡ ናቸው።
2. አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነና በውስጡ የሚገኙት ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ስለተብራሩልን ነው።
3. አዲስ ኪዳን ለሰው ልጆች ፍላጐት የእግዚአብሔር መልእክት ስለሆነ ነው። ይኸውም:-
   ሀ/ ሰው ለጽድቅና ከኃጢአት ለመንጻት ያለውን ጥማት ያረካል።
   ለ/ ሰው በዚህ ዓለም ስለ ዕለት ኑሮው የሚያስፈልጉትን ነገሮች ያቀርብለታል።

አዲስ ኪዳን በመጀመሪያ የተጻፈው በምን ቋንቋ ነበር? በዚያ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች የዘወትር መገልገያ በነበረው በግሪክ ቋንቋ ነበር። በዚያ ዘመን ይኖሩ የነበሩት አይሁድ ይነጋገሩበት የነበረው ቋንቋ ግሪክ ነበር። ከሉቃስ በስተቀር የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በሙሉ አይሁዶች ነበሩ። ሆኖም ጽሑፋቸውን የጻፉት ብዙዎች ሊያነቡት እንዲችሉ በማሰብ በግሪክ ቋንቋ ነበር።

አሁን በአዲስ ኪዳን ውስጥ የምናገኛቸውን ጽሑፎች ሰብስበው በአንድ ላይ ለመጠረዝ የጥንቲቷ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በሚከተሉት ሁለት መመሪያዎች ተጠቀሙ።

1. ጸሐፊዎች ሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች መሆን ነበረባቸው።
2. በዚያን ዘመን በነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቶ ትምህርት ለመቅሰም የሚነበቡ መሆን ነበረባቸው።

ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጽሑፎች የኢየሱስን ቃላት፥ ሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች የጻፉአቸውን የኢየሱስን ሥራዎች የሚተነትኑ ጽሑፎች ናቸው። ለምሳሌ:- ጳውሎስ፥ ሉቃስ፥ ጴጥሮስ፥ ዮሐንስ እና ማርቆስ።

የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ዘወትር ለመንፈሳዊ ጥቅም በቤተ ክርስቲያን ይነበቡ የነበሩት ናቸው። የእነዚህም የመጀመሪያ ረቂቆች እርግጠኛነት እስከ አሁን ድረስ በሚገኙ በእጅ በተጻፉት ጽሑፎች ተረጋግጦአል። በአሁኑ ወቅት 4500 የሚያህሉ የአዲስ ኪዳን የእጅ ጽሑፍ ብራናዎች ይገኛሉ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት የመጻሕፍት ዝርዝር እንደሚከተሉት ናቸው።

1. አራት ወንጌሎች፡- እነዚህ ጌታችን በምድር ላይ በተመላለሰበት ወቅት የነበረውን ሕይወት፥ ትምህርትና አገልግሎት ያቀርቡልናል።
2. የሐዋርያት ሥራ፡- ይህ ታሪካዊ መጽሐፍ ሲሆን በተጨማሪ ጌታችን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የቀጠለውን ሥራ እያይዞ ያቀርብልናል።
3. መልእክቶች ወይም ደብዳቤዎች፡-

ሀ/ የጳውሎስ መልዕክቶች፡-

1. ስድስት የጉዞ መልዕክቶች፡- ገላትያ፥ 1 እና 2 ተሰሎንቄ፥ 1 እና 2 ቆሮንቶስና ሮሜ።
2. አራት የእስር ቤት መልዕክቶች፡- ኤፌሶን፥ ቆላስይስ፥ ፊሊሞና እና ፊልጵስዩስ።
3. ሦስት ምክር አዘል መልዕክቶች፡- 1 እና 2 ጢሞቴዎስ እና ቲቶ።

ለ/ አጠቃላይ መልዕክቶች፡- እነዚህ በተለይ ለአንድ ቤተ ክርስቲያን ወይም ግለሰብ የተጻፉ አይደሉም! 1፥ 2 እና 3 ዮሐንስ፥ 1 እና 2 ጴጥሮስ፥ ዕብራውያንና ያዕቆብ ናቸው።

ሐ/ ትንቢት የራዕይ መጽሐፍ።

## የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅደም ተከተል

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አቀማመጥ በተጻፉበት ዘመን ቅደም ተከተል እንዳልሆነ ግለጽ ነው። የመጻሕፍት አገጣጠም አዲስ ኪዳንንና ብሉይ ኪዳንን በሚያገናኝ ቅደም ተከተል መሆኑ ሲታይ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎትና ሕይወት በሐዋርያት አማካይነት እንዴት እንደቀጠለ ለመግለጥ ተቀነባብሮአል። ለምሳሌ፡- ማቴዎስ ኢየሱስን የሚያቀርበው የብሉይ ኪዳንን ትንቢት ፈጻሚ አድርጎ ነው። የማቴዎስ ወንጌል ብሉይንና አዲስን የሚያቀራኝ ስለሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አቀማመጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው።

የሐዋርያት ሥራ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የጀመረውን ተግባር በሐዋርያቱ አማካይነት የሚቀጥል መሆኑን ስለሚገልጥ ከወንጌሎች በኋላ ተጨመረ! የሐዋ/ሥራ 1፡1 በተጨማሪ ደግሞ ቀጥለው የሚገኙትን መጻሕፍት የጻፉትን ሰዎች ያስተዋውቃል። የራዕይ መጽሐፍ በመጨረሻ ላይ ይገኛል! እርሱም፡- ስለ ደኅንነት፥ ፍርድና የእግዚአብሔር ድል አድራጊነት የተሰጡትን መልእክቶች በማቅረብ ጥሩ መደምደሚያ ይሰጣል።

## አዲስ ኪዳን የተጻፈበት ዘመን

አይሁዶች በሮም መንግሥት ላይ ስላመፁ በ70 ዓ.ም. የኢየሩሳሌም ከተማ ቲቶ በተባለ የጦር ጄኔራል ትዕዛዝ ፈረሰች። ይህ ዘመን ለአይሁዶችና ለክርስቲያኖች እጅግ የከፋ የመከራ ወቅት ነበር። አዲስ ኪዳን በሙሉ ከ70 ዓ.ም. በፊት ማለት ሐዋርያት ይኖሩ በነበረበት ዘመን ሳይጻፉ አልቀሩም። አንዳንዶች ከ70 ዓ.ም. ተጽፈው ይሆናል።

## ጥያቄዎች

**መልሶቹ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተሰጥተዋል።**

1. አዲስ ኪዳን የተጻፈበት ምክንያት ምንድነው? ሦስት መልሶች ስጡ።
2. አዲስ ኪዳን ለአይሁዶች ብቻ የተጻፈ አለመሆኑን በምን እናውቃለን?
3. የቀድሞ አማኞች የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ሰብስበው በአንድ ላይ እንዲያደርጉ የረዱአቸው ሁለት መመሪያዎች ምንና ምን ናቸው?
4. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ትክክለኛነት በዘመናችን እንዴት ሊረጋገጥ ቻለ?
5. የሚበዙት የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉት ለማን ነበር?
6. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከተጻፉበት ዘመን ቅደም ተከተል ይልቅ አሁን በሚገኙበት አቀማመጥ የተደረጉበት ምክንያት ምንድነው? ሦስት ምሳሌዎች ስጡ።
7. የጳውሎስ ያልሆኑት መልዕክቶች የእርሱ ከሆኑት የሚለዩት በምንድነው?

## የቤት ሥራ

1. ምንም ችግር ሳይገጥማችሁ የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት በቶሎ መጥቀስ እስከምትችሉ ድረስ ስም ስማቸውን አጥኑ። አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሚያጠናውን መጽሐፍ በፍጥነት ማውጣትና የእግዚአብሔር ቃል በሚሰበክበት ጊዜም በቀላሉ ሊከታተል የሚችለው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።
2. የማቴዎስ ወንጌል 1-7 አንብባችሁ በውስጡ የሚገኙትን ዋና ዋና ታሪኮች በአእምሮአችሁ ያዙ።

## ምክር ለመምህሩ

በእያንዳንዱ ጥናት ላይ ከተወሰነለት ጊዜ በላይ አያጥፉ። ይህ ትምህርት የአዲስ ኪዳን አጠቃላይ የሆነ ጥናት ነው እንጂ ጥቅስ በጥቅስ የሚጠና ጥናት አይደለም።

# ትምህርት ሁለት

## የአራቱ ወንጌሎች መግቢያ

1. ማቴዎስ ኢየሱስን ንጉሥ ወይም መሢህ አድርጎ ያቀርበዋል። ይህ ወንጌል በተለይ ለአይሁዶች የተጻፈ ቢሆንም ለሰው ሁሉ የሚሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው።
2. ማርቆስ ኢየሱስን አገልጋይ አድርጎ ያቀርበዋል። ማርቆስ ምናልባት ይህንን ወንጌል የጻፈው ሮማውያንን እያሰበ ሳይሆን አይቀርም።
3. ሉቃስ ኢየሱስን ፍጹም ሰው አድርጎ ያቀርበዋል። ሉቃስ ምናልባት ይህንን ወንጌል በሚጽፍበት ጊዜ ግሪኮችን በአእምሮው ውስጥ ይዞ ሳይሆን አይቀርም።

4. ዮሐንስ ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎ ያቀርበዋል። ይህ ወንጌል የተጻፈው ለሚያምኑበትና ሌሎችም ደግሞ እንዲያምኑበት ጭምር ነው፤ ዮሐ.20፡31።

# የማቴዎስ ወንጌል መግቢያ

## የወንጌሉ መሠረታዊ ነጥቦች

1. ጸሐፊው ሐዋርያው ማቴዎስ ሲሆን በተጨማሪ ሌዊ ተብሎ ይጠራል፤ ሉቃ.5፡29።
   ሀ/ የእልፍዮስ ልጅ ነበር፤ ማቴ.2፡14-15።
   ለ/ ቀረጥ ሰብሳቢ አይሁድ ነበር፤ ማቴ.9፡9።
   ሐ/ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነበር፤ ማቴ.10፡3፤ የሐዋ/ሥራ 1፡13።
2. መቼ እንደተጻፈ በትክክል አይታወቅም። ነገር ግን በ50 እና በ80 ዓ.ም. መካከል ሳይሆን አይቀርም።

የመጽሐፉ ዓላማዎች ከዚህ በታች የሚቀርቡት ናቸው:-

1. ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ የእርሱን ሥራዎችና ትምህርት በአጭሩ እንዲያውቁ ነበረ።
2. አማኞችን ለመርዳት ነበረ፤ እነርሱም ደግሞ በተራቸው ያላመኑትን በተለይ ከአይሁድ ወገን የሆኑትን እንዲያስተምሩ ለማድረግ ነበረ። ይኸውም:-
   ሀ/ ብሉይ ኪዳን ስለ መሲሁ የነገራቸው ትንቢቶች በኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደተፈጸሙ ያሳያል፤ ለምሳሌ:-
      1. ንጉሣዊውን የትውልድ ሐረግ፤ ማቴ.1፡18-28።
      2. የተወለደበትን ሥፍራ፤ ማቴ.2፡1፤ ሚክ.5፡2።
   ለ/ ክርስቶስ እንዴት የቤተ ክርስቲያንን መሠረት እንደጣለ ያሳያል፤ ማቴ.16፡18፤ 18፡17።
   ሐ/ አይሁዶች ለመካድ የሚጥሩትን የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድና ትንሣኤ አስፈላጊነት ያስተምራል፤ 27፡62-66፤ 28፡11-25።

የማቴዎስ ወንጌልን ልዩ የሚያደርጉት ባሕርያት ከዚህ በታች ቀርበዋል:-

1. የኢየሱስን የዘር አቆጣጠር ወደ ኋላ ተመልሶ በአይሁዶች ዘመን ትልቅ ሥፍራ ከሚሰጠው ከአብርሃም ይጀምራል፤ ማቴ.1፡1። ኢየሱስ በወንድ የዘር ሐረግ ከዳዊት በኩል የንጉሥ ትውልድ መሆኑን ያቀርባል።
2. የኢየሱስ አገልግሎት ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች ብቻ መሆኑን ይገልጸው ማቴዎስ ብቻ ነው፤ ማቴ.15፡24። በተጨማሪ ሐዋርያቱ የእስራኤልን ቤት እንዲያገለግሉ ኢየሱስ ማዘዙን ይገልጻል፤ ማቴ.10፡5-6።
3. ኢየሱስ በአይሁድ ሃይማኖት መሪዎች ላይ በጣም የጠነከረ ፍርድ እንደተናገረባቸው ያወሳል፤ ማቴ.23፡1-39።
4. እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ለአሕዛብ መንገድ እንደሚከፍትላቸው ይገልጻል፤ ማቴ.12፡18፤ 21።
5. በሌሎቹ ወንጌሎች ያልተጠቀሱ ሁለት ተአምራት አስፍሯል።
   ሀ/ በአሳ አፍ ውስጥ የተገኘውን ሳንቲም ተአምር፤ ማቴ.17፡24-27።
   ለ/ የቅዱሳን ከሞት የመነሣትን ተአምር፤ ማቴ.27፡51-53።
6. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ሰፊ ትምህርት ያቀርባል፤ ማቴ.24።

7. ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የተገኘው በማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው፤ ማቴ.16፥18፤ 18፥17።
8. ሐዋርያት ወደ ዓለም ሁሉ ሄደው አሕዛብን ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ ኢየሱስ የሰጣቸውን ትእዛዝ ማቴዎስ ያስረዳል፤ ማቴ.28፥19-20።
9. ኢየሱስ በእግዚአብሔር የአባትነት ባሕርይ ላይ ትኩረት እንደሰጠ ማቴዎስ ያስገነዝባል።

## ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ ማን ነበር?
2. ማቴዎስ በተለይ ለአይሁዶች የጻፈው ለምንድነው?
3. የኢየሱስን ሞት በሚመለከት ረገድ አይሁድ ሊክዱ የሚሞክሩአቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
4. የማቴዎስን ወንጌል ከሌሎቹ ወንጌሎች የተለየ ከሚያደርጉት፥ ሦስት ወይም ከዚህ በላይ የሆኑትን ባሕርያት ዘርዝሩ።

## የቤት ሥራ

ከነገው ትምህርት በፊት ማቴ.8፥14 አንብቡ።

## ምክር ለመምህሩ

ተማሪዎቹ ማንበብ እንዳይሰለቹ ያነቃቁአቸው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተመደበለትን ጊዜ ብቻ ይጠቀሙ። በማቴዎስ ወንጌል ጥናት ማብቂያ ላይ ክለሳ ይኖራል፤ ስለዚህ ለክለሳ ሌላ የትምህርት ጊዜ አያጥፉ።

# ትምህርት ሦስት

## የማቴዎስ ወንጌል አጠቃላይ አስተዋፅዖ

ወንጌሉ ሦስት ታላላቅ ክፍሎች አሉት። በእያንዳንዱ ዋና ዋና ክፍል ሥር የሚገኙትን ነጥቦች በማስተዋል ተመልከቷቸው።

1. የንጉሡ መምጣትና የሚያደርገው ዝግጅት፡- 1፥1-4፥12።
   ሀ/ መወለዱ፤ 1-2።
   ለ/ የእርሱ መልእክተኛ ማለት መጥምቁ ዮሐንስ፤ 3፥1-12።
   ሐ/ ጥምቀቱ፤ 4፥1-11።
2. የንጉሡ አገልግሎት፡- 4፥13-16፥21።
   ሀ/ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች» እያለ ያውጃል፤ 4፥17።
   ለ/ የተራራውን ስብከት ይሰብካል፤ 5-7።
   ሐ/ የታመሙትን ይፈውሳል፤ 8፥1-9፥34።
   መ/ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለአገልግሎት ይልካቸዋል፤ 9፥35-10፥42።

ሠ/ ታላቅነቱን ይገልጻል፤ 11-12።

ረ/ ስለ መንግሥተ ሰማያት ያቀረባቸው ምሳሌዎች፤ 13፡1-52።

3. የንጉሡ መጠላትና መከራ፡- 13፡53-28፡20።

ሀ/ በናዝሬት የደረሰበት ተቃውሞ፤ 13፡53-58። በአካባቢው ይኖሩ የነበሩት ሰዎች በመልእክቱና በተአምራቱ የተገረሙ ቢሆኑም እንኳ የአገራቸው ሰው መሆኑና ቤተሰቡን ያውቁ ስለ ነበር አልተቀበሉትም።

ለ/ የመጨረሻ አገልግሎቱና ትምህርቱ፤ 14፡1-20፡16።

1. ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ መሰከሩ፤ 16፡13-16።
2. ኢየሱስ የሚሞትበትን ዓላማ መግለጽ ይጀምራል፤ 16፡21።

ሐ/ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞና ለከተማይቱ የሰጣት ማስጠንቀቂያ፤ 20፡17-22፡46።

መ/ ስለ ፍርድ ትንቢት ይናገራል፤ ያስጠንቅቃል፤ 23-25።

ሠ/ ሥቃዩና ሞቱ፤ 26-27።

ረ/ ትንሣኤው፤ 28።

ኢየሱስ በመሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነት ካጣ በኋላ እንኳ እስከ ሞቱ ድረስ አገልግሎቱን የቀጠለ መሆኑን አስተውሉ። ስለዚህ ክፍል ለ እና ሐ አይነጣጠሉም።

ማቴዎስ የኢየሱስን ታሪክ እንዴት አድርጎ እንደገለፀው ከዚህ በታች የሚገኘው ንድፍ ያመለክተናል። የኢየሱስ ዝና እስከ 13፡53-58 ድረስ እየጨመረ እንደሄደ ንድፉ ያሳየናል። በ13፡53-58 ላይ ኢየሱስ በወገኖቹ እንደተጠላ እንመለከታለን። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኢየሱስ ዝና ይቀንሳል። ወደ ኢየሩሳሌምም ከወጣ በኋላ በመስቀል ላይ ይሰቀላል፤ ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ይነሣል።

የወንጌል ይዘት በጭሩ




በማቴዎስ ውስጥ 15 ተአምራትና 20 ምሳሌዎች ይገኛሉ።

## በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. 1፡1 የዳዊትና የአብርሃም ልጅ የሆነው የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ። የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የሚለው አጠራር ለአይሁዶች የተለየ ትርጉም ነበረው።
2. 2፡2 ከምሥራቅ የመጡ ጥበበኞች የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው? ብለው ጠየቁ። ስለ መሢሁ የትውልድ ሥፍራ የተነገረው ትንቢት መፈጸሙን ይጠቁማል፤ ሚክ.5፡2።
3. 28፡18 «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።» በሰማይና በምድር የሚገኙት ሥልጣናት ሁሉ የኢየሱስን የንጉሥነት መብት ያውጃሉ። እንግዲህ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ እያስተማራችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው» በማለት ሐዋርያትን አዘዛቸው።

## በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ተፈጸመ፡- 14 ጊዜ ይገኛል። 4. የዳዊት ልጅ፡- 14 ጊዜ ይገኛል።
2. ጻድቅ፡- 9 ጊዜ ይገኛል። 5. የዘመን ወይም የዓለም መጨረሻው፡-
3. መንግሥት፡- 51 ጊዜ ይገኛል። 13 ጊዜ ይገኛል።
4. የዳዊት ልጅ፡- 14 ጊዜ ይገኛል።
5. የዘመን ወይም የዓለም መጨረሻ 13 ጊዜ ይገኛል።

በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የቀረቡትን የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ አወራረድ እንመልከት። በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተገለጸው በወንዱ በኩል የሚመጣው ሕጋዊ የዘር አቆጣጠር ሲሆን በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ደግሞ በማርያም በኩል የሚመጣው እውነተኛ የሥጋ ዝምድና የዘር አቆጣጠር ነው። ከዚህ በታች የሚገኘው ንድፍ ይህንኑ ሁኔታ ያሳያል።




## ጥያቄዎች

1. የማቴዎስን ወንጌል ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ግለጹ።
2. በገሊላ የሚኖሩት የኢየሱስ ወገኖች መሲህነቱን እንዳይቀበሉ ያደረጋቸው ችግር ምን ነበር?
3. ማቴዎስ ያቀረበው የዘር አቆጣጠር ለአይሁዶች ምን የተለየ ትርጉም አለው?
4. ሦስቱ ቁልፍ ጥቅሶች ማለት 1፡1፤ 2፡2ና 28፡18-20 ስለ ኢየሱስ ማንነት ምን ምን ያሳያሉ?
5. «ተፈፀመ» «የዳዊት ልጅ» እና «መንግሥት» የሚሉት ሦስት ቃላት በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታዩ ናቸው። የእነዚህ ቃላት ጥቅም ምን እንደሆነ ተወያዩበት።

## የቤት ሥራ

ማቴዎስ 15-21 አንብቡ።

# ትምህርት አራት

ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ካስተማራቸው ትምህርቶች ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:-

1/ አምስት ስብከቶች ወይም ንግግሮች፤ እነርሱም ከዚህ በታች ቀርበዋል።
   ሀ. የተራራው ስብከት፤ 5-7።
   ለ. ለአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ትዕዛዝ ሰጠ፤ 10።
   ሐ. የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌዎች 13፡1-52።
   መ. የታላቅነትና የይቅርታ ትርጉም፤ 18።
   ሠ. የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ 24-25።
2/ እግዚአብሔር በሰዎች መካከል እንደሚገኝ በሰጠው ተስፋ ማቴዎስ ወንጌሉን ይጀምርና በዚሁ ነጥብ ይደመድመዋል።
   ሀ. እግዚአብሔር ከኛ ጋር፤ 1፡23።
   ለ. እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ፤ 28፡20።

የማቴዎስ ወንጌል ይዘት ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው ነው። ይህ ዝርዝር ለጥናት የቀረበ ሳይሆን ወደፊት ተማሪዎች ሲያስተምሩ እንዲጠቀሙበት ነው።

1/ የኢየሱስ ሥልጣንና የበላይነት:-
   ሀ. በሕግ ላይ፤ 5፡21-22፤ 27-28።
   ለ. በሰንበት ላይ፤ 12፡8።
   ሐ. በነቢያት ላይ፤ 12፡41።
   መ. በቤተ መቅደሱ ላይ፤ 12፡5-6።
   ሠ. ከንጉሥ ሰሎሞን የሚበልጥ ነው፤ 12፡42።
2/ በኢየሱስ የተፈፀሙት ትንቢቶች የሚከተሉት ናቸው:-
   ሀ. የኢየሱስ ልደት:- ማቴ. 1፡22-23፤ ኢሳ. 7፡14ን ይፈጽማል።
   ለ. ኢየሱስ የተወለደበት ሥፍራ:- ማቴ. 2፡6፤ ሚክ. 5፡2ን ይፈጽማል።
   ሐ. የኢየሱስ ከግብፅ መመለስ:- ማቴ. 2፡15፤ ሆሴዕ 11፡1ን ይፈጽማል።
   መ. የሕፃናት መገደል በቤተልሔም:- ማቴ. 2፡15፤ ኤር. 31፡ 15ን ይፈጽማል።
   ሠ. አዋጅ ነጋሪው ወይም መልእክተኛው:- ማቴ. 3፡3፤ ኢሳ. 40፡3ን ይፈጽማል።
   ረ. የኢየሱስ አገልግሎት:- ማቴ. 4፡15-16፤ ኢሳ. 42፡6-7ን ይፈጽማል።
   ሰ. የኢየሱስ የፈውስ አገልግሎት:- ማቴ. 8፡17፤ ኢሳ. 40፡6-7ን ይፈጽማል።
   ሸ. ኢየሱስ እንደ የእግዚአብሔር አገልጋይ:- ማቴ. 12፡18-21፤ ኢሳ. 42፡1-4ን ይፈጽማል።
   ቀ. ኢየሱስ በምሳሌ ያስተማረው ትምህርት:- ማቴ. 13፡35፤ መዝ. 76/77/፡2ን ይፈጽማል።

በ. የኢየሱስ ራሱን ለእስራኤላውያን መስጠት፡- ማቴ. 21፡4-5፤ ዘካ. 9፡9ን ይፈጽማል።

ተ. የኢየሱስ መታሰር፡- ማቴ. 26፡26፤ ኢሳ. 50፡6ን ይፈጽማል።

ቸ. የኢየሱስ መሰደብና መሳለቂያ መሆን፡- ማቴ. 26፡66ና 27፡39-44፤ ኢሳ.53፡ 2-11ን ይፈጽማል።

ነ. የኢየሱስ በ30 ብር መሸጥ፡- ማቴ. 27፡9፤ ኤር. 18፡1-4ንና ዘካ.11፡12-13ን ይፈጽማል።

3/ መንግሥተ ሰማያት የሚለው አጠራር ኢየሱስ ንጉሥ መሆኑን ይከሰታል።

ሀ. መጥምቁ ዮሐንስ መንግሥተ ሰማያትን አውጆአል፤ 3፡1-3።

ለ. ኢየሱስ የመንግሥተ ሰማያትን ሕግ አስተምሯል፤ 5-7።

ሐ. ኢየሱስ መንግሥተ ሰማያትን በሚመለከት ብዙ ምሳሌዎችን ተናግሯል፤ 13።

መ. ኢየሱስ ለንጉሥ የሚሰጠውን ክብር ተቀብሏል፤ 21፡8-10።

ሠ. አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በእስራኤል ላይ ከእርሱ ጋር እንደሚፈርዱ ኢየሱስ ተናግሯል፤ 19፡28።

ረ. ኢየሱስ ንጉሥ ሆኖ እስከሚመጣበት ጊዜ ድረስ ኢየሩሳሌምን ተሰናብቷታል፤ 22፡15ና 25፡31።

## ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ያስተማራቸው 5 ትምህርቶች ምን ምን ናቸው?
2. የማቴዎስ ወንጌል የሚጀምርበትና የሚደመድምበት ታላቅ ተስፋ የትኛው ነው?
3. የኢየሱስን የበላይነት ሥልጣን የሚያሳዩትን 5 ነገሮች ጥቀሱ።
4. ማቴዎስ ብዙ የተፈጸሙትን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች የሚጠቅሳቸው ለምንድነው?
5. ማቴዎስ «መንግሥተ ሰማያት» በሚለው አጠራር በብዛት የተጠቀመበት ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

ማቴዎስ 22-28 አንብቡ።

# ትምህርት አምስት

ማቴዎስ ባቀረበው ዘገባ ውስጥ በተለያዩ አቅጣጫዎች ኢየሱስ ንጉሥ መሆኑን ያሳያል። ለምሳሌ፡-

1. ማቴዎስ ወንጌል፥ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? በሚል ጥያቄ ይጀምራል፤ 2፡1-2። አይሁድ እግዚአብሔር ስለሚመጣው ንጉሣቸው ማለትም ስለ መሢሁ የሰጠውን ተስፋ ያውቁ ነበር፤ ስለዚህ መሢሁ መጥቶ ከሮም አገዛዝ ነፃ እንደሚያወጣቸው ይጠብቁና ተስፋ ያደርጉ ነበር።
2. ማቴዎስ ያቀረበው ታሪክ ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ የሚለውን ጥያቄ ባቀረበላቸው ጊዜ ነበር፡- ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ጴጥሮስ፡- አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መልስ ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የሚገለጽበት

ወቅት ገና ስላልደረሰ ለማንም ሰው እንዳይናገሩ ያስጠነቅቃቸዋል። ዝቅ ብሎ የቀረበውን ንድፍ ተመልከቱ።

3. ማቴዎስ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ ብሎ ክርስቶስ በተናገረው ቃል ወንጌሉን ይደመድመዋል። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ይህንን ሥልጣን እንደሚሰጣቸው ከነገራቸው በኋላ ሄደው አሕዛብን እንዲያስተምሩ አደራ ይሰጣቸዋል።

የሐዋርያት ታማኝነት ወንጌል ለእኔና ለእናንተ እንዲደርሰን አደረገ። ለሐዋርያት ተሰጥቶ የነበረው የክርስቶስ ሥልጣን ዛሬም የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለሆኑት አማኞች ይሰጣቸዋል።

የኢየሱስ አገልግሎት ማብቂያ




## በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ከሚገኙት ትምህርቶች አንዳንዶች የሚከተሉት ናቸው

1. አማኑኤል እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ማለት ነው፤ 1፡23። ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት ለ400 ዓመታት ያህል እግዚአብሔር በነቢያት አማካይነት ለሕዝቡ ምንም ነገር አልተናገረም።
2. ቃሉን መስማት የሚገባችሁ እንዴት እንደሆነ አስተውሉ፤ 13፡20-21። የእግዚአብሔርን ቃል አድምጦ አለመታዘዝ ይቻላል፤ ስለዚህ አማኝም እንኳ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ መስማት ይገባዋል።
3. እኛ ሳንጠይቀው በፊት እንኳ እግዚአብሔር ፍላጎታችንን ያውቃል፤ 6፡8። ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ለመሆኑና ለእኛም እንደሚያስብልን ማረጋገጫ ነው። ሆኖም የምንፈልገውን ነገር እንድንጠይቀው ይሻል፤ 7፡7፤ ሉቃስ 11፡9።
4. ደስ ይበላችሁ፤ ኃጢአተኛ የሚፀድቅበትን መንገድ እግዚአብሔር አዘጋጅቷል፤ 9፡13።
5. ስለ ክርስቶስ ነፍሱን የሚያጣ ያድናታል፤ 10፡39።
6. ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርንም ቃል በመታዘዝ ጭምር እንጂ፤ 4፡4።
7. ክርስቶስ፦ «ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁ» ብሏል፤ 18፡20። ለአምልኮና ለጸሎት ትልቅ ስብሰባ ማድረግ የሚያስፈልገን ነገር አይደለም።

8. ኢየሱስ ቀድሞ የኢየሩሳሌምን ዛሬ ደግሞ የዘመኑ ሰዎችን «እሰበስባችሁ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ፤ እናንተ ግን አልወደዳችሁም» ይላቸዋል፤ 23፡37። ኢየሱስ አሁንም የዓለም ሕዝብ በሙሉ ወደ እርሱ እንዲመጣ ለማድረግ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይጥራል፤ ይጠራል ይለምናልም።
9. «የሰው ልጅ የሚመጣበትን ቀንና ሰዓት አታውቁምና እንግዲህ ንቁ» ክርስቶስ ባልታሰበ ሰዓት ይመጣል። ስለ መጨረሻው ጊዜም ብዙ ምልክቶች ሰጥቷል፤ ሁሉም ደግሞ ተፈጽመዋል፤ 25፡13። በ70 ዓ.ም. የሆነው የኢየሩሳሌም ከተማ መፍረስ የኢየሱስ ዳግም ምፅዓት ማረጋገጫ ነው። ኢየሱስ የኢየሩሳሌም ከተማ ግንብ ፈራርሶ ይወድቃል፤ እርሱም በአሕዛብ ቁጥጥር ሥር ትውላለች ብሎ ተንብዮ ነበር፤ 24፡2፤ ሉቃስ 21፡24።
10. «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» 28፡19-20። ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ለሚያምኑት ሁሉ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። ይህንን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እንገኛለን?

## ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በአገልግሎቱ ዘመን ውስጥ ስለ ሞቱ መግለፅ የጀመረው መቼ ነበረ? እስከዚያስ የቆየው ለምን ይመስልሃል?
2. አማኑኤል በተወለደበት ወቅት በምን በምን ምክንያት የተለየ ነበረ?
3. የኢየሱስ የመጨረሻ ትዕዛዝ የተሰጠው ለማን ነው? ዛሬ እንዴት ልንፈጽመው እንችላለን?

## ምክር ለመምህሩ

ዝቅ ብለው የተዘረዘሩትን አሥር ነጥቦች በደንብ አስተምረው እንደሆነና ተማሪዎች ተረድተዋቸው በአዕምሮአቸው ይዘዋቸው እንደሆነ ያረጋግጡ።

1. የማቴዎስ ወንጌል ዓላማ፤ ትምህርት 2።
2. የማቴዎስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት፤ ትምህርት 2።
3. የማቴዎስ ወንጌል ጠቅላላ አስተዋፅዖ፤ ትምህርት 3።
4. ቁልፍ ጥቅሶች፤ ትምህርት 3 በቃላችሁ አጥኑአቸው።
5. ቁልፍ ቃላት፤ ትምህርት 3።
6. በማቴዎስና በሉቃስ ወንጌሎች የቀረቡት የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ልዩነትና ምክንያቱ፤ ትምህርት 3።
7. የማቴዎስ ወንጌል የሚጀምርበትና የሚደመድምበት የተስፋ ቃል፤ ትምህርት 4።
8. የኢየሱስን ሥልጣንና የበላይነት የሚገልፁ 5 ነገሮች፤ ትምህርት 4።
9. በኢየሱስ የተፈፀሙትን ትንቢቶች አጥኑአቸው፤ ትምህርት 4።
10. የኢየሱስ አገልግሎት ሂደት፤ 16፡13-20 ንድፉ በትምህርት 5 ውስጥ ይገኛል።

# ትምህርት ስድስት

## የማርቆስ ወንጌል መግቢያ

## የመጽሐፉ መሠረታዊ ነጥቦች

ጸሐፊው ማርቆስ ነው፤ አንዳንዴ ዮሐንስ ማርቆስ ተብሎ ተጠርቷል የሐዋ.12፡12።

1. በመጀመሪያው ወንጌላዊ ጉዞ ማርቆስ ከጳውሎስና በርናባስ ጋር አብሮ ተጉዞ ነበር፤ ነገር ግን ሳይፈጽም አቋርጦ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል፤ የሐዋ. 13፡5፤ 13።
2. ማርቆስ የበርናባስ የእህቱ ልጅ ነበር፤ ቆላ. 4፡10።
3. በሁለተኛው ወንጌላዊ ጉዞ ወቅት ጳውሎስና በርናባስ በማርቆስ ምክንያት ባለመስማማታቸው ተለያይተው ነበር፤ የሐዋ. 15፡37።
4. በኋላም ማርቆስ የጳውሎስ ረዳት ሆነ፤ ፊልሞና 24፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡11።
5. ጴጥሮስ ማርቆስን «ልጄ» ብሎ ይጠራው ነበር፤ 1ኛ ጴጥ. 5፡13። የማርቆስ ወንጌል የተጻፈ በ50ና በ75 ዓ.ም. መካከል ሳይሆን አይቀርም። የፊተኛው አማራጭ ይመረጣል።

## የወንጌሉ ዓላማ

1. መልካሙን የምሥራች ማለትም የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰዎች ለማቅረብ ነው፤ 1፡1።
2. የሮምን ክርስቲያኖች በማስመልከት የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ ክርስቲያኖች ኔሮ በተባለው የሮም ገዥ ተሰደው በሥቃይ ላይ ነበሩ። ስለዚህ፦
   ሀ/ በሮም ይገኙ የነበሩት ክርስቲያኖች የዕለት ችግራቸውን የሚያቃልልላቸውን አምላክ ይፈልጉ ነበር።
   ለ/ የሮም ክርስቲያኖች የአይሁዶችን ያህል የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዕውቀት ስላልነበራቸው ማርቆስ የኢየሱስን የትውልድ ሐረግ አያቀርብላቸውም፤ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችንም እምብዛም አይጠቅስላቸውም።
   ሐ/ ማርቆስ በትምህርቱ ላይ ሳይሆን በኢየሱስ አገልግሎት ላይ ይበልጥ ያተኩራል፤ ኢየሱስን አገልጋይ አድርጎ ያቀርበዋል፤ 10፡45።

## የማርቆስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት

1. ወንጌልን ወይም መልካሙን የምሥራች ለየት ባለ አኳኋን ገልጾታል።
   ሀ/ ኢየሱስ ሰብኮታል፤ 1፡ 14-15።
   ለ/ ሕይወታችንን መሳውዕት ልናደርግለት ይገባል፤ 8፡35፤ 10፡29-30።
   ሐ/ ለአሕዛብ ሁሉ መሰበክ ይኖርበታል፤ 13፡10፤ 14፡9።
2. የማርቆስ ወንጌል 16 ምዕራፎች ሲኖሩት ከወንጌሎች ሁሉ አጠር ያለ ነው። ለምሳሌ፦

ሀ/ የኢየሱስ ልደት አልተጠቀሰም። የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ በማርቆስ ዓላማ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም።

ለ/ ማርቆስ በንጉሥነቱ ማዕረግ ላይ ባለማተኮሩ የእረኞቹንና የጠቢባኑን ጉብኝትም አልጠቀሰም። በዚህ ወንጌል ውስጥ ንጉሥ ወይም አምላክ የሚል የማዕረግ ስም ጨርሶ ለኢየሱስ አልተሰጠም፤ ማርቆስ ዘወትር የሚጠራው «ጌታ» ብሎ ነው።

3. ማርቆስ ብዙዎቹን የኢየሱስ ታምራት ለምሳሌ እንደ ፈውስ፤ አጋንንት ማውጣት፤ ነፋስን ማዘዝና 5000 ሰዎችን መመገብ የመሳሰሉትን የሚጠቅሳቸው ለየት ባለ አኳኋን ነው። የአገልጋዩ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶታል።

4. በዚህ ወንጌል ኢየሱስ ሰዎችን ከፈወሳቸው በኋላ ለማንም አትናገሩ ብሎ የማስጠንቀቁ ሁኔታ ትኩረት ተደርጎበታል፤ 1:25፤ 34፤ 44፤ 3:12፤ 5:43፤ 7:36። ኢየሱስ መሲህ መሆኑን ያመኑትን ደቀ መዛሙርት ስለ ምስጢሩ ለማንም እንዳያወሩ አስጠነቀቃቸው፤ 8:29-30። ኢየሱስ በክብር ተገልፆ በነበረበት ወቅት አብረውት ከእርሱ ጋር የነበሩትን ደቀ መዛሙርት ለማንም እንዳይናገሩ ከለከላቸው፤ 9:9። ምክንያቱም:-

ሀ/ ኢየሱስ በሚያደርጋቸው ታምራት ሕዝቡ ተደንቀው ቃሉን ከመስማት እንዳይከለከሉአቸው ይጠነቀቅ ነበር።

ለ/ አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንኳ እንዲያስተምር ሕዝቡ ፋታ አይሰጡትም ነበር። አ1 5. ማርቆስ ኢየሱስን ይከተሉ ስለነበሩት ሰዎች በተደጋጋሚ ጽፏል። እነዚህ ሰዎች ጸሐፊዎችና ፈሪሳውያን በኢየሱስ ዝና እንዲቀኑ አድርገዋቸዋል፤ 2:15-16፤ 3:20፤ 22:12-13።

6. የማርቆስ ወንጌል በኢየሱስ ድርጊቶች የተሞላ ነው። በአጠቃላይ በወንጌሉ ውስጥ አንዱን የኢየሱስ ድርጊት ከሌላው ጋር ለማያያዝ እንዲረዱ «ወዲያውኑ» እና የመሳሰሉት ቃላት በብዛት ይገኛሉ።

7. በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ ስሜቶች በተለይ ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ:-

ሀ/ ርህራሄው- 1:41፤ 6:34፤ 8:2።

ለ/ ቁጣው- 3:5፤ 10:14። አ2 ሐ/ ትካዜውና ሐዘኑ- 14:34-35።

መ/ ጭንቀቱ- 7:34፤ 8:2።

8. ማርቆስ አንድ ጊዜ ብቻ ከነቢያት መጽሕፍት ይጠቅሳል፤ 1:2። በአንፃሩ ግን ማቴዎስ ብዙ ጊዜ ከነቢያት መጽሕፍት ይጠቅሳል።

9. ማርቆስ ከኢየሱስ ምሳሌዎች 4 ብቻ ሲጠቅስ ማቴዎስ 14 ጽፏል። ምክንያቱም:- አገልጋይ ያገለግላል- ማርቆስ። ንጉሥ ያውጃል- ማቴዎስ።

10. ኢየሱስ አናጢ እንደነበር የሚነግረን የማርቆስ ወንጌል ብቻ ነው።

## ጥያቄዎች

1. የማርቆስ ስም የተጠቀሰባቸውን ሦስት የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ጻፉ።
2. ሦስቱ የማርቆስ ወንጌል ዓላማዎች ምን ምንድር ናቸው?
3. አምስቱን የማርቆስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት ዘርዝሩ።
4. የማርቆስ ወንጌል የተፃፈበትን ዘመን አብራሩ።
5. ማርቆስ ያቀረበው የኢየሱስ ሕይወት ታሪክ ማቴዎስ ካቀረበው የሚለየው እንዴት ነው?

## የቤት ሥራ

ማርቆስ 5-8 አንብቡ።

## ምክር ለመምህሩ

የሚቀጥለውን ትምህርት ከማስተማርዎ በፊት ተማሪዎቹ ማር. 5-8 ማንበብ አለባቸው። ለእያንዳንዱ ትምህርት ከተወሰነለት ጊዜ በላይ ሰዓት አያባክኑ።

# ትምህርት ሰባት

## የማርቆስ ወንጌል አጠቃላይ አስተዋጽዖ

1. ወንጌሉ አገልጋዩን ለማስተዋወቅ የተጠናቀረ ዘገባ ነው፤ 1፡1-13። ለምሳሌ:-
   ሀ/ መልእክተኛው መጥምቁ ዮሐንስ የአገልጋዩን መገለጥ ይሰብካል፤ 1፡1-8።
   ለ/ የኢየሱስ ጥምቀት፤ 1፡9-10።
   ሐ/ የድምፅ ከሰማይ መምጣት፤ 1፡11።
   መ/ የኢየሱስ መፈተን፤ 1፡12-13።
2. የአገልጋዩ ተግባር ተገልጿል፤ 1፡14-13፡37። ለምሳሌ:-
   ሀ/ የኢየሱስ ታምራት- የፈውስ፤ የአጋንንት ማስወጣት፥ በተፈጥሮ ኃይላት ላይ ሥልጣኑን የመግለጥና ብዙ ሕዝብ የመመገብ ታምራት ናቸው።
   ለ/ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ይጠራል፤ 1፡16-20፤ 2፡13-20፤ 3፡13-19።
   ሐ/ ኢየሱስ ያቀረባቸው ትምህርቶች:-
      1. ሕዝቡን በምሳሌዎች ያስተምራል፤ 4፡1-34፤ 12፡1-12፤ 13፡28-31። በተጨማሪ ከጠላቶቹ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች ይመልሳል፤ ስለዚህ ነገር በትምህርት 8 ውስጥ በዝርዝር ቀርቧል።
      2. ደቀ መዛሙርቱን ሥነ ሥርዓትን በሚመለከት፤ 8፡34-38። ትሕትናን በሚመለከት፤ 9፡33-50። የባለጠግነትን ወጥመዶች በሚመለከት፤ 10፡23-27። ታማኝነትን በሚመለከት፤ 10፡28-31። ጸሎትን በሚመለከት 11፡20-26። የዘመንን መጨረሻ በሚመለከት አስተማራቸው፤ 13፡1-37።
   መ/ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስተምሩና እንዲፈውሱ ይልካቸዋል፤ 6፡7-13።
3. አገልጋዩ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሆኖ ተገኘ፤ ማር. 14-15። ለምሳሌ:-
   ሀ/ የአይሁድ ባለሥልጣኖች ኢየሱስን ለመግደል ሴራ ይጠነስሳሉ፤ 14፡1-2፤ 10-11።
   ለ/ የመጨረሻው ፋሲካና የጌታ እራት፤ 14፡17-25።
   ሐ/ የኢየሱስ ሥቃይ በጌቴሴማኒ 14፡32-41።
   መ/ የኢየሱስ መከዳትና እስራት፤ 14፡43-52።
   ሠ/ የኢየሱስ በሊቀ ካህኑና በአይሁድ ሸንጎ ፊት፤ 14፡53-65።
   ረ/ ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት፤ 15፡1-23።
   ሰ/ የኢየሱስ መስቀል፤ 15፡24-41።

ሽ/ የኢየሱስ መቀበር፤ 15፡42-47።

4. አገልጋዩ በክብር ከፍ ከፍ ብሏል፤ 16።
   ሀ/ የኢየሱስ ትንሣኤ 16፡1-8።
   ለ/ የኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ መገለፅ፤ 16፡9-14።
   ሐ/ ኢየሱስ አሥራ አንዱን ሐዋርያት የላካቸው ተልዕኮ፤ 16፡15-18።
   መ/ የኢየሱስ ዕርገት፤ 16፡19-20።

## በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

እነዚህን ጥቅሶች በቃላችሁ አጥኗቸው፡-

1. ማር. 1፡35 - ኢየሱስ በጸሎት ያደረገው ዝግጅት
2. ማር. 8፡34-37 - የአገልግሎት ዋጋና ሽልማቱ
3. ማር. 10፡29-30 - ኢየሱስ ለሚያገለግሉት የሰጠው ተስፋ
4. ማር. 10፡45 - የኢየሱስ አገልግሎት ሌሎችን መጥቀምና ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ መስጠት ነበር።

## በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ማገልገል ወይም መርዳት፤
2. ወዲያውኑ፥ በቀጥታ፥ ከዚህ በኋላ ወዘተ የመሳሰሉ ቃላት የኢየሱስን ድርጊት ወይም ሥራዎች የሚገልጹ ቃላት ናቸው።

## ጥያቄዎች

1. የማርቆስ ወንጌል አራት ዋና ዋና ክፍሎች ጻፍ።
2. ማርቆስ የሚያተኩረው በየትኛው የኢየሱስ ሕይወት ክፍል ነው?
3. ኢየሱስ ወደ አባቱ ማለትም ወደ እግዚአብሔር አብ በሚመለስበት ወቅት አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ ምን አደረገ?
4. ማርቆስ የተመለከተውን የኢየሱስ ሕይወት ክፍል በትክክል የሚያሳየው ቁልፍ ጥቅስ የቱ ነው?
5. በማርቆስ ወንጌል ውስጥ በተደጋጋሚ የተጠቀሱት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

## የቤት ሥራ

ማርቆስ 9-12 አንብቡ።

# ትምህርት ስምንት

## የማርቆስ ወንጌል ይዘት

የኢየሱስ ማንነት በሚከተሉት አጠራሮች ተገልጧል፦

1. «የእግዚአብሔር አገልጋይ» ተብሎ ቀርቧል፤ ኢሳ. 52፡13-53፡12።
2. «የሰው ልጅ» የሚል መጠሪያ ስም ተሰጥቶታል፤ 8፡31፤38፤ 9፡9፤ 12፤ 31፤ 10፡33፤ 13፡34፤ 14፡62። በተጨማሪ ዳኔል 7፡13ና 1ኛ ቆሮ. 15 ይህንን መጠሪያ ስም ስለሚያብራሩ ተወያዩባቸው።
3. ሊያገለግል የመጣው የሰው ልጅ «የእግዚአብሔር ልጅ» ተብሎ ተጠርቷል።
   ሀ/ በማርቆስ - 1፡1።
   ለ/ በእግዚአብሔር - 1፡11፤ 9፡7።
   ሐ/ በአጋንንት - 3፡11፤ 5፡7።
   መ/ በኢየሱስ በራሱ - 14፡62።
   ሠ/ በመስቀል ላይ ሳለ በመቶ አለቃው - 15፡39።

## የኢየሱስ ተግባር

1. ሊያገለግል መጣ፤ 10፡45።
2. ሰዎችን ከኃጢአትና ከፍርድ ለማዳን ቤዛ ሊሆን መጣ፤ 10፡45።
3. በእግዚአብሔር በሰዎች መካከል ሕብረት ለመፍጠር የአዲስ ኪዳን ደም የሆነው የራሱን ደም አፈሰሰ፤ 14፡24።
4. ከእርሱ ዕርገት በኋላ በምድር ላይ የነበረው አገልግሎት እንዳይቋረጥ አብረውት ያሉትን ሰዎች አሰለጠናቸው፤ 3፡14።

## የክርስቶስ ትምህርት

1. በወንጌሉ ውስጥ የሚገኙት አራቱ ምሳሌዎች፦
   ሀ. ዘሪውና መሬቱ 4፡1-20።
   ለ. መብራቱ - 4፡21-25።
   ሐ. ዘሩ - 4፡26-29።
   መ. የወይኑ እርሻ ባለቤት - 12፡1-11።
2. የሃይማኖት መሪዎች የነበሩት ጠላቶቹ ላቀረቡለት ጥያቄዎች ኢየሱስ መልስ ይሰጣቸዋል።
   ሀ. ለፈሪሳውያንና ለጸሐፊዎች፦
      1. ልማዶችን በሚመለከት - 7፡1-13።
      2. መፈታትን በሚመለከት - 10፡1-12።
      3. ታላቁን ትዕዛዝ በሚመለከት - 12፡28-34።
   ለ. ለጸሐፊዎችና ለካህናት አለቆች፦ የእርሱን ሥልጣን በሚመለከት፤ 11፡27-33።
   ሐ. የሄሮድስ ወገን ለየነበሩት፤ ግብርን በሚመለከት፤ - 12፡13-17።

መ. ለሰዱቃውያን፡- ትንሣኤን በሚመለከት - 12፡18-27።

3. ኢየሱስ ያቀረበላቸው አራት አንገብጋቢ ጥያቄዎች፡-
   ሀ. «ሰዎች እኔ ማን እንደሆንሁ ይላሉ?» 8፡27-29።
   ለ. «ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?» 8፡36-37። ይህ ጥያቄ የሚገኘው በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብቻ ነው።
   ሐ. «ለምን ቸር ትለኛላችሁ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም፤» 10፡18።
   መ. «እኔ የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ እኔ የምጠመቃትን ጥምቀት ልትጠምቁ ትችላላችሁን?» 10፡38።

## ጥያቄዎች

1. በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ለኢየሱስ ከተሰጡት ስሞች ሁለት ጥቀሱ።
2. ኢየሱስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ የመሰከሩት አምስቱ እነማን ናቸው?
3. አራቱን የኢየሱስ ተግባሮች ዘርዝሩ።
4. የኢየሱስ ጥላቶች እነማን ነበሩ? አራቱን ዘርዝሩ።
5. ኢየሱስ የሰውን ነፍስ በማስመልከት ያቀረበው አንገብጋቢ ጥያቄ ምን የሚል ነው?

## የቤት ሥራ

ማርቆስ 13-16 አንብቡ።

# ትምህርት ዘጠኝ

የማርቆስ ወንጌል ዓይነተኛ ርእስ ኢየሱስ «አገልጋዩ ነው» የሚለው ነው። የማርቆስ ወንጌል የሚጀምረው አገልጋዩ በሚያደርገው ዝግጅት ነው፤ 1፡1-13። ዝግጅት ያደረገውም፡-

1. በጥምቀቱ-1፡9።
2. በእግዚአብሔር ምርጫ-1፡11፤ 9፡7።
3. በደረሰበት ፈተና ነው፤ 1፡12-13፤ ዕብ. 5፡8፤ የሐዋ. 3፡18፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡13።

የማርቆስ ወንጌል ትኩረት የሚያደርገው በአገልጋዩ ሥራ ወይም አገልግሎት ላይ ነው፤ 10፡45። በተጨማሪ ዮሐንስ 9፡4 ተመልከቱ። የማርቆስ ወንጌል የሚደመድመው በአገልጋዩ በክብር ከፍ ከፍ ማለት ነው፤ 16፡19፤ ፊልጵ. 2፡8-9።

## በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ዋና ዋና ጭብጦች፡-

1. ኢየሱስ «ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ» አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት መረጣቸው፤ 3፡13-21። ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ለመሆን ፈቅደው ጊዜያቸውን የሚሰጡትን ይጠቀምባቸዋል፤ ሉቃስ 10፡42ንና ዮሐ. 15፡6-8ን አንብቡ።

2. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ካሠለጠነ በኋላ ለአገልግሎት ላካቸው፤ 6፡12-13። ዛሬም የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት መሠልጠን ያስፈልጋቸዋል፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡13ን፤ 2ኛ ጢሞ. 2፡2፤ 15ንና 2ኛ ጴጥ. 1፡10ን አንብቡ።
3. ኢየሱስ የመጣው ሌሎችን ሊያገለግል ነው፤ 10፡43-45። ኢየሱስ የአማኝ ምሳሌ ነው፤ ማቴ. 10፡24ን፤ ዮሐ. 12፡26ን፤ ገላ.5፡14ንና 1ኛ ጴጥ. 2፡21ን አንብቡ።
4. ኢየሱስ ለጠላቶቹ መልስ ሰጥቷቸዋል፤ 12፡13-40። እኛም ደግሞ እምነታችንን ለሚፈታተኑ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጀን መሆን ይኖርብናል፤ ቆላ. 4፡3-6፤ 1ኛ ጴጥ. 3፡15። ሆኖም ኢየሱስ በሐሰት በተከሰሰበትና በተቀለደበት ጊዜ ምንም መልስ አልሰጠም፤ 15፡4-5። ስለዚህ አልፎ አልፎ ዝም ማለት ይመረጣል። የትኛውን ማድረግ እንደሚጠቅመን መንፈስ ቅዱስ ሊመራን ይችላል።
5. አገልጋዩ ኢየሱ በክብር ከፍ ከፍ ብሏል፤ 16፡19። በተጨማሪ ፊልጵ. 2፡7-9ን አንብቡ። ታማኝ የሆነ አገልጋይ በዚህ ምድር ላይ ክብር ላይቀበል ይችላል፤ ሮሜ. 8፡17ን፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡58ንና 1ኛ ጴጥ. 5፡10ን አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. አገልጋዩ ለሥራው ራሱን ያዘጋጀው እንዴት ነበረ?
2. ኢየሱስ በምድር ላይ ከነበረው አገልግሎቱ ከማዳንና ታምራት ከማድረግ ሌላ ዋና ዓላማው ምን ነበር?
3. ታማኙ አገልጋይ ኢየሱስ ለግሉ ያተረፈው ጥቅም ምን ነበረ?
4. ከአገልጋዩ ከኢየሱስ ሕይወት ለክርስቲያኖች የሚጠቅም ሁለት ምሳሌ ስጡ።

## የቤት ሥራ

የወንጌሎቹ መግቢያን፤ የማቴዎስንና የማርቆስን ወንጌሎች ጥናት ክለሳ በማድረግ ከትምህርት 1-10 ያለውን ክፍል አጥኑ።

## የኢየሱስን ሥራ የሚገልጥ ንድፍ




## ምክር ለመምህሩ

ተማሪዎቹ ዝቅ ብለው የተዘረዘሩትን 7 ነጥቦች በሚገባ ተረድተዋቸውና እነርሱንም በማስመልከት የቀረበውን ትምህርት ማጥናታቸውን ያረጋግጡ። እነርሱም፡-

1. የማርቆስ ወንጌል ዓላማ፤
2. የማርቆስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት፤
3. የማርቆስ ወንጌል አጠቃላይ አስተዋፅዖ፤
4. በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች፤
5. በማርቆስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት፤
6. ከኢየሱስ የምድር አገልግሎት ሦስት ዋና ክፍሎች ማለትም፡-
   ሀ/ የመፈወሱ፥ አጋንንት የማውጣቱና ሕዝቡን የመመገብ ታምራት ማድረጉ፤
   ለ/ ደቀ መዛሙርቱን ከጠራ በኋላ ማሰልጠኑ፤
   ሐ/ ለኃጢአት ዋጋ እንዲሆን ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ መስጠቱ ናቸው።
7. በምድር ላይ የነበረው አገልግሎት በደቀ መዛሙርቱ አማካይነት እንደቀጠለ የሚሉት ናቸው።

# ትምህርት አሥር

## ለፈተና ዝግጅት የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌሎች ክለሳ

## የማቴዎስና የማርቆስ ወንጌሎች የማወዳደሪያና የማነፃፀሪያ ሰንጠረዥ

### ማቴዎስ

1. ሰዎች በእርሱ እንዲያምኑ ለማድረግ የኢየሱስን የምድር ላይ አገልግሎት ያቀርባል።
2. ኢየሱስን እንደ መሢህ ያቀርበዋል።
3. በኢየሱስ የተፈጸሙትን ብዙ የብሉይ ኪዳንን ትንቢቶች ጠቅሷል።
4. በወንድ በኩል የመጣውን ወይም ንጉሣዊውን የኢየሱስ የዘር ሐረግ ያቀርባል።
5. የኢየሱስን ልደትና ወደ ግብፅ የመሰደድን ታሪክ በአጭሩ ያቀርባል።
6. ለኢየሱስ ትምህርት ትልቅ ሥፍራ ሰጥቶታል፤ ንጉሡ ያውጃል።
7. የማቴዎስ ዓላማ ኢየሱስ መሢህ እንደነበረ ለአይሁድ ለማረጋገጥ ነበር።
8. ኢየሱስ ሥልጣን በተሞላበት ሁኔታ የሃይማኖት መሪዎችን፥ የፈሪሳውያንንና የሰዱቃውያንን ግብዝነት ይነቅፋል፤ ማቴ. 23።
9. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅዓትና ስለ መጨረሻዎቹ ጊዜያት ትምህርት ይሰጣል፤ ማቴ. 24-25።
10. ማቴዎስ «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» የሚለውን የመጨረሻ ትዕዛዝ ያቀርባል።
11. ማቴዎስ 28 ምዕራፎች አሉት።
12. ማቴዎስ ከኢየሱስ ታምራት አሥራ አራቱን አስፍሯል።

### ማርቆስ

1. አጠቃላይ አቀራረብ ከማቴዎስ ጋር ተመሳሳይ ነው።
2. ኢየሱስን እንደ አገልጋይ ያቀርበዋል።
3. ከብሉይ ኪዳን አንድ ትንቢት ብቻ ግልፅ በሆነ መንገድ ጠቅሷል።
4. ምንም የኢየሱስን የዘር ሐረግ አላቀረበም። በማርቆስ ዓላማ ውስጥ አስፈላጊ ልነበረም።
5. የኢየሱስን የልደት ታሪክ አልሰጠም።
6. የኢየሱስን አገልግሎት ትኩረት ሰጥቶታል፤ አገልጋዩ ያገለግላል።
7. ለሮማውያን ክርስቲያኖች የሮም ገዥ የነበረው ኔሮ ባመጣባቸው ስደት ውስጥ የሚገጥማቸውን የዕለት ችግር በሙሉ ኢየሱስ እንደሚያስወግድላቸው ማረጋገጥ የማርቆስ ዓላማ ነበር።
8. ኢየሱስ የሃይማኖት መሪዎች የሚያቀርቡለትን ጥያቄ ይመልሳል፤ ማር. 12።
9. ስለ መጨረሻዎቹ ጊዜያት ትምህርት ይሰጣል፤ ሆኖም እንደ ማቴዎስ በዝርዝር አይደለም፤ ማር. 13።

10. «ሂዱና ... ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ» የሚል ተመሳሳይ ትዕዛዝ አቅርቧል።
11. ማርቆስ 16 ምዕራፎች አሉት።
12. ማርቆስ አራት ታምራት ብቻ አስፍሯል።

## ምክር ለመምህሩ

በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ የተሰጡትን ጥያቄዎች ከከለሱ በኋላ ከትምህርት 1-10 ካለው ክፍል ጥያቄ አውጣጥተው ፈተና ያዘጋጁ።

## የቤት ሥራ

ለፈተና ዝግጅት አድርጉ።

# ትምህርት አሥራ አንድ

## ምክር ለመምህሩ

ተማሪዎችዎን ከትምህርት 1-10 ካሉት ክፍሎች አውጣጥተው ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑአቸው።

## የቤት ሥራ

ለሉቃስ ወንጌል ጥናት ለመዘጋጀት ሉቃስ 1-6ን አንብቡ።

# ትምህርት አሥራ ሁለት

## የሉቃስ ወንጌል መግቢያ

የመጽሐፉ መሠረታዊ ነጥቦች

1. ጸሐፊው ሉቃስ ነበር።
   ሀ/ ሐኪም ነበር፤ ቆላ. 4፡14።
   ለ/ ከእሕዛብ ወገን ያመነ ነበር፤ ቆላ. 4፡14።
   ሐ/ የጳውሎስና የማርቆስ ጓደኛ ነበር፤ ፊልሞና 24፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡1።
2. የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው በ60 ዓ.ም. ገደማ ነበር።

## የሉቃስ ወንጌል ዓላማ

1. ሉቃስ በምዕ. 1፡1-2 ላይ የቀድሞ ክርስቲያኖች ያዩአቸውንና ያመኑባቸውን ነገሮች በቅደም ተከተል የሚያቀርብ መሆኑን ይናገራል።
2. ሉቃስ ታሪኩን የጻፈው በተለይ ግሪኮች እንዲጠቀሙበት በማሰብ ነው። እነርሱ ሁሉ ነገር እንከን የሌለው ሆኖ እንዲቀርብላቸው ስለሚፈልጉ እርሱም ኢየሱስን ፍፁም ሰው አድርጎ ያቀርብላቸዋል።

## የሉቃስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት

1. ሉቃስ ከማቴዎስና ከማርቆስ ይልቅ የኢየሱስን ስሜቶች በማስመልከት ጽፏል። ለምሳሌ፡-
   ሀ/ ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም አለቀሰ፤ 13፡14።
   ለ/ ኢየሱስ በጸሎት ቃተተ፤ 22፡44።
   ሐ/ ኢየሱስ በኀዘን ለሚገኙት ያዝናል፤ 7፡13፤ 8፡52።
   መ/ የኢየሱስ ምሳሌዎች የእርሱን ብርቱ ስሜት ይገልጻሉ፤ ሉቃስ 15።
2. የሉቃስ ወንጌል ከተቀሩት ወንጌሎች ሁሉ ይረዝማል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ረዥሙ መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌል ነው።
3. ሰው ሁሉ እኩል እንደሆነ ሉቃስ ጠበቅ አድርጎ ይገልጻል። ለምሳሌ፡-
   ሀ/ መላእክት ለእረኞች የተናገሩት መልእክት ለሰው ሁሉ የተሰጠ መልእክት ነበር፤ 2፡10።
   ለ/ ኢየሱስ ሕፃን ሳለ ስምዖን በቤተ መቅደስ ውስጥ ስለ እርሱ የተነበየው ትንቢት እንዲህ የሚል ነበር፡- «ለሰዎች ሁሉ ደህንነት ይሰጣል» 2፡31-32።
   ሐ/ በ3፡6 ላይ ሉቃስ ከኢሳ. 52፡10 ላይ የጠቀሰው ጥቅስ «ሥጋ የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ያያል» የሚል ነው።
   መ/ ኢየሱስ ማንኛውንም ዓይነት ሰው ለመርዳት ይፈቅድ እንደነበረ የሉቃስ ወንጌል ያሳያል። ኢየሱስ ሴቶችን፥ ሕፃናትንና የተገለሉትን ለምሳሌ እንደ ለምፃሞች፥ ሰማሪያውያንና አሕዛብ ያሉትን ረድቷቸዋል።
4. ብዙ ግሪኮች የተማሩ ሰዎች ስለነበሩ ግጥምና ዜማ ይወዱ ነበር። ስለዚህ ሉቃስ፡-
   ሀ/ የኢየሱስ እናት የማርያምን የምስጋና ግጥም ያቀርብላቸዋል፤ 1፡46-55።
   ለ/ የዘካርያስን የምስጋና ንግግር ያቀርብላቸዋል፤ 1፡68-79።
   ሐ/ የመላእክቱን የምስጋና ንግግር ያቀርብላቸዋል፤ 2፡8-14።
5. ሉቃስ ከማቴዎስና ከማርቆስ ይልቅ ስለ ጸሎት ሰፊ ትምህርት ይሰጣል፤ 11፡1-3፤ 18፡1-4፤ 22፡45-46 ተመልከቱ። ዘጠኙ ኢየሱስ የፀለየባቸው ጊዜያት በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ተጠቅሰዋል፤ 6፡12፤ 9፡16፤ 18፤ 9፤28-29፡ 11፡2-4፤ 22፡17፤ 19፤ 32፤ 41-44፤ 23፡34፤ 46።
6. ሉቃስ ከማቴዎስና ከማርቆስ ይልቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ይጠቅሳል።
7. የሚቀጥሉትን ነገሮች የሚነግረን ሉቃስ ብቻ ነው፡-
   - ኢየሱስ የደም ላብ እንዳላበው፤
   - ኢየሱስ በኤማሁስ መንገድ ላይ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት እንዳነጋገራቸው፤
   - ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ 11 ጊዜ ስለ መታየቱ፤

- ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተናገራቸው ቃላት፡-
  «አባት ሆይ ይቅር በላቸው» 23፡24።
  «ዛሬ ከእኔ ጋር ትሆናለህ» 23፡43።
  «ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» 23፡46።

## ጥያቄዎች

1. ስለ ሉቃስ ማንነት ሦስት ነገር ጻፉ።
2. ሉቃስ ስለ ኢየሱስ መረጃ የሰበሰበው ከየት ነበረ?
3. የኢየሱስን ስሜቶች የሚያሳዩ ሦስት ሁኔታዎች ጥቀሱ።
4. ሉቃስ የሰውን እኩልነት በማስመልከት ከጻፋቸው ሁኔታዎች ጥቂቶቹን ዘርዝሩ።
5. ሉቃስ ወንጌሉን በሚጽፍበት ጊዜ በተለይ እነማንን ያስብ ነበር?

## የቤት ሥራ

ለሚቀጥለው ትምህርት ዝግጅት ሉቃስ 7-12ን አንብቡ።

# ትምህርት አሥራ ሦስት

## የሉቃስ ወንጌል አጠቃላይ አስተዋጽዖ

1. የኢየሱስ ልደትና የልጅነት ወቅት፤ 1፡5-3፡20።
2. የኢየሱስ ጥምቀትና መፈተን፤ 3፡31-4፡13።
3. የኢየሱስ አገልግሎት በገሊላ፤ 4፡14-9፡50።
4. ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ፤ 9፡51-19፡10።
5. ኢየሱስ በኢየሩሳሌምና በአካባቢዋ፤ 19፡11-22፡46።
6. የኢየሱስ ሞትና ድል፤ 22፡47-24፡53።

ኢየሱስ በምድር ላይ የነበረው አገልግሎት ድርብ ነበር።

1. ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለመርዳት ነበረ፤ 4፡18። ኢየሱስ ከምዕራፍ 1፡1-9፡50 በሽተኞችን ፈወሰ፥ አጋንንትን አስወጣ፥ ምሳሌዎችን አስተማረ፥ ባሕሩን ፀጥ አደረገ፥ በተጨማሪ አምስት ሺህ የተራቡ ሰዎችን መገበ። ሰዎች በሥጋ የሚደርስባቸውን ሁሉ ኢየሱስ ራሱ ይሰማው ነበር። ሆኖም ከጥቂት ደቀ መዛሙርት በስተቀር የእግዚአብሔር ልጅና ለእነርሱ የመጣ መሲህ መሆኑን ሕዝቡ ሊቀበሉት አልወደዱም፤ 4፡22-30። ስለዚህ ኢየሱስ የመጣበትን ሁለተኛ ዓላማ ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ይጓዛል። በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ሉቃስ 9፡51 ማዕከላዊ ነጥብ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ኢየሱስ «የሚወጣበት ጊዜ እንደደረሰ አውቆ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና።»
2. ኢየሱስ የመጣው ሰዎችን ለማዳን ነበረ፤ 9፡56ን አንብቡ። ኢየሱስ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ ሰዎችን ማዳን፥ ማስተማርንና ደቀ መዛሙርቱን ማሠልጠን አላቋረጠም።

ነገር ግን የኢየሱስ ዋና ዓላማ የሰዎችን መንፈሳዊ ፍላጎት ማርካት ነበር። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሕይወቱን ለዓለም ኃጢአት እንዲሰዋና በእርሱ ኃያልነት ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲሰጥ እግዚአብሄር ያዘጋጀው ጊዜ ደረሰ።

## ሉቃስ 9፡51

እንደ ሉቃስ አቀራረብ ይህ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ማዕከላዊ ነጥብ ነው። የተሰጠውን ንድፍ በሚገባ ብታጠኑት የሉቃስን ወንጌል አጠቃላይ ይዘት ባጭሩ ለመያዝ በጣም ይረዳችኋል። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የሚገኝ ቁልፍ ቃል «የሰው ልጅ» የሚለውን ነው። ቁልፍ ጥቅሶች፡-

1. ሉቃስ 2፡40ና2፡52።
2. ሉቃስ 5፡32ና 19፡10 ኢየሱስ እንዴት ኃጢአተኞችን ሊጠራና ሊያድን እንደመጣ ይናገራሉ።
3. በሉቃስ 9፡62 ኢየሱስ ወደኋላ ስለመመለስ ያስጠነቅቃል።
4. በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ማዕከላዊው ጥቅስ ሉቃስ 9፡51 ነው እነዚህን በቃል አጥኑ።

<u>የሉቃስ ወንጌል ንድፍ</u>

ኢየሱስ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቀና



## ጥያቄዎች

1. የሉቃስ ወንጌልን ስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ዘርዝሩ።
2. በምድር ላይ የኢየሱስ ድርብ ዓላማ ምንድነው?
3. በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እንደተጠቀሰው በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ማዕከላዊው ነጥብ ምን ነበር? ለምን?
4. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን የሚያቀናው ለምንድን ነው? 9፡15 ተመልከቱ።

## የቤት ሥራ

ሉቃስ 13-18 አንብቡ። በዚህ ክፍል ውስጥ ቁልፍ የሆኑትን ጥቅሶች አጥኑ።

# ትምህርት አሥራ አራት

ሉቃስ ኢየሱስን ፍፁም ሰው አድርጐ ያቀርበዋል። ኢየሱስ በልደቱና በዕድገቱ እኛን ይመስል ነበር። የደረሱበት ፈተናዎች በእኛ ላይ እንደደረሱ ዓይነት ናቸው። ስሜቶቹም ልክ እንደ እኛ ናቸው። ሆኖም እንደ እኛ ሥጋ ለባሽ ቢሆንም ከእኛ ልዩ ነበር። ባሕርዩ ልዩ ነው፤ የተላከውም ለተለየ ዓላማ ነበር። የኢየሱስ ንግግርና ሕይወቱ ሌሎች ሰዎች ያልነበራቸው ሥልጣን ታይቶበታል። ለምሳሌ፦

1. ኢየሱስ «ወንድሞቹን ሊመስል» ወደዚህ ዓለም እንደመጣ ተገልጿል ዕብ. 2፡17። በተጨማሪ የኢየሱስ ሕይወት የኛን እንደሚመስል ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡ፦ 1፡25-26፤ 2፡1-7፤39-52።
2. ኢየሱስ «በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ» ሰው ነበር፤ ዕብ. 4፡15። ኢየሱስ የተፈተነባቸውን መንገዶች ለማወቅ የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ፦ 4፡1-30፤ 20፡19-47፤22፡39-46፤63-65፤70፤71፤23፡33።
3. ኢየሱስ «በድካማችን የሚራራልን» ሰው ነበር፤ ዕብ. 4፡15። ኢየሱስ በድካማችን እንደሚራራልን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ለመመልከት እነዚህን ጥቅሶች አንብቡ፦ 7፡13፤ 9፡12፤ 19፡41-44፤ 22፡21-32፤ 23፡39-45፤ 24፡36-48።
4. ኢየሱስ «የእኔ ምግብ የላከኝን ፈቃድ ማድረግ ነው» ብሎ የተናገረ ሰው ነበር፤ ዮሐ. 4፡34። ቀጥለው የሚቀርቡት ጥቅሶች ኢየሱስ የመጣበትን ዓላማ ስለሚያስረዱ ተመልከቷቸው፦ 2፡49፤4፡18-19፤5፡32፤6፡13-16፤ 19፡10። በተጨማሪ ሉቃስ 23፡46ን ከ1ኛ ጢሞ. 2፡6ና ሉቃስ 24፡5-6 ጋር አገናዝቡት።
5. ኢየሱስ «እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም» ተብሎ የተነገረለት ሰው ነበር፤ ዮሐ. 7፡46። ኢየሱስ የተናገረባቸው ጥቂቶቹ ነገሮች ምን ነበሩ? ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ጥቅሶች ኢየሱስ ከተናገራቸው ነገሮች መካከል የሚያሳዩን ጥቅሶች ናቸው፦ 5፡32፤ 17፡2፤4፤9-10፤18፡14፤25፤ 29-30፤19፡10። ኢየሱስ ያስተማረው መመሪያና ሲያስተምርበት የነበረው ሥልጣን ሕዝቡን አስደንቋቸው ነበር።

## ጥያቄዎች

መምህር፤ የጥያቄዎቹን መልሶች በመጽሐፉ ጀርባ ላይ ይመልከቱ።

1. የኢየሱስ ልደትና የሕፃንነት ወቅት ከእኛ ጋር የሚመሳሰለው በምን ዓይነት መንገድ ነው?
2. ኢየሱስ የተፈተነባቸውን መንገዶች ግለጹ።
3. ኢየሱስ ያለውን ርህራሄና አዘኔታ የገለጸው በምን ዓይነት ወቅት ነው?
4. ኢየሱስ አባቱን «የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ይሁን» ብሎ ተናገረ። ኢየሱስ አባቱን በመታዘዝ ረገድ ከፈጸማቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን ጻፉ፤ ከጥያቄዎቹ በላይ በሚገኘው ክፍል ውስጥ በተራ ቁጥር «4» የተዘረዘሩትን ጥቅሶች ተመልከቱ።
5. ሕዝቡ በኢየሱስ ንግግር ተደንቀዋል። ኢየሱስ ከተናገራቸው ከእነዚህ ንግግሮች መካከል ጥቂት አሥፍሩ።

## የቤት ሥራ

ሉቃስ 19-24 አንብቡ። በተጨማሪ በትምህርት አሥራ ሦስት ውስጥ የተሰጡትን ቁልፍ ጥቅሶች ከልሷቸው።

# ትምህርት አሥራ አምስት

## በመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌሎች መካከል የተደረገ ውድድርና ንፅፅር

### ማቴዎስና ማርቆስ

1. ማቴዎስ ኢየሱስን «መሢህ» አድርጐ ያቀርበዋል፤ ማርቆስ ደግሞ «አገልጋይ» አድርጐ ያቀርበዋል።
2. ማቴዎስ በወንድ በኩል ያለውን ወይም ንጉሣዊውን የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ከአብርሃም፥ ከዮሴፍና ከዳዊት ጀምሮ ያቀርባል። ማቴዎስ ይህንን የሚያቀርበው ከኢየሱስ ልደት ታሪክ ጋር ነው፤ ማርቆስ ምንም የዘር ሐረግ አያቀርብም።
3. ማቴዎስ የኢየሱስን ልደት፥ ወደ ግብፅ ያደረገውን ጉዞና እንደገና ወደ ናዝሬት የመመለሱን ታሪክ ያቀርባል። ማርቆስ የኢየሱስን ልደትና የልጅነቱን ወቅት በሚመለከት ምንም ታሪክ አያቀርብም።
4. ማቴዎስ በኢየሱስ ትምህርት ላይ ሲያተኩር፤ ማርቆስ ደግሞ በኢየሱስ አገልግሎት ላይ ያተኩራል።
5. ማቴዎስ 28 ምዕራፎች ሲኖሩት ማርቆስ ደግሞ 16 ምዕራፎች አሉት።
6. ማቴዎስ «ሂዱና ... አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» ሲል ማርቆስ ደግሞ «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ስበኩ» ይላል።

7. ማቴዎስ ባቀረበው ኢየሱስን ሽቶ በቀባችው ሴት ታሪክ ውስጥ የውዱ ሽቶ መባከን በአይሁዶች ተጋኗል፤ ማቴ. 26፡6-13። ሆኖም ኢየሱስ ሴትየዋን በመደገፍ ያደረገችው ነገር ለመታሰቢያዋ እንዲሆን ተናግሯል።
8. በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልካቸው «ወደ ጠፉት የእስራኤል በጎች ብቻ ሂዱ» ብሏቸዋል፤ 10፡6።

## ሉቃስ

1. ሉቃስ ኢየሱስን «ፍፁም ሰው» አድርጎ ከማቅረቡም በላይ በተጨማሪ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ጓደኛ አድርጎ ያቀርበዋል።
2. ሉቃስ የሚያቀርበው የዘር ሐረግ ተፈጥሮአዊውን ወይም በሥጋ ዝምድና ከአዳም በዳዊት በኩል አድርጎ እስከ ኢየሱስ እናት ማርያም ድረስ የሚመጣውን ነው። ይህም የቀረበው ከጥምቀቱ ታሪክ ጋር ነው። በትምህርት ሦስት ላይ የሚገኘውን ንድፍ ተመልከቱ።
3. ሉቃስ የኢየሱስን የሕፃንነትና የልጅነቱን ወቅት በሰፊው ያቀርባል። የኢየሱስን የልጅነት ወቅት፥ ቤተ መቅደሱን ለመጎብኘት ያደረገውን ጉዞና ኢየሱስ ማርያምንና ዮሴፍን ይታዘዛቸው እንደ ነበረ የሚያመለክቱ ታሪኮች ያቀረበው ሉቃስ ብቻ ነው።
4. ሉቃስ ኢየሱስ ለሕዝቡ በነበረው ርህራሄ ላይ ያተኩራል። ለምሳሌ፦ ለሕፃናት-8፡42፤49-56፤ 9፡37-42፤18፡15-17። ለሴቶች- 7፡11-15፤36-50፤8፡1-3፤10፡38-42፤24፡10። ስማቸው በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ከተጠቀሱት ሴቶች መካከል ብዙዎቹ በሌሎች ወንጌሎች ውስጥ አልተጠቀሱም። ለተቸገሩ ሁሉ- 11፡37-44፤ 14፡1-4፤ 19፡1-10፤ 24፡13-32።
5. ሉቃስ 24 ምዕራፎች አሉት። ወንጌሉ ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ ረዘም ያለ ነው።
6. ሉቃስ «ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ተሰብኳል፤ እናንተም ለዚህ ነገር ምስክሮች ናችሁ» ይላል።
7. ሉቃስ ባቀረበው ኢየሱስን ሽቶ በቀባቸው ሴት ታሪክ ውስጥ ሕዝቡ ኃጢአተኛ በመሆንዋ ሲፈርድባት ሴቲቱ ግን በኃጢአትዋ እንዳዘነችና ኢየሱስ ይቅርታ እንዳደረገላት ሉቃስ ይናገራል፤ 7፡36-39፤50። ታሪኮቹ ግን የተለያዩ ሳይሆኑ አይቀሩም።
8. በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልካቸው «ወደ እያንዳንዱ ከተማና ሥፍራ ሂዱ» ብሏቸዋል፤ 10፡1።
9. ሉቃስ ኢየሱስን ሰዎችን ሁሉ በእኩልነት የሚመለከት አድርጎ ያቀርበዋል።

ሦስቱን ወንጌሎች የጻፉት ጸሐፊዎች እርስ በእርሳቸው በተለያዩ ነገሮች ላይ ትኩረት የሰጡ መሆናቸውን አስተውሉ። በተጨማሪ እነዚህ ሦስቱ ዘገባዎች የኢየሱስን ተግባር አብራርተው እንደሚያቀርቡልንና እርሱ ማን እንደሆነ ለማወቅ እንድንችል የሚረዱን መሆናቸውን አስተውሉ።

## ጥያቄዎች

1. ሉቃስ ባቀረበው ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ፍፁም ሰው መሆኑን የሚያሳዩ በዛ ያሉ ነገሮችን ጥቀሱ።
2. ኢየሱስን ሽቶ ስለቀባችው ሴት ማቴዎስና ሉቃስ ያቀረቧቸውን ታሪኮች አወዳድሩ።
3. ኢየሱስ ለሕፃናት ርህራሄ ያሳየበትን አንድ ሁኔታ ጥቀሱ።

4. ኢየሱስ ሴቶች ከሌሎች ሰዎች ጋር እኩል እንደሆኑ አድርጎ የሚመለከት መሆኑን በተግባር ያሳየባቸውን ሁለት ነገሮች ጥቀሱ።

## የቤት ሥራ

ቁልፍ ጥቅሶችንና እነርሱ የሚገኙባቸውን የምንባብ ክፍሎች አጥኑ። የመጽሐፉን አጠቃላይ አሳብ ለመረዳት ስለ ሉቃስ ወንጌል የቀረቡትን ጥናቶች ከልሱ።

# ትምህርት አሥራ ስድስት

## ከሉቃስ ወንጌል የምንማራቸው ዋና ዋና ትምህርቶች

1. ስለ ኢየሱስ የልጅነት ወቅትና ዕድገቱ የሚያስረዱን ጥቅሶች 2፡40ና 2፡52 ናቸው። ኢየሱስ በአካል ዕድገቱ በሁሉ እንደማንኛውም ልጅ ነበር። ነገር ግን በቤተ መቅደስ ከመምህራን ጋር ባደረገው የንግግር ልውውጥ ባሳየው ጥበብ ከማንኛውም ልጅ በላይ ለመሆኑ ማስረጃ እናገኛለን፤ 2፡46-47። አንድ ልጅ ማደግ የሚገባው በምን በምን አቅጣጫዎች እንደሆነ 2፡52 ይገልፃል፤፦ ይኸውም በአዕምሮ፥ በአካል፥ በመንፈሳዊና በማህበራዊ ኑሮ አቅጣጫዎች ነው። ማንኛውም ወላጅ ልጆቹን ሲያሳድግ በዚሁ መንገድ መሆን እንዳለበት ማቀድ ይኖርበታል፤ ምሳሌ 22፡6ን አንብቡ።
2. ኢየሱስ የሴቶችን ክብር ከፍ ከፍ ያደረገ መሆኑን የሉቃስ ወንጌል ያሳያል፤ ለእነርሱም ድጋፍ ሰጥቷቸዋል፤ 7፡3-39። ሴቶች በእርሱ አገልግሎት ውስጥ ተሳትፎ አድርገዋል፤ 8፡1-3። ለሚያዝኑት ራርቶላቸዋል፤ 7፡11-18። የታመሙትን ፈውሷቸዋል፤ 4፡38-50፤8፡41-48። ምክር ለግሷቸዋል፤ 10፡38-42። ሴቶች ምንም እንደማያውቁ፤ እንደ ደንቆሮና እንደ ገረድ ተቆጥረው በነበሩበት ወቅት ኢየሱስ በእኩልነት ተመልክቷቸዋል።
3. ኢየሱስ ተከታዮቹን ትኩረት ይሰጣቸውና ያስብላቸውም ነበር። በተጨማሪ እነርሱን ለመምከርና ከእነርሱ ጋር ለመነጋገር ጊዜውን ሰውቷል። ኢየሱስ የሥልጣን ጥማትን በመቃወም ሲያስተምራቸው ለጴጥሮስ ደግሞ የሚከዳው መሆኑን አስቀድሞ ነግሮታል፤ 22፡24-34። የደቀ መዛሙርትነትን ዋጋ በሚመለከት አስተምሯቸዋል፤ 9፡23-26። ስለ ትሕትና አስተምሯቸዋል፤ 9፡46-48። በኤማሁስ መንገድ ላይ ለሁለት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ገልጾላቸዋል፤ 24፡13። አዲስ የሆኑ አማኞችና ተከታዮች ትምህርት፤ መጽናናትና ምክር ያስፈልጋቸዋል ይህ ኃላፊነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ድርሻ ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዱ ምዕመን ጭምር ነው፤ ቆላ. 3፡16።
4. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና፤ 9፡51። ለመፈጸም የመጣውን ተግባር ከፍፃሜ እንዳያደርስ ለሚያሰናክሉት ነገሮች ምንም ፊንታ አልሰጣቸውም። ኢየሱስ የመጣው ለዓለም ኃጢአት መስዋዕት ሊሆን ነው። በሉቃስ 9፡62 ላይ ኢየሱስ «ማንም እርፍን ይዞ ወደኋላው የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም» ብሎ ተናግሯል። እኛም የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት እንደመሆናችን መጠን ተመሳሳይ ዓላማ ሊኖረን ይገባል፤ ተጠራጥረን ወደኋላችን መመልከት የለብንም፤ ያዕ. 1፡6-8፤ ፊልጵ. 3፡10-15።

## ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በልጅነቱ ያደገባቸው አራት የዕድገት አቅጣጫዎች ምንድናቸው?
2. ኢየሱስ በዘመኑ ሴቶችን ከፍ ያደረገባቸውን በዛ ያሉ መንገዶች ዘርዝሩ።
3. በሉቃስ ውስጥ የሚገኘው የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ በማቴዎስ ውስጥ ከሚገኘው የሚለየው እንዴት ነው?
4. ሉቃስ ብቻ ስለ ኢየሱስ የልጅነት ወቅት የጻፈው ምንድነው?

## የቤት ሥራ

ወደ ዮሐንስ ወንጌል ጥናት ከመሸጋገራችሁ በፊት የሉቃስን ወንጌል ከልሱት። ዮሐንስ 1-5 አንብቡ።

## ምክር ለመምህሩ

ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዳይሰለቹ ያንቃቁአቸው። በወጣው ፕሮግራም መሠረት ተመርተው የማያስተምሩ ከሆነ ትምህርቱን በወቅቱ አይፈጽሙም፤ ስለዚህ ለእያንዳንዱ ትምህርት ከተወሰነለት ጊዜ በላይ አይጨምሩ።

# ትምህርት አሥራ ሰባት

## የዮሐንስ ወንጌል መግቢያ

የመጽሐፉ መሠረታዊ ነጥቦች

1. መጽሐፉ የተጻፈው ከ80-100 ባሉት ዘመናት መካከል ወይም ከዚያ በፊት ሊሆን ይችላል።
2. ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ነበረ።

   ሀ/ የዘብዴዎስና የሰሎሜ ልጅ ሲሆን የያዕቆብ ወንድም ነበር።

   ለ/ አሣ አጥማጅ ነበር፤ ደግሞም « የነጐድጓድ ልጅ» በመባል ይጠራ ነበር።

   ሐ/ ኢየሱስ በጠራው ጊዜ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር።

   መ/ «ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር» እርሱ ነበር።

   ሠ/ በፍጥሞ ደሴት በግዞት ይኖር ነበር፤ ነገር ግን በኋላ ተመልሶ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ያስረዳል።

   ረ/ በተጨማሪ የዮሐንስን መልዕክቶችና ራዕይን የጻፈው እርሱ ነው።

## የዮሐንስ ወንጌል ዓላማ

1. [illegible]

2. በዮሐንስ 10፡10 ላይ ኢየሱስ « እኔ ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲበዛላችሁም መጣሁ» ይላል። የኢየሱስ ፍላጎት እርሱን እንደ አዳኝ የሚቀበሉት ሁሉ ጠለቅ ያለ መንፈሳዊ ዕውቀትና እምነት እንዲያገኙ ነው።

## የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው ለማን ነበር?

1. ኢየሱስ ተስፋ ተሰጥቷቸው የነበረው መሢህ እንደሆነ ከአይሁድ ወገን ላመኑት ክርስቲያኖች ለማረጋገጥ ነበር።
2. ከአሕዛብ ወገን ለሆኑት ክርስቲያኖች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲያውቁ ለማድረግ ነበር።
3. ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ እንዲያምኑ ነበር። ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃልና ልጁ ክርስቶስን ማቅረብ የወንጌሉ መልእክት ነው።

## የዮሐንስ ወንጌል ልዩ ባሕርያት

1. በተቀሩት ወንጌሎች ውስጥ ተጽፈው የሚገኙት የኢየሱስ ምሳሌዎች በአጠቃላይ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አይገኙም፤ ደግሞም በውስጡ የሚገኙት ታምራት በሌሎቹ ወንጌሎች ከሚገኙት ያንሳሉ።
2. የዮሐንስ ወንጌል በሌሎቹ ወንጌሎች ውስጥ የማይገኙ ብዙ ድርጊቶች አስፍሯል፤ ለምሳሌ፡-
   ሀ/ ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገው ንግግር፤ ዮሐ. 3።
   ለ/ የኢየሱስ የቤተ ሳይዳውን ሰው መፈወስ፤ ዮሐ. 5።
   ሐ/ የኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት፤ ዮሐ. 11።
   መ/ የኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠብ፤ ዮሐ. 13።
   ሠ/ የኢየሱስ ለማርያም መግደላዊት መገለጥ፤ ዮሐ. 20።
3. የአይሁድን በዓላት በማስመልከት ኢየሱስ በሠራው ሥራ ላይ ዮሐንስ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፤ ዮሐ. 2፡23፤ 6፡4፤ 7፡2፤ 10፡22፤ 13፡1።
4. በአምስት አቅጣጫዎች ኢየሱስ ከአይሁድ ሃይማኖት የሚበልጥ ሆኖ ቀርቧል።
   ሀ/ ኢየሱስ ከኦሪት ሕግ ይበልጣል፤ ዮሐ. 1-17።
   ለ/ ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ ይበልጣል፤ ዮሐ. 2፡19-21።
   ሐ/ ኢየሱስ ከቤተ መቅደሱ ክብር ይበልጣል፤ ዮሐ. 1፡14።
   መ/ ኢየሱስ ከበዓላት ይበልጣል፤ ዮሐ. 7፡37-39።
   ሠ/ ኢየሱስ መመለክ የሚገባው መሆኑን እምኖ ተቀብሏል፤ ዮሐ. 9፡38፤ 20፡28።
5. ዮሐንስ የኢየሱስን ታምራት የአምላክነቱ ምልክቶችና ማረጋገጫዎች ናቸው ብሎ ይጠራቸዋል፤ ምክንያቱም የዮሐንስ የመጀመሪያ ዓላማ የኢየሱስን ማንነት መግለፅ ነበር።
6. ዮሐንስ ኢየሱስን ከፍጥረት አስቀድሞ የነበረ አድርጐ ስለሚያቀርበው ምድራዊ የዘር ሐረግን አያቀርብም።
7. ኢየሱስ ከብዙ ግለሰቦች ጋር ሲነጋገር ዮሐንስ ያቀርበዋል። ዮሐንስ ብቻ ኢየሱስን «ቃል» ብሎ ይጠራዋል። ዮሐንስ ብቻ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበ ይናገራል። ከዚህ በታች የሚገኙትን ቃላት ኢየሱስ በመስቀል ላይ እንደተናገረ ዮሐንስ ብቻ ይገልጻል፡-

«ተፈፀመ» 19፥30።
«አንቺ ሴት እነሆ ልጅሽ» 19፥26-27።
«ተጠማሁ» 19፥28።

8. ማቴዎስ ኢየሱስን የአይሁዶች «መሢህ» አድርጐ ያቀርበዋል።

ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለማርያም መግደላዊት እንደተገለጠላት ዮሐንስ ብቻ ያስታውቃል።

## ጥያቄዎች

1. ሦስቱ የዮሐንስ ጽሑፎች ምን ምን ተብለው ይጠራሉ?
2. ሁለት የዮሐንስ ወንጌል ዓላማዎችን ጥቀሱ።
3. ዮሐንስ ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት የሚያስረዱትን ጥቅሶች ጻፉ።
4. የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው ለማን ነበር?
5. ዮሐንስ ብቻ ካሠፈራቸው የኢየሱስ ሥራዎች አንዳንዶችን ዘርዝሩ
6. ኢየሱስ ከአይሁድ ወጐች ሁሉ በላይ መሆኑን የሚገልጹትን ሁኔታዎች ጥቀሱ።
7. ማቴዎስ ኢየሱስን መሢህ አድርጐ ሲያቀርበው ማርቆስ አገልጋይ አድርጐ ያቀርበዋል፤ ሉቃስ ደግሞ ፍጹም ሰው አድርጐ ያቀርበዋል ዮሐንስ ለኢየሱስ የሚሰጠው ልዩ መጠሪያ ስም ምንድንነው?
8. ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ የኢየሱስን የዘር ሐረግ ያላቀረበው በምን ምክንያት ይሆን?

## የቤት ሥራ

ለሚቀጥሉት ትምህርቶች ዝግጅት ዮሐንስ 6-10ን አንብቡ።

# ትምህርት አሥራ ስምንት

## የዮሐንስ ወንጌል አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የኢየሱስ ምፅዓት፤ 1፥1-18።
2. ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል በነበረው አገልግሎት አምላክነቱን ይመሰክራል፤ 1፥19-6፥71።
3. አይሁዶች ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ተጠራጠሩ ብሎም አልተቀበሉትም፤ 7፥1-11፥53።
4. ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በሕዝቡ መካከል የሚሰጠውን አገልግሎት ፈጸመ፤ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ 11፥54-12፥50 ማዕከላዊ ነጥብ ነው።
5. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለይቶ ለብቻቸው አስተማራቸው፤ 13፥1-17፥26።
6. ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው እግዚአብሔር መሆኑን ይመሰክራል፤ 18፥1-20፥31።
7. ከሞት የተነሣው የክርስቶስ የመጨርሻ መታየት ይገለጻል፤ 21፥1-25።

## በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1፡ 11-12፤ 2፡ 31፤ 3፡ 16-18፤ 6፡ 27፤ 14፡ 1-3፤ 16፡ 28 ናቸው።

# ትምህርት አሥራ ዘጠኝ

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለ ኢየሱስ አምላክነት የተጠቀሱ ብዙ ዓይነት ምስክርነቶች ይገኛሉ።

1. ስለ ኢየሱስ አምላክነት ቢያንስ ሰባት ሰዎች መስክረዋል።
   - ሀ/ መጥምቁ ዮሐንስ - 1፡ 29-36።
   - ለ/ እንድርያስ - 1፡ 41።
   - ሐ/ ፊልጶስ - 1፡ 45።
   - መ/ ናትናኤል - 1፡ 49።
   - ሠ/ ጴጥሮስ - 6፡ 68።
   - ረ/ ማርታ - 11፡ 27።
   - ሰ/ ቶማስ - 20፡ 28።
2. ኢየሱስ ራሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሰባት ጊዜ መስክሯል። ኢየሱስ «እኔ ነኝ» ብሎ በተናገረ ጊዜ በዘጸአት 3፡ 14-15 ላይ የሚገኘውን አሳብ ለማመልከት ሳይፈልግ አልቀረም።
   - ሀ/ «እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ» 6፡ 48።
   - ለ/ «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ» 8፡ 12።
   - ሐ/ «በሩ እኔ ነኝ» 10፡ 9።
   - መ/ «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» 10፡ 11።
   - ሠ/ «እኔ ትንሣኤና ሕይወት ነኝ» 11፡ 25።
   - ረ/ «እኔ መንገድ፥ እውነትና ሕይወት ነኝ» 14፡ 6።
   - ሰ/ «እኔ የወይን ግንድ ነኝ» 15፡ 5።
3. ኢየሱስ አምላክነቱን የሚያረጋግጡ ሰባት ታምራትን አድርጓል።
   - ሀ/ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል፤ 2፡ 1-12።
   - ለ/ የአንድ ሹም ልጅ ፈውሷል፤ 4፡ 46-54።
   - ሐ/ በቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ዳር ላይ የነበረውን ሰው ፈውሷል፤ 5፡ 1-27።
   - መ/ አምስት ሺህ ሰዎች መግቧል፤ 6፡ 1-14።
   - ሠ/ በባሕር ላይ ተራምዷል፤ 6፡ 15-21።
   - ረ/ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ፈውሷል፤ 9፡ 1-41።
   - ሰ/ አልዓዛርን ከሞት አስነሥቷል፤ 11፡ 1-44።

ከዚህ ትምህርት ቀጥሎ የሚቀርበውን ንድፍ ተመልከቱ። እነዚህን 21 ማረጋገጫዎች በአእምሮአችሁ መያዝ ይጠቅማችኋል።

4. በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ የኢየሱስን አምላክነት የሚያሳይ ነጥብ ይገኝበታል፡- 1፡ 49፤ 2፡ 11፤ 3፡ 16፤ 4፡ 26፤ 5፡ 25-26፤ 6፡ 33፤ 7፡ 37፤ 8፡ 58፤

9፡37፤ 10፡30፤ 11፡27፤ 12፡32፤ 13፡13፤ 14፡1፤ 15፡5፤ 16፡7፤ 17፡1፤ 18፡37፤ 19፡30፤ 20፡28፤ 21፡22። በእያንዳንዱ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ ራሱ ወይም ሌላ ሰው ስለ አምላክነቱ ምስክርነት ይሰጣል።

ዮሐንስ እንዳቀረበው የክርስቶስ አገልግሎት ንድፍ




በወንጌሉ ውስጥ ይህ ክፍል ማዕከላዊው ነጥብ ሊሆን ይችላል።

# ጥያቄዎች

1. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ስለ ኢየሱስ አምላክነት የመሰከሩትን የሰባት ሰዎች ስም ጥቀሱ።
2. ኢየሱስ ራሱን በማስመልከት ያቀረባቸው ሰባት ምስክርነቶች ምን ምንድናቸው?
3. የኢየሱስን አምላክነት የሚያመለክቱትን ሰባት ታምራት ጥቀሱ።
4. እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ራሱን «እኔ ነኝ» ብሎ ሲጠራ የነበረው ሁኔታ ምን ዓይነት ነበር?

# የቤት ሥራ

ዮሐንስ 11-15ን አንብቡ። በሚቀጥለው ገጽ ላይ ያለውን ንድፍ አጥኑ።



## በዮሐንው አንጌል ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ማመን፤ ከ90 ጊዜ በላይ ይገኛል።
2. ሕይወት ወይም የዘላለም ሕይወት።
3. ቃል።
4. እውነት እውነት።

ዮሐንስ ባቀረበው ዘገባ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ በዮሐ. 11፡54-12፡36 ተገልጿል። ኢየሱስ አምላክነቱን በትምህርቱና በታምራቱ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገልጽላቸው አይሁድ ተቃወሙት፤ ደግሞም የሚጠፋበትን መንገድ ማቀድ ጀመሩ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ በግልጽ በአይሁድ መካከል አልተመላለሰም። ሆኖም ደቀ መዛሙርቱን ማስተማር አላቋረጥን።

## ጥያቄዎች

1. የዮሐንስን ወንጌል አጠቃላይ አስተዋፅዖ አጥኑ።
2. ዮሐንስ ከቀረበው ከኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ ማዕከላዊውን ነጥብ አብራሩ።
3. ከዮሐንስ ወንጌል ጥቂት ቁልፍ ጥቅሶችን ጥቀሱ።
4. ከዮሐንስ ወንጌል ጥቂት ቁልፍ ቃላት ጻፉ።

## የቤት ሥራ

ዮሐንስ 16-21ን አንብቡ። በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የሚገኙትን ቁልፍ ጥቅሶች በቃላችሁ አጥኑ።

# ትምህርት ሃያ

1. በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ኢየሱስ የተጓዘባቸውን አውራጃዎችና አገሮች የሚያሳየውን ካርታ በማስተዋል ተመልከቱ። በተጨማሪ የጐበኛቸውን ዋና ዋና ከተሞች ትኩረት አድርጉባቸው። የእነዚህን አውራጃዎችና አገሮች አነስተኛ ንድፍ ለመንደፍ ተለማመዱ። ከካርታው ቀጥሎ በሚገኘው ገጽ ላይ ያለውን ሰንጠረዥ እየተመለከታችሁ እያንዳንዱ ምዕራፍ የሚገልጽውን ወቅት በማየት ኢየሱስ የት በታ እንደሆነ አስተውሉ።
2. ኢየሱስ ለሃይማኖት መሪዎች ከተናገራቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን ከሚከተሉት ጥቅሶች አንብባችሁ ተረዱ። የሃይማኖት መሪዎች እነዚህን ንግግሮች አንቀበልም ከማለታቸውም በላይ ኢየሱስን እንዲቃወሙ አደረጓቸው፤ ዮሐ.5፡17-18፤ 25-27፤ 42፤ 6፡26-27፤ 8፡44-45፤ 58-59። በዮሐንስ 1፡11-12 ላይ ኢየሱስ «የእርሱ ወደሆነው መጣ፤ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም» የሚል ዐረፍተ ነገር እናነባለን። የሃይማኖት መሪዎች ብሉይ ኪዳንን ያውቃሉ፤ ደግሞም ኢየሱስ «መሢሁን» ወይም

«የእግዚአብሔር ልጅ» ለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች ማቅረቡን አውቀዋል፤ ነገር ግን አልተቀበሉትም።

3. እነዚህን ጥቅሶች ልብ ብላችሁ ከተመለከታችሁ በኋላ ትርጉማቸውን ተወያዩበት፡-
   ሀ/ ዮሐ. 10፡10ን ከዮሐ. 7፡37-39 ጋር።
   ለ/ ዮሐ. 10፡28-29 ከዮሐ. 11፡25-26 ጋር።
   ሐ/ ዮሐ. 6፡27ን ከማቴ. 6፡19 ጋር።
   መ/ ዮሐ. 13፡10 ከ1ኛ ዮሐ. 1፡9 ጋር።
   ሠ/ ዮሐ. 16፡33ን ከ1ኛ ቆሮ.15፡24 ጋር።
4. በዮሐንስ 16፡8-14 ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ምን ምንድናቸው?
5. ኢየሱስ ለአማኞች የጸለየውን ጸሎት ዮሐንስ በምዕ. 17 ላይ ጽፎታል። ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑት የሚሰጣቸው ስጦታዎች ምን እንደሆኑ አስተውሉ፤ ዮሐ. 17፡2፤6፤26፤ 17፡8፤ 14፤ 17፡13፤22።



1. ኢየሱስ የተጓዘባቸው አራት አውራጃዎች ስም ጥቀሱ። ኢየሱስ የጐበኛቸው ዋና ዋና ከተሞች እነማን ናቸው?
2. የሃይማኖት መሪዎች ኢየሱስን እንዳይቀበሉ ያደረጋቸው መሠረታዊ ምክንያት ምንድነው?
3. ሦስቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ምን ምንድናቸው?
4. ኢየሱስ ለአማኞች ከሰጣቸው ስጦታዎች ጥቂቶቹ ምን ምንድናቸው? መልሳችሁን ከዮሐ. 17 አውጡ።

## የቤት ሥራ

ለፈተና ዝግጅት አራቱን ወንጌሎች ከልሱ።

| ፔሬያ | ይሁዳ | ሰማርያ | ገሊላ |
|---|---|---|---|
| | 1፡1—42 | | |
| | | | 1፡43—2፡12 |
| | 2፡13—3፡36 | | |
| | | 4፡1- 42 | |
| | | | 4፡43፡54 |
| | 5፡1—47 | | |
| | | | 6፡1—7፡9 |
| | 7፡10—10፡39 | | |
| 10፡40—11፡16 | | | |
| | 11፡17—20፡31 | | |
| | | | 21፡1—25 |

# ትምህርት ሃያ አንድ

## የአራቱ ወንጌሎች ክለሳ

| ማቴዎስ | ማርቆስ | ሉቃስ | ዮሐንስ |
|---|---|---|---|
| 1· ፀሐፊው — ማቴዎስ የተባለው ቀረጥ ሰብሳቢ አይሁዳዊ ሲሆን በኋላ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ሆኗል ።<br>2· የተፃፈበት ዘመን ከ50 — 80 ዓ· ም·<br>3· ኢየሱስ እንደ ንጉስ ወይም በተስፋ እንደተሰጠው «መሢህ» ተደርጐ ቀርቧል ።<br>4· የተፃፈው በተለይ ለአይሁዶች ነበር ። ብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳንን ያያይዛቸዋል ።<br>5· የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ በወንድ በኩል ያለው ወይም ንጉሳዊው ሲሆን ከመሢሁ ጋር የሚያያዝ ነበር ። የቀረበው ከልደቱ ታሪክ ጋር ነው ። | 1· ፀሐፊው — ማርቆስ ወይም ዮሐንስ ማርቆስ የተባለው ከጴጥሮስና ጳውሎስ ጋር ያገለግል የነበረው ነው ።<br>2· የተፃፈበት ዘመን ከ40 — 75 ዓ· ም·<br>3· ኢየሱስ የእግዚአብሔር አገልጋይ ተደርጐ ቀርቧል ።<br>4· የተፃፈው በተለይ ለሮማውያን ነበር ። ይህ መጽሐፍ በተግባር የተሞላ መጽሐፍ ነው ።<br>5· ምንም የትውልድ ሐረግ አልቀረበም ። ምክንያቱም ከዓላማው ጋር የሚስማማ አይደለም ። | 1· ፀሐፊው — ሉቃስ የተባለው ከአሕዛብ ወገን የሆነ ሐኪም ሲሆን የጳውሎስና የማርቆስ ጓደኛ ነበር ።<br>2· የተፃፈበት ዘመን 60 ዓ· ም· ገደማ ።<br>3· ኢየሱስ ፍፁም ሰውና «የሰው ልጅ» ተደርጐ ቀርቧል ።<br>4· የተፃፈው በተለይ ለግሪኮች ነበር ።<br>5· የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ከእውነተኛ የሥጋ ዝምድና በእናቱ በማርያም በኩል የሚመጣው ነው ። የቀረበው ከጥምቀቱ ታሪክ ጋር ነው ። | 1· ፀሐፊው — ዮሐንስ የተባለው «ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር» ነው ።<br>2· የተፃፈበት ዘመን ከ80 — 100 ዓ· ም·<br>3· ኢየሱስ «የእግዚአብሔር ልጅ» ተደርጎ ቀርቧል ።<br>4· የተፃፈው አይሁድና አሕዛብ እንዲያምኑና የተትረፈረፈ ሕይወት እንዲያገኙ ነበር ።<br>5· ምንም የትውልድ ሐረግ አልቀረበም ፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ልጅ መጀመሪያ የለውም ፤ እርሱ ከፍጥረት በፊት ነበረ ።<br>6· ዮሐንስ በኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ ያደረገው ፤ አይሁዶች የአምላክነቱን ምልክቶች ብዙዎቹን አንቀበልም |

6. በዚህ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ የሚሆነው ፤ ደቀ መዛሙርቱ እርሱ መሢህ እንደ ሆነ ሲመሰክሩ ነበር ፣ ማቴ. 16 ፣ 13—20 ።
7. «ቤተ ክርስቲያን» ግልፅ በሆነ መንገድ የሚጠቀሳት የማቴዎስ ወንጌል ብቻ ነው ፣ ማቴ. 16 ፣ 18 ፤ 18 ፣ 17 ።
8. ማቴዎስ የኢየሱስን ትምህርትና አገልግሎት በተመጣጣኝ ደረጃ ያቀርባል ።
9. ማቴዎስ ከሌሎቹ ወንጌል ፀሐፊዎች ይልቅ ከብሉይ ኪዳን በብዛት ይጠቅሳል ።
10. ማቴዎስ የኢየሱስን ዳግም ምፅዓት በሚመለከት ሰፊ ትምህርት ያቀርብልናል ።
11. ቁልፍ ቃላት ፦ ተፈፀመ — ጻድቅ — መንግሥት — የዳዊት ልጅ — የዘመን ወይም የዓለም ፍፃሜ የሚሉት ናቸው ።
12. ቁልፍ ጥቅሶች ፦
ማቴ. 1 ፣ 1 ፤ 2 ፣ 2 ፤ 28 ፣ 18 ናቸው ።

6. በዚህ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ የሚሆነው ፤ ደቀ መዛሙርቱን ለአገልግሎት ሲልክ ነበር ፣ ማር. 6 ፣ 7 — 13 ፣ 30 ፣ 31 ።
7. ኢየሱስ አናጢ እንደነበረ የሚናገር የማርቆስ ወንጌል ብቻ ነው ። ማር. 6 ፣ 3 ።
8. ማርቆስ ከኢየሱስ ትምህርት ይልቅ ሥራውን ያቀርባል ።
9. «ወንጌል» የሚለው ቃል ከሌሎቹ ወንጌሎች ይበልጥ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ተጠቅሷል ።
10. የማርቆስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌሎች መከከል አጭሩ ነው ።
11. ቁልፍ ቃላት ፦ ማገልገል ወይም መርዳት — ወዲያውኑ — በቀጥታ ወዘተ የሚሉት ናቸው ።
12. ቁልፍ ጥቅሶች ፦
ማር. 1 ፣ 35 ፤ 8 ፣ 34 — 37 ፤ 10 ፣ 29 — 30 ፣ 45 ናቸው ።

6. በዚህ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ የሚሆነው ፤ ኢየሱስ ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም ሲያቀና ነበር ፣ ሉቃስ 9 ፣ 51 ።
7. እረኞች በሕፃንነቱ ወቅት ኢየሱስን እንደጎበኙትና ስለ ልጅነቱ ወቅት የተረከው የሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው ፣ ሉቃስ 2 ፣ 8 — 20 ፣ 40 — 50 ።
8. ሉቃስ የኢየሱስን ፀሎቶች ብዙዎቹን ያቀርባል ።
9. ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ሁኔታ እንዳለቀሰ የሚነግረን የሉቃስ ወንጌል ብቻ ነው ።
10. የሉቃስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌሎች መከከል ረጅሙ ነው ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ረጅሙ መጽሐፍ ነው ።
11. ቁልፍ ቃል ፦
የሰው ልጅ የሚለው ነው ።
12. ቁልፍ ጥቅሶች ፦
ሉቃስ 2 ፣ 4 ፣ 52 ፤ 5 ፣ 32 ፤ 9 ፣ 62 ፤ 19 ፣ 10 ናቸው ።

ባሉበት ጊዜ ነበር ፣ ዮሐ. 11 ፣ 54 — 12 ፣ 50 ። ከዚህ በኋላ አይሁድ ሊገድሉት አቀዱ ፣ ዮሐ. 11 ፣ 54 ።
7. የአልዓዛርን ከሞት መነሳት የሚያቀርበው የዮሐንስ ወንጌል ብቻ ነው ፣ ዮሐ. 11 ፣ 1 — 45 ።
8. ዮሐንስ ረጃጅም የሆኑትን የኢየሱስ ስብከቶች በብዛት ያቀርባል ።
9. ኢየሱስ ከኒቆዲሞስ ጋር ያደረገውን ንግግር የሚነግረን የዮሐንስ ወንጌ ብቻ ነው ።
10. በዮሐንስ ወንጌል ምንም ምሳሌዎች አይገኙም ። በዮሐንስ ውስጥ የሚገኙት ታምራት በሌሎቹ ወንጌሎች ውስጥ ከሚገኙት ያንሳሉ ።
11. ቁልፍ ቃላት ፦
እመን — ሕይወት — ቃል — እውነት እውነት — የእግዚአብሔር ልጅ የሚሉት ናቸው ።
12. ቁልፍ ጥቅሶች ፦
ዮሐ. 1 ፣ 11 ፣ 12 ፤ 3 ፣ 16 — 18 ፤ 6 ፣ 27 ፤ 14 ፣ 1 — 3 ፤ 16 ፣ 28 ፤ 20 ፣ 31 ናቸው ።

## ለትምህርት ሃያ አንድ የተዘጋጁ የክለሳ ጥያቄዎች

1. አራቱ ወንጌሎች በተለይ የተጻፉላቸውን የተለያዩ ተቀባዮችን ስም ጻፉ።
2. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የኢየሱስ የትውልድ ሐረግ ያልቀረበው ለምንድነው? በማርቆስ ወንጌል ውስጥስ?
3. ማቴዎስ የኢየሱስን ሕጋዊ ወይም ንጉሣዊ የትውልድ ሐረግ ያቀረበው ለምንድነው?
4. በአራቱ ወንጌሎች ውስጥ የሚገኙትን የኢየሱስ አገልግሎት ማዕከላዊው ነጥብ አስፍሩ። በዚህ ነጥብ ላይ ኢየሱስ የአገልግሎቱን አቅጣጫ የለወጠበት ምክንያት ምንድነው? አስረጂ ጥቅስ ጭምር ስጡ።
5. ቤተ ክርስቲያንን ግልፅ በሆነ መንገድ የሚጠቅሳት የትኛው ወንጌል ነው?
6. የኢየሱስን ጸሎቶች በብዛት የሚያቀርበው የትኛው ወንጌል ነው?
7. የኢየሱስን ተግባር በብዛት የሚያቀርበው የትኛው ወንጌል ነው?
8. ብዛት ያላቸውን ረጃጅም ስብከቶች የሚያቀርበው የትኛው ወንጌል ነው?
9. የኢየሱስን ትምህርትና ተግባሮች በተመጣጠነ ሁኔታ የሚያቀርበው የትኛው ወንጌል ነው?
10. እያንዳንዱ ወንጌል የኢየሱስን አገልግሎት ለመጠቆም በተለያዩ ስሞች ተጠቅመዋል፤ እያንዳንዱ የተጠቀመበትን ስም ስጡ።
11. ከአራቱም ወንጌሎች አንድ አንድ ቁልፍ ቃል ጥቀሱ።
12. ከአራቱም ወንጌሎች አንድ አንድ ቁልፍ ጥቅስ ጥቀሱ።
13. ረጅሙ ወንጌል የትኛው ነው? አጭሩስ?
14. ስለ ኢየሱስ ዳግም ምፃት ሰፊ ትምህርት የሚያቀርበው የትኛው ወንጌል ነው?

## የቤት ሥራ

ከአራቱ ወንጌሎች ተውጣጥቶ ለሚቀርብላችሁ ፈተና ተዘጋጁ።

# ትምህርት ሃያ ሁለት

## ምክር ለመምህሩ

ከአራቱ ወንጌሎች አውጣጥተው ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑ።

ተማሪዎቹ የእስራኤልን ክፍለ አገሮች የሚያሳይ ቀላል ካርታ የመሳል ችሎታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፤ በተጨማሪ የአራቱን ወንጌሎች ይዘት ባጭሩ ማወቅ ይገባቸዋል።

## የቤት ሥራ

ለሚቀጥለው ትምህርት ዝግጅት የሐዋ. 1-7 አንብቡ። መምህር! ተማሪዎቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዳይሰለቹ ያነቃቁአቸው።

# ትምህርት ሃያ ሦስት

## የመጽሐፉ መሠረታዊ ነጥቦች

1. ጸሐፊው ሉቃስ ነበር። ሉቃስ ከጻፋቸው ሁለት መጻሕፍት መካከል የመጀመሪያው ወንጌሉ ነበር። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ የሉቃስ ስም ተጠቅሶ አይገኝም፤ ነገር ግን የሐዋ. 1፡1 ይህ መጽሐፍ የሉቃስ ወንጌል ተከታይ ክፍል እንደሆነ ያሳየናል። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ያለ ጥርጥር ሉቃስ ነው። በሉቃስ ወንጌል አጠቃላይ ጥናት ውስጥ የቀረቡትን ሐሳቦች ተመልከቱ።
2. የተጻፈበት ዘመን 65 ዓ.ም. ገደማ ነበር። የሐዋርያት ሥራ ጳውሎስ በእስር ቤት እንዳለ ይደመድማል። ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር ስለነበር በዚያ ዘመን ማለት ከ70 ዓ.ም. በፊት ስላለው ሁኔታ ይጽፋል። የሉቃስ ወንጌል የተጻፈው ከሐዋርያት ሥራ በፊት መሆኑ ግልጽ ነው። ሉቃስ የፊልጵስዩስ ተወላጅ ሲሆን የሐዋርያትን ሥራ የጻፈው ምናልባት ከጳውሎስ ጋር በሮም በነበረበት ዘመን ሳይሆን አይቀርም።

## የሐዋርያት ሥራ ዓላማዎች

1. የሐዋ. 1፡1 «ኢየሱስ ያደረገውንና ያስተምር ዘንድ ስለጀመረው ነገር ሁሉ ለማሳየት» በማለት የምጽሐፉን ዓላማ ያብራራል።
2. መጽሀፉ የመጀመሪያዎቹን 30 ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማለትም የወንጌልን ከኢየሩሳሌም እስከ ሮም መዳረስ ያቀርባል።
   ሀ/ ወንጌሎችን ከመልእክቶች ጋር ያያይዛል።
   ለ/ በክርስቶስ አገልግሎት ዘመንና በእኛ መካከል መሸጋገሪያ ድልድይ ያበጃል።
   ሐ/ የክርስትና ትምህርቶችንና ልማዶችን ያብራራል።

## የሉቃስ ምንጮች

1. በይሁዳ ስለሚገኙት ሰዎች አገልግሎት የተረዳው ከኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበር።
2. ስለ ሰማሪያውያን አገልግሎት የተረዳው ከፊልጶስ ነበር።
3. በሶርያ፥ በእስያ፥ በግሪክና በሮም ስለነበረው አገልግሎት የተረዳው ከጳውሎስ ወይም እርሱ ራሱ የጳውሎስ የሥራ ባልደረባ ስለ ነበር ከግል ልምምዱ ነበር።

## ከሐዋርያት ሥራ መልእክቶች ጋር ያለው ግንኙነት

1. የገላትያ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በአንጾኪያ፥ በኢቆንዮን፥ በልስጥራና በደርቤ ከነበረው አገልግሎት የተነሣ ነበረ፤ የሐዋ. 13፡14-14፡28።
2. የፊልጵስዩስ መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በፊልጵስዩስ በሰጠው አገልግሎት ምክንያት ነው፤ የሐዋ. 16፡11-40።

3. 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ የተጻፉት ጳውሎስ በተሰሎንቄ በሰጠው አገልግሎት ሳቢያ ነው፤ የሐዋ. 17፡1-9።
4. 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ የተጻፉት ጳውሎስ በቆሮንቶስ በሰጠው አገልግሎት ሳቢያ ነው፤ የሐዋ. 18፡1-16።
5. የኤፌሶን መልእክት የተጻፈው ጳውሎስ በኤፌሶን በሰጠው አገልግሎት ምክንያት ነው፤ የሐዋ. 19፡1-41፤ 20፡17፤35።

## ጥያቄዎች

1. የሐዋርያት ሥራ ከ70 ዓ.ም. በፊት መጻፉን በምን እናውቃለን?
2. የመጀመሪያዎቹ 30 ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማወቅ ለምን ይጠቅማል?
3. ሉቃስ የጥንቲቱን ቤተ ክርስቲያን ዝርዝር ታሪክ ሊያቀርብ የቻለበት ምክንያት ምንድነው?
4. የሐዋርያትን ሥራ መጻፉን የምናውቀው እንዴት ነው?
5. ጳውሎስ መልእክቶቹን የጻፈው ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

የሐዋ. 8-14ን አንብቡ።

# ትምህርት ሃያ አራት

1. ይህንን ካርታ በማጥናት ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያለውን ዕቅድ በአእምሮአችሁ ውስጥ አስቀምጡ። ንድፍ ወይም ቀላል ካርታ በመሳል በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ዘመን ወንጌል የተዳረሰባቸው ሥፍራዎች የትኞቹ እንደሆኑ ለማወቅ ሞክሩ።
2. የክርስቶስ ትዕዛዝ «በኢየሩሳሌም፥ በይሁዳ፥ በሰማርያ እስከ ምድር ዳር ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» የሚል ነበር፤ የሐዋ. 1፡8። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ወንጌል ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በይሁዳ በኩል እስከ ሮም ድረስ እንዴት እንደተዳረሰ እንመለከታለን። ከዚህ በላይ የሚገኘውን ካርታ ካጠናችሁ በኋላ እርሱን ሳትመለከቱ ሌላ ለመሥራት ተለማመዱ።
3. የሐዋ. ሥራን በምታነቡበት ጊዜ ይህንን የወንጌል መስፋፋት በአእምሮአችሁ ውስጥ ይዛችሁ 28 ቱን ምዕራፎች በእነዚህ ስድስት ክፍሎች ለመከፋፈል ሞክሩ። እነዚህን ክፍሎች ከጳውሎስ ወንጌላዊ ጉዞዎች ጋር ለማዛመድ አትጨነቁ።
4. በሐዋ. 15 የተመዘገበው ስብሰባ የሆነው በጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ መጨረሻ ላይ በ49 ዓ.ም. ነበረ። በዚህ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ውጥረት ተፈጥሮ ነበር። ይኸውም በአይሁድና በአሕዛብ እኩልነት ምክንያት ነበር፤ የሐዋ. 15ን አንብቡ።
5. የሐዋ. ሥራን በማንበብ ላይ እንዳላችሁ የዋና ከተሞችን ስምና የሚገኙበትን ሥፍራ ከካርታው ላይ ለማጥናት ሞክሩ፤ ለምሳሌ ኢየሩሳሌም፥ ደማስቆ፥ 2ቱ አንጾኪያዎች፥ ኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስ ወዘተ የሐዋ. ሥራን በምታጠኑበት ጊዜ <u>የሐዋርያት ሥራ መልክዓ ምድር</u> በተሰኘው መጽሐፍ ተጠቀሙ።




## ጥያቄዎች

1. ወንጌል የተዳረሰባቸውን 6 አገሮች በቅደም ተከተል ጻፉ።
2. በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውጥረት የፈጠረው ምንድነው? ይህንን ታሪክ የሚያቀርበው የትኛው ምዕራፍ ነው?
3. ቀላል ካርታ ሠርታችሁ 6ቱን አገሮች በየሥፍራቸው አስቀምጧቸው።

## ምክር ለመምህሩ

እርስዎ ደግሞ ሲያስተምሩ ይህንን ካርታ በቀላሉ ማድረግ ይኖርብዎታል፤ ከዚያም ተማሪዎቹም እንዴት መሳል እንደሚገባቸው ከተማሩ በኋላ በመጀመሪያ አገሮቹን፥ ቀጥሎ ዋና ከተሞቹን በተገቢ ሥፍራዎች ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።

## የቤት ሥራ

የሐዋ. 15-21ን አንብቡ። ካርታውንም አጥኑ።

# ትምህርት ሃያ አምስት

## የሐዋርያት ሥራ አጠቃላይ አስተዋፅዖ

ይህንን ክፍል በምታጠኑበት ጊዜ ባለፈው ትምህርት ውስጥ የተሰጠውን ካርታ አገናዝቡ።

1. የወንጌል ምስክርነት በኢየሩሳሌም በይሁዳ፤ የሐዋ. 1-7። ከይዘቱ ዋና ዋና ነጥቦች:-
   ሀ. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትዕዛዝ፤
   ለ. የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፤
   ሐ. በሐዋርያት በተለይም በጴጥሮስ የተሰጠው ምስክርነት፤
   መ. የጥንቲቱ ቤተ ክርስቲያን የነበራት ጥብቅ ሥነ ሥርዓት፤ ሐናኒያና ሰጲራ፤
   ሠ. ስደትና የእስጢፋኖስ ሞት ናቸው።
2. የወንጌል ምስክርነት በሰማርያና ከአርሷ ባሻገር፤ የሐዋ. 8-11። ይዘቱ ባጭሩ:-
   ሀ. ስደት ክርስቲያኖችን ሲበትናቸው ምስክርነት ያስፋፋል፤
   ለ. ፊልጶስ በሰማርያ፤ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ክርስቲያን፤
   ሐ. የጳውሎስ መለወጥ፤
   መ. የጴጥሮስ ራዕይና ለአሕዛብ ወንጌልን እንዲያደርስ የመጣበት ጥሪ፤
3. የወንጌል አገልግሎት በሶሪያዋ አንጾኪያና የጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ፤ የሐዋ. 12-14። ይዘቱ ባጭሩ:-
   ሀ. የተደራረበ ስደትና የጴጥሮስ ከእስር ቤት ነፃ መውጣት፤
   ለ. የሄሮድስ ሞት፤
   ሐ. ጳውሎስ ወደ እስያ ያደረገው የመጀመሪያ ጉዞ፤
4. የወንጌል ምስክርነት በእስያ፤ የሐዋ. 15-16። ይዘቱ ባጭሩ:-
   ሀ. በኢየሩሳሌም ተደርጎ የነበረው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የአሕዛብን እኩልነት የሚመለከት ስብሰባ ነበረ።
   ለ. በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረ ውጥረት እኩልነትን የሚመለከት ነበር።
   ሐ. ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ለማቋቋምና ለማጽናት በእስያ በኩል አድርጎ ወደ አውሮፓ ተጓዘ።
5. የወንጌል ምስክርነት በግሪክ አገር፤ የሐዋ. 17-21። ይዘቱ ባጭሩ:-
   ሀ. ጳውሎስ ያንን ሥፍራ ለቆ እንዲወጣ ያደረገው የተሰሎንቄ ብጥብጥ ነበረ።
   ለ. ጳውሎስ በአቴን አርዮስፋጎስ በተባለው ሥፍራ።
   ሐ. በቆሮንቶስ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች።
   መ. ጳውሎስ ለአገልግሎት ወደላካቸው ቤተ ክርስቲያን ወደ ሶሪያዋ አንጾኪያ ተመለሰ፤
   ሠ. ጳውሎስ በመቄዶንያና በግሪክ አገር።
   ረ. ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ይመለሳል።
6. የወንጌል ምስክርነት ወደ ሮም በተደረገው ጉዞ ላይ፤ የሐዋ. 22-28። ይዘቱ ባጭሩ:-
   ሀ. ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ሲታሠር ለተሰበሰቡት ሕዝብ ያቀረበው መከላከያ፤
   ለ. ጳውሎስ ወደ ቂሣርያ ሲወሰድ በዚያ በፊልክስ፥ በፊስጦስና በንጉሥ አግሪጳ ፊት ቀርቦ ይናገራል።
   ሐ. ጳውሎስ ወደ ሮም ይላካል፤ በባሕር የተነሣው ማዕበልና የመርከቡ መሰበር፤

መ. ጳውሎስ በመላጥያ የሰጠው ምስክርነት፤
ሠ. ጳውሎስ በሮም ለአይሁድና ለአሕዛብ የሰጠው ምስክርነት።

## የሐዋርያት ሥራ የዘመን ቅደም ተከተል

### 35-45 ዓ.ም.

ዋና ዋና ድርጊቶች የሚከተሉት ናቸው:-

1. የመንፈስ ቅዱስ መውረድ፤
2. በኢየሩሳሌም የተደረገው ምስክርነትና የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን አጀማመር፤
3. የጴጥሮስ አገልግሎትና የቤተ ክርስቲያን ዕድገት፤
4. የቤተ ክርስቲያን ስደትና የእስጢፋኖስ ሞት፤
5. የጴጥሮስ ራዕይና ወንጌልን ለአሕዛብ እንዲያደርስ የመጣለት ጥሪ፤
6. ፊልጶስ ወንጌልን ወደ ሰማርያ ይወስዳል፤ የኢትዮጵያዊው መለወጥ።

### 45-55 ዓ.ም.

1. ጳውሎስ የርዳታ ገንዘብ ወደ ኢየሩሳሌም ማድረሱ፤
2. የጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ፤
3. ጳውሎስ በቆሮንቶስ፤ የጳውሎስ 2ኛ ወንጌላዊ ጉዞ፤
4. የጳውሎስ 3ኛ ወንጌላዊ ጉዞ።

### 55-65 ዓ.ም.

1. የጳውሎስ በኢየሩሳሌም መያዝ፤
2. የጳውሎስ በቂሣርያ መታሠር፤
3. ጳውሎስ በሮም 2 ጊዜ በእስር ቤት ውስጥ መታሠር፤
4. የጳውሎስ ሞት፤ ሰማዕትነቱ።

## ጥያቄዎች

1. የሐዋርያትን ሥራ ስድስት ክፍሎች ከነምዕራፎቻቸው አቅርቡ።
2. ሦስቱን የሐዋርያት ሥራ የዘመን ቅደም ተከተል ክፍሎች አቅርቡ፤ ደግሞም በእያንዳንዱ ክፍል የተደረጉትን ነገሮች አጥኑ።

## የቤት ሥራ

የሐዋርያትን ሥራ 22-28ን አንብቡ።

# ትምህርት ሃያ ስድስት

## የሐዋርያት ሥራ ዋና ዋና ነጥቦች

| | ለአይሁድ | ለአሕዛብ |
|---|---|---|
| ስብከቶች | 1. ጴጥሮስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ፣ 2 ፣ 14 — 41 ።<br>2. ጴጥሮስ የቆሎ ከ.ዳኖችን ፍፃሜ በሚመለከት የሰበከው ስብከት ፣ 3 ፣ 5 — 12 ።<br>3. ጴጥሮስ በከፍተኛ የፍርድ ሸንጐ ፊት ያቀረበው ስብከት ፣ 4:5-12<br>4. እስጢፋኖስ በከፍተኛ የፍርድ ሸንጐ ፊት ያቀረበው ስብከት ፣ 7 ፣ 1 — 53 ። | 5. ጴጥሮስ በቆርነሌዎስ ቤት ፣ 10 ፣ 34 — 43 ።<br>6. ጳውሎስ በእምነት ስለመጽደቅ ያቀረበው ፣ 13 ፣ 16 — 41 ።<br>7. ጳውሎስ ከኤፌሶን ሽማግሌዎች ጋር ያደረገው መሠነባበቻ ፣ 10 ፣ 17 — 35 ።<br>8. ጳውሎስ በአርዮስፋጐስ ፣ 17 ፣ 20 — 31 ። |
| | 9. ጳውሎስ ለሕዝቡ ያቀረበው መከላከያ ፣ 22 ፣ 1 — 21 ። | 10. የጳውሎስ መከላከያ በፊልክስ ፊት ፣ 24 ፣ 10 — 25 ። |
| | 11. ጳውሎስ በአግሪጳ ፊት ያቀረበው መከላከያ ፣ 26 ፣ 1 — 23 ። | |
| ጉዞዎች | 1. ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ያደረገው ፣ 8 ፣ 5 — 25 ። | 2. ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ለማስተማር ወደ ጋዛ ያደረገው ፣ 8 ፣ 26 — 39 ። |
| | 3. ፊልጶስ ወደ ቂሳርያ ያደረገው ፣ 8 ፣ 40 ።<br>4. ጴጥሮስ ወደ ልዳ ያደረገው ፣ 9 ፣ 32 ።<br>5. ጴጥሮስ ወደ ኢዮጴ ያደረገው ፣ 9 ፣ 36 ። | |

| | ለአይሁድ | ለአሕዛብ |
|---|---|---|
| ጉዞዎች | | 6. ጴጥሮስ በቂሳርያ ወደሚገኘው ወደ ቆርነሌዎስ ቤት ያደረገው፣ 10፣23—33።<br>7. የጳውሎስ የመጀመሪያ ወንጌላዊ ጉዞ፣ 13—14።<br>8. የጳውሎስ ሁለተኛ ወንጌላዊ ጉዞ፣ 15፣36—18፣22።<br>9. የጳውሎስ ሦስተኛ ወንጌላዊ ጉዞ፣ 18፣23—21፣14።<br>10. ጳውሎስ ወደ ሮም ያደረገው ጉዞ፣ 23፣23—28፣16። |
| ግጭቶች | 1. ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ከሃይማኖት መሪዎች ጋር የፈጠረው፣ 4፣1—4፣13—22።<br>2. ሐዋርያት ከካህናትና ከሰዱቃውያን ጋር የፈጠሩት፣ 5፣17—22።<br>3. እስጢፋኖስ ስለሰበከ በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ፣ 7፣54—60።<br>4. ጴጥሮስ ታሰረ፣ ያዕቆብ ደግሞ በሄሮድስ ተገደለ፣ 12፣1—19። | 5. ጳውሎስ ከጠንቋዩ ከኤልማስ ጋር ያደረገው ግጭት፣ 13፣6—13።<br>6፡ ጳውሎስ በልስጥራ በድንጋይ ተወገረ፣ 14፣19—20።<br>7. ጳውሎስና ሲላስ በፊልጵስዩስ ተደበደቡ፣ 16፣16—34።<br>8. በኤፌሶን የተነሳው ሁከት፣ 19፣23—41። |

| | ለአይሁድ | ለአሕዛብ |
| --- | --- | --- |
| | 9. ጳውሎስ በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ ተያዘ፤ 21፡27—30። | |
| ታምራት | 1. የሐዋርያት በበዓለ ሃምሳ ቀን በልሳን መናገር፤ 2፡4—13።<br>2. አንካሳው ሰው በጴጥሮስ አማካይነት ተፈወሰ፤ 3፡1—11።<br>3. በሐዋርያት አማካይነት ብዙዎች ተፈወሱ፤ 5፡12—16።<br>4. ሽባው ሰው በጴጥሮስ አማካይነት ተፈወሰ፤ 9፡32—35።<br>5. ዶርቃ ከሞት ተነሳች፤ 9፡36—42።<br>6. የጴጥሮስ ራእይ፤ 10፡9—15።<br>7. ጴጥሮስ ከእስር ቤት ነፃ ወጣ፤ 12፡5—19። | 8. ሽባው ሰው በልስጥራ በጳውሎስ አማካይነት ተፈወሰ፤ 14፡6—10።<br>9. ጳውሎስ አጋንንትን አስወጣ፤ 16፡16—18።<br>10. በምድር መናወጥ የእስር ቤቱ ደጆች ተከፈቱ፤ 16፡25—29።<br>11. በኤፌሶን ብዙዎች በጳውሎስ አማካይነት ተፈወሱ፤ 19፡11—17።<br>12. ጳውሎስ በጢሮአዳ አውጤኪስን ከሞት አዳነው፤ 20፡8—12።<br>13. ጳውሎስ በመላጥያ በእባብ ሲነደፍ አልተጎዳም፤ 20፡1—6። |

| ዋና ዋና ሰዎች | ለአይሁድ | ለአሕዛብ |
|---|---|---|
| | 1. ጴጥሮስ ፣ 2 ፣ 14 — 15 ፣ 11 ።<br>2. ዮሐንስ ፣ 4 ፣ 13 — 22 ።<br>3. ሃናንያና ሰጲራ ፣ 5 ፣ 1 — 11 ።<br>4. ገማልያል ፣ 5 ፣ 33 — 39 ።<br>5. እስጢፋኖስ ፣ 6 ፣ 5 — 7 ፣ 60 ።<br>6. ጳውሎስ ፣ 8 ፡ 3 ፤ 9 ፣ 1 — 28 ፣ 31 ።<br>7. ፊልጶስ ፣ 8 ፣ 5 — 40 ። | |
| | | 8. ኢትዮጵያዊው ሰው ፣ 8 ፣ 26 — 39 ።<br>10. ቆርኔሌዎስ ፣ 10 ፣ 1 — 8 ፣ 19 — 48 ። |
| | 9. ዶርቃ ፣ 9 ፣ 36 — 40 ። | |
| | 11. በርናባስ ፣ 11 ፣ 30 ፤ 12 ፣ 24 ፤ 13 ፣ 1 — 15 ፣ 41 ።<br>12. ዮሐንስ ማርቆስ ፣ 13 ፣ 5 ፣ 13 ፤ 15 ፣ 37 — 39 ።<br>13. ሲላስ ፡ 15 ፣ 32 ፣ 40 ፤ 16 ፣ 19 ፣ 25 — 17 ፣ 4 10 ፣ 15 ፤ 18 ፣ 5 ። | |
| | | 14. ጢሞቴዎስ ፣ 16 ፣ 1 — 5 ፤ 17 ፣ 15 ፤ 18 ፣ 5 ።<br>15. ልድያ ፣ 16 ፣ 14 ፣ 15 ።<br>16. ሉቃስ ፣ 16 ፣ 10 ፤ 20 ፣ 6 ፣ 13 — 21 ፣ 17 ። |
| | ማሳሰቢያ ፦<br>በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ጴጥሮስና ጳውሎስ በድርጊት ላይ የሚታዩ ዋነኞቹ ሰዎች ናቸው ። | «እኛ» የሚለው ቃል ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር አብሮ እንደነበረ ይጠቁማል ።<br>17. አቂላና ጵርስቅላ ፣ 18 ፣ 2 ፣ 18 ፣ 19 ፣ 26 ።<br>18. ፊልክስ ፣ 24 ፣ 14 — 27 ።<br>19. ፊስጦስ ፣ 25 ፣ 1 ።<br>20. አግሪጳ ፣ 25 ፣ 23 — 26 ፣ 1 ፣ 27 ፣ 32 ። |

| | የአይሁድ | የአሕዛብ |
|---|---|---|
| በጣም ጠቃሚ የሆኑ ሁኔታዎች | 1. መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት ድፍረትና ኃይል ሰጣቸው፡ 2፡1—4። | |
| | 2. በስደት ሳቢያ የወንጌል መስፋፋት፡ 8፡1። | |
| | 3. የጳውሎስ መለወጥ፡ ከዚህ በኋላ ለአሕዛብ ታላቅ መልእክተኛና ቤተ ክርስቲያን መስራች ሆነ፡ 9፡1—16። | |
| | | 4. የኢትዮጵያዊው መለወጥ፡ ምስክርነት ለአፍሪካ፡ 8፡26—40። |
| | 5. እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለውን ፈቃድ ያረጋገጠው የጴጥሮስ ራእይ፡ 10፡1—48። | |
| | 6. በኢየሩሳሌም የነበረው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፡ 15። | |
| | 7. መቄዶኒያዊው ለጳውሎስ ያደረገለት ጥሪ፡ 16፡9። | |
| | | 8. ጳውሎስ በሮም ሰበከ፡ 28፡16—31። |

ከዚህ የሚከተለው ዝርዝር በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ስሞቻቸው የተጠቀሱ ከተሞችና ደሴቶች ነው። የሐዋርያት ሥራን መልከዓ ምድር ካጠናችሁ በኋላ እነዚህን ሥፍራዎች በተገቢ ቦታቸው ለማስቀመጥ ሞክሩ። የሐዋርያትን ሥራ ስታነቡ ካርታውን መመልከት መልካም ነው። በአንዳንዱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች በስተጀርባ ካርታዎች ይገኛሉ።

| የአይሁድ | የአሕዛብ |
|---|---|
| 1. ኢየሩሳሌም ፥ 1 ፥ 12 ፤ 8 ፥ 1 ፤ 11 ፥ 27 ። | 7. የሶሪያዋ አንጾኪያ ፥ 11 ፥ 19 — 27 ፤ 14 ፥ 26 ። |
| 2. ሰማርያ ፥ 8 ፥ 5 ። | 8. ጴርጌን ፥ 14 ፥ 25 ። |
| 3. ደማስቆ ፥ 9 ፥ 2 — 22 ። | 9. የጲስድያዋ አንጾኪያ ፥ 13 ፥ 14 ። |
| 4. ኢዮጴ ፥ 9 ፥ 36 ፤ 10 ፥ 8 ፥ 23 ። | 10. ልስጥራ ፥ 14 ፥ 6 — 20 ፤ 16 ፥ 1 ። |
| 5. ቂሳርያ ፥ 10 ፥ 24 ፤ 21 ፥ 8 ። | 11. ደርቤ ፥ 14 ፥ 6 ፥ 20 ፤ 16 ፥ 1 ። |
| 6. ጢሮስ ፥ 21 ፥ 3 ። | 12. ኤፌሶን ፥ 19 ፥ 1 ፥ 26 ። |
| | 13. ቆሮንቶስ ፥ 18 ፥ 1 ። |
| | 14. አቴን ፥ 17 ፥ 16 ፥ 22 ። |
| | 15. ተሰሎንቄ ፥ 17 ፥ 1 ፥ 11 ። |
| | 16. ፊልጵስዩስ ፥ 16 ፥ 12 ። |
| | 17. ጢሮአዳ ፥ 16 ፥ 8 ፥ 9 ፤ 20 ፥ 6 ። |
| | 18. ትያጥሮን ፥ 16 ፥ 14 ። |
| | 19. ጠርሴስ ፥ 21 ፥ 39 ። |
| | 20. ቤሪያ ፥ 17 ፥ 10 ፥ 13 ። |
| | 20. ቤሪያ ፥ 17 ፥ 10 ፥ 13 ። |
| | 21. ሚሊጢኒ ፥ 20 ፥ 15 ፤ 28 ፥ 1 ። |
| | 22. ሮም ፥ 28 ፥ 14 — 16 ፥ 30 ። |
| | 23. ቆጵሮስ ፥ 4 ፥ 36 ፤ 13 ፥ 4 ፤ 15 ፥ 40 ። |
| | 24. ኢቆንዮን ፥ 14 ፥ 1 ፥ 21 ። |

## ጥያቄዎች

1. ከሐዋርያት ሥራ ሦስት ዋና ዋና ስብከቶችን ጥቀሱ።
2. በቀደሙት ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ግጭት ነበር? እግዚአብሔር ይህንን ግጭት እንዴት አድርጐ ተጠቀመበት?
3. ከሞት ስለተነሡ ሰዎች ሁለቱን ተዓምራት ጥቀሱ።
4. በቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑት ሁለት ሰዎች ማንና ማን ነበሩ?
5. ከሐዋርያት ሥራ ቁም ነገሮች በርከት አድርጋችሁ ጥቀሱ።

## የቤት ሥራ

ሮሜ 1-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሃያ ሰባት

## የሮሜ መልእክት መግቢያ፤ የመጽሐፉ መሠረታዊ ነጥቦች

1. ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው።
2. የተጻፈበት ዘመን 57 ዓ.ም. ገደማ ነው።
3. ይህ መልእክት የተጻፈው ምናልባት ጳውሎስ በሦተኛው ወንጌላዊ ጉዞው መጨርሻ ላይ በቆሮንቶስ በነበረበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም፤ የሐዋ. 20፡2-3ና ሮሜ 15፡19። የክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነችው ፌበን ደብዳቤውን የምታደርስለት መልክተኛው እንደሆነች ጽፏል፤ ሮሜ 16፡1-2። ክንክራኦስ በቆሮንቶስ አጠገብ የምትገኝ ከተማ ናት።

## የሮሜ መልእክት ዓላማ

1. ጳውሎስ ከኢየሩሳሌም መልስ ወደ ሮምና እስፔን የመሄድ ዓላማ ስለነበረው ለሚያደርገው ጉብኝት በሮም የሚገኙትን አማኞች ለማዘጋጀት ፈልጐ ነበረ፤ ሮሜ 15፡24።
2. ጳውሎስ በግሪክና እስያ የነበረው አገልግሎት እንዳበቃ ተሰምቶታል፤ ሮሜ 15፡23። ሆኖም በኢየሩሳሌም እሞት ይሆናል የማለት ሥጋት ስላደረበት በሮም ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ስለ ክርስትና እምነት ሰፊ ገለጻ ሊያደርግላት እንደሚገባው ያውቅና ይፈልግ ነበር።
3. ጳውሎስ ለሮም ክርስቲያኖች እንደሚጸልይላቸው አስረግጦ በመንገር ሊያበረታታቸው ይፈልጋል፤ ሮሜ 1፡9።

## የሮሜ መልእክት ልዩ ባህርያት

1. ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህንን መጽሐፍ ወደር የሌለው የክርስትና እምነት ማብራሪያ አድርገው ይገምቱታል።
2. ጳውሎስ የሚጽፍላቸውን ሰዎች ከዚህ በፊት የማያውቃቸው መሆኑንና ላልመሠረታት ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ረጅሙ መግቢያ ያመለክታል።
3. ይህ መልእክት ደብዳቤ ሳይሆን ትምህርት መሰል ነው።
4. መለኮታዊው ትምህርት በክርክር መልክ ቀርቧል።
5. በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ተጠቅሰዋል።
6. በመጽሐፉ መደምደሚያ ላይ ሐዋርያው ሰላምታ የላከላቸው ሰዎች ረጅም የስም ዝርዝር ይገኛል።

## በሮሜ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

ወንጌል፣ ሕግ፣ ኃጢአት፣ ሥጋ፣ ጽድቅ፣ መንፈስ፣ እምነት፣ አሕዛብ፣ ፀጋ፣ አይሁድ ወይም እስራኤል ናቸው።

## በሮሜ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. ሮሜ 3፡10-12-ስለ ሰው ኃጢአተኝነት የቀረበ ሐተታ።
2. ሮሜ 5፡1፤8፤ 6፡23-ስለ ሰው ደኅንነት እግዚአብሔር ያለው ዓላማ።
3. ሮሜ 7፡24-ራሱን ለማጽደቅ የሰው ጥረት ከንቱነት።
4. ሮሜ 8፡1-ሰው በክርስቶስ ያለው ተስፋና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ።
5. ሮሜ 8፡28-የእግዚአብሔር ገናናነት።
6. ሮሜ 10፡9፤ 10፤ 17-በክርስቶስ ማመን የእርሱን አዳኝነት መመስከርን ያጠቃልላል።
7. ሮሜ 11፡33-ከሁሉ የሚበልጠው የእግዚአብሔር ጥበብ።
8. ሮሜ 12፡1-2-በድል ሕይወት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ።
9. ሮሜ 14፡12-አማኝ ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል።
10. ሮሜ 15፡1-የክርስቲያን ኃላፊነት።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ለሮም ቤተ ክርስቲያን የጻፈበትን ሁለት ምክንያቶች ጥቀሱ።
2. ጳውሎስ ሮምን የሚጐበኝባቸው ዓላማዎች ምን ምንድናቸው?
3. ጳውሎስ እስካሁን ሮምን ያልጐበኘው ለምንድነው?
4. ቁልፍ ጥቅሶችን አስተውሉ፤ የተቻላችሁን ያህል በቃላችሁ አጥኑ።

## የቤት ሥራ

ሮሜ 5-6 አንብቡ።

# ትምህርት ሃያ ስምንት

## የሮሜ መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የሰው ኃጢአተኝነትና በኃጢአት ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ፤ 1፡1-3፡20።
2. ሰውን ከኃጢአት ለማዳን እግዚአብሔር ያከናወነው ተግባር፤ 3፡21-6፡23።
3. የአሮጌውና የአዲሱ ተፈጥሮ ግጭትና በክርስቶስ ያገኘነው ድል፤ 7-8። የሮሜ መልዕክት ማዕከላዊው ነጥብ በምዕ. 7 መጨርሻና በምዕ. 8 መጀመሪያ ላይ ነው።
4. እግዚአብሔር ለአይሁድ ያለው ዓላማ፤ 9-11።
5. የክርስትና ሕይወት መመሪያ ደንቦች፤ 12-15።
6. የጳውሎስ ሰላምታና የመጨረሻ ትዕዛዞች፤ 16።

## የሮሜ መልእክት ንድፍ፡




## የመልእክቱ ይዘት ባጭሩ

1. ሮሜ 1-3 የሰውን ኃጢአተኛ ባሕርይ ገልጦ ያሳያል። በንድፍ ላይ «የሰው የማሽቆልቆል ጕዳና የእግዚአብሔር አፀፋ» የሚለውን ተመልከቱ። እግዚአብሔር ለሰው ስለ ራሱ በቂ የሆነ ራዕይና ምስክርነት ሰጥቷል፤ ነገር ግን አይሁድና አሕዛብ ሁለቱም እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሰጣቸውን ራዕይ አንቀበልም በማለታቸው ዓለም በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ ሆነ።
2. ሮሜ 4-6 ከክርስቶስ ውጪ ሰው ተስፋ ቢስ እንደሆነ ይተነትናል።
   ሀ/ ሰዎች ሁሉ የአዳም ቤተሰብ ስለሆኑ ኃጢአተኞች ናቸው፤ 5፡12።
   ለ/ የአሪት ሕግ ሰዎችን ሊያድን አይችልም፤ ይፈርድባቸዋል፤ 5፡20፤ 7፡5።
   ሐ/ የኃጢአት ዋጋ ሞት ነው፤ የእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው፤ 6፡23።

# የሰው የማሽቆልቆል ጉዳናና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እርምጃ
# የሰጠው አጸፋ ሮሜ 1

**የሰው የማሽቆልቆል ጉዳናና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እርምጃ የሰጠው አፀፋ ሮሜ 1**

1. ሰው የእግዚአብሔርን ክብር ለጣዖታት አምልኮ ለወጠ ፡ 1 ፡ 23 ።

   → እግዚአብሔር ለክፉ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ፡ 1 ፡ 24 ።

2. ሰው የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ለወጠ ፡ 1 ፡ 25 ።

   → እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው ፡ 1 ፡ 26 ።

3. ሰው የተፈጥሮ የፆታ ግንኙነትን ለወጠ ፡ 1 ፡ 26 ፡ 27 ።

   → እግዚአብሔር ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው ፡ 1 ፡ 28 ።

3. ሮሜ 7-8 በኃጢአት ላይ ያለውን ግጭትና የሰላምን ምንጭ ይተነትናል።
   ሀ/ ሰው በደካማነቱ የእግዚአብሔርን ጻድቅ ሕግ ሊጠበቀው እንደማይችል 7:7-10 ያስረዳል።
   ለ/ የአማኙ አዲስ ተፈጥሮ እግዚአብሔርን መታዘዝ ይፈልጋል፤ የአሮጌ ሥጋው ተፈጥሮ ግን ያሸንፈዋል። ስለዚህ በመካከላቸው የማያቋርጥ ጦርነት አለ፤ 7:15።
   ሐ/ «ማን ያድነኛል» ብሎ በልቡ ሲጮህ እግዚአብሔርም ወዲያውኑ ሊያድነው ይችላል፤ 7:24።
   መ/ ሰው ከፍተኛ ኃይል እንደሚያስፈልገው ተረድቶ የራሱን የግል ፕረት በውስጡ ለሚኖረው ለመንፈስ ቅዱስ በሚተውበት ወቅት ነፃነትን ይጐናፀፋል፤ 8:1-2።
   ሠ/ ከክርስቶስ ፍቅር ማንም ሊለየን እንደማይችል የሚያረጋግጥ ዋስትና መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጠን ነፃነት ጋር እናገኛለን። የዚህም ውጤት ሰላም ነው፤ 8:18-25። የመጀመሪያዎቹ ሁለት የሮሜ ክፍሎች ግጭትን የሚመለከቱ ናቸው፤ ምዕ. 1-3ና ምዕ. 4-6። ከዚያም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ግጭት ወደ ሰላም ይለወጣል፤ 7-8። የመጨረሻዎቹ ሁለት ክፍሎች ከኃይልና ከሰላም ጋር የተያያዙ ናቸው፤ 9-15።
4. ሮሜ 9-11 አይሁድን በሚመለከት የእግዚአብሔር ቃል ተሽሯል? አልተሻረም። ሰው ምንም ደካማ ቢሆን እግዚአብሔር ታማኝ ነው። እግዚአብሔርን የማወቅ ልዩ መብት ተሰጥቷቸው የነበሩት አይሁድ በኃጢአታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ሁላቸውንም እንዳሉ ለተወሰነ ጊዜ ትቷቸዋል፤ ሆኖም እግዚአብሔር አልረሳቸውም። ለእነርሱ ያለውንም ዓላማ ወደፊት ይፈጽመዋል። እግዚአብሔር ገናና ሲሆን ሁሉንም ነገር የሚፈጽመው ለሰው ጥቅም ነው።
5. ሮሜ 12-15 በሰው ውስጥ የሚኖረውን የመንፈው ቅዱስን የሥራ ውጤት ያሳያል። ይህም በሮሜ 7ና 8 ውስጥ ያለው ነፃ አውጪ ኃይል በተግባር መግለፅ ነው።
   ሀ/ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሲሰጡ እርሱ ለአገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን የመንፈስ ስጦታዎች ይሰጣቸዋል።
   ለ/ ከሌሎች ክርስቲያኖችና ከማያምኑ ሰዎች ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት ማድረግና ለመንግሥት ባለ ሥልጣኖች መታዘዝ ተግባራዊ የክርስቲያን አገልግሎት ነው።
   ሐ/ ተግባራዊ የክርስቲያን አኗኗር በሌሎች ላይ የሚፈርድ ሳይሆን በእምነት ደካማ የሆነውን ወንድም የሚደግፍ ነው።
6. ሮሜ 16 የጳውሎስን ሰላምታ ያቀርባል።

## ጥያቄዎች

1. የሮሜ መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ ከነምዕራፎቹ አሥፍሩ።
2. ሰው ላቀረበለት ተቃውሞ የእግዚአብሔር መልስ ምንድነው?
3. በሮሜ 1-7 የሚገኘው የግጭቱ መነሾ ምንድነው?
4. ሰዎች እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሰላም የሚያገኙት እንዴት ነው?
5. በክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት የክርስቶስ ድል የተገለፀባቸውን መንገዶች ጻፉ።

## <u>የቤት ሥራ</u>

ሮሜ 9-12ን አንብቡ።

# ትምህርት ሃያ ዘጠኝ

## <u>የሮሜ መልዕክት ማዕከላዊ ነጥብ</u>

1. የመጀመሪያዎቹን ስድስት ምዕራፎችና እንዲሁም ከ9-15 ያሉትን ምዕራፎች ወደኋላም ሆነ ወደፊት ለመመልከት ሮሜ 7ና 8 ምቹ ምዕራፎች የሆኑት ለምንድነው?
   ሀ/ <u>የልብ ጩኸት</u>፦ 7፡24 «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ፤ ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?» ይህ በሮሜ 1-3 ውስጥ የሰው ዕርዳታ የማጣት ሁኔታ ውጤት ነው።
   ለ/ <u>መልስ</u>፦ 8፡1 «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም፤ ይህ በሰው ውስጥ የሚኖረው ከኃጢአት ጋር በሚደረገው ጦርነት ኃይልን የሚሰጠው የመንፈስ ቅዱስ የሥራ ውጤት ሲሆን ሰው በሮሜ 4-6 ውስጥ የሚገኘውን የማጽደቅ ሥራ እንዲለማመድና በህይወቱ ውስጥም ተግባራዊ እንዲሆን ይረዳዋል።
   ሐ/ <u>ዋስትና</u>፦ ዓለም ሳይፈጠር በፊት እግዚአብሄር ለሰው የነበረውን ዕቅድና ዓላማ ሮሜ 9-11 ይገልፃል። በሮሜ 8፡1ና 11 ላይ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ ለሰው ኃይልን በመስጠት በኃጢአት ላይ ድል አድራጊ ሕይወት እንዲኖር ያደርገዋል። ሰው ይህንን ኃይል የሚገኘው በውስጡ ለሚኖረው ለመንፈስ ቅዱስ ራሱን በሚያስረክብበት ጊዜ ነው።
2. ሮሜ 7 ክርስቶስ ለሰው የፈጸመው ድል መፈተኑን ያቀርባል።
   ሀ/ 7፡1-15 በክርስቶስ የሚያምን ለአሪት ሕግ የሞተ ነው። የአሪት ሕግ ቅዱስ ነው፤ ነገር ግን ሰው በክርስቶስ ውስጥ እስከሆነ ድረስ በሕግ ፍርድ በታች አይደለም።
   ለ/ 7፡16-24 አማኝ አሁንም የሚመላለሰው በሥጋዊ አካል ነው። የሥጋ ወይም የአሮጌው ተፈጥሮ ምኞቶች በክርስቶስ ከተገኘው ከአዲሱ ሕይወት ተፈጥሮ ምኞቶች ጋር ጦርነት ማድረግ አያቋርጡም።
   ሐ. በክርስቶስ በኩል አማኝ የእግዚአብሔርን ሕግ ይወዳል፤ ነገር ግን የመታዘዝ ኃይል ያጥረዋል።
3. አማኝ ሥጋን ድል የሚያደርግበት መንገድ፦
   ሀ/ ክርስቶስ ለእኛ ሲል ኃጢአታችን ሊሸከም መጣ፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡24። የነበረብንን ኩነኔ አስወገደልን፤ 8፡1።
   ለ/ የአማኝ የኃይል ምንጭ የሆነው መንፈስ ቅዱስ በኃጢአት ላይ ድልን ያስገኛል፤ 8፡9-13።
   ሐ/ አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ከክርስቶስ ጋር ወራሽ ነው፤ 8፡14-17፤ ገላ. 4፡4።
   መ/ አማኝ ከዚህ ሕይወት ፈተናና መከራ በኋላ ፍጹም ነፃነት የሚያገኝ መሆኑ ተስፋ ተሰጥቶታል፤ 8፡18-25።
   ሠ/ አማኝ አሁን ስለ እርሱ የሚማልድ መንፈስ ቅዱስ አለው፤ 8፡26-27።

ረ/ አማኝ እግዚአብሔር በሕይወት ውስጥ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ እርሱ ክርስቶስን እንዲመስል ለመለወጥ በማሰብ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ዋስትና አለው፤ 8፡28።

ሰ/ አማኝ ምንም ነገር ከክርስቶስም ፍቅር እንደማይለው የሚያረጋግጥ ዋስትና አለው፤ 8፡29-39።

<u>ሦስት መልክ ያለው የእግዚአብሔር ማዳን</u>

| ያለፈ | የአሁን | የወደፊት |
|---|---|---|
| ሰው በክርስቶስ ሆኖ ከኃጢአት ክስና ኩነኔ ድኗል፣ 5፣8፤ 6፣23። | አማኝ በኃጢአት ላይ ድል አድራጊ ሕይወት ለመኖር ከኃጢአት ልምድና ኃይል ድኗል፣ 8፣1፣2፣11። | ክርስቶስ ሲመጣ አማኝ ከኃጢአት ፍፁም ነፃ ይወጣል፣ 8፣18—23፤ 1ኛ ዮሐ. 3፣2። |

## ጥያቄዎች

1. ምዕ. 7-8 የመልእክቱ ማዕከላዊው ነጥብ የሆነው ለምንድነው?
2. በሮሜ 1-7 ውስጥ ሰው «ማን ያድነኛል?» ብሎ የጮኸው ምን ዓይነት ኃይል ቢያጥረው ነው?
3. አማኝ ይህንን ኃይል የሚያገኘው መቼ ነው?
4. የኃጢአትን ፈተናዎች በሚመለከት አማኝ ያሉትን ሁለት የተስፋ ቃሎች ጥቀሱ።
5. መንፈስ ቅዱስ አሁን ለአማኝ የሚሠራቸውን ሁለት ነገሮች ጥቀሱ።

## የቤት ሥራ

ሮሜ 13-16ን አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ

1. እግዚአብሔር በሰው ሁሉ ላይ ይፈርዳል፤ 1-3። «ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል» የተሰኘውን ንድፍ ተመልከቱ።

ሀ/ የእግዚአብሔር ቁጣ የተገለፀበት የሰው ኃጢአት ምንድነው? 1፡18-23።

ለ/ የእግዚአብሔር ቁጣ የተገለፀው እንዴት ነው? በንድፉ ላይ «የሰው የማሽቆልቆል ጉዳናና የእግዚአብሔር አጸፋ» የሚለውን ተመልከቱ፤ 1፤24፤ 26ና 28 አንብቡ።

ሐ/ እግዚአብሔር በሰው ላይ ለመፍረድ የሚጠቀምባቸው 3 መመሪያዎች የትኞች ናቸው? 8:2፤ 6፤ 11ና 16 አንብቡ።

<u>ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል</u>

| አይሁድ | ወይም | አህዛብ |
|---|---|---|

| አይሁድ በሲና ተራራ የተቀበሉት ሕግ አላቸው | አህዛብ የሕሊና ሕግ አላቸው |
|---|---|

ሁሉም ሕግን ስለ ጣሱ ሁሉም በድለዋል ።

2. እግዚአብሔር ሰዎችን ከኃጢአታቸው ሊያድናቸው ይችላል፤ 4-6።
   ሀ/ ሰው ያለ ክርስቶስ ምን ዓይነት ሁኔታ ይኖረዋል? ሰው በምርጫና በተግባር በኃጢአት የተሞላ ነው፤ 1-3። ሰው የአዳም ልጅ በመሆኑ በሙላ ሁኔታው በኃጢአት የተሞላ ነው፤ 4-6።
   ለ/ ኃጢአት እንዴት ወደ ዓለም ገባ? 5:12፤ 18ና 19 አንብቡ።
   ሐ/ ሰው የጸደቀውና ከኃጢአት የዳነው እንዴት ነው? 5:1፤ 6፤ 8፤ 9ና 18።
   መ/ ጽድቅ በእምነት የሚገኝ ከሆነ መልካም ሥራ ምን ያደርጋል? 6:1-10 አንብቡ። ከክርስቶስ ጋር ለኃጢአት የሞትን ስንሆን በአዲስ ሕይወት ለመኖር ነፃነት አግኝተናል።
3. ኃጢአት ከመሥራት እግዚአብሔር ሊጠብቀን ይችላል፤ 7-8።
   ሀ/ ከአሪት ሕግና በውስጣችን ከሚኖረው ኃጢአት ብርቱ የትኛው ነው? 7:14-15 አንብቡ።
   ለ/ ኃጢአትን እንዲያሸንፍ ለአማኝ ውስጣዊ ኃይል የሚሰጠው ማን ነው? 7:28-8:4።
   ሐ/ በሮሜ 8ና በሮሜ 5-6 ውስጥ በሚገኙት የክርስቲያን ሕይወቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? አማኝ ከኃጢአት ቅጣት የመዳን ተስፋ እንዳለው ምዕ.5-6 ይገልጻል። እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ኃጢአት ድል የማድረጊያ ኃይል ለአማኙ እንደሰጠው ምዕ. 8 ይገልጻል።
   መ/ በአማኝ ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምንድነው? 8:2፤ 11፤ 16፤ 17።
4. እግዚአብሔር ለእስራኤል የራሱ የሆነ ዕቅድ አለው፤ 9-11።
   ሀ/ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን ተስፋ ሰርዞታል? አልሰረዘውም፤ 11:2-5 አንብቡ። ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ምሕረት ታላቅነት ለአይሁድ ባለው ታማኝነት ተገልጿል።

ለ/ እግዚአብሔር እርሱ ለሚፈቅደው ለአይሁድም ይሁን ለአሕዛብ ለማንኛውም ሰው ምሕረቱን የመግለፅ መብት ያለው ለምንድነው? 9፡14-21 አንብቡ። እግዚአብሔር የሁሉ የበላይ ነው። እግዚአብሔር የሰው ፈጣሪ ነው። ሰው ጻድቅና ፈጣሪ የሆነውን እግዚአብሔርን ሊጠይቀው መብት አለው? እስራኤል አሁንም በመንግሥት ደረጃ የማመን ዕድል አላት? 11፡25-27 አንብቡ። የእግዚአብሔር የበላይነት የተሰኘውን ንድፍ ተመልከቱ።

<u>የእግዚአብሔር የበላይነት ከሮሜ 8፡28—30</u>

| በለፈው | አሁን | ወደፊት |
|---|---|---|
| 1. እግዚአብሔር ያውቀናል፡ 8፡29። 2. እግዚአብሔር ክርስቶስን እንድንመስል አቅዷል፡ 8፡29። | 1. እግዚአብሔር መርቶናል አፅድቆናል፡ 8፡30። 2. ክርስቶስን እንድንመስል ነገሮችን ሁሉ ለበጐ ያደርጋቸዋል፡ 8፡28። | 1. ከክርስቶስ ጋር ክብር ያሰጠናል፡ 8፡30። 2. ጌታን እናየዋለን፡ ደግሞም ለዘላለም እርሱን እንመስላለን፡ 8፡29፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡2። |

5. አማኞች የተቀደሰ ኑሮ እንዲኖሩ እግዚአብሔር ይፈልጋል፤ 12-15።

ሀ/ አማኝ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች አንፃር መመላለስ ያለበት እንዴት ነው? 12፡1-2። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ - 12፡3-13፤ 14፡1-15፡6 - ሌሎች ክርስቲያኖችን በመውደድና በማገልገል - ሮሜ 12፡14-21 - ለሰው ሁሉ ቸር በመሆን ነው።

ለ/ ክርስቲያን ከዓለም ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ማድረግ የሚገባው ምንድነው?

1. ሮሜ 13፡1-7 ለገዢዎች መታዘዝ፤
2. ሮሜ 13፡8-14 ጐረቤቶቹን መወድድ ነው።

ሐ/ እውነተኛ የክርስቲያን ኑሮ ምን ያረጋግጥልናል? ሮሜ 15፡6ን አንብቡ። እንደ መንፈስ ቅዱስ ኃይል አድርጉ መለማመድ እነዚህን ፍሬዎች ለሕይወት እንደሚሰጥ ሮሜ 8 ያረጋግጣል።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለሰው ደህንነት ያለው ዕቅድ ከሮሜ 1 እስከ 8 ድረስ እንዴት እየተብራራ እንደሚሄድ አስረዱ።
2. የእግዚአብሔር ግዳን በሮሜ 12-15 ውስጥ እንዴት ተደርጐ እንደተገለጠ አስረዱ።

## የቤት ሥራ

ለፈተና ዝግጅት የሐዋርያት ሥራንና ሮሜን ከልሱ ።

# ትምህርት ሠላሳ አንድ

## የሐዋርያት ሥራና የሮሜ ክለሳ

1. በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የነበረውን የወንጌል መስፋፋት ለማሳየት የሚያስረዳ ካርታ ሣሉ። የሚከተሉትን አገሮች ተራ ቁጥሮች በካርታው ውስጥ በተገቢ ሥፍራቸው አሥፍሩ።
   ሀ/ ይሁዳ
   ለ/ ሰማርያ
   ሐ/ ሶርያ
   መ/ እስያ
   ሠ/ ግሪክ
   ረ/ ሮም

የሚከተሉትን ከተሞች ተራ ቁጥሮች በካርታው ውስጥ በተገቢው ሥፍራቸው አስቀምጡ።
   ሰ/ ኢየሩሳሌም
   ሸ/ የሶርያዋ አንጾኪያ
   ቀ/ ልስጥራ
   በ/ ፊልጵስዩስ
   ተ/ ቆሮንቶስ
   ቸ/ ተሰሎንቄ

2. በሚከተሉት ሥፍራዎች የተፈጸመ አንዳንድ ጠቃሚ ድርጊት አሥፍሩ።
   ሀ/ በኢየሩሳሌም፤ የሐዋ. 2፡1-4፤ 15፡1-29።
   ለ/ በደማስቆ መንገድ ላይ፤ የሐዋ. 9፡1-9።
   ሐ/ በጋዛ አጠገብ በበርሃ ውስጥ፤ የሐዋ. 8፡26-40።
   መ/ በቤት ጣራ ላይ፤ የሐዋ. 10፡9-18።
   ሠ/ በፊልጵስዩስ እስር ቤት፤ የሐዋ. 16፡25-34።

3. የሚከተሉትን አዛምዱ፡-

___ ሀ. ልድያ1. ድንኳን ሰፊዎች ነበሩ።
___ ለ. ሄሮድስ2. ከሞት ተነሡ
___ ሐ. ጳውሎስ በአርዮስፋጎስ3. በፊልጵስዩስ ከተማ
የመጀመሪያው አማኝ ነበረች።
___ መ. አቂላና ጵርስቅላ4. በትል ተበልቶ ሞተ።
___ ሠ. ሐናንያና ሰጲራ5. «ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን
እኔ እነግራችኋለሁ» አላቸው።
___ ረ. ዶርቃና አውጤኪስ6. በኃጢአታቸው ምክንያት ሞቱ።

_________ሰ. የተሰሎንቄ አማኞች7. «ሰማይ ተከፍቶ አየሁ» አለ።

_________ሸ. ከሐዋርያት በስተቀር8. «ቃሉንም ተቀበሉ፤ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር።»

_________ቀ. ጳውሎስ በልስጥራ9. በሳውል ስደት ምክንያት ተበታተኑ።

_________በ. እስጢፋኖስ10. «እኛም ደግሞ እንደናንተው የምንሰማ ሰዎች ነን» አለ።

4. እነዚህን ስብከቶች የሰበከው ማን ነበር?

ሀ. በበዓለ ሐምሳ ቀን1. ጳውሎስ

ለ. በቆርኔሌዎስ ቤት2. ጴጥሮስ

ሐ. በአርዮስፋጎስ3. ፊልጶስ

መ. በንጉሥ አግሪጳ ፊት

ሠ. በጋዛ በረሃ ለኢትዮጵያዊው ሰው።

5. በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ 3 መለኮታዊ ትምህርቶችን ጻፉ።

መልሶች:- ኃጢአት፥ መጽደቅ፥ የእግዚአብሔር የበላይነት፥ የመንፈስ ቅዱስ መቀደስ።

6. ጳውሎስ ወደ ሮም መሄድ የፈለገው ለምንድነው?

መልስ:-

ሀ/ በምሥራቅ ያለው አገልግሎት እንደተፈጸመ ስለተሰማው ነው፤ ሮሜ15:23።

ለ/ በሮም ከሚገኙት ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት እንዲኖረው ስለፈለጉ ነው፤ ሮሜ 1:24።

ሐ/ ወንጌል ሊሰብክላቸው ስለፈለገ ነው፤ ሮሜ 15:16።

7. የሮሜ መልእክት ማዕከላዊው ትኩረት ምንድነው? ምዕራፎችን ጥቀሱ።

8. ከሮሜ መልእክት የሰጠውን ውድቀት የሚተነትኑት ምዕራፎች የትኞቹ ናቸው? ሮሜ 1-3።

9. እግዚአብሔር ለአይሁድ ያለውን ዕቅድ በአጭሩ አብራሩ፤ ሮሜ 9-11።

10. የሰው ደህንነት ያለፈ የአሁንና የወደፊት መልክ ምንድነው?

ያለፈው - ስለ ኃጢአት ቅጣት ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመው፤

አሁን - አማኝ ከኃጢአት ኃይል መዳኑና

ወደፊት - አማኝ ከኃጢአትና ከዚህ ሥጋ ሰውነት ፍጹም እንደሚድን ነው።

11. ከሮሜ 12-14 ሦስት የክርስቲያን አገልግሎት መመሪያዎችን ጥቀሱ።

ሀ/ ራስን ለእግዚአብሔር ማቅረብ፤

ለ/ ያለ ግብዝነት አማኞችንና የማያምኑትን መውደድና

ሐ/ ለመንግሥት መገዛት ናቸው።

12. በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ማዕከላዊ ትኩረት ብለን የጠራነው ውጥረት ምን ነበር?

መልስ:- የኢየሩሳሌም ጉባዔ ነበረ፤ ምክንያቱም በአይሁድና በአሕዛብ እኩልነት ላይ ያደረገው ስብሰባ ነው፤ የሐዋ. 15።

## የቤት ሥራ

ለፈተና ዝግጅት የሐዋርያት ሥራና ሮሜን አጥኑ።

# ትምህርት ሠላሳ ሁለት

## ምክር ለመምህሩ

ከሐዋርያት ሥራና ሮሜ አውጣጥተው ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑ።

## የቤት ሥራ

1ኛ ቆሮንቶስ 1-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ ሦስት

## የ1ኛ ቆሮንቶስ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን 56 ዓ.ም. ገደማ ነው። የተጻፈበት ሥፍራ ኤፌሶን ነው፤ 2ኛ ቆሮ. 16፡7-9።

## የቆሮንቶስ ከተማ

1. የአካይያ ወይም ግሪክ ዋና ከተማ ነበረች።
2. ከሰሜን፥ ከደቡብ፥ ከምሥራቅና ከምዕራብ ከየትም አቅጣጫ ለሚመጡ ይህች ሥፍራ የመገበያያ ማዕከልና መተላለፊያ ነበረች።
3. ይህች ከተማ ሁለት የባሕር ወደቦች አሏት። ክንክራኦስ በኤጅያን ባሕር በኩል ሲሆን ሌላው ደግሞ በስተ ምዕራብ በቆሮንቶስ ባሕረ ሰላጤ በኩል ነው፤ የሐዋርያት ሥራን ካርታ ተመልከቱ።
4. በጣም ሀብታም፥ የብዙ አትሌቲክስ ውድድሮች ማዕከልና የመዝናኛ ከተማ ነበረች።
5. የፍቅር አምላክ የተባለችውን የግሪክ ጣዖት በማምለክ የታወቀች ከተማ ነበረች። ይህም በብዙ ሴትኛ አዳሪዎች የሚካሄድ በጣም አስነዋሪ አምልኮ ነበር።

## የጳውሎስ አገልግሎት በቆሮንቶስ

1. ጳውሎስ ቆሮንቶስን የጐበኘው በ2ኛው ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት ሲሆን በዚሁ ጊዜ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንን መሠረተ፤ የሐዋ. 18፡1-17።
2. ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሲኖር ከአቂላና ጵርስቅላ ጋር አብሮ ድንኳን ይሰፋ ነበር፤ የሐዋ. 18፡1-3። በዚያም የቆየው አንድ ዓመት ተኩል ነበር፤ የሐዋ. 18፡11።
3. ጳውሎስ እንደልማዱ በአይሁድ ምኩራቦች በመስበክ አገልግሎቱን ጀመረ። አይሁድ ወንጌልን አንቀበልም ሲሉ ለአሕዛብ በመስበክ ቀጠለ፤ የሐዋ. 18፡4-7።

4. ሲላስና ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር በቆሮንቶስ ነበሩ፤ የሐዋ. 18፡5።

## የመልእክቱ ዓላማዎች ሁለት ናቸው

1. የነበራቸውን ጥያቄ ለመመለስ ነበር። ጳውሎስ በሚከተሉት ሥፍራዎች አንድ በአንድ መልስ ይሰጣቸዋል፤ 1ኛ ቆሮ. 7፡1፤ 25፤ 8፡1፤ 12፡1፤ 15፡1።
2. በክርስቶስ የተገኘው አዲስ ሕይወት አዲስ አኗኗር እንደሚጠይቅ ክርስቲያኖችን ለማስተማር ነበር፤ 1ኛ ቆሮ. 3፡16-17፤ 6፡11፡19-20።

የመልእክቱ አቢይ ትምህርት የክርስቲያን አኗኗር ነው። በአንዲት አዲስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚኖሩትን ችግሮች እንድንረዳና ችግሮቹን የሚፈቱ መንፈሳዊ መመሪያዎች 1ኛ ቆሮንቶስ ያቀርብልናል።

በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች፡- 1ኛ ቆሮ. 6፡19-20፤ 10፡13፤ 11፡31፤ 15፡57-58 ናቸው።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ይህንን ደብዳቤ ለምን ጻፈ?
2. ጳውሎስ ይህንን ደብዳቤ የጻፈው መቼና የት ሆኖ ነው?
3. ስለ ቆሮንቶስ ከተማ በዝርዝር አስረዱ።
4. ጳውሎስ በአዳዲስ ሥፍራዎች ወንጌልን ሲያስተምር የሚጠቀምበት ዘዴ ምንድነው?
5. የ1ኛ ቆሮንቶስ አቢይ ትምህርት ምንድነው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ቆሮንቶስ 5-8 አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ አራት

## የ1ኛ ቆሮንቶስ አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. ምዕ. 1-4 በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረ መከፋፈል።
2. ምዕ. 5-8 ክርስቲያኖችና በኃጢአት ላይ የሚያተኩሩ ሐሳቦች።
3. ምዕ. 9-12 የክርስቲያን ነፃነትና ኃላፊነት።
4. ምዕ. 13-16 መንፈሳዊ ስጦታዎችና ትንሣኤ።

የ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክት የሚያተኩረው በክርስቲያን ነፃነትና ኃላፊነት ላይ ነው።

## 1ኛ ቆሮንቶስ




## የእያንዳንዱ ክፍል ይዘት ባጭሩ

1.' 1ኛ ቆሮ. 1-4 ክፍፍል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡-

ሀ/ የሰውን ጥበብና መመሪያዎችን በሚመለከት፤ 1፡10-31።

ለ/ መንፈሳዊ የመለየት ችሎታ በሚመለከት፤ 2፡1-16።

ሐ/ መንፈሳዊ ዕድገትና አገልግሎት በሚመለከት፤ 3፡1-11።

መ/ የአግኞችን ሽልማቶች በሚመለከት፤ 3፡12-4፡8።

ሠ/ የሐዋርያትን ሚና በሚመለከት፤ 4፡9-21።

2. 1ኛ ቆሮ. 5-8 ክርስቲያኖችና በኃጢአት ላይ የሚያተኩሩ ሐሳቦች

ሀ/ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን ከማውገዝ ቸል ማለት፤ 5፡1-3።

ለ/ በወንድሞች መካከል የሚፈጠሩ ጠቦችን በአሕዛብ ፍርድ ቤት ማቅረብ፤ 6፡1-8።

ሐ/ በሕይወትና በጋብቻ ውስጥ የንጽህና ጉድለት፤ 6፡9-7፡40።

መ/ ለጣዖታት የተሰዋ ምግብ ስለ መብላት፤ 8፡1-13።

3. 1ኛ ቆሮ. 9-12 የክርስቲያን ነፃነትና ኃላፊነት፡-

| በክርስቶስ የተገኘ ነፃነት | ኃላፊነቱ |
| --- | --- |
| 1. ወንጌልን በመስበክ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን ነገሮች ማግኘት ፣ 9፡ 13 — 15። | 1. ይኸውም ገንዘብ በመቀበል መስበካችሁ የወንጌልን ምስክርነት እስካላሰናከለ ድረስ ነው ፣ 9፡ 15 — 23። |
| 2. እግዚአብሔርን ማምለክ ፣ 10፡ 1 — 6። | 2. ከጣዖት አምልኮ መሸሽ ፣ 10፡ 1። |
| 3. የጌታን እራት መሳተፍ ፣ 10፡ 6 — 19። | 3. ራሳችንን መመርመርና ለመሳተፍ ብቁ ካልሆንን አለመውሰድ ወይም ከአህዛብ አምልኮ ጋር አንድ አድርጎ አለማሰብ ፣ 10፡ 20፡ 21፤ 11፡ 28 — 31። |
| 4. በገበያ የሚሸጠውን ነገር ሁሉ መመገብ ፣ 10፡ 23 — 26። | 4. ይኸውም ወንድምን የማያሰናክልና እግዚአብሔርን የሚያከብር እስከሆነ ድረስ ነው ፣ 8፡ 9፡ 13፤ 10፡ 31። |
| 5. በጉባኤ በሚደረግ አምልኮ ወቅት ሴቶች ራሳቸውን እንዲከናነቡ ፣ 11፡ 5። | 5. ይኸውም ሌሎችን እስካላሳዘነ ወይም የወንጌልን ምስክርነት እስካላደናቀፈ ድረስ ነው። የባሕልን ሕግ አለመጣስ ፣ 9፡ 12፡ 22፤ 11፡ 16። |

## <u>ነፃነት ካለ ኃላፊነትም አለ</u>

6. የመለኮታዊ ሥልጣን አመጣጥ አቅጣጫ በ1ኛ ቆሮ. 11፡3 ላይ ተሰጥቷል።
   - እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ ነው።
   - ክርስቶስ የወንድ ራስ ነው።
   - ወንድ የሴት ራስ ነው። ስለዚህ በአንድ ቤት ውስጥ ሁለት ራሶች ሊኖሩ አይችሉም! ኤፌ. 5፡22-25ን አንብቡ።

4. 1ኛ ቆሮ. 13-16 መንፈሳዊ ስጦታዎችና ትንሣኤ፡-
   ሀ/ መንፈሳዊ ስጦታዎች! 13-14 ስጦታዎች በአጠቃላይ በፍቅር ላይ መዋል ይገባቸዋል! 1ኛ ቆሮ. 13።
   ለ/ የትንቢት ስጦታ ወይም ስብከት ቤተ ክርስቲያንን ስለሚያንፅ ራስን ብቻ ከሚያንፁ ስጦታዎች ይልቅ ልንሻው ይገባናል! 14፡ 1-5።
   ሐ/ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በልሳን መናገርን በሚመለከት በስሕተት ላይ ወድቃ ስለነበር ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ መመሪያ ሰጥቷል! 14፡6-39።
   መ/ የሙታን ትንሣኤ! 15፡1-8፡-
   1. የክርስቶስ ትንሣኤ! 15፡1-8።
   2. የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት! 15፡20-23።
   3. በክርስቶስ ጠላቶች ላይ የተገኘው ድል! 15፡24-28።
   4. የአማኞች አካል ወደማይበሰብስ አካል መለወጥ! 15፡42-50።
   5. የአማኞች ትንሣኤ! 15፡51-58።

   ሠ/ የጳውሎስ የመጨረሻ ንግግርና ሰላምታ! ምዕ. 16፡-

1. ለሌሎች አማኞች ማድረግ ስለሚገባቸው ዕርዳታ ቤተ ክርስቲያንን ያዛል፤ 16፡1-3።
2. የጳውሎስ ዕቅዶች፤ 16፡4-12።
3. የጳውሎስ የመጨረሻ ምክር፤ 16፡13-18።

## ጥያቄዎች

1. አራቱን የ1ኛ ቆሮንቶስ ክፍሎች ከነምዕራፎቹ አሥፍሩ።
2. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ክፍሎች ምን ምን ነበሩ?
3. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በኃጢአት ላይ የሚያተኩሩት ሐሳቦች ምን ነበሩ?
4. በሁሉም ሥጦታዎች አገልግሎት ውስጥ ሊኖር የሚገባው ባሕርይ ምንድነው?
5. ቤተ ክርስቲያንን በተለይ የሚያንፅ የትኛው ስጦታ ነው?
6. የመጨረሻው የክርስቲያን ተስፋና ድል ምንድነው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ቆሮንቶስ 9-12ን አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ አምስት

## የ1ኛ ቆሮንቶስ አጭር ማብራሪያ

### 1ኛ ቆሮንቶስ 1-4

የእነዚህ አራት ምዕራፎች ዋና ጭብጥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥልጣንን በሚመለከት በነበረው መከፋፈል ላይ ነው። እነዚህ ሰዎች በአራት ቡድን ተከፋፍለው ነበር፤ ይኸውም አንዳንዶቹ የጳውሎስ ነን፤ ሌሎቹ የጴጥሮስ ነን፤ የተቀሩት የአጵሎስ ነንና የተረፉት ደግሞ መሪያችን ክርስቶስ ነው ይሉ ነበር፤ 1፡12። እያንዳንዱ ቡድን የራሱን ታላቅነት ለማሳየት ይመካ ነበር እንጂ ማናቸውም ለክርስቶስ ተገቢውን ሥፍራ አልሰጡትም ነበር።

ጳውሎስ መከፋፈላቸው ሥጋዊ ሕፃናት እንደሆኑ የሚያረጋግጥ መሆኑን ይነግራቸዋል። መንፈሳዊ እውነቶችን ማስተዋል ተስኗቸው ነበር። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን መሠረት ስለሆነ በአሁኑ ዘመንና በፍርድ ጊዜ ለእርሱ መልስ ሰጪዎች ናቸው፤ 2፡1-16፤ 3፡10-23፤ 4፡1-8።

### 1ኛ ቆሮ. 5-8

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል ሲኖር፤ አንድነት ሲጠፋና መንፈሳዊ ብስለት ሲጎድል ኃጢአትን ወደ መለማመድ ይመራል። ከእነዚህም ነገሮች መካከል አንዳንዶቹ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኙ ነበር።

እነርሱ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኘውን የሥነ ምግባር ጉድለት አያወግዙም ነበር። በመካከላቸው ጠቦች ሲኖሩ ፍርድ ለማግኘት በአሕዛብ ፍርድ ቤት ያቀርቡ ነበር። ጳውሎስ እነዚህን ነገሮች በራሳቸው መካከል መፍረድ እንደሚገባቸው ይነግራቸዋል። በተጨማሪ ለጣዖት የተሠዋ ሥጋ ስለመብላት ያለው አለመስማማት አንዳንዶችን አሰናክሎ ነበር። ደካማ ወንድምን የሚያሰናክሉና እንዲጠፉ የሚያደርጉ ማናቸውንም ነገሮች ማድረግ እንደማይገባ በማስጠንቀቅ ይህን ክፍል ይደመድማል። ነፃነት አለን፤ ነገር ግን ከነፃነት ጋር ኃላፊነት ተቆራኝቷል።

## 1ኛ ቆሮ. 9-12

የእግዚአብሔር ቃል ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ጥያቄ ዝርዝር መልስ አይሰጠንም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እንዲመሩን መመሪያዎችን ይሰጠናል። ላመኑም ሆነ ላላመኑ ኃላፊነት አለብን።

ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ አማካይነት ከኃጢአትና ከአሪት ሕግ ኩነኔ ነፃ ወጥቷል። ሆኖም ይህ አዲስ ነፃነት ያለ አግባብ መተርጎም የለበትም። ይህም ማለት ከኃጢአት ነፃ መውጣት ማለት እንጂ ኃጢአትን ለመሥራት ነፃነት ማግኘት ማለት አይደለም። መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን እንድናሸንፍ ኃይል ይሰጠናል። ነፃነት ካለ ኃላፊነትም አለ።

ክርስቶስ ራስ ሲሆን ወንድ የእርሱ ወኪል በመሆን የቤቱና የቤተሰቡ ራስ ነው። ሚስት የእርሱ ረዳት በመሆን በእርሱ መሪነት ሥር መተዳደር ይኖርባታል። ብዙ ኃጢአቶችና ውድቀቶች እግዚአብሔርን አልታዘዝም የማለት ውጤቶች ናቸው። በአምልኮአችን፥ በጌታ እራት፥ በመብላትና በመጠጣት እንዲሁም እግዚአብሔር እርሱን እንድናገለግልበት በሚሰጠን ሥጦታዎች ውስጥ ነፃነት ከኃላፊነት ጋር የሚለውን መመሪያ በሥራ ላይ ማዋል አለብን፤ ቆላ. 3፡17፤ 23ን አንብቡ። በተጨማሪ በትምህርት 34 ውስጥ የተሰጡትን ጥቅሶች ተመልከቱ።

## 1ኛ ቆሮንቶስ 13-16

ለእግዚአብሔር ቃል መመሪያዎች መታዘዝ እርሱ ለአገልግሎት ወደሚሰጠን ሥጦታዎች ትክክለኛ አጠቃቀም እንድንመራ ያደርገናል። ሥጦታዎች ሁሉ ከፍቅር ጋር በአገልግሎት ላይ መዋል አለባቸው። ፍቅር ተቆጣጣሪ ካልሆነ የሥጦታዎች ሁሉ አጠቃቀም የተዛባ ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ በምዕ. 14 ውስጥ በልሳኖች ስለመናገር መመሪያ ይሰጣል፤ ምክንያቱም በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዚህ ሥጦታ አጠቃቀም ትክክል አልነበረም።

ዛሬ እኛ ማመናችንና መመላለሳችን በእምነት መሆን አለበት። እነዚህን ሥጦታዎች በትክክል ለመምራት ጥበብ፥ ፍቅርና የመለየት ችሎታ መሻት ይኖርብናል። መንፈሳዊ ሥጦታዎች እንድናገኝ እግዚአብሔር ከፈቀደ ይሰጠናል፤ መስጠት ወይም አለመስጠት የርሱ ውሳኔ ነው። «መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ ሰው ሊሰጥ የሚፈልገውን ስጦታዎች ይሰጣል» 2ኛ ቆሮ. 12፡11።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምናልባት በሙታን ትንሣኤ የማያምን ቡድን ሳይኖር አይቀርም። ስለዚህ ጳውሎስ በምዕ. 15 ስለ ትንሣኤ ያቀረበው አስደናቂ ትምህርት የጥያቄዎቻቸው መልስ ነው። ትንሣኤ የለም ብሎ መካድ ከወንጌል እውነቶች መካከል እጅግ ትልቅ የሆነውን መካድ ነው። ክርስቶስ ከሞት ካልተነሣ እምነታችን ከንቱ ነው። ክርስቶስ

በሕይወት ስለሚኖር እኛም ደግሞ እንኖራለን። ምዕ. 16 የጳውሎስን የመጨረሻ የትዕዛዝ ቃላትና ሰላምታ ያቀርብልናል። የመጨረሻዎቹ ቃላትም «ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ጐልምሱ፥ ጠንክሩ፥ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን» የሚል ነበር፤ 16፡13።

## ጥያቄዎች

1. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መቆጣጠር ያለበት ዓይነተኛ ነገር ምንድነው?
2. መተንበይ ወይም መስበክ ከልሳኖች ይልቅ ታላቅ ስጦታ ነው የተባለው በምን ምክንያት ነው?
3. 1ኛ ቆሮ. 14ን ካነበባችሁ በኋላ ጳውሎስ በልሳኖች ስለመናገር የሚሰጠውን መመሪያዎች ጻፉ።
4. የክርስቶስ ትንሣኤ ለወንጌል በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
5. የጳውሎስ የመጨረሻ ተግሳፅ ምንድነው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ቆሮ. 13-16ን አንብቡ።

# ትምህርት ሰላሳ ስድስት

1. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበሩትን ችግሮች አስተውሉአቸው። እነዚህ ችግሮች በአሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ይገኛሉ? ተወያዩበት። ከችግሮች ጥቂቶቹ፡-
   ሀ/ በአመራር ውስጥ የነበረ ክፍፍል፤ 1፡10-31።
   ለ/ በሥነ ምግባር ጉድለቶች ላይ አለመፍረድ፤ 5፡1-13፤ 6፡18-20።
   ሐ/ የጋብቻ ችግሮች፤ 6፡9-7፡40።
   መ/ በአማኞች መካከል የተፈጠሩ ጠቦችን ወደ አሕዛብ ፍርድ ቤት መውሰድ፤ 6፡1-8።
   ሠ/ የክርስቲያን ነፃነትና ኃላፊነቱ ናቸው፤ 6፡12።
2. የክርስቲያን ነፃነት 3 መመሪያዎች ምን ምንድናቸው? አጥኗቸው።
   ሀ/ 8፡9፤13 ለደካሞች የማሰናከያ ድንጋይ አለመሆን፤
   ለ/ 9፡12፤22 የወንጌልን ምስክርነት አለማደናቀፍ፤
   ሐ/ 10፡31 ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር ማድረግ ናቸው፤ ቆላ. 3፡17፤ 23።
3. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶችን በሚመለከት መሠረታዊ ችግር ምን ነበር? 11፡1-16። እነዚህ ሴቶች የጣሱት የትኛውን መመሪያ ነው? መለኮታዊውን የሥልጣን አመጣጥ አቅጣጫ ነበር፤ 11፡3። ከዚህ ቀደም ተብሎ ነፃነትን በሚመለከት የተሰጡት 3 መመሪያዎች በሴቶች ችግር ውስጥ በተግባር ላይ መዋል የሚችሉት እንዴት ነው? 2ኛውን ጥያቄ ተመልከቱ።
4. በጌታ እራት ወቅት ይደረጉ የነበሩት የሥርዓት ጉድለቶች ምን ምንድናቸው? 11፡17-22።

ሀ/ ከጌታ እራት ጋር በአንድ ላይ የራስን ምግብ መመገብ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተለመደ ነገር ነበር፤ ሀብታሞቹ ብዙ የሚበሉት ነገር ይዘው ሲቀርቡ ድሆቹ ዘወትር ምንም አይኖራቸውም ነበር፤ 11፡17-21።

ለ/ እነዚህ ሰዎች የጌታን እራት ትርጉም በጥንቃቄ እንዳልተረዱት ጳውሎስ ተሰምቶት ነበር። ጳውሎስ የራሳቸውን ምግብ በቤታቸው እንዲመገቡና በጌታ እራት ወቅት ደግሞ ልባቸውን እንዲመረምሩና ሳይዘጋጁ የጌታን እራት መውሰድ እንደማይገባቸው ያሳስባቸዋል፤ 1ኛ ቆሮ. 11፡22፤ 27።

5. ትንሣኤን በሚመለከት የነበረው ችግርና ጥያቄ ምን ነበር? 1ኛ ቆሮ. 15። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ምናልባት በትንሣኤ የማያምኑ ሰዎች ነበሩ። ስለዚህ ጳውሎስ በዚህ ነገር ላይ በጣም ረዘም ያለ ትምህርት ይሰጣል።

ሀ/ ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሣኤ ትርጉም ተንትኖ ያቀርባል፤ 15፡1-19።

ለ/ ክርስቶስ ከመቃብር ስለተነሣ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ይነሣሉ፤ 15፡22-24።

ሐ/ ሞት የአማኝ የመጨረሻ ጠላት ነው፤ 15፡25-28።

መ/ ከሞት የተነሣው ሰው የማይበሰብስ መንፈሳዊ አካል ይሆናል፤ 15፡44።

ሠ/ ትንሣኤ እጅግ ታላቅ የሆነ የአማኝ ተስፋ ነው፤ 15፡50-58፤ 1ኛ ተሰ. 4፡13-18።

6. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ችግሮችና ጥያቄዎች ጋር ካደረገው ነገር ምን እንማራለን?

ሀ/ እነርሱን ለመምራት ጳውሎስ ሕግ ወይም ደንቦች ከመስጠት ይልቅ መመሪያዎችን ሰጠ።

ለ/ ጳውሎስ የማያወላውል መልስ ሰጣቸው።

ሐ/ በእነርሱ እምነት ላይ እንደ የበላይ ወይም ጌታ ራሱን አልቆጠረም ነበር።

መ/ የሚመራው በመንፈስ ቅዱስ ነበር። የሚሰጣቸውም የራሱን ሐሳብ አልነበረም።

ሠ/ ጳውሎስ አመቺ ሆኖ ባገኘው ሁኔታ ሁሉ ምስጋናና ማበረታቻ ይሰጥ ነበር።

## ጥያቄዎች

1. አንዳንዶቹ የጳውሎስ ምክር ባሕርይዎች ምን ዓይነት ነበሩ?
2. የክርስቲያንን ነፃነት የሚመለከቱ ሦስት መመሪያዎች ጻፉ።
3. በ1ኛ ቆሮ. 14፡40 አገልግሎቶችን ሁሉ መምራት ያለበት መመሪያ ምን ነበር?
4. የክርስቶስ ትንሣኤ ለአማኞች በሙሉ የሚሰጠው ተስፋ ምንድነው? 15፡19-26።
5. በመጨረሻ ላይ የሚደመሰሰው ጠላት ማን ነው?

## የቤት ሥራ

2ኛ ቆሮንቶስ 1-3ን አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ ሰባት

## የ2ኛ ቆሮንቶስ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን 57 ዓ.ም. ገደማ ነው። በ3ኛ ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት ከመቄዶንያ ተጽፎ ነበር።

## የመልዕክቱ ዓላማ

1. ጳውሎስ በቆሮንቶስ ለሚገኙት በእርሱ ሥልጣን ላይ ጥያቄ ለነበራቸው አማኞች ሐዋርያነቱን ለማስረዳትና መብቱን ለማስጠበቅ፤ ስለ ራሱ ሕይወት ምስክርነትና ስለ አገልግሎቱ ይነግራቸዋል።
2. ጳውሎስ አስራትና ምፅዋት ስለመስጠት መመሪያዎች ይሰጣቸዋል።
3. ጳውሎስ ክርስቲያኖች ራሳቸውን እንደሚመረምሩና በክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲፈትኑ ያሳስባቸዋል።

## የመጽሐፉ ልዩ ባሕርያት

1. ጳውሎስ ከማንኛቸውም መልእክቶች ይልቅ በዚህ መልእክት ውስጥ የራሱን የሕይወት ታሪክ ሰፋ ባለ ይገልጻል።
   ሀ/ ከደማስቆ እንዴት በቅርጫት ውስጥ ገብቶ እንዳመለጠ፤ 11፡32-33።
   ለ/ እስከ ሦስተኛ ሰማይ ድረስ ተነጥቆ ስለተለማመደው ነገር፤ 12፡1-4።
   ሐ/ በሥጋው ውስጥ ስላለው መውጊያ፤ 12፡7።
   መ/ በራሱ ላይ የደረሱበት ያልተለመዱ ችግሮች፤ 11፡23-27።
2. ጳውሎስ በራሱ ታሪክ መመካት ቢፈልግ ኖሮ የሚያስመካ ምክንያት እንዳለው ለማሳየት ፈልጐ ነው። ሆኖም አጠያያቂ ናቸው ብለው ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹ የጠረጠሯቸው ነጥቦች ትክክል መሆናቸውን ለማስረዳት ዓላማው ነበረ፤ 2ኛ ቆሮ. 10-11።
3. ስለ አሥራትና ምፅዋት አገልግሎት እንዲሁም ከሞት በኋላ ስላለው ተስፋ የተሰጣቸው ትምህርቶች የአዲስ ኪዳን ጠቃሚ ትምህርቶች ናቸው።

## በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. 1፡3-4 መጽናናት፣
2. 5፡17 አዲስ ሕይወት፣
3. 6፡17-18 መለየት፣
4. 3፡5፤ 9፡8፤ 12፡9 ብቃት።

## በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. መጽናናት፥
2. ብቃት፥
3. መለያየት፥
4. መፈተን ናቸው።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን የጻፈበት ሁለት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?
2. በ2ኛ ቆሮ. የተገለጹት የጳውሎስ የግል የሕይወት ታሪክ ዝርዝሮች አንዳንዶቹ ምንድናቸው?
3. ጳውሎስ ይህንን መልእክት የጻፈው መቼና የት ሆኖ ነው?
4. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ቃላት የሚገኙባቸውን ጥቅሶች ጻፉ።
   ሀ/ መጽናናት፥
   ለ/ መለያየት፥
   ሐ/ ብቃት።

## የቤት ሥራ

2ኛ ቆሮንቶስ 4-6ን አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ ስምንት

## የ2ኛ ቆሮንቶስ አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የጳውሎስ የግል ምስክርነት፤ ምዕ. 1ና 2።
2. ጳውሎስ የአገልግሎት መመሪያዎቹን ያብራራል፤ ምዕ. 3-6።
3. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያደርገው የተሳካ ዕርቅ፤ ምዕ. 7።
4. ጳውሎስ ስለ አሥራትና ምፅዋት ያቀረበው ማነሳሻ፤ ምዕ. 8ና 9።
5. ጳውሎስ መንፈሳዊ ግጭቶችንና ሐሰተኛ መምህራንን በሚመለከት የሰጠው ማስጠንቀቂያ፤ ምዕ. 10-13።

የ2ኛ ቆሮንቶስ ንድፍ የተሰኘው በሚቀጥለው ገጽ ተመልከቱ።

## የ2ኛ ቆሮንቶስ ንድፍ




የጳውሎስ የተሳካ ዕርቅ ብጥብጡ እንዲያከትም አደረገ፤ 2ኛ ቆር. 7። ጳውሎስ የመጀመሪያ መልእክቱን ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከጻፈ በኋላ የእርሱን አመራርና ሥልጣን በመቃወም አመፅ ተፈጠረ፤ 11፡5፤ 12፡11። ይህም ነገር የተጀመረው ራሳቸውን ሐዋርያት ብለው በሰየሙ በአይሁድ ክርስቲያኖች ነበር። እነዚህ ሰዎች ክብርና ትርፍ ለራሳቸው ይፈልጉ ስለነበር ጉዳዩ ቤተ ክርስቲያንን እስከማፍረስ ድረስ የሚያሰጋ ነበር።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈላቸው የመጀመሪያውና የ2ኛው መልእክቶች መካከል ችግሩን ሰምቶ በፍጥነት ወደ ቆሮንቶስ ይጓዛል፤ 13፡1-2። ጳውሎስ የነበረውን ተቃውሞ ማብረድ ስላልቻለ ወደ ኤፌሶን ከተመለሰ በኋላ ቤተ ክርስቲያን የአመፁን መሪ እንድትቀጣው የሚያዛት ጠንከር ያለ ደብዳቤ ይጽፋል፤ ጳውሎስ ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ደብዳቤ እንደጻፈ 2ኛ ቆር. 2፡4ና 9 ይጠቁመናል።

ቲቶ ይህን የጳውሎስ ደብዳቤ ይዞ ወደ ቆሮንቶስ ለማድረስ ሄደ። ጳውሎስ በኤፌሶን ሆኖ የቤተ ክርስቲያኒቱን መልስ ለመስማት በጉጉት በመጠባበቅ ላይ ነበር። ቲቶም ወደ ኤፌሶን ሳይመጣ ቀረና ጳውሎስን በመቄዶንያ ተገናኝቶት የሚያበረታታ ዜና ያሰማዋል። ቲቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበሩት ብዙዎቹ አባሎች ንስሐ እንደገቡና የአመፁን መሪ እንደቀጡት ብሎ የሚያበስረውን መልካም ወሬ ለጳውሎስ ነገረው፤ 7፡6-16። ይህም ነገር ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነበረውን ኀዘንና ስጋት እንዲያከትም አደረገው። የጳውሎስ ምስክር እና ጸሎቶች በተሳካ ዕርቅ መልካም ፍጻሜ አገኙ።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ያቀረበውን መከላከያ እንዲሰጥ ያስገደደው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ችግር ምንድነው?
2. የ2ኛ ቆሮንቶስ አጠቃላይ አስተዋፅዖና የምዕራፍ አከፋፈል አጥኑ።
3. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በተነሣው ተቃውሞ ውስጥ የጳውሎስ ዋና ሸክም ምን ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ? ይህ ወቅት ለቤተ ክርስቲያኒቱ የውድቀት ጊዜ የሆነው ለምንድነው? ተወያዩበት።

## የቤት ሥራ

2ኛ ቆሮንቶስ 7-9ን አንብቡ።

# ትምህርት ሠላሳ ዘጠኝ

## የእያንዳንዱ ክፍል ይዘት ባጭሩ

## 2ኛ ቆሮንቶስ 1ና 2 ምስክርነት

ጳውሎስ ይህንን የ2ኛ ቆሮንቶስን መጽሐፍ የሚጀምረው በቆሮንቶስ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሸክም እየተሰማው ነው። በአንደኛ ቆሮንቶስ ውስጥ ከተጠቀሱት ችግሮች ሌላ ቤተ ክርስቲያኒቱ በጳውሎስ ላይ የነበራትን እምነት እያጣች ነው። ስላገኘው መጽናናት እግዚአብሔርን ያመሰግናል።

ጳውሎስ ወንጌልን በቀና መንገድና በትሕትና ስለሰበከላቸው ሕሊናው በእግዚአብሔር ፊት ንፁህ እንደሆነ ያብራራል። ወደ እነርሱ መምጣት ምንም ቢፈልግም እንደገና በኀዘን መምጣት ስለማይሻ እንደሚዘገይ ይነግራቸዋል። ሰይጣን የመግባት ዕድል አግኝቶ እንዳይከፋፍላቸውና በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያኒቱ የአመፁን መሪ ይቅርታ እንድታደርግለት ይማፀናል።

## 2ኛ ቆሮንቶስ 3-6 ማብራሪያ

ጳውሎስ የአዲሱን ቃል ኪዳን አገልግሎትና ወንጌል ከሙሴ አሪት የበለጠ አገልግሎት እንዳላቸው ያብራራል፤ 3፡6-18።

ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን አባሎች ሲጽፍ፤ እናንተ ያላመኑት ሰዎች የሚያነቡት መልእክት ናችሁ ብሎ ይነግራቸዋል። እግዚአብሔር ከእንግዲህ ወዲህ ቃል ኪዳኑን በድንጋይ ጽላት ላይ አስፍሮ ሳይሆን ሕይወትና ነፃነት በሚሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በሰዎች ልብ ውስጥ እንደሚፅፍ ይነግራቸዋል።

ጳውሎስ የወንጌል መልእክት ታማኝነትና ግልፅነት የተጕናጸፈው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ኃይል መሆኑን ያብራራል። ይህ አገልግሎት ሥቃይ ያለበት አገልግሎት ሲሆን መንፈስ ቅዱስ አማኝ ከክርስቶስ ጋር የመኖሩን ተስፋ የሚያስተጋባ ፀጋንና ተስፋን የሚሰጥ ነው።

የእኛ የወንጌል አገልግሎት በሥራችን ላይ ፍርድ የሚሰጠውን ክርስቶስን ማስደሰት አለበት። ነገር ግን ያስታረቀን የክርስቶስ ፍቅር ፍላጐታችንን በመቆጣጠር አምባሳደሮች አድርጐን ስለ እርሱ ለሌሎች እንድንመሰክር ያደርገናል።

ጳውሎስ በወንጌል አገልግሎት በተሰማሩት ሰዎች ላይ የሚደርሱትን መከራዎችና ስደቶች ይዘረዝራል፤ ሆኖም ትዕግሥተኞች እንዲሆኑና አባት ለሚሆናቸው ለእግዚአብሔር ራሳቸውን እንዲለዩ ይማፀናቸዋል።

## 2ኛ ቆሮንቶስ 7 ድል

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በነበረው ክፍፍልና በእርሱ ላይ በተነሣው ተቃውሞ ታውኮ ነበር። ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ የአመጹን መሪ እንድትቀጣ የተማሳፀ ደብዳቤ ጽፎ ነበር። ከዚያም ቲቶ የደብዳቤውን መልስ ይዞለት እስኪመጣ ድረስ በጕጕትና በጸሎት ሆኖ ይጠብቅ ነበር። ቲቶ ጳውሎስን በመቄዶንያ እንዳገኘውና በጣም የሚያበረታታ ዜና እንዳመጣለት እናነባለን፤ 2፡13፤ 7፡6-16። በቆሮንቶስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ንስሐ በመግባት የአመጹን መሪ ቀጥታዋለች።

የጳውሎስ ጸሎትና ልመናዎች መልስ አግኝተዋል። ለቤተ ክርስቲያኒቱ የነበረው ፍርሃትና ሸክም ወደ ደስታ ተለውጧል፤ 7፡13።

## 2ኛ ቆሮንቶስ 8ና 9 ማበረታቻ

የሚቀጥለው የጳውሎስ ሸክም በኢየሩሳሌም በረሃብ ምክንያት ለሚሰቃዩት ክርስቲያኖች ነበር። በእስያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ምንም ድሃ ቢሆኑም እንኳ እርዳታ የመስጠት ዕድል እንዲያገኙ ከለመኑ በኋላ በለጋስነት ሰጡ። ጳውሎስ ሁኔታውን በቆሮንቶስ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ይነግራቸዋል። በተጨማሪ የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት በፍፁም ፈቃደኝነት የሰጡበት ምክንያት አስቀድመው ራሳቸውን ለጌታ ስለሰጡ እንደሆነ በመንገር የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያንም ሰዎች እርዳታ እንዲያደርጉ ዕድል ይሰጣቸዋል።

ከዚያም ጳውሎስ ስለ መስጠት መመሪያዎችን ያቀርብና እግዚአብሔር ከልግስናና ከሙሉ ልባቸው የሚሰጡትን እንደሚሸልም በመንገር ያበረታታቸዋል፤ 9፡6-8። ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የመቄዶንያንን አብያተ ክርስቲያናት የመስጠት ምሳሌ እንድትከተል ከልቡ ይማፀናታል፤ በተጨማሪ ሀብታም ሲሆን ስለ እኛ ድሃ የሆነውን ክርስቶስን ምሳሌነት ያሳስባቸዋል።

## የ2ኛ ቆሮንቶስ 10-13 ማስጠንቀቂያ

ጳውሎስ አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የጠረጠሩትን እና ጥያቄ ያቀረቡበትን ሥልጣኑን ተከላክሏል። ጳውሎስ ስለ ራሱ መመካት አይፈልግም፤ ነገር ግን የቆሮንቶስ ሰዎች

ሁኔታ በክርስቶስ ያለውን ሥልጣን ለማረጋገጥ ሲል እንዲመካ አስገድዶታል። ሆኖም ጳውሎስ «ሰው መመካት ያለበት በጌታ ብቻ ነው» ይላል።

ጳውሎስ የክርስቲያን ጦርነት መንፈሳዊ እንደሆነና ሰይጣን አዕምሮአችንንና ሐሳባችንን እንደሚያጠቃ ያሳስባቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ሐሳቦቻችንን ሊቆጣጠርና ለክርስቶስ እንዲታዘዙ ሊያደርጋቸው ይችላል፤ 10፡4-5። ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በማስተያየት መለካትና ማወዳደር የለብንም፤ ነገር ግን የእኛ መለኪያ መሆን ያለበት ክርስቶስ ነው።

ጳውሎስ የክርስቶስ ሐዋርያ እንደመሆኑ መጠን ያለውን ቅንነት ለመግለጽ የደረሱበትን መከራዎችና ስደቶች በዝርዝር ያቀርባል። የሚመካው ለእግዚአብሔር እንጂ ክብርን ለራሱ ለማግኘት አይደለም፤ 11፡23-28። ጳውሎስ በእጁ ሠርቶ በመተዳደሩ ተነቅፎ ነበር፤ ነገር ግን እርሱ ድንኳን በመስፋት ለኑሮው የሚያስፈልጉትን ያገኝ የነበረው ማንም ሰው ወንጌልን ለጥቅሙ ይሰብካል እንዳይለው ነበር። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዕርዳታ ልከውለታል፤ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ግን ምንም ነገር አልወሰደም፤ 11፡7-9።

ጳውሎስ ስለ ንግግሩ ቀላልነት ተነቅፏል፤ 11፡6። ነገር ግን የጳውሎስ ትምህርትና ዕውቀት ታላቅ ነበር። ቀላል አድርጐ ወንጌልን የሰበከው ለሁሉ ሰው ግልፅ እንዲሆን በማሰብ ነበር፤ 1ኛ ቆሮ. 2፡1-5። ጳውሎስ በሌሎች ዘንድ እንዲነቀፍ ያደረገው የአካል ጉድለት ነበረው። ይህንን ነገር እግዚአብሔር የሰጠው ከእርሱ ባገኛቸው ራዕዮች እንዳይመካ መሆኑን ጳውሎስ ይናገራል፤ 12፡7። ጌታም «ፀጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈፀማልና» ብሎታል። ጳውሎስ «ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ» ይላል፤ 12፡1-10።

በመደምደሚያው ላይ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች እምነት ንጹሕና ሌሎችን የሚያንፅ መሆኑን ለማረጋገጥ ራሳቸውን እንዲመረምሩ ያነቃቃቸዋል። ጳውሎስ «ደህና ሁኑ፥ ፍፁማን ሁኑ፥ በአንድ ልብ ሁኑ፥ በሰላም ኑሩ» በማለት ጽፎላቸዋል፤ 13፡5፤ 11።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ከሚመለከት ችግር የተሰማው በምን ምክንያት ነበር?
2. ወንጌል ከሙሴ ሕሪት የሚበልጠው እንዴት ነው? 3፡6-18።
3. ክርስቲያን ወንጌልን መመስከር የሚገባው ለምን እንደሆነ የሚያስረዱ ሁለት ምክንያቶች ጥቀሱ፤ 5፡9-10፤ 14-15።
4. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ውጥረት የተረጋጋው እንዴት ነበር?
5. ጳውሎስ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ገንዘብ እንዲያዋጡ የለመነበት ዓላማ ምንድነው?
6. ጳውሎስ የሥጋው መውጊያ እንዲወገድለት የጸለየውን ጸሎት እግዚአብሔር ያልመለሰለት ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

2ኛ ቆሮንቶስ 10-13ን አንብቡ።

# ትምህርት አርባ

ጳውሎስ 2ኛ ቆሮንቶስን እንዲፅፍ ያነሣሣው በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ልዩ ችግር ምን ነበር? በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በጳውሎስ ሥልጣንና አገልግሎት ላይ ተቃውሞ ተነሥቶ ነበር። ይኸውም ራሳቸውን ሐዋርያት ነን ብለው በሰየሙ ሐሰተኛ መምህራን መሪነት ነበረ።

እነርሱ እንደዚህ ይሉ ነበር፡-

1. ጳውሎስ የተመላለሰው እንደ ሥጋ ፈቃድ ነው፤ 10:2።
2. ጳውሎስ ፈሪ ነው። ጠንካራ ደብዳቤዎችን ጽፏል፤ ነገር ግን ንግግሩ ደካማ ነው፤ 10:10።
3. ጳውሎስ በእጁ በመሥራቱና ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ ባለመቀበሉ የሐዋርያነት መብት ስለሌለው ነው፤ 11:7።
4. ጳውሎስ ከመጀመሪያዎቹ 12 ሐዋርያት መካከል አንዱ ስላልሆነ ለማስተማር የሚበቃ አይደለም፤ 11:5፤ 12:11-12፤ 13:1።
5. ጳውሎስ ትምክሕተኛ ነው፤ 10:8፤ 15። አታላይም ነው፤ 12:6።

ጳውሎስ እነዚህን የሐሰት ክሶች የሚጋፈጠው እንዴት ነው? ጳውሎስ ለሐሰተኛ ክሳቸው መልስ በመስጠት ሥልጣኑን ይከላከላል፤ ምክንያቱም በእርሱ የማገልገል መብት ላይ የነበረው ጥርጥርና ክርክር የቆሮንቶስን ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስ የሚያሰጋ ነበር።

በ2ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የሚገኘው ጠቃሚ ትምህርት ምንድነው?

1. የወንጌል አገልግሎት፤ ምዕ. 2-6።
   - ሀ/ በቅጣት ላይ ለነበሩት እንኳን ሳይቀር የፍቅር አገልግሎት መስጠት ነው፤ 2:5-11።
   - ለ/ መንፈሳዊ አገልግሎት እንጂ የእሪት ሕግ አገልግሎት አይደለም፤ 3:16-18።
   - ሐ/ የእውነተኝነትና የታማኝነት አገልግሎት ነው፤ 4:1-6።
   - መ/ የመከራ አገልግሎትና በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የሚሰጠው ነው፤ 4:8-18፤ 5:9-10።
   - ሠ/ የዘላለም ተስፋ የሚያስገኝ አገልግሎት ነው፤ 4:17-18፤ 5:1-8።
2. በአዲስ ኪዳን የሚገኙት የመስጠት መመሪያዎች፤ ምዕ. 8-9።
   - ሀ/ ከድህነታችሁ ስጡ፤ 8:2፤
   - ለ/ በለጋስነት ስጡ፤ 8:3።
   - ሐ/ ባላችሁ መጠን ስጡ፤ 8:12-14።
   - መ/ አትረፍርፋችሁ ስጡ፤ 9:6።
   - ሠ/ በፈቃደኝነትና በደስታ ስጡ፤ 9:7።
3. ክርስቲያን ከሚያረክሰው ነገር መለየት አስፈላጊው ነው፤ 6:14-7:1።
4. ክርስቲያን ከሰይጣን ጋር ጦርነት ያደርጋል፤ 10:3-6።
5. ክርስቶስ አፅናኛችንና ብቃታችን ነው፤ 1:3-7፤ 2:14፤ 3:4-6፤ 12:9-10።
6. የክርስቲያን የዘላለም ቤት ተስፋ አለው፤ 5:1-10።
7. ራስን የመመርመር ኃላፊነት አለበት፤ 13:5።

8. የጳውሎስን የመጨረሻ ትዕዛዝ ከ13፡ 11 አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. በጳውሎስ ላይ የቀረቡት ክሶች ምን የሚሉ ነበሩ?
2. ስለ አሥራትና ምፅዋት የቀረቡት መመሪያዎች ምን የሚሉ ናቸው?
3. የእውነተኛ የወንጌል አገልግሎት ጥቂት ባሕርያት ምን ምንድናቸው?

## የቤት ሥራ

1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስን ከልሱ።

# ትምህርት አርባ አንድ

## የ1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ ክለሳ

1. ጳውሎስ ከቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ነበር?
   - ሀ/ ጳውሎስ በ2ኛው ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት በቆሮንቶስ ወንጌልን ሰብኳል፤ የሐዋ. 18፡ 1-17።
   - ለ/ ጳውሎስ በዛ ባሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግሮች ላይ ለመነጋገር ሲል የመጀመሪያው የቆሮንቶስ መልእክት የጻፈው በሦስተኛው ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት ነበረ፤ ትምህርት 34ን ተመልከቱ።
   - ሐ/ ጳውሎስ ከኤፌሶን ወደ ቆሮንቶስ ፈጣንና አሳዛኝ የሆነ ጉብኝት አድርጓል፤ ነገር ግን ችግሮቹን ለማቃለል አልቻለም፤ 12፡ 14፤ 13፡ 1-2 ሁለተኛ ጉብኝት እንዳደረገ ይጠቁመናል።
   - መ/ ጳውሎስ ከአሳዛኙ ጉብኝት ቀጥሎ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ብጥብጥ የፈጠረውን ሰው እንዲቀጡ የሚያዝ ደብዳቤ ጳውሎስ ይጽፍና በቲቶ እጅ ይልካል፤ 2፡ 3-11።
   - ሠ/ የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጳውሎስ ላይ ተቃውሞ ያስነሡትን ሰዎች እንደቀጣቻቸው፤ ብዙ ሰዎችም ንስሐ እንደገቡና የጳውሎስንም ሥልጣን መልሰው እንዳጸደቁት የሚያበስረውን ዜና ቲቶ ይዞ ከቆሮንቶስ ይመለሳል፤ 2፡ 13፤ 7፡ 13-16። እነዚህ ጥቅሶች ግን በ1ኛ ቆሮንቶስ 5 ላይ የተጠቀሰውን ሁኔታ አይጠቁሙም።
   - ረ/ ጳውሎስ 2ኛ መልእክቱን የጻፈው ቲቶ ዜናውን ከቆሮንቶስ ካመጣለት በኋላና በ3ኛ ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት በመቄዶንያ ሆኖ ነበር።
2. የ1ኛ ቆሮንቶስ አቢይ ትምህርት ምንድነው? ትምህርት 33ን ተመልከቱ።
3. በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የተጠቀሱት የቤተ ክርስቲያኒቱ ችግሮች ምን ምን ነበሩ? ትምህርት 34 ቁጥር 2ን ተመልከቱ።
4. የመለኮታዊ ሥልጣን አመጣጥ አቅጣጫ ምንድነው? ትምህርት 34 ቁጥር 6 ተመልከቱ።
5. እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታዎች የሚሰጠው ለምንድነው? ኤፌ. 4፡ 8፤ 11-12።

6. የክርስቲያን ነፃነት መመሪያዎች ምንድናቸው? ትምህርት 36 ቁጥር 2ን ተመልከቱ።
7. 2ኛ ቆሮንቶስ እንደሚያስረዳን ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሸክም የተሰማው ለምን ነበር?
8. በጳውሎስ ሥልጣን ላይ ተንሥቶ የነበረው ችግር የተወገደው እንዴት ነበር?
9. በ2ኛ ቆሮንቶስ ስጦታዎችንና ምፅዋትን ስለመስጠት ምን ምን መመሪያዎች ተሰጥተዋል?
10. ክርስቲያን አጠራጣሪ ሐሳቦች ሲያጋጥሙት የሚመራበት መመሪያ ከ1ኛ ቆሮንቶስ የሚያገኘው ምንድነው? ትምህርት 34 ቁጥር 1-2ን ተመልከቱ።

## የቤት ሥራ

ከ1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ ተውጣጥቶ ለሚቀርብላችሁ ፈተና ተዘጋጁ።

# ትምህርት አርባ ሁለት

## ምክር ለመምህሩ

ከ1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ አውጣጥተው ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑ።

## የቤት ሥራ

ገላትያ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት አርባ ሦስት

## የገላትያ መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን ወደ 48 ዓ.ም. ገደማ ነው። ገላትያ የምትገኘው የት ነው? ከዚህ በታች የሚገኘውን ካርታ ተመልከቱ።




በገላትያ መልእክት ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙት ሁኔታዎች የተፈፀሙት መቼ ነበረ ?

| የሐዋርያት ሥራ | | ገላትያ |
|---|---|---|
| የጳውሎስ በመጀመሪያው የወንጌላዊ ጉዞ ኢቆንዮንን፣ ልስጥራንንና ደርቤን ጐበኘ፣ የሐዋ. ሥራ 13፣14። | ← → | ከኢየሩሳሌም የመጡ አሁንም የኦሪትን ሕግ ሥርዓት የሚጠብቁ ከአይሁድ ወገን ያመኑት ሰዎች የአህዛብ አማኞች ሐሳባቸውን እንዲቀበሉት ለማስገደድ ሞከሩ፣ ገላ. 1፣7፤ 5፣10። |
| የ49 ዓ. ም. የኢየሩሳሌም ጉባኤ፣ የሐዋ. ሥራ 15። | ← → | ገላትያ የተፃፈው በ49 ዓ. ም. ከተደረገው ጉባኤ በፊት ነው። በገላትያ 2፣1 ያለው ከሐዋርያት ሥራ 11፣29፣30 ጋር ሳይገናዘብ አይቀርም። |

ማሳሰቢያ፦ ገላትያ የሚለው ቃል ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች አሉት፤ ይኸውም አንዳንዴ ሕዝብን ሲጠቀም ሌላ ጊዜ ደግሞ በዚህ ስም ይጠራ የነበረውን አውራጃ ያመለክታል። በተለያዩት ካርታዎች ላይ አጠቃቀሙ ልዩ ሊሆን ስለሚችል እንዳትደነጋገሩ።

የኢየሩሳሌም ጉባዔ የተወያየበት ችግር ምን ነበር? የሐዋ. 15፡5።

ቀድሞ ፈሪሳውያን የነበሩ ከአይሁድ ወገን ያመኑት ክርስቲያኖች በዚህም ወቅት ግዝረትንና ሌሎች የኦሪት ሕግ ሥርዓቶችን ይጠብቁ ነበር። የአሕዛብ አማኞችም የኦሪትን ሕግ

መጠበቅ አለባቸው ብለው አጠንክረው ተናገረዋል፤ በተጨማሪ ደግሞ አሕዛብ ከአይሁድ ጋር እኩል እንዳልሆኑ ያስቡ ነበር። በዚህ ጉዳይ ላይ ከበድ ያለ አለመግባባት ስለተፈጠረ ጳውሎስና በርናባስም ከሐዋርያትና ከተቃዋሚዎቹ ጋር አሳብ ለአሳብ ለመለዋወጥ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፤ የሐዋ. 15። በኢየሩሳሌም ጉባዔ ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ ጳውሎስን እየደገፈ ለአሕዛብ ለመመስከር እንዴት እንደተጠራ ይተርክላቸዋል። መንፈስ ቅዱስም ለሐዋርያትና ለአይሁድ አማኞች በተሰጠበት አኳኋን ለአሕዛብም ደግሞ እንደተሰጣቸው ይነግራቸዋል፤ የሐዋ. 10:43-48። ያዕቆብም በጉባዔው መካከል ተነሥቶ የአሕዛብ ማመን በብሉይ ኪዳን የተነገረ መሆኑን በግልፅ ያስተምራል፤ አሞፅ 9:9-12።

አሕዛብ የኦሪትን ሕግ እንዲጠብቁ መገደድ እንደሌለባቸው በመስማማት ጉባዔው ይበተናል፤ የሐዋ. 15:19-24። ጉባዔው በመንፈስ ቅዱስም ተመርቶ ለአሕዛብ አቢያተ ክርስቲያናት 4 ደንቦች ብቻ ይሰጡአቸዋል። እነርሱም:-

1. ለጣዖታት የተሰዋ ሥጋ እንዳይበሉ፤
2. ደም እንዳይበሉ፤
3. ታንቀው የሞቱ እንስሳትን ሥጋ እንዳይበሉና
4. ከዝሙትና እንዲርቁ የሚሉት ናቸው።

ይህ አለመስማማት ከዚህ በፊት በሶርያዋ አንጾኪያ በጳውሎስና በጴጥሮስ መካከል ግጭት ፈጥሮ ነበር፤ ገላ. 2:11-14።

አይሁድ ክርስቲያኖች በክርስቶስ አምነው ድነው ነበር። ሆኖም ብዙዎቹ አሁንም ግዝረትንና ሌሎች የኦሪት ሥርዓቶችን መጠበቅ አላቋረጡም ነበር፤ በምኩራብና በቤተ መቅደስ ስብሰባዎች ይካፈላሉ፤ መስዋዕቶችን ይሰዋሉ፤ ደግሞም የምግብ ሕጎችን ይጠብቃሉ። እነዚህ የአይሁድ ወግ አጥባቂ ክርስቲያኖች የአሕዛብ አማኞች እነርሱን እንዲከተሉ ለማስገደድ ሞከሩ።

አንዳንድ አይሁድ ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም እስከመጡበት ጊዜ ድረስ ጴጥሮስ በአንጾኪያ በነበረበት ወቅት ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይመገብ ነበር፤ ከዚያም አሕዛብን ለመገረዝ የፈለጉትን እነዚህን አይሁዶች ፈርቶ ከእነርሱ ተለየ። ሆኖም ጳውሎስ ጴጥሮስን «አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለህ በአሕዛብ ኑሮ ስትኖር አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልካቸው» በማለት ገሰጸው፤ ገላ. 2:14-16።

## ጥያቄዎች

1. የገላትያን አብያተ ክርስቲያናት በዝርዝር መዝግቡ።
2. ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ የሚያተኩርበት ችግር ምንድነው?
3. የኦሪት ሥርዓቶችን ሳይጠብቁ ያመኑትን አሕዛብ እግዚአብሔር እንደተቀበላቸው የሚያሳይ ምን ማስረጃ አለ?
4. መልካም ተግባር በማድረግ እንጸድቃለን ማለት በፀጋ ላይ ሥራን የመጨመር ችግር በዘመናችን ባሉት ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ እናገኛለን? ተወያዩበት።

## የቤት ሥራ

ገላትያ 4-6 አንብቡ።

# ትምህርት አርባ አራት

## የገላትያ መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. ጳውሎስ ስለሰበከው ወንጌልና ስለ ሐዋርያዊ ሥልጣን የሰጠው ማብራሪያ፤ ገላ. 1-2።
   ጳውሎስ ወንጌሉ የተገለፀለት በራዕይ እንጂ በሌሎች ሐዋርያት አማካይነት አልነበረም፤ ገላ. 1፡11-24 የጳውሎስ ወንጌል በሐዋርያት የተመሰከረለት ነበር፤ ገላ. 2፡1-10። ጳውሎስ በሐዋርያት አለቃ በጴጥሮስ ፊት ለወንጌል ተሟገቷል፤ ገላ. 2፡11-21።
2. ጳውሎስ ስለ ክርስትና የሚያቀርበው ትምህርት፤ ገላ. 3፡4።
   ሀ/ ጻድቅ ሆኖ መገኘት ያለምንም የኦሪት ሕግ ሥራ በእምነት ከክርስቶስ የሚገኝ ነው፤ ገላ. 3፡1-24። የኦሪት ሕግ ጊዜያዊ ብቻ ነበር፤ ገላ. 3፡19-20። የኦሪት ሕግ የተሰጠው ኃጢአትን ለመግለጥ እንጂ ከኩነኔ ለማዳን አይደለም፤ ገላ. 3፡21-22። የኦሪት ሕግ ለክርስቶስ መንገድ አዘጋጅቶለታል፤ ገላ. 3፡23-4፡7።
   ለ/ የክርስቲያንን ሕይወት የሚመራው ፀጋ እንጂ የኦሪት ሕግ አይደለም፤ ገላ. 3፡24-29። ክርስቶስ በሚሰጠው ነፃነት የተቀበሉት ሁሉ አንድ ሆነዋል፤ ገላ. 3፡25-29። ያመኑት ሁሉ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆችና ወራሾች ናቸው፤ ገላ. 4፡1-7። የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ እንጸድቃለንና በፀጋ ድነናል የሚሉት ትምህርቶች የማይዛመዱ ናቸው፤ ገላ. 4፡8-31።
3. ጳውሎስ ወንጌልን በተግባር ሲተረጉም፤ ገላ. 5-6።
   «በነፃነት ፀንታችሁ ቁሙ» ገላ. 5፡1-10። «በመንፈስ ተመላለሱ» ገላ.5፡11-16። «እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም» ገላ. 6፡1-10።

የገላትያ መልእክት ንድፍ



ምዕ. 1-2 ጳውሎስ ከሰበከው ወንጌልና ከጨበጠው ሥልጣን የተነሣ ለተፈጠሩት ጥያቄዎች መልሶች ያቀርባሉ። ሆኖም የነዚህ መልሶች በመለኮታዊና በተግባራዊ ትምህርቶ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ጳውሎስ የወንጌልን እውነትና የራሱን ሥልጣን ያረጋገጣቸው በግል ምስክርነት፥ በእግዚአብሔር ቃል ማስረጃዎችና የአብርሃምና የሁለት ልጆቹንም ምሳሌ በመጠቀም ነው። ክርስቲያኖች እንደ ይስሐቅ «የተስፋ ልጆች» ስለሆኑ ነፃ ናቸው። እንደገና ወደ ባርነት ቀንበር የምንመለሰው ለምንድነው? የኦሪት ሕግ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ምንም ሥፍራ የለውም፤ ምክንያቱም እኛ በክርስቶስ አማካይነት ለኦሪት ሕግ ሞተናል፤ ገላ. 2፡10-20። በኃጢአት ተጠምደን እንዳንኖር ክርስቶስ ነፃነት ሰጥቶናል። የኦሪት ሕግ ሥርዓቶችን መጠበቅ የወንጌል ተፈላጊ አካል ነው ብሎ በሚያስገድደው ሐሰተኛ ትምህርት ጳውሎስ በጣም የተረበሸው ለምንድነው? 2ኛ ቆሮ. 10-11 አንብቡ።

1. ከኩነኔ ጻድቅ ሆኖ መገኘት የሚቻለው ክርስቶስን በማመንና እርሱ ለሰው ባደረገው ሥራ ብቻ ሆኖ ሳለ ተቃራኒው ትምህርት ግን ሥራንና እምነትን አጣምሮ ለማቅረብ ሞክሯል። ነገር ግን ሰው በክርስቶስ የማዳን ሥራ ላይ ምንም ነገር ሊጨምርበት አይችልም።
2. የጳውሎስ ሥልጣን አገልግሎት በጥርጣሬ ላይ እንዲወድቅ አድርጉ ነበር።
3. በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ከፍፍል፥ ጥርጥርና መደናገር እንዲፈጠር አድርጉ ነበር።

ኢየሱስ ስለ ሐሰተኛ መምህራን ምን ይላል? ማቴ. 23 አንብቡ።

1. ኢየሱስ ፈሪሳውያን በውጭ ጻድቅ የሚመስሉ ሲሆኑ ልባቸው በተንኮልና በኃጢአት የተሞላ ነው፤ ግብዞችም ናቸው ብሏል።
2. ፈሪሳውያን ሕዝቡ ከትንሽ ቅመም እንኳ ሳይቀር አስራት እንዲያወጣ ሲጠይቁ እነርሱ ግን የበለጡትን የሕግ ነገሮች እንደ ፍርድ፤ ምሕረትና እምነት የመሳሰሉትን ስለማይጠብቁ ዕውሮች መሪዎች ናቸው ብሏል።

የጳውሎስ መልዕክቶች በሦስት ክፍሎች እንደተከፈሉ ከዚህ ቀደም ተምረናል። ገላትያ ከጳውሎስ የጉዞ መልእክቶች መካከል አንዱ ነው። የጉዞ መልዕክቶች፡-

1. ገላትያ፤
2. 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ፤
3. 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ፤
4. ሮሜ ናቸው። የአጻጻፋቸው ቅደም ተከተል ምናልባት ከፍ ብሎ እንደተዘረዘረው ሳይሆን አይቀርም።

## የእያንዳንዱ መልእክት አቢይ ትምህርት

1. ገላትያ ደህንነት በፀጋ።
2. 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ - የክርስቶስ መመለስ፤ የጌታ ቀን።
3. 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስ - የክርስቲያን ባሕርይ።
   - የጳውሎስ ሥልጣን።
4. ሮሜ - በእምነት ጻድቅ ሆኖ መገኘት።

የእያንዳንዳቸውን የጳውሎስ መልእክቶች አቢይ ትምህርት አጥኑ።

## ጥያቄዎች

1. ሦስቱ የገላትያ ዋና ዋና ክፍሎች ምን ምንድናቸው?
2. የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች የሚያስተምሩት ምን ነበር?
3. የገላትያ ዋና መለኮታዊ ትምህርት ምንድነው?
4. ጳውሎስ በሐሰተኛው ትምህርት በጣም የተረበሸው ለምን ነበር?
5. የጳውሎስን መልእክቶች አቢይ ትምህርት አጥኑ።

## የቤት ሥራ

ገላትያ 1-6 በክለሳ መልክ አንብቡ።

# ትምህርት አርባ አምስት

## የገላትያ መልእክት ማብራሪያ

### 1. ማብራሪያ ገላ. 1-2

ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ የተቀበለውን ሥልጣን ለማረጋገጥ ሦስት ማስረጃዎች ያቀርባል። 1ኛ. ወንጌልን የተቀበለው በራዕይ አማካይነት ከእግዚአብሔር ነው፤ ከሌሎችም ሐዋርያት አልተቀበለውም፤ ገላ. 1፡11-24። 2ኛ. ጳውሎስ 3 ዓመታት ካመነ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ሐዋርያትን በመጠየቅ እነርሱ የሚሰብኩት ወንጌል እርሱ ከሰበከው ጋር አንድ እንደሆነ አረጋገጧል፤ ገላ. 1፡18፤ የሐዋ. 11፡29-30። 3ኛ. የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች ጳውሎስ ከሐዋርያት አለቃ ከጴጥሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት ተጠራጠሩ። ጳውሎስ በአንጾኪያ ከጴጥሮስ ጋር አለመስማማት እንደፈጠረ ተናግሯል፤ ነገር ግን ጴጥሮስ ስለ ግብዝነቱ በመሳሳቱ እርሱ ራሱ የሐዋርያትን አለቃ ገስፆት ነበር፤ ገላ. 2፡12-24።

ወደ ክርስቶስ ከመጣ በኋላ ተመልሶ ወደ አሪት ሕግ ማፈግፈግ ክርስቶስ አያድንም እንደማለት ይቆጠራል ብሎ ጳውሎስ ተናግሯል። ነገር ግን እኛ በክርስቶስ ሆነን ለአሪት ሕግ ሞተናል፤ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለእግዚአብሔር ለመኖር ነፃ ወጥተናል።

### 2. መለኮታዊ ትምህርት ገላ. 3-4

ደህንነት በፀጋ እንጂ በአሪት ሕግ አይደለም። የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች ለብዙ መቶ ዓመታት ያከበርነውን ሕግ ጳውሎስ አንቋሽሾታል ብለው ክስ አቅርበውበታል። ጳውሎስ ሲመልስላቸው የሰው ደህንነት የሕግን ሥርዓቶች በመጠበቅ ሳይሆን ሰውም የሚፀድቀው በእምነትና በፀጋ ብቻ መሆኑን አስረድቷቸዋል። የገላትያ አማኞች በእምነታቸው ምክንያት በደረሰባቸው ስደት ለምን እንደገና ወደ አሪት ሕግ እስራት ለመመለስ እንደሚፈልጉ ጳውሎስ ይጠይቃቸዋል። መከራ የተቀበሉት በከንቱ ነበር?

ከዚያም አብርሃም የፀደቀው በእምነት እንደነበር ለማረጋገጥ ጳውሎስ ከብሉይ ኪዳን ይጠቅስላቸዋል፤ ዘፍጥ. 15፡6። እግዚአብሔር ደግሞ በዘፍጥ. 22፡18 ላይ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በአብርሃም ምክንያት እንደሚባረኩ ወይም እንደሚፀድቁ ተናግሯል። የኦሪት ሕግ የማይጠብቁት ሰዎች እንደሚረገሙ ጳውሎስ ከዘዳ. 27፡26 በመጥቀስ ያሳስባቸዋል። ነገር ግን በእምነት ለፀደቁት ሰዎች ክርስቶስ የሕግን እርግማን ተሸክሞላቸዋል፤ ገላ. 3፡13-14። ጳውሎስ የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች የሰበኩትን ሕግ በመጥቀስ የተሳሳቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተጠቀመበት የአብርሃም በረከት ለአሕዛብ የሚደርሰው በአንድ በኩል ብቻ ነው፤ ይኸውም በእምነት አማካይነት በክርስቶስ በኩል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች በፍፁም አልታጠፉም፤ ስለዚህ የአብርሃምም ቃል ኪዳን በሕግ አልተሻረም። ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው ተስፋ በክርስቶስ በኩል ተፈጽሟል።

ታዲያ እግዚአብሔር የኦሪትን ሕግ ለምን ሰጠ? የኦሪት ሕግ ጊዚያዊ ሲሆን የተሰጠውም ኃጢአትን ለማጋለጥ ነበር፤ ገላ. 3፡21-22። ሰው ችግሩን መረዳት አለበት፤ ይኸውም ለደህንነት ወደ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት በእግዚአብሔር ቁጣ ሥር መሆኑን ነው። የኦሪት ሕግ ለክርስቶስ መንገድ አዘጋጀለት እንጂ አንድ አይሁድ እንኳ አላዳነም። ከዚህ ይልቅ ኃጢአታቸውን ተረድተው ለምሕረት ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ አድርጓቸዋል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ከነበሩት ሰዎች የዳኑት ልክ እንደ ዛሬ ዘመን ሰዎች በእምነት አማካይነት በፀጋ ነበር፤ ዘፍ. 6፡8ን ከዕብ. 11፡7 ጋር አንብቡ። እነርሱ የክርስቶስን መምጣት ወደፊት ሲጠባበቁ እኛ ደግሞ ዛሬ ክርስቶስ ያደረገውን ነገር ወደኋላ መለስ ብለን እንመለከታለን።

ቀጥሎ ጳውሎስ ለእነርሱ ያለውን ፍቅር መሠረት በማድረግ ይለምናቸዋል። ለእነርሱ ካለው ፍቅር የተነሣ እውነትን እንደሚነግራቸው ይገልጽላቸዋል። በመጨረሻም ጳውሎስ ሁለቱን የአብርሃም ልጆች እንደምሳሌ ይጠቀምባቸዋል እስማኤል በሕግ ቀምበር ሥር ያሉት ሰዎች ምሳሌ ሲሆን የባርነትን ሥርዓት ይጠቁማል። ይስሐቅ ግን በክርስቶስ በኩል በነፃነት የተወለዱት ሰዎች ምሳሌ ነው። ሣራ ይስሐቅን ለመውለድ ብዙ ዓመታት እንደጠበቀች ሁሉ አይሁድም ደግሞ የክርስቶስን መምጣት ለብዙ ዓመታት ተጠባብቀዋል። አሁን በክርስቶስ ያሉት በሙሉ ከአይሁድም ከአሕዛብም ሁሉቱም የነፃነት ልጆች ናቸው።

## 3. ተግባራዊ ትምህርት ገላ. 5-6

የክርስቲያን ነፃነት ወደ ስሕተት ይመራል? ከኦሪት ሕግ ነፃ የወጣ ሰው እንዳሻው ሊኖር ይችላል?

በክርስቶስ የሚያምን ሰው በእርሱ በኩል በእምነት ባገኘው ነፃነት ፀንቶ ሊቆም ይችላል። ወደ ኦሪት ሥርዓቶች ማፈግፈግ ወደ ባርነት መመለስ ነው። እግዚአብሔር በመንፈስ እንድንመላለስ ወደ ነፃነት ጠርቶናል፤ በነፃነትም እንዲጠብቀን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ይሰጠናል።

የሰው ኃጢአት ዋጋ በመስቀል ላይ ተከፍሏል። አሮጌው የሥጋ ተፈጥሮ በክርስቶስ ያገኘነውን አዲሱን ሕይወት ወይም ተፈጥሮ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግና ለማሸነፍ ስለሚጣጣር አሁንም በአማኝ ሕይወት ውስጥ ጦርነት እየተካሄደ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሲኖር ደካማውን ለመርዳትና ለማጽናናት፤ በችግሩ ውስጥ ከሚገኙት ጋር ሐሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥና አንዱ የአንዱን ሸክም ለመሸከም

ፍቅርና ፍላጐት ይሰጠዋል። ይህ በመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚመላለስ ሰው ብቻ ሊፈጽመው የሚችለው የክርስቶስ የፍቅር ሕግ ነው።

ሐሰተኞቹ መምህራን ስለ ግዝረት በመመካታቸው ጳውሎስ ይገስጻቸዋል። ለክርስቶስ አገልግሎት ሲል የጳውሎስ ሰውነት በሙሉ ጠባሳ የተሸከመ ቢሆንም ከክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል በስተቀር ሌላ ትምክሕት እንደሌለው ይናገራል። ክርስቶስ የሰጠው ነፃነት ኃላፊነትን ያስከትላል።

## የገላትያ መልእክት ጥቅም

1. ጻድቅ ሆኖ መገኘት ከእምነት እንደሆነና ደህንነት በፀጋ ብቻ መሆኑን በግልፅ ያስተምራል።
2. ክርስትና ከአይሁድ እምነት የተለየ መሆኑ በዚህ መልእክት ተገልጧል።
3. ይህ መልእክት አሁንም በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ለሆነው በፀጋ ላይ ሥራ ስለ መጨመር ትምህርት መልስ ይሰጣል።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ስለ ራሱ ሥልጣን ያቀረባቸው 3 ማረጋገጫዎች ምን ምን ነበሩ?
2. በገላትያ መልእክት ውስጥ ዋናው መለኮታዊ ትምህርት ምንድነው?
3. እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ቃል ኪዳን ፍፃሜ ያገኘው በማን ነው?
4. በክርስቶስ የተገኘው ነፃነት ኃጢአት የመሥራት ፈቃድ ይሰጣል? መልሳችሁን አብራሩት።

## የቤት ሥራ

ለዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ክለሳ ተዘጋጁ።

# ትምህርት አርባ ስድስት

## የዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ክለሳ

## ምክር ለመምህሩ

የዓመቱን የመጀመሪያ አጋማሽ ፈተና ከማቴዎስ እስከ ገላትያ ካሉት ክፍሎች አውጥተው ያዘጋጁ። ተማሪዎችዎን ለክለሳ እንዲረዳቸው ከእያንዳንዱ ትምህርት በኋላ የሚገኙትን ጥያቄዎች ይጠይቁአቸው። የዓመቱን የመጀመሪያ አጋማሽ ፈተና ለማዘጋጀት ስለሚረዳዎት የሚከተሉትን ትምህርቶች ይከልሱአቸው:- ትምህርት 5፣ 15፣ 21፣ 31፣ 41ና 45።

## ምክር ለተማሪዎች

ለዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ፈተና ለመዘጋጀት ከማቴዎስ ወንጌል እስከ ገላትያ መልእክት ድረስ ክለሳ አድርጉ።

# ትምህርት አርባ ሰባት

## ምክር ለመምህሩ

ለዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑ። የሚከተለው የዓመቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ፈተና ምን እንደሚመስል ለማሳየት የቀረበ ምሳሌ ነው። መልሶቹ ከፈተናው በኋላ ተሰጥተዋል።

## መልሶቹ ከፈተናው በኋላ ተሰጥተዋል።

1. ማዛመድ

__________ሀ/ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅሰው ወንጌል 1. እስጢፋኖስ
__________ለ/ የኢየሱስን እናት የማርያምን እውነተኛ 2. ጴጥሮስና
የሥጋ ዝምድና የሚያቀረበው ወንጌል ጳውሎስ
__________ሐ/ የሐዋርያት ሥራ ሁለት ዋና ዋና 3. ኤልማስ
የባሕርይ ምሳሌዎች
__________መ/ በተለይ ለሮማውያን የተጻፈው ወንጌል 4. ፊልጶስ
__________ሠ/ በስፈት ድሆችን ታገለግል የነበረችው 5. ሉቃስ
ሴት
__________ረ/ ከኢትዮጵያ ለመጣው ሰው ወንጌልን 6. ጢሞቴዎስ
አብራራለት
__________ሰ/ የመጀመሪያው ክርስቲያን ሰማዕት 7. ማርቆስ
__________ሸ/ ጳውሎስ «ልጄ» ብሎ የሚጠራው ወጣት 8. አቂላና
ጵርስቅላ
__________ቀ/ በቆሮንቶስ ከተማ ድንኳን ሰፊዎች 9. ማቴዎስ
__________በ/ ስጦታዎችንና ምዕዋቶችን ስለ መስጠት 10. ዶርቃ
የተለየ ትምህርት የሚያቀርበው መልእክት
__________ተ/ የመጽሐፉ አቢይ ትምህርት የክርስቲያን 11. 2ኛ ቆሮንቶስ
ጠባይ ነው
__________ቸ/ የአካይያ ወይም የግሪክ ዋና ከተማ 12. 1ኛ ቆሮንቶስ

__________ኀ/ የታሪክ መጽሐፍ13. ግሪክ
__________ነ/ አዲስ ኪዳን የተጻፈበት ቋንቋ14. የሐዋርያት ሥራ
__________ኘ/ በጳፋ የነበረው አስማተኛ15. ቆሮንቶስ

## 2. በባዶ ሥፍራ መሙላት

ሀ/ የ____________ወንጌል ኢየሱስን የሰው ልጅ አድርጐ ያቀርበዋል።
ለ/ የማርቆስ ወንጌል ኢየሱስን____________አድርጐ ያቀርበዋል።
ሐ/ የ____________ወንጌል ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጐ ያቀርበዋል።
መ/ የማቴዎስ ወንጌል በተለይ የተጻፈው ለ____________ነበር።
ሠ/ በ____________ወንጌል ማዕከላዊው ነጥብ የሚሆነው ኢየሱስ 12ቱን ደቀ መዛሙርት እንዲሰብኩና እንዲፈወሱ ሲልካቸው ነው።
ረ/ የማቴዎስ ወንጌል ማዕከላዊው ነጥብ የሚሆነው የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እርሱ____________እንደሆነ መመስከር ሲጀምሩ ነው።
ሰ/ በ____________መልእክት ውስጥ ጳውሎስ ሐዋርያ መሆኑን እና ወንጌልን የመስበክ መብት ለመከላከል ተገዶ ነበር።
ሸ/ የ____________ወንጌል ብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳንን ያያይዛል።
ቀ/ «እመን» የ____________ወንጌል ቁልፍ ቃል ነው።
በ/ ማርቆስ ከእነርሱ ጋር አብሮ የመጓዝ አሳብ በ____________ና____________በ መካከል አለመስማማትን ፈጠረ።
ተ/____________አንድ ሰው «ወደ መቄዶንያ መጥተህ እርዳን» የሚል ጥሪ ሲያደርግለት በራዕይ ተመልክቶ ነበር።
ቸ/ በበዓለ ሐምሳ ቀን በ____________ከተማ____________ሲሰበክ የሚያህሉ ሰዎች በክርስቶስ አምነዋል።
ኀ/____________ና____________በሄሮድስ ተገደሉ።
ነ/ በ____________መልዕክት ውስጥ ጳውሎስ ለመስበክ ያለውን ነፃነት ለማስከበር የግል የሕይወት ታሪኩን በይበልጥ ያቀርባል።
ኘ/ በኢየሩሳሌም የነበረው ስለ____________ደንቦች አወጣ።

## 3. እውነት ወይም ሐሰት

________ሀ/ ገላትያ ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው መልእክቶች መካከል አንዱ ነው።
________ለ/ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አቀማመጥ በተጻፈበት ዘመን ቅደም ተከተል ነው።
________ሐ/ የአዲስ ኪዳን ቃላት ትክክለኛ መሆናቸው በተገኙ በብዙ የግሪክ ብራናዎች ተረጋግጧል።
________መ/ በኢየሱስ ዘመን አይሁድ ይጠቀሙበት የነበረው ቋንቋ አራምኛ ነበር።
________ሠ/ ኢየሩሳሌም የተደመሰሰችው በ70 ዓ.ም. ቲቶ በተባለው የሮም ጦር አዛዥ አማካይነት ነው።
________ረ/ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ የሰፈረው የኢየሱስ የዘር ሐረግ እስከ አዳም ድረስ ይደርሳል።
________ሰ/ እግዚአብሔር ከአይሁድ ጋር ለመሥራት ያቀደውን ፈጽሟል
________ሸ/ ሰው በምርጫና በሥራው ኃጢአተኛ ነው።

________ቀ/ ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ ጨርሶ ወደ ሮም አልሄደም።
በ/ እግዚአብሔር ለፈቀደው ምሕረቱን የማሳየት መብት አለው።

## 4. ምርጫ:- ተስማሚውን መልስ ምረጡ

1. የአሪት ሕግ
   ሀ/ ኃጢአትን ለማሳየት እንጂ ከኃጢአት ለማዳን አልተሰጠም።
   ለ/ ሰውን ያጸድቃል።
   ሐ/ ከፀጋ ጋር ተመሳሳይ ነው።
2. የአይሁድ ወግ አጥባቂነት
   ሀ/ ደህንነት በፀጋ ብቻ እንደሆነ ያስተምራል።
   ለ/ የእምነትና የአሪት ሕግ ሥራ ሁለቱም ለደህንነት አስፈላጊ እንደሆነ ያስተምራል።
   ሐ/ ሰው በእምነት እንደሚጸድቅ ያስተምራል።
3. የገላትያ መልእክት ዋና ትምህርት
   ሀ/ የጳውሎስ የሐዋርያነቱ ሥልጣን
   ለ/ የክርስቲያን መንፈሳዊ አረማመድ
   ሐ/ ጻድቅ ሆኖ መገኘት ያለ አሪት ሕግ ሥራ በክርስቶስ በኩል በእምነት ነው የሚል ነው።
4. ደርቤ፤ ልስጥራና ኢቆንዮን በውስጥ የሚገኙ ከተሞች ናቸው።
   ሀ/ ሶርያ
   ለ/ መቄዶንያ
   ሐ/ ገላትያ
5. የ1ኛ ቆሮንቶስ ዓላማ
   ሀ/ በኃጢአት ላይ ለሚያተኩሩት ሐሳቦች መልስ ለመስጠት፤ የክርስቲያን ነፃነትና መንፈሳዊ ሥጦታዎች ነበር።
   ለ/ በክርስቶስ እምነው ስለሞቱት ለማብራራት ነበር።
   ሐ/ መስጠትን በሚመለከት መመሪያን ማቅረብና እምነታቸውን እንዲፈትኑ ማድረግ ነበር።

## 5. ትምህርቱን ከሚያቀርበው የመልእክት ክፍል ጋር በይበልጥ የሚስማማውን ምረጡ።

1. ሀ/ ጻድቅ የሆነው የእግዚአብሔር ሕግ ሰው ሊጠብቀው ከሚችለው በላይ ይጠይቀዋል።
   ለ/ ጻድቅ የሆነው የእግዚአብሔር ሕግ ለሰው ኃጢአቱንና ችግሩን በማሳየት ወደ ክርስቶስ ያቀርበዋል።
2. ሀ/ እግዚአብሔር በበላይነት መብቱ ሁሉን ነገር ለሰው ጥቅም ያደርጋል።
   ለ/ እግዚአብሔር የበላይ ስለሆነ ምሕረቱን ለሰው ሊገልፅ ወይም ላይገልፅ ይችላል።
3. ሀ/ አዲሱ ተፈጥሮ ከአሮጌው የሥጋ ተፈጥሮ ጋር በጦርነት ላይ ነው።
   ለ/ ሰው ከፍተኛ ኃይል እንደሚያስፈልገው ሲረዳና በግል መፍጨርጨሩ ለማሸነፍ አለመቻሉን ሲገነዘብ፤ በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ድል ያደርገዋል።
4. ሀ/ ወንድ የሴት ራስ ነው።

ለ/ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ ባልም የሚስት ራስ ነው።

5. ሀ/ በክርስቶስ ነፃነት አለን።

ለ/ የክርስቲያን ነፃነት ለሌሎች ኃላፊነት አለበት።

6. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር ድርሰቶች ጻፉ።

1. ክርስቲያን ለአገሩ መንግሥት ያለበት ኃላፊነት ምንድነው?
2. የክርስቲያን ደህንነት ያለፈ የአሁንና የወደፊት ገጽታ በአጭሩ አብራሩ።
3. በሐዋርያት ሥራ የተጠቀሰው የኢየሩሳሌም ጉባዔ ምክንያት በአጭሩ አብራሩ።
4. የመንፈሳዊ ሥጦታዎች ዓላማ ምንድነው?
5. የእግዚአብሔር ቃል ለእያንዳንዱ ጥቃቅን ጥያቄ የተብራሩ ደንቦችን አይሰጠንም፤ ነገር ግን ከዚህ ይልቅ የምንመራባቸውን መመሪያዎች ይሰጠናል። ከክርስቲያን ነፃነት አንፃር የተሰጡትን መመሪያዎች አብራሩአቸው።

## ምክር ለመምህሩ

ይህ ፈተና ለምሳሌ ብቻ የቀረበ ነው። እርስዎ ባስተማሩት መሠረት ከማቴዎስ እስከ ገላትያ ያሉትን ጠቅላላ ትምህርቶች ያጠቃልላል ብለው የሚያምኑበትን ተመሳሳይ ፈተና በዚህ መልክ ያዘጋጁ።

## የፈተናው መልሶች

### 1. ማዛመድ

9 ሀ
5 ለ
2 ሐ
7 መ
10 ሠ
4 ረ
1 ሰ
6 ሸ

### 2. በባዶ ሥፍራዎች መሙላት

ሀ/ ሉቃስ
ለ/ የእግዚአብሔር አገልጋይ
ሐ/ ዮሐንስ
መ/ አይሁዶች
ሠ/ ማርቆስ
ረ/ መሲህ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ
ሰ/ 2ኛ ቆሮንቶስ
ሸ/ ማቴዎስ
ቀ/ ዮሐንስ

በ/ ጳውሎስና በርናባስ
ተ/ ጳውሎስ
ቸ/ ኢየሩሳሌም - ጴጥሮስ - 3000
ኀ/ ያዕቆብና መጥምቁ ዮሐንስ
ነ/ 2ኛ ቆሮንቶስ
ኘ/ ጉባዔ - ሥጋ ስለመብላት

## 3. እውነት ወይም ሐሰት

ሐሰት ሀ
ሐሰት ለ
እውነት ሐ
እውነት መ
እውነት ሠ
እውነት ረ
ሐሰት ሰ
እውነት ሸ
ሐሰት ቀ
እውነት በ

## 4. ምርጫ

ሀ. 1
ለ. 2
ሐ. 3
መ. 3
ሠ. 1

## 5. በይበልጥ ተስማሚ የሆነውን ምረጡ

ሀ. 2
ለ. 1
ሐ. 2
መ. 2
ሠ. 2

## 6. አጫጭር መልሶች

ሀ/ መገዛት፣ ክብር መስጠትና ታዛዥነት፣ ግብር መክፈል፤ ሮሜ 13፡1-7።
ለ/ ያለፈው፡- ከኃጢአት ቅጣት ድነናል።
የአሁኑ፡- ከኃጢአት ኃይል በመዳን ላይ ነን።
ወደፊት፡- ከኃጢአት ፈጽሞ ነፃ እንሆናለን።
ሐ/ በአይሁድና በአሕዛብ ክርስቲያኖች መካከል የተፈጠረ ግጭት።
መ/ ለማነፅ፣ ለማበረታታት ወይም ሌሎችን ለማጠናከር።
ሠ/ ደካማውን ላለማሰናከል። ከነፃነት ጋር ለሌሎችና ለእግዚአብሔር ኃላፊነት አለ።

## የቤት ሥራ

ኤፌሶን 1-3ን አንብቡ።

# ትምህርት አርባ ስምንት

## መግቢያ

1. ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፤ እርሱ በእስር ቤት ሳለ ከጻፋቸው መልእክቶች መካከል አንዱ ሲሆን በሮም እስር ቤት ሳለ የጻፈው ነው፤ ትምህርት 1 ሐ ተመልከቱ።
2. የተጻፈበት ዘመን 60 ዓ.ም. ገደማ ነው። ብዙ የኤፌሶን መልእክት ቃላት ከቆላስይስ መልእክት ጋር ስለሚመሳሰሉ ሁለቱ መልእክቶች በአንድ ወቅት መጻፋቸው አያጠራጥርም።
3. የተጻፈው ለማን ነበር? ምናልባት ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያናትና በአካባቢያቸው ለነበሩት ነው፤ ሆኖም በየትም ሥፍራና በማንኛውም ወቅት ለሚገኙ አማኞች ችምር ነው።
4. ኤፌሶን የምትገኘው የት ነበር? በትምህርት 43 ውስጥ የሚገኘውን ካርታ ተመልከቱ።
5. በኤፌሶን መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት፡- በበረከት መመላለስ።
6. በኤፌሶን መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች፡- ኤፌ. 1፡3 መንፈሳዊ በረከት በክርስቶስ። ኤፌ. 4፡1 በክርስቶስ በተጠራንበት መጠራት በሚገባ ተመላለሱ።
7. የኤፌሶን ከተማ፡- የሮም አውራጃ በነበረቸው በእስያ ከሚገኙት ከተሞች መካከል እጅግ በጣም ታዋቂ ከተማ ነበረች። ይህች ከተማ የባሕር ወደብና የንግድ ማዕከል ነበረች። በተጨማሪ የግሪክ ጣዖት የነበረቸው የዲያና ማዕከላዊ የአምልኮ ሥፍራ ነበረች፤ የሐዋ. 19፡23-41።

## የኤፌሶን መልእክት ዓላማ

1. ቤተ ክርስቲያናት የመንፈስን አንድነት እንዲጠብቁ የቀረበ ልመና ነበር፤ ኤፌ. 4፡3።
2. እግዚአብሔር ያቀደውን ዓላማ በቤተ ክርስቲያን አማካይነትና በክርስቲያን አረማመድ ውስጥ ለማብራራት ነበር።

## የኤፌሶን መልእክት ልዩ ባሕርያት

1. ይህ መልእክት ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መልእክቶች ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን ይገልጻታል፤ ኤፌ. 2፡19-22 አንብቡ።
2. አይሁድና አሕዛብ በክርስቶስ አካል ውስጥ እኩል መሆኑን ያስተምራል፤ ኤፌ. 2፡11-18፤ 3፡1-12 አንብቡ።
3. በቤተሰብና በቤት ውስጥ ስለሚገኙት ግንኙነቶች ጠቃሚ መመሪያ ይሰጣል፤ ኤፌ. 5፡21-6፡9 አንብቡ።
4. አማኝ ከክፉ መንፈሳዊ ኃይላት ጋር ያለውን ግጭት ይገልጻል፤ ኤፌ. 6፡10-20 አንብቡ።

5. ቤተ ክርስቲያን ከዚህ ዓለም ጋር በአንድነት እንዴት መመላለስና መኖር እንዳለባት ግልፅ የሆነ መመሪያ ይሰጣል፤ ኤፌ. 4፡1-3፤ 17-32፤ 5፡1-21።

## ጥያቄዎች

1. የኤፌሶን መልእክት አቢይ ትምህርት ምንድነው?
2. የኤፌሶን መልእክት የተጻፈው ለማን ነበር?
3. በኤፌሶን መልእክት ውስጥ የሚገኙት ሁለት ቁልፍ ቃላትና ሁለት ቁልፍ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?
4. ከክፉት ኃይላት ጋር ለምናደርገው ጦርነት ምን ዝግጅት ተደርጓል?
5. ይህ መልእክት ለኤፌሶን ሰዎች ያለው ዓላማ ምንድነው?

## የቤት ሥራ

ኤፌሶን 4-6 አንብቡ።

# ትምህርት አርባ ዘጠኝ

## የኤፌሶን መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የአዲሱ ሕይወት ሀብቶች ወይም በረከቶች፤ ምዕ. 1-3
   ሀ. መግቢያ፤ ምዕ. 1፡1-3።
   ለ. በክርስቶስ የምናገኛቸው መንፈሳዊ ሀብቶች፤ 1፡4-14።
   ሐ. የጳውሎስ የመጀመሪያ ጸሎት ‐አማኞች ዕውቀት እንዲያገኙ ነው፤ 1፡15-23። መ. በክርስቶስ ያገኘነው መንፈሳዊ ሥፍራ፤ 2፡1-22።
   ሠ. የጳውሎስ 2ኛ ጸሎት አማኞች ያገኙትን ዕውቀት በሥራ ላይ እንዲያውሉት ብርታት እንዲያገኙ ነው፤ 3፡14-21።
2. የአዲሱ ሕይወት ምስክርነት ወይም ባሕርይ፤ ምዕ. 4-6
   ሀ. በኅብረት ወይም በአንድነት መመላለስ፤ 4፡1-32።
   ለ. የእግዚአብሔር ተከታዮች መሆን፤ 5፡1-6፡9።
   ሐ. መንፈሳዊ ኃይላትን መዋጋት፤ 6፡10-20።
   መ. መደምደሚያ፤ 6፡21-24።

በክርስቶስ ሆኖ ከመንፈሳዊ ሀብቶቹ ወይም በረከቶቹ ጋር ያገኘውን ሥፍራ ወይም አቋም ‘ተረዳ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በክርስቶስ አማካይነት ያገኘውን አዲስ ሕይወት ‘ሳያል። በክርስትና ኅብረታችን አንድነትና ውህደት ይኖራል። የእግዚአብሔር ተከታዮች ‘ንደመሆናችን መጠን በፍቅር እንመላለሳለን፤ ከክፉ ኃይላት ጋር የምናደርገውን ጦርነት ‘ናካሄዳለን።

የኤፌሶን ክርስቲያኖች በሚገባ ክርስቶስንና ያከናወነላቸውን ሥራዎች ለማወቅ እንዲች ጳውሎስ ጸለየ። ቀጥሎም ክርስቶስን ካወቁ በኋላ ከክፉ ኃይላት ጋር ስላላቸው ጦርነትና በዓለ ኑሮአቸው ውስጥ በዚህ ዕውቀት በመጠቀማቸው ኃይል እንዲያገኙ ጸለየላቸው።

## የኤፌሶን መልእክት




3. የአማኞች መንፈሳዊ ሀብቶች ምን ምንድናቸው?
   - ሀ. መረጠን፤ ኤፌ. 1፡4።
   - ለ. ልጆቹ አደረገን፤ ኤፌ. 1፡5።
   - ሐ. ተቀባይነት እንዲኖረን አደረገን፤ ኤፌ. 1፡6።
   - መ. አዳነን፤ ኤፌ. 1፡7።
   - ሠ. ይቅር አለን፤ ኤፌ. 1፡7።
   - ረ. ፈቃዱን ገለፀልን፤ ኤፌ. 1፡8-10።
   - ሰ. ውርስ አወረሰን፤ ኤፌ. 1፡11-12።
   - ሸ. አተመን፤ ኤፌ. 1፡13።
   - ቀ. የርስታችንን መያዣ ሰጠን፤ ኤፌ. 1፡14።
4. ከእምነታችን የተነሣ ያገኘው ሥፍራ ምንድነው?
   - ሀ. በክርስቶስ ውስጥ ነን፤ ኤፌ. 1፡3።

ለ. በሰማያዊ ዓለም ውስጥ ገብተናል፤ ኤፌ. 1፡3።
ሐ. የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ኤፌ 1፡5።

## ጥያቄዎች

1. በክርስቶስ ያለንን አዲስ ሕይወት ያገኘነው መቼ ነበር?
2. አዲስ ሕይወት ሊያገኝ የሚችለው ማን ነው?
3. በክርስቶስ የሚገኘው ሕይወት ምን ይሰጣል?
4. አማኝ አዲሱን ሕይወት የሚገልፅባቸውን ሦስት መንገዶች ጥቀሱ።
5. የአማኝን መንፈሳዊ ሀብቶች ዘርዝሩ።

## የቤት ሥራ

ኤፌ. 1-6 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ

## የኤፌሶን መልዕክት አጭር ማብራሪያ

### ኤፌሶን 1

በክርስቶስ የተሰጠን መንፈሳዊ በረከቶች ወይም ሀብቶች ከአሁን ጀምሮ የኛ ናቸው። ወደፊት ብቻ እናገኛለን ብለን መጠበቅ አያሻንም። እግዚአብሔር ባርኮናል፥ መርጦናል፥ ልጆቹ እንድንሆን አስቀድሞ ወስኖናል፥ ውርስ አዘጋጅቶልናል፤ በማኅተሙ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ አትሞናል፥ ክርስቶስ ሥልጣን ባለው ሥፍራ አስቀምጦናል። እነዚህ ነገሮች በሙሉ የተመደቡልን ከዓለም መፈጠር በፊት ነበር፤ ኤፌ. 1፡4። አማኞች የእግዚአብሔር ጥሪና በውስጣቸው የሚሠራውን የኃይሉን ታላቅነት እንዲያውቁ እግዚአብሔር ዕውቀትና ጥበብ እንዲሰጣቸው ጳውሎስ ጸልዮላቸዋል።

### ኤፌሶን 2

በክርስቶስ የዘላለምን ሕይወት የሰጠን እንደ ፀጋው ስጦታ እንጂ እንደ ጥረታችን ወይም እንደ መልካም ሥራችን አይደለም። የክርስቶስ ሆነን እርሱ በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መልካም አኗኗር እንድንኖር እግዚአብሔር አቅዷል።

እግዚአብሔር ከአይሁድና ከአሕዛብ ወገን ያመኑትን ሁሉ በክርስቶስ አንድ አድርጓል። እርሱ በመካከላቸው የነበረውን ልዩነትና ክፍፍል አስወግዶ ሰላማቸው ሆኗል።

### ኤፌሶን 3

የቤተ ክርስቲያን ወይም የእግዚአብሔር ጉባዔ ትርጉም ባለፉት ዘመናት ምስጢር ሆኖ ቆይቶ ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለሐዋርያትና ለነቢያት ገልጾታል። እግዚአብሔር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አማካይነት ማመን እንዳለባቸው ገልጿል።

አሁን ያመኑት ሁሉም የአንዱ አካል የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባሉች ናቸው። እግዚአብሔር በአካሉ አማካይነት መላእክት ለሚመስሉት መሪዎች ዓላማውን እየገለጸላቸው ነው። ለዓለሙ ምስክሩ እንዲሆን በዚህ አካል ይጠቀምበታል።

ጳውሎስ የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በእርሱ ሥቃይና እሥራት ተስፋ እንዳይቆርጡ ይለምናቸዋል። እግዚአብሔር ይህንን ነገር የፈቀደው ለእነርሱ ጥቅም ነው።

አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ ብርታትን አግኝተው እግዚአብሔር በክርስቶስ ያለውን ፍቅር እንዲያስተውሉና የእነርሱ የነበረውን ኃይል እንዲጠቀሙበት እንደገና ይጸልያል። የክርስቶስ ወገን ከሆንን እነዚህ ነገሮች የኛም ናቸው።

## ኤፌሶን 4

የኤፌሶን ክርስቲያኖች የክርስቶስ ወገን በመሆናቸው ለእነርሱ የተሰጠው የእግዚአብሔር ኃይል ለዓለም እንደተመሰከረ ጳውሎስ ይነግራቸዋል። ለዓለም ከሚቀርበው ምስክርነት መካከል በአማኞች ውስጥ የሚገኘው ኅብረት ዋነኛው ነጥብ ነው። ኅብረታቸውን ለመጠበቅ እንዲችሉ ጳውሎስ ሰባት ሁኔታዎችን ይዘረዝራል ኤፌ. 4፡4-6 አንብቡ። በተጨማሪ በወንጌል አገልግሎታችን ውስጥ እንድንጠቀምባቸው እግዚአብሔር ሥጦታዎችን ይሰጣል። እነዚህ ስጦታዎች አባሉችን ለማነፅና ለማበረታታት እንዲችሉ እግዚአብሔር የክርስቶስን አካል ፍላጐት ተመልክቶ ያከፋፍላቸዋል።

የአካሉ አባሉች ስጦታዎቻቸውን በሚለማመዱበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ይጽናናሉ፤ የሐሰት ትምህርት ተገንዝበው እንዲያጋልጡት ያስችላቸዋል። እያንዳንዱ አባል የራሱ የሆነ ሥጦታ አለው፤ ለሰይጣንም መግቢያ ቀዳዳ ሳይሰጡት በአንድነትና በፍቅር መሥራት ይኖርባቸዋል። ጳውሎስ በክርስቶስ ውስጥ ያለን ሰዎች ልንሠራቸውና ላንሠራቸው የሚገቡንን ነገሮች ይዘረዝራል፤ ኤፌ. 4፡25-32።

## ኤፌሶን 5

ክርስቶስን ለዓለም የምናውጅበት ወይም የምንመሰክርበት ሌላው መንገድ ከእግዚአብሔር እንደተወለዱ ልጆች በመኖራችን ነው። በፍቅር፥ በንጽህናና በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መመላለስ አለብን፤ 5፡1-14።

ክርስቲያኖች ያሉንን ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም በጥበብና በጥንቃቄ መኖር ይገባናል። ሞኞች ሳንሆን የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። በመንፈስ መሞላትና እርስ በእርሳችን በእግዚአብሔር ቃል፥ በዜማና በምስጋና ቅኔ መያያዝ አለብን።

ቤታችንና የቤተሰብ ግንኙነታችን እግዚአብሔር በሰጠን መመሪያዎች ላይ የተመሠረቱ ከሆኑ ለዓለም ምስክርነት ያቀርባሉ። ክርስቶስ ራሱ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደመሆኑና ራሱን ለእርሷ አሳልፎ እንደሰጠ እያንዳንዳችንም ለሌላው ራሳችንን መስጠት ይኖርብናል።

እግዚአብሔር ቤቶቻችን የእርሱ ምስክሮች እንዲሆኑ በማቀድ በውስጣቸው የመለኮታዊ ሥልጣን አመጣጥ አቅጣጫ ገልጾልናል፤ ኤፌ. 5፡22-6፡9።

ኤፌሶን 6

ሦስተኛው የምንመሰክርበት መንገድ ከሰይጣን የክፋት ኃይላት ጋር በምናደርገው ጦርነት ነው። እግዚአብሔር የሰይጣንንና የአጋንንትን ኃይላት የክፋት ዕቅድ ለመቋቋምና ለመመከት እንድንችል የምንጠቀምበት መንፈሳዊ የጦር ዕቃ አዘጋጅቶልናል። ነገር ግን በመጣሪያችን የሰይጣንን ተንኮል ለመቋቋም ትጉህና የተዘጋጀን መሆን ያስፈልገናል፤ ኤፌ. 6፡12-18። በጸሎት አማካይነት በማንኛውም ጊዜ የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት እንችላለን።

## ጥያቄዎች

1. አሁን በክርስቶስ ያሉን ሀብቶች ምን ምንድናቸው?
2. መንፈሳዊ ሀብቶቻችን የተወሰኑት መቼ ነበር?
3. ክርስቶስ ሰላማችን የሆነው በምን መንገድ ነው?
4. እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቀምባት አንድ መንገድ ግለጹ።
5. እግዚአብሔር መንፈሳዊ የጦር ዕቃ ለቤተ ክርስቲያን የሰጠበት ዓላማ ምንድነው?
6. ቤተሰብ ለዓለም ምስክር የሚሆነው ምን ሲሆን ነው?
7. ለምናደርገው መንፈሳዊ ጦርነት እግዚአብሔር ምን አዘጋጅቶልናል?

## የቤት ሥራ

ፊልጵስዩስ 1-2 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ አንድ

## ለፊልጵስዩስ መልእክት የቀረበው መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን ወቅቱ በሮም እሥር ቤት ሳለ ነው፤ ፊልጵ. 1፡6። የጻፈበት ዘመን 61 ዓ.ም. ገደማ ሳይሆን አይቀርም።

## የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን

ጳውሎስ በዚያ ወንጌልን የሰበከው በ2ኛ ወንጌላዊ ጉዞው ወቅት ነው፤ የሐዋ. 16፡21። ይች ቤተ ክርስቲያን በአውሮፓ ከተመሠረቱት መካከል የመጀመሪያዋ ናት። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ብዙ ሴቶች ነበሩ፤ የሐዋ. 16፡13-14፤ ፊልጵ. 4፡2-3። ለጳውሎስ ከባድ ፍቅር የነበራቸውና ስጦታዎችም የሚልኩለት ነበሩ፤ ፊልጵ. 4፡14-16።

በትምህርት 43 ውስጥ የሚገኘውን ካርታ ተመልከቱ።

## የፊልጵስዩስ መልዕክት ዓላማ

1. ጳውሎስ የጻፈላቸው እስራቱን በማመልከት ሊያጽናናቸው ፈልጐ ነበር። ይህንን እሥራት ጌታ ወንጌልን ለማስፋፋት እንደሚጠቀምበት ይነግራቸዋል፤ ፊልጵ. 1፡12-14።
2. ጳውሎስ የጻፈላቸው የኦሪትን ሕግ መጠበቅ ለደህንነት አስፈላጊ ነው ብለው ካስተማሩት የአይሁድ ወገ አጥባቂዎች እንዲጠነቀቁ ለማድረግ ነበር፤ ፊልጵ. 3፡3-9።
3. ጳውሎስ የጻፈላቸው በአፍሮዲጡ በኩል ስለላኩለት ሥጦታ ምስጋና ለማቅረብና /ፊልጵ. 4፡10፤ 15-16/ ስለ ደረሰባቸው መከራ ለማጽናናት ነበር፤ ፊልጵ. 4፡4-7፤ 19።

## የፊልጵስዩስ መልዕክት ልዩ ባሕርያት

1. ይህ መልዕክት ጳውሎስ ስለ ፊልጵስዩስ ሰዎች ያለውን ፍቅር የሚገልፅ ሞቅ ያለ የግል ደብዳቤ ነው፤ ፊልጵ. 1፡3፤5፤8-9፤4፡1።
2. የምስጋና ደብዳቤ ነው፤ ፊልጵ. 4፡15-16።
3. ለክርስትና ትምህርት የሰጠው ሥፍራ አነስ ያለ ነው።
4. በወንጌል አገልግሎት ውስጥ ለሴቶች የተለየ ሥፍራ ይሰጣቸዋል፤ ፊልጵ. 4፡2-3።

## ጠቃሚ ርዕሶች

1. በመከራ መደሰት
   ሀ/ ፊልጵ. 1፡1-2፡2፡18 በጳውሎስ መከራ ላይ ያተኩራል።
   ለ/ ፊልጵ. 3፡1-4፡23 በቤተ ክርስቲያን መከራ ላይ ያተኩራል።
2. ትሕትናን በሚመለከት ምሳሌአችን ክርስቶስ ነው፤ 2፡5-11።
3. የወንጌል አገልግሎት፤ ፊልጵ. 1፡5፤ 7፤ 12፤ 17፤ 27፤ 2፡22፤ 4፡13፤ 15 አንብቡ።
4. ጳውሎስ ጢሞቴዎስና አፍሮዲጡ ዓይነተኛ አገልጋዮች መሆናቸውን ያሳያል፤ ፊልጵ. 2፡17-30።

## በፊልጵስዮስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ፊልጵ. 1፡21፤ ክርስቶስ ሕይወታችን
2. ፊልጵ. 2፡5፤ ክርስቶስ ምሳሌአችን።
3. ፊልጵ. 3፡7፤ ክርስቶስ የእምነታችንና የተስፋችን ምንጭ።
4. ፊልጵ. 4፡13፤ ክርስቶስ ብርታታችን።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስን መልእክት የጻፈበት 3 ምክንያቶች ጥቀሱ።
2. ጥቂቶቹ የፊልጵስዩስ መልእክት ልዩ ባሕርያት ምን ምንድናቸው?
3. ለያንዳንዱ ምዕራፍ ቁልፍ ጥቅስ ጥቀሱ።

4. ጳውሎስ ለመከራና ለጭንቀት ጊዜያት የሰጠው ምክር ምን ነበር?

## የቤት ሥራ

ፊልጵስዩስ 3-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ ሁለት

## የፊልጵስዩስ መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. ክርስቶስ ሕይወታችን፤ ምዕ. 1፡።
2. ክርስቶስ ምሳሌአችን፤ ምዕ. 2።
3. ክርስቶስ የእምነታችንና የተስፋችን ምንጭ፤ ምዕ. 3።
4. ክርስቶስ ብርታታችን፤ ምዕ. 4።

የፊልጵስዩስ መልእክት ንድፍ፡




በፊልጵስዩስ መልእክት ውስጥ በማንኛውም አቅጣጫ ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት ሚያተኩረው በደስታ ላይ ነው። ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ክርስቲያኖችና በየትም ሥፍራ ሚገኙትን አማኞች በክርስቶስ ባገኙት ሕይወት በእምነታቸውና በመከራቸው ደስተኞች ንዲሆኑና የእግዚአብሔር ሰላምም ልባቸው በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚጠብቁ ያሳስባቸዋል።

# የፊልጵስዩስ መልእክት አጭር ማብራሪያ

## ፊልጵስዩስ 1

ጳውሎስና ጢሞቴዎስ የተወደዱ ለነበሩት ለፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ሰላምታ ይልኩላቸዋል። ጳውሎስ ለእነርሱ እንደጸለየላቸው ክርስቶስም በእነርሱ ውስጥ የጀመረውን መልካም ሥራ እንደሚቀጥል እምነት እንዳለው ይነግራቸዋል።

ስለ ደረሰበት ጳውሎስ የፊልጵስዩስን አማኞች ያጽናናቸዋል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወንጌልን ለማስፋፋት ይጠቀምበት ስለነበረ ነው። ጳውሎስ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ ነው፤ ብሞት ለእኔ ጥቅም ነው፤ ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር መሆን ነውና፤ ሆኖም እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ቆይቼ በእምነታችሁ እንዳጽናናችሁ እፈልጋለሁ» ብሎ ያበረታታቸዋል።

ጳውሎስ ለወንጌል ሲል ብዙ መከራ ደርሶበታል፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡23-27 አንብቡ። የፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ እንደ ነበሩ ያውቃል። ነገር ግን በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙና ጠላቶቻቸውን እንዳይፈሩ ይነግራቸውል። በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ መከራ ይደርስባቸዋል፤ ነገር ግን ክርስቶስ ሁልጊዜ ድል አድራጊ ነው።

## ፊልጵስዩስ 2

ክርስቶስ ኢየሱስ ምሳሌአችን ነው። አቋማችን የክርስቶስን ሊመስል ይገባል። እርሱ በፈቃዱ ራሱን አዋረደ። ሰማያዊ ጌትነቱንና ክብሩን ትቶ እንደ አገልጋይ ሆነ። የሚያሳፍረውን የመስቀል ሞት እንኳ እስከ መሞት ድረስ ለአባቱ ታዘዘ። ክርስቶስ መዳኛችን ስለ ሆነ እርሱ በፈቃደኝነት ይህንን ደህንነት ለእኛ በሰጠበት አኳኋን ልንጠቀምበት ይገባናል፤ ዮሐ. 6፡27-29።

ማጉረምረምና በሌሎች ላይ ስሕተት መፈለግ የለብንም። ከዚህ ይልቅ በዚህ ዓለም ውስጥ ስንመላለስ በጨለማ እንደሚያበራ ብርሃን ልንሆን ይገባናል። ጳውሎስ በፈቃዱ ሕይወቱንና ኃይሉን መስዋዕት አድርጐ ለእግዚአብሔር አፈሰሰ፤ ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን ብለው ይህንን ለማድረግ የፈቀዱት ብዙ ሰዎች አልነበሩም። ሆኖም ፈቃደኞች ከሆኑት አንዱ ጢሞቴዎስ ነበረ፤ ጳውሎስ በእሥር ቤት ታሥሮ ለመምጣት ባልቻለበት ጊዜ እርሱን ወደ ፊልጵስዩስ እንደላከው ይናገራል።

## ፊልጵስዩስ 3

ጳውሎስ ግዝረት ለደህንነት አስፈላጊ ነው ብለው ከሚያስተምሩት የአሪት ሕግ መምህራን እንዲጠብቁ የፊልጵስዩስን አማኞች አስጠንቅቋቸዋል። በክርስቶስ እንጂ በሥጋ ሥራ አይደሰቱ። በክርስቶስ መሆናችንን የሚገልጥ የቃል ኪዳኑ ምልክት ከኃጢአት መለየት ነው። የእኛም ዓላማ ክርስቶስን ለማወቅና በእርሱ መከራ ለመካፈል ፈቃደኞች መሆን አለብን። ለርሱ የተለየን ስለሆንን የሥጋችን ምኞቶች እንዲመሩን ፈንታ መስጠት የለብንም። ወደፊት እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የከበረ አካል ለመልበስ እንጠባበቃለን።

አማኞች በመከራና በጭንቀት ጊዜም እንኳ ቢሆን ደስተኞች እንዲሆኑ ጳውሎስ ይመክራቸዋል። እኛም ዘወትር ስንጸልይ ከምስጋና ጋር መጸለይ ይኖርብናል፤ ይህም ለልባችን የእግዚአብሔርን ሰላም ይሰጠዋል። አዕምሮአችንን በመልካም አስተሳሰቦች የምንሞላ ከሆነ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን ይሞላዋል፤ ፊልጵ. 4፡8 አንብቡ። በሕይወታችን ውስጥ ለሚያጋጥሙን ለማንኛውም ዓይነት ሁኔታ እግዚአብሔር የራሱን ሰላም ሲሰጠን የዕለት ችግራችንንም ያቃልልልናል።

## ጥያቄዎች

1. መከራ እንኳ ቢመጣ ከክርስቶስ ጋር የተደረገ ትክክለኛ ግንኙነት ውጤቱ ምንድነው?
2. በፊልጵስዩስ ላለችው ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጣት ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
3. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እንደ ወኪሉ አድርጐ ለመላክ የመረጠው ለምንድነው?
4. ጳውሎስ እሥራቱን በሚመለከት ምን አለ?
5. አማኞች ዘወትር መደሰት ያለባቸው ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

ቆላስይስ 1-2 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ ሦስት

## ለቆላስይስ መልእክት የቀረበው መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ሲሆን በዚህ ወቅት በሮም እስር ቤት ውስጥ ነበር። የተጻፈበት ዘመን 60 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል።

## የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን

ቆላስይስ የምትገኘው ከኤፌሶን በስተ ምሥራቅ 150 ኪሎ ሜትር ርቃ ነው፤ በትምህርት 43 ውስጥ የሚገኘው ካርታ ተመልከቱ። ጳውሎስ ይህንን መልእክት በጻፈበት ወቅት ገና ቆላስይስን አልጐበኛትም ነበር፤ ነገር ግን ምናልባት ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሁኔታ ከኤጳፍራ ሰምቶ ይሆናል፤ ቆላ. 1፡7፤ 4፡12። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሚገኙት አብዛኞቹ አማኞች ከአሕዛብ ወገን ያመኑ ነበሩ።

## የቆላስይስ መልእክት ዓላማ

1. አማኞችን ወደ መንፈሳዊ ዕድገት ለመምራት ነው፤ ቆላ. 1፡28።

2. በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከተሰጠው ሐሰተኛ ፍልስፍና እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ ነው፤ ቆላ. 2፡8፤ 18-23።
3. ለቆላስይስና ሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያናት ያለውን ሸክም ለማሳወቅ ነው፤ ቆላ. 2፡1።

## በቆላስይስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ሙላት፤ 1፡19-25፤ 2፡9።
2. ምስጢር፤ 1፡26-27፤ 2፡2።
3. ፊተኛ፤ 1፡18።

## በቆላስይስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. ቆላ. 1፡23፤ «ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት ፀንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል።»
2. ቆላ. 1፡27-28፤ «የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው፤ በክርስቶስ ፍፁም የሚሆን ሰው።»
3. ቆላ. 3፡16፤ «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ።»
4. ቆላ. 4፡2፤ «ከማመስገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ።

በቆላስይስና በኤፌሶን መልእክቶች መካከል የሚገኝ ተመሳሳይነት

| ቆላስይስ | ኤፌሶን |
| --- | --- |
| ሀ) በተፈጥሮ ሁሉ ላይ የክርስቶስ ራስ መሆን ነው፣ 1፣16 – 18፤ 2፣10። | ሀ) በተለይ በቤተ ክርስቲያን ላይ ራስ መሆኑ፤ ኤፌ. 1፣22፣23። |
| ለ) ፀሎት፣ ቆላ. 1፣9 – 14 | ለ) ፀሎት፣ ኤፌ. 3፣14 – 21 |
| ሐ) የዕውቀትንና የጥበብን አስፈላጊነት ያስተም ራል፡ ቆላ. 1፣9። | ሐ) የዕውቀትንና የጥበብን አስፈላጊነት ያስተም ራል፣ ኤፌ. 1፣17። |
| መ) በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን ስህተት የሚቃወም ትምህርት ይሰጣል፤ | መ) በየትም ሥፍራ የሚገኝ ሐሰተኛ ትምህርትን የሚቃወም ትምህርት |
| ሠ) የቤተ ሰብ ግንኙነቶችን የሚመለከት ትምህ ርት፣ 3፣18 – 23። | ሠ) የቤተ ሰብን ግንኙነቶች የሚመለከት ትምህ ርት፡ 5፣21 – 6፣9። |

## በቆላስይስ መልእክት ውስጥ የሚገኙ ጠቃሚ ትምህርቶች

1. የክርስቶስ ራስነት በተፈጥሮ ሁሉ ላይ፤ ቆላ. 1፡14-19።
2. ቤዛነት፤ ቆላ. 1፡14-20፤ 2፡14-15።
3. ስለ ሰው ፍልስፍና የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤ ቆላ. 2፡8፤ 18-23።
4. የክርስቲያን ባሕርይ፤ ቆላ. 3፡1-17።
5. የክርስቲያን ግንኙነቶች፤ ቆላ. 3፡18-4፡6።

በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ዋና ችግር ከክርስቲያኖች አለመብሰል የተነሣ ነበር። ለምሳሌ፡-

1. ለክርስቶስ የሚገባውን ሥፍራ ስላልሰጡት ጳውሎስ ስለ ክርስቶስና ስለ ሥራው ጻፈላቸው፤ 1፡15-23።
2. በሰብዓዊ ፍልስፍና ተስበው ነበር፤ 2፡4፤ 8።
3. አንዳንዶች ለደኅንነት የኦሪትን ሕግ መጠበቅ አስፈላጊ ነው ብለው አስተምረው ነበር፤ 2፡8፤ 16፤ 3፡11።
4. አንዳንዶች የመላእክትን አምልኮ አስተምረው ነበር፤ 2፡18።
5. አንዳንድ ደንቦች እያወጡ ራሳቸውን ከሌሎች የበለጠ በማድረግ ይመኩ ነበር፤ 2፡20-23።

## ጥያቄዎች

1. የቆላስይስ መልእክት ዓላማ ምን ነበር?
2. የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን በውስጥዋ ወደነበረው ዋና ስሕተት የመራት መሠረታዊ ችግር ምን ነበር?
3. ጳውሎስ የሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
4. የክርስቶስን የበላይነት መረዳት የሚያስፈልገው ለምንድነው?
5. የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህንን ስላልተረዱ ምን ደረሰባቸው?

## የቤት ሥራ

ቆላስይስ 3-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ አራት

## የቆላስይስ መልእክት አስተዋፅዖ

1. ወንጌል፤ ቆላ. 1። ክርስቶስ በፍጥረት ላይ ያለውን የበላይነት ያብራራል።
2. ክብር፤ ቆላ. 2፡1-3፡4። በአማኞች ውስጥ የክርስቶስ በኩርነትን ይገልጻል።
3. ዕድገት፤ ቆላ. 3፡5-4፡6። በክርስቲያን አኗኗር ውስጥ የክርስቶስ የበላይነት ያበሥራል።
4. ሰላምታ፤ ቆላ. 4፡7-18። የጳውሎስ ሰላምታ ለቆላስይስና ለሉዶቅያ ሰዎች ነው።

ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ምኞትና ጸሎት መንፈሳዊ ብስለት እንድታገኝ ነበር፤ 1፡28 አንብቡ። ጳውሎስ በትምህርቱ ውስጥ የነበረው ግብ የቆላስይስ አማኞች ፍፁም እንዲሆኑ ወይም በክርስቶስ እንዲጐለምሱ ነበር። ይህ ነገር የሚቻለው መንፈስ ቅዱስ ኑሮአችውን እንዲቆጣጠር ሲፈቅዱለት ብቻ ነበር፤ 1ኛ ተሰ. 5፡23-24፤ 2ኛ ተሰ. 2፡13 አንብቡ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ራሳችንን መለየት ቅድስና ተብሎ ይጠራል።

ጳውሎስ ክርስቶስ የተፈጥሮ ሁሉና የአካል ራስ እንደሆነ አድርጐ ግልፅ በሆነ መንገድ ያቀርበዋል። ከዚያም የቆላስይስ አማኞች በሐሰት ትምህርት ተስበው እንዳይጠፉ

ያስጠነቅቃቸዋል። ጳውሎስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ዕውቀት እንዲኖራቸው፤ ጥበብና ማስተዋል አግኝተው በርሱ ሐሳብ እንዲመላለሱ ይጸልያል። ላለመብሰል ችግራቸው የሚሆነው መፍትሔ የእግዚአብሔር ፈቃድ ዕውቀትና ማስተዋል እንዲሁም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

<u>የቆላስይስ መልእክት ንድፍ</u>




## የቆላስይስ መልእክት አጭር ማብራሪያ

### ቆላስይስ 1

በዚህ በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ ክርስቶስ «ሁሉ በሁሉ» ሆኖ ቀርቧል። ከሰላምታው በኋላ ጳውሎስ የቆላስይስ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል ዕውቀትና መንፈሳዊ ጥበብ እንዲኖራቸው፥ እንዲሁም ለዚህ ዕውቀትና ጥበብ ለመታዘዝ ማስተዋል እንዲያገኙ ይጸልያል። ጳውሎስ ክርስቶስን እንደ ቤዛ - 1፡14፤ እንደ ፈጣሪ - 1፡15፤ 17፤ እንደ የአካሉ ራስ፤ እንደ የሰው አስታራቂና - 1፡20-22። እንደ የሕዝቡ ቀዳሽ አድርጐ ያቀርበዋል፤ 1፡22።

ይህ የወንጌልና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ባለፉት ዘመናት ምስጢር ሲሆን አሁን በክርስቶስ ለሆኑት ተገልጾላቸዋል ብሎ ጳውሎስ ይናገራል።

## ቆላስይስ 2፡1-3፡4

ይህ የወንጌል ምስጢር ለአይሁድና ለአሕዛብ ለሁሉቱም «የክብር ተስፋ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው» የሚል ነው። ጳውሎስ በቆላስይስና በሎዶቅያ ላሉት አድማጮቹ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ተለይተው እንዳይወሰዱ አሳስቧቸዋል፤ 2፡1። ከአንዳንድ ሐሰተኛ መምህራን ፍልስፍና - 2፡8፤ ከመላእክት አምልኮና - 2፡18 ከአይሁድ ወግ አጥባቂነትም እንዲጠበቁ ያሳስባቸዋል፤ 2፡20-23። አማኞች በክርስቶስ ፍፁማን ሆነዋል። በደህንነታችን ላይ ምንም የምንጨምርበት ነገር የለም። ክርስቶስ የአካል ራስ ነው፤ እርሱ ሕያው ሆኖ ስለሚኖር በእምነት የክርስቶስ ወገን የሆንን ሁላችን እርሱ በፈጸመልን ሥራ በሕይወት እንኖራለን። አማኝ የክርስቶስ አካል በመሆኑ ከእርሱ ጋር ለኃጢአት ኃይልና ኩነኔ ሞቶ ተነሥቷል። እርሱ ሕይወታችንና የእምነታችን ምንጭ ሆኗል። የሚያስፈልገው ሁሉ በክርስቶስ ስለተፈጸመ እርሱ ባከናወነው ሥራ ላይ ለመጨመር ከሚሞክር ከማንኛውም ትምህርት መጠንቀቅ አለብን። ይህንን የክርስቶስን ሙላት ለማግኘት ጥረትና ፍላጐት እንዲኖረን ያስፈልጋል። ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ በርሱ ክብር ውስጥ ተካፋዮች እንሆናለን።

## ቆላስይስ 3፡5-4፡6

የክርስቶስ የአካል ክፍል ስለሆንን ለእርሱ ክብር መኖር አለብን። በመጀመሪያ አሮጌውን የሥጋ ምኞት መግደል አለብን፤ 3፡5፤ 7። ከዚያም አዲሱን ሕይወት መልበስ ይኖርብናል፤ ይህም አዲስ ሕይወት በክርስቶስ በኩል ያገኘነው ነው። ኃይላችን በሆነውና የመንፈስን ፍሬዎች በሕይወታችን ውስጥ በሚያፈራው በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ራሳችንን ማኖር ይኖርብናል፤ 3፡12-15።

የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት፥ እርስ በርስ ለመማርና ለመጽናናት ጊዜ መውሰድ አለብን። ማንኛውንም ነገር ስንሠራ ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ በክርስቶስ ስም መሆን ይኖርበታል። በቤተሰባችንና በመሥሪያ ቤታችን ደረጃ እንዲሁም ከክርስቶስ ውጭ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር በምናደርጋቸው ግንኙነቶች ውስጥ ለክርስቶስ ብለን መሥራት አለብን።

## ቆላስይስ 4፡7-18

በዚህ መልእክት መደምደሚያ ላይ ጳውሎስ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን አማኞች እንዲረዳቸውና እንዲያበረታታቸው የሚልከውን ቲኪቆስን ያስተዋውቀዋል። በተጨማሪ አሁን ክርስቲያን የሆነውን አናሲሞስን እንደገና ወደ እነርሱ እንዲመለስ ይልከዋል፤ የፊልሞናን መልእክት አንብቡ። ከዚህ በኋላ ጳውሎስ በሮም ለሚገኙ ለሌሎች ክርስቲያኖች ሰላምታ ያቀርብላቸዋል። ወንጌልን በማስተማር ታማኞች ናቸው ብሎ ከቆጠራቸው አብረውት ከሚሠሩ ሰዎች ጋር ሊያስተዋውቃቸው ይፈልጋል።

ይህ የቆላስይስ መልእክት በተጨማሪ የአግረጻ ሰላምታ ታክሎበት ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ጭምር የተጻፈ ነበር፤ 4፡16-17። ጳውሎስ እሥራቱን እንዲያስቡ በማሳሰብ ደብዳቤውን በምክር ይደመድማል።

# ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን የጸለየው ስለምን ነበር?
2. የአማኝ የክብር ተስፋ ምንድነው?
3. ለጌታ የምንሰጠው አገልግሎት መመራት ያለበት በምን መመሪያ ነው?
4. የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በአማኝ ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው?

# የቤት ሥራ

ለሚቀርብላችሁ የሙከራ ፈተና ኤፌሶንን፣ ፊልጵስዩስንና ቆላስይስን ከልሱ።

# ትምህርት ሃምሳ አምስት

## የጳውሎስ የእሥር ቤት ደብዳቤዎች ክለሳ

## የቤተ ክርስቲያን ችግሮችና መፍትሔዎች

የጳውሎስ የእስር ቤት ደብዳቤዎች ክለሳ የቤተ ክርስቲያን ችግሮችና መፍትሄዎች

| መጽሐፍ | ችግር | መፍትሄ |
|---|---|---|
| ኤፌሶን | የአንድነት አስፈላጊነት፣ ኤፌ. 4፣ 1—6። | «የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ፣ ኤፌ. 6፣ 10—18። |
| ፊልጵስዩስ | መከራ፣ ፊል. 1፣ 29። | «ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ!» ፊል. 4፣ 4—6። |
| ቆላስይስ | መንፈሳዊ አለመብሰል ቆላ. 1፣ 10። | «የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በእናንተ ይኖራል» ቆላ. 1፣ 27። |
| ፊልሞና | ንስሐ የገባው የኮበለለ ባሪያ፣ ፊልሞና 10—12። | አናሲሞስን እንደ ወንድም ተቀበለው፣ ፊልሞና 16። |

## የመልእክቶቹ ዓላማ

1. ኤፌሶን፦ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ያቋቋመበት ዓላማ ክርስቲያን እንዴት መመላለስና ሰይጣንን ድል ማድረግ እንዳለበት ለማብራራት ነው።
2. ፊልጵስዩስ፦ ስለ ደረሰባቸው ፈተና ክርስቲያኖችን ለማጽናናትና ስለሰጡት ስጦታ የፊልጵስዩስን ክርስቲያኖች ለማመስገን ነው፤ ፊልጵ. 4፡4-7።
3. ቆላስይስ፦ መንፈሳዊ ዕድገትን ለማበረታታትና ከሰብዓዊ ፍልስፍና እንዲጠነቀቁ ለማሳሰብ ነው፤ ቆላ. 1፡28።

## ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ምክሮች

1. ኤፌሶን፦ በተጠሩበት መጠራት በሚገባ እንዲመላለሱ፤ 4፡1። የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ እንዲጥሩ፤ 4፡3። በክርስቶስ ፍቅር እርስ በርሳቸው አንዱ ለሌላው ራሱን እንዲሰጥ፤ 5፡21። የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ እንዲለብስ፤ 6፡12-18።
2. ፊልጵስዩስ፦ ሁልጊዜ እንዲደሰቱ፤ 4፡4። ስለማንኛውም ነገር በምስጋና እንዲጸልዩ፤ 4፡6። እውነተኛ፥ ታማኝና ንፁህ የሆነውን ነገር እንዲያስቡ፤ 4፡8።
3. ቆላስይስ፦ በክርስቶስ ፍፁም ወይም የጐለመሱ እንዲሆኑ፤ 1፡28። አዕምሮአቸውና ምኞታቸው በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ እንዲያተኩር፤ 3፡12። በጥበብ በመመላለስ ጊዜውን እንዲዋጁ፤ 4፡5። ሁሉን ነገር ለክርስቶስ እንደሆነ አድርገው እንጂ ለሰው እንደሆነ አድርገው እንዳይሠሩ፤ 3፡17።

ከእያንዳንዳቸው አንድ አንድ ቁለፍ ቃል አጥኑ።

1. ኤፌሶን፦ «በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።»
2. ፊልጵስዩስ - «በጌታ ደስ ይበላችሁ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ።»
3. ቆላስይስ - «የክብር ተስፋ የሆነው ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው።»

## የጳውሎስ አገልግሎት

### በኤፌሶን የሐዋ. 19፡1-20፡1

1. ጳውሎስ በዚያ የነበሩትን አማኞች ስለ መንፈስ ቅዱስ አስተማራቸው፤ የሐዋ. 19፡1-7።
2. ለሦስት ወራት በመኩራብ አስተማረ፤ የሐዋ. 19፡8።
3. የጢራኖስ በሚባል ት/ቤት ለ2 ዓመታት አስተማረ፤ የሐዋ. 19፡9-10።
4. ብዙ ሰዎችን ፈወሰ፤ ብዙዎችም አመኑ፤ ደግሞም የአስማት መጻሕፍታቸውን አቃጠሉ፤ የሐዋ. 19፡11-12።
5. ከኤፌሶን እንዲወጣ ካደረጉት ዲያና ከተባለችው ጣዖት አምላኪዎች ጋር ከፍተኛ ግብግብ አድርጓል፤ የሐዋ. 19፡33-20፡1።

### በፊልጵስዩስ የሐዋ. 16፡11-40

1. በወንዝ ዳር ሴቶችን አገኘ፤ የሐዋ. 16፡3።
2. ሊድያ ክርስቶስን በግሪክ አገር ካመኑት መካከል የመጀመሪያዋ ናት፤ የሐዋ. 16፡14-15።
3. ስለ ወደፊት መተንበይ ትችል ከነበረችው ልጃገረድ ጳውሎስ አጋንንት አስወጣ፤ የሐዋ. 16፡16-18።
4. ጳውሎስና ሲላስ ተደብድበው በእስር ቤት ተጥለው ነበር፤ የሐዋ. 16፡14-18።
5. የእስር ቤቱ ጠባቂና ቤተሰቡ ድነው ነበር፤ የሐዋ. 16፡25-34።
6. ጳውሎስና ሲላሳ ፊልጵስዩስን ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ፤ የሐዋ. 16፡33-40።

### በቆላስይስ

1. ጳውሎስ ቆላስይስን እንደጐበኘ የሚናገር ጽሑፍ አይገኝም፤ ቆላ. 1፡7፤ 4፡12። ጳውሎስ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ያገለግል የነበረው:-
   ሀ/ በመልእክቶች አማካይነት ነበረ። የቆላስይስ መልእክትና ምናልባትም ሌሎች መልእክቶች።
   ለ/ በጸሎቱ አማካይነት ነበር፤ ቆላ. 1፡3።

# ትምህርት ሃምሳ ስድስት

## ምክር ለመምህሩ

ከኤፌሶን፥ ፊልጵስዩስና ቆላስይስ መልእክቶች አውጣጥተው ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኑ።

## የቤት ሥራ

1ኛ ተሰሎንቄ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ ሰባት

## የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ሁለቱም የጳውሎስ የጉዞ መልእክቶች ናቸው፤ ትምህርት 1 ሐ ተመልከቱ። ሌሎቹን 4 የጳውሎስ የጉዞ መልእክቶች ቀደም ብለን አጥንተናቸዋል፤ እነርሱም ሮሜ፥ 1ኛና 2ኛ ቆሮንቶስና ገላትያ ናቸው።

የተጻፈበት ዘመን 51 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም። ምናልባትም እነዚህ የጳውሎስ የመጀመሪያ ጽሑፎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የተጻፈው ከቆሮንቶስ ሲሆን ወዲያው የተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን እንደተመሠረተች ነው። ለማን? ካመኑ ጥቂት ጊዜ ለሆናቸው ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ነው።

## የመልእክቶቹ ዓላማ

1. ስለ ሞቱት ሰዎችና ስለ ጌታ መመለስ ለማስተማርና ለማፅናናት ነበር፤ 1ኛ ተሰሎ. 4፡13-18፤ 2ኛ ተሰሎ. 3፡1-5።
2. ከእነርሱ ጋር ጥቂት ሳምንታት ባሳለፈበት ወቅት ያስተማራቸውን መሠረታዊ እውነቶች መልሶ ለማስተማር ነበር፤ 1ኛ ተሰሎ. 1፡5-10፤ 2ኛ ተሰሎ. 2፡13-17።
3. ቅዱስ ኑሮ እንዲኖሩ ለማበረታታት ነበር፤ 1ኛ ተሰሎ. 1፡12፤ 2ኛ ተሰሎ. 3፡6-15።
4. በስደት ውስጥ ያሉትን ለማፅናናት ነበር፤ 1ኛ ተሰሎ. 2፡14፤ 3፡1-4፤ 2ኛ ተሰሎ. 1፡5-10።
5. ስለ ክሕደት ለማስጠንቀቅ ነበር፤ 2ኛ ተሰሎ. 2፡1-12።

## በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የነበሩ ችግሮች

በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ በቅርብ ጊዜ ያመኑት አማኞች ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ መመለስና በክርስቶስ አምነው ስለሞቱት ያስተማረውን ትምህርት በትክክል አልተረዱም ነበር።

1. አንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በድንገት ይመጣል ብለው ይጠባበቁ ስለነበር ሥራቸውን ትተው ሥራ ፈቶች ከመሆናቸው የተነሣ በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ ይገቡ ነበር፤ 1ኛ ተሰ. 4፡11፤ 2ኛ ተሰ. 3፡11-13።
2. ክርስቶስን ይጠባበቁ የነበሩት ሌሎች ሰዎች ደግሞ በክርስቶስ አምነው ለሞቱት ክርስቶስ ሲመጣ ምን ይሆኑ ይሆን በማለት ይጨነቁ ነበር፤ 1ኛ ተሰሎ. 4፡13-18፤ 2ኛ ተሰሎ. 2፡1-4።

## በተሰሎንቄ መልእክቶች ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1ኛ ተሰሎ. 4፡16-17፤ «ጌታ ራሱ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና...» 2ኛ ተሰሎ. 3፡2፤ «ነገር ግን የሚያፀናችሁ ከክፉም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።»

## የጳውሎስ አገልግሎት በተሰሎንቄ

ጳውሎስ ለ3 ሰንበቶች በተሰሎንቄ ሕዝቡን ሲያስተምር ቆይቷል። በዚህ ወቅት ጥቂት አይሁዶችና ግሪኮች እንዲሁም ብዙ ሴቶች አምነው ከጳውሎስና ሲላስ ጋር ተባበሩ። አንዳንድ ቀናተኛ አይሁዶች ተቃውሞ በማስነሣታቸው ጳውሎስና ሲላስ ከተማይቱን ለቀው መሸሽ ነበረባቸው። የሐዋ. 17፡1-7 አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. በምዕ. 1 ውስጥ ሕዝቡ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች ይናገራቸው የነበሩት 3 ነገሮች ምን ምን ነበሩ?
2. በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበረው ችግር ምን ነበር?

3. ለሁለቱም መልእክቶች ቁልፍ ጥቅሶች ጻፉ።
4. ጳውሎስ በተሰሎንቄ ምን ያህል ጊዜ አገለገለ?
5. በመጀመሪያ በተሰሎንቄ ያመነው ማን ነበር?

## የቤት ሥራ

1ኛ ተሰሎንቄ 1-5 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ ስምንት

## የ1ኛ ተሰሎንቄ መልእክት አስተዋፅዖ

ቤተ ክርስቲያን፤ ምዕ. 1
ሐዋርያው ጳውሎስ፤ ምዕ.2
ጢሞቴዎስ፤ ምዕ. 3
የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት፤ ምዕ. 4ና 5

## የ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክት አስተዋፅዖ

ፍርድ፤ ምዕ. 1
አመፀኛው ሰው፤ ምዕ. 2
የክርስቲያን ባሕርይ፤ ምዕ 3 በተጨማሪ 1ኛ ተሰሎ. 4፡1-17።

## ለተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ምክሮች

ምክሮቹ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኝ ለማንኛውም ክርስቲያን ያገለ' እነዚህ፡-

1. በእምነት፥ ፀንታችሁ ቁሙ።
2. በጌታ የሚገዙአችሁን አክብሩ።
3. እርስ በርሳችሁ ተናነፁ፤ ደግሞም በመካከላችሁ ሰላም ይኑር።
4. የማይታዘዙትን አቅኑ፤ ደካማውን አበረታቱ።
5. ደስ ይበላችሁ፤ ጸልዩ፤ አመስግኑ፤
6. ሁሉን ፈትኑ፤ እትታለሉ።
7. ከፋትን ሁሉ አስወግዱ።
8. የዕለት ጉርሳችሁን ሠርታችሁ አግኙ፤ በሌሎች ላይ አትደገፉ።
9. በሰላም ኑሩ፤ የራሳችሁን ሥራ ተከታተሉ።
10. ከዘሙት ራቁ።
11. ትጉ፤ መልካም የሆነውን ነገር አስቡ።

## የ1ኛና የ2ኛ ተሰሎንቄ ንድፍ




ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ያለውን ሸክም አስተውሉ፤ 1ኛ ተሰ. 3፡1-5፤ 2፡17-20 አንብቡ። የጳውሎስን ማፅናኛ ተመልከቱ፤ 1ኛ ተሰሎ. 3፡6-11 አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. የክርስቶስን መምጣት ለሚጠባበቁት አማኞች ጳውሎስ በ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ የሰጠው ማስጠንቀቂያዎችና ትእዛዞች ምን ምን ነበሩ?
2. የ1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ መሠረታዊ አቢይ ትምህርት ምንድነው?
3. ክርስቶስ ለመንገሥ ወደዚህ ምድር ከመምጣቱ በፊት ማን ይገለጻል?
4. ጳውሎስ ለተሰሎንቄ አማኞች ሸክም እንደሚሰማው ለመግለጽ ምን አደረገ?

## የቤት ሥራ

2ኛ ተሰሎንቄ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት ሃምሳ ዘጠኝ

## 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ ማጠቃለያ

1ኛ ተሰሎንቄ አበክሮ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ቀን ነው፤ የኸውም በአየር ላይ የሚገለፅበትን ጊዜ ነው፤ 1ኛ ተሰሉ. 4፡13-18።

2ኛ ተሰሎንቄ አብክሮ የሚናገረው ስለ ጌታ ቀን ወይም ኢየሱስ መንግሥቱን ለማቋቋም ወደ ምድር ስለመመለሱ ነው፤ 2ኛ ተሰሉ. 2፡1-12።

### 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አንድ

ጳውሉስ ሰላምታ ሲያቀርብ በተሰሉንቄ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞች ስላላቸው እምነት፥ ፍቅርና ትዕግሥት ምስጋናውን ያቀርባል። ከዚያም በእነርሱ መካከል የሰጠውን አገልግሎት እንደገና እያወሳ መከላከያ ያቀርባል፤ ደግሞም እምነታቸው በመቄዶንያና በአካይያ አካባቢ በሙሉ ምን ያሀል እንደተነገረለት ያትትላቸዋል። በአካባቢያቸው ያሉት ሰዎች የተሰሉንቄ አማኞች ሕያውን እውነተኛ የሆነውን እግዚአብሔርን ማገልገል ከጣዖታት አምልኮ እንዴት እንደተመለሱና ከሚመጣው ከእግዚአብሔር ቁጣ የሚያድነንን የእግዚአብሔርን ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት እንደሚጠባበቁ ይናገሩ ነበር።

### 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ ሁለት

የጌታ መመለስ፥ ታማኝ አገልግሎት ላበረከቱት ደስታና ሽልማት ነው። ጳውሉስ በእነርሱ መካከል ስለነበረው አገልግሎትና ስለ ውጤቶቹ መናገር ይቀጥላል። ከዚያም ጳውሉስ ቃሉ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አድርገው ስለተቀበሉትና ለክርስቶስ ሲሉ መከራ ስለደረሰባቸው እግዚአብሔርን ያመስግናል።

### 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ ሦስት

ክርስቶስ ስለሚመለስ ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው መፋቀርና የተቀደሰ አኗኗር መኖር አለባቸው። ጳውሉስ በስደት ምክንያት ተሰሉንቄን እንዲለቅ ተገዶ ነበር። ከዚያም ወደ አቴና ሄደ። ነገር ግን ተሰደው ለነበሩት ክርስቲያኖች ይጨነቅ ነበር። ከዚያም ጢሞቴዎስ እንዲያጽናናቸው ጳውሉስ ይልከዋል፤ እርሱም መልካም ዜና ይዞለት ይመለሳል። ስለዚህ ጳውሉስ እግዚአብሔርን ያመስግንና እርስ በርሳቸው ያላቸውን ፍቅር እንዲጨምሩና በእምነታቸውም እንዲፀኑ መጸለዩን ይቀጥላል።

### 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አራት

ክርስቶስ ሲመጣ የሞቱት ቅዱሳን ይነሡና በሕይወት ካሉት ቅዱሳን ጋር አብረው ይነጠቃሉ። በ1ኛ ተሰሉንቄ 4፡1-12 ውስጥ የክርስቲያንን አኗኗር የሚመለከቱ አምስት መመሪያዎች ይገኛሉ። እነርሱም፡- 1. ከዝሙት መራቅ፤ 2. ክርስቲያን ወንድምን

አለማታለል፤ 3. እርስ በርስ መፋቀር፤ 4. በሰላም መኖርና የራስን ኑሮ መከታተል፤ 5. የዕለት ጉርስን በእጅ ሠርቶ ማግኘትና በሌሎች አለመደገፍ ናቸው።

የክርስቶስን ምፅዓትና በእርሱ አምነው የሞቱትን ሰዎች በሚመለከት ቤተ ክርስቲያኒቱ ተደናግራ ነበር። ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎ. 4፡13-18 ውስጥ አምነው ለሞቱትና እርሱም ሲመጣ በሕይወት ለሚገኙት ለሁሉቱም ሲል ክርስቶስ በአየር ውስጥ ሆኖ ለቅዱሳኑ እንደሚመጣ የሚነግረውን ታላቅ ተስፋ ጻፈላቸው።

## 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አምስት

ክርስቶስ የሚመለስበትን ሰዓት አናውቅም። ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ እንዲሁ ይመጣል። ሆኖም አማኞች ሆነን የክርስቶስን የመምጫ ሰዓት ባናውቅም በጨለማና በድንቁርና ውስጥ የምንመላለስ አይደለንም። እኛ የብርሃን ልጆች ስለሆንን ግድ የለሾች አንሁን፤ ነገር ግን ከዚህ ይልቅ በአዕምሮ የበሰልንና ንቁ እንሁን። በክርስቶስ ኢየሱስ በመሆናችን በእግዚአብሔር ቁጣ ሥር አይደለንም። ከክርስቶስ ጋር ለዘላለም አብረን ስለምንኖር በዚህ ተስፋ እንድንጽናና እርስ በርሳችንም እንበረታታ።

በቁ. 12-22 ውስጥ ረዘም ያሉ ምክሮች ቀርበዋል፤ እነዚህን ምክሮች እንብቡአቸው። አማኞች እንደመሆናችን መጠን ራሳችንን ማለት መንፈሳችንን፥ ሥጋችንንና አካላችንን መግዛት ይኖርብናል፤ ክርስቶስ ሲመለስ ደግሞ ከኃጢአት ነፃ እንሆናለን። ይህን የሚያደርግልን የጠራን እግዚአብሔር መሆኑን ጳውሎስ በመልእክቱ ውስጥ ካቀረባቸው ነገሮች መካከል የመጨረሻው ታላቅ ተስፋ ነው።

## 2ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ አንድ እስከ ሦስት

የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በመከራ ላይ ስለነበሩ የመጨረሻው ታላቅ ስደት መጥቷል ብለው ስለ ጌታም መመለስ በጥርጣሬ ላይ ወድቀው ነበር። ጳውሎስም ከሰላምታው በኋላ በስደት ምክንያት ይቀበሉት ስለነበረው መከራ ያበረታታቸዋል። ከዚያም ክርስቶስ ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት ታላቅ አመፅ እንደሚኖርና የአመፅ ሰው በምድር ላይ እንደሚገለጥ ይነግራቸዋል። ሆኖም በአሁኑ ወቅት የአመፅን ሰው የሚቆጣጠር አለ፤ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን አይቀርም። ይህ የከፋት ተቆጣጣሪ ከዚህ ሥፍራ እስካልሄደ ድረስ የአመፅ ሰው በፍፁም አይገለጥም። የክርስቶስ መምጣት የማይቀር ስለሆነ አትስነፉ፤ እየሠራችሁ የዕለት ጉርሳችሁን አግኙ፤ መልካም ነገር ለመሥራት አትታክቱ፤ የግድየለሽ ሰዎች ጓደኝነት እንዲያሰናክላችሁ ፈንታ አትስጡት፤ ከዚህ ይልቅ ራሳችሁን ከእነርሱ ለዩ ብሎ ጳውሎስ አበረታታቸው።

## ጥያቄዎች

1. አንዳንዶቹን አማኞች ያሰነፋቸውና የዕለት ጉርሳቸውን ሠርተው እንዳያገኙ ያደረጋቸው ምክንያት ምን ነበር?
2. የአመፅ ሰው እንዳይገለጥ የሚከለክለው ማን ነው?
3. ጳውሎስ በተሰሎንቄ 4 ውስጥ የሚያቀርባቸው 5ቱ የክርስቲያን አኗኗር መመሪያዎች ምን ምንድናቸው

4. ነቅቶ ለሚያገለግለው የሚሰጠው ሽልማት ምንድነው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ጢሞቴዎስ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት ሰልሳ

## የ1ኛ ጢሞቴዎስ መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈበት ዘመን በ64 ዓ.ም. ገደማ ነው። የተጻፈው ለጢሞቴዎስ ነው።

## ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ በክርስቶስ ያመነው በጳውሎስ ስብከት ነበር። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን «በእምነት የወለድሁት እውነተኛ ልጄ» ብሎ ይጠራዋል። ጢሞቴዎስ በልስጥራና በኢቆንዮን አማኞች ዘንድ በጣም የተመሰከረለት ነበር፤ የሐዋ. 16፡1-2። የጢሞቴዎስ አባት አሕዛብ ሲሆን እናቱ አይሁዳዊት ነበረች። ጢሞቴዎስ በሕፃንነቱ ወቅት ብሉይ ኪዳንን ከእናቱ ተምሯል፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡5፤ 3፡14-15። ጢሞቴዎስ ከጳውሎስ ጋር ተጉዟል፤ በኋላ ደግሞ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ጉዳይ እንዲያጠናክር በዚያ እንዲቆይ ተደርጓል፤ 1ኛ ጢሞ. 1፡3-4። ጳውሎስ በሮም ሆኖ ሲጽፍለት ጢሞቴዎስ፥ ዮሐንስ ማርቆስና እዚያ ትተቸው የነበሩትን ዕቃዎች ይዞለት ቶሎ ብሎ እንዲመጣ ይጠይቀዋል፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡9፤ 11ና 13። ጢሞቴዎስ ኃላፊነት ሊቀበል የሚችል ወጣት ነበር፤ ፊልጵ. 2፡19-20 አንብቡ። ሆኖም ወጣትና ምናልባትም ዓይን አፋር ስለነበር ማበረታቻ አስፈልጎት ነበር፤ 2ኛ ጢሞ. 1፡6-7፤ 4፡12-16፤ 6፡20-21።

## የ1ኛ ጢሞቴዎስ ዓላማ

1. ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የግል ኃላፊነቱን በሚመለከትና የጌታ አገልጋይ እንደመሆኑ ምሳሌነትን እንዲያሳይ ትእዛዝ ይሰጠዋል።
2. ጳውሎስ በማስተማር፥ በማስተባበርና ቤተ ክርስቲያንን በማስተዳደር ረገድ የሚኖሩበትን የመሪነት ኃላፊነቶች በማስመልከት ለጢሞቴዎስ ትእዛዞችን ይሰጠዋል።

1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስና ቲቶ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ትምህርት አዘል መልእክቶች ተብለው ይጠራሉ፤ ይኸውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙ አገልጋዮች ላይ የሚያተኩር ስለሆነ ነው። እነዚህ መልእክቶች በሙሉ የተጻፉት በጳውሎስ የመጨረሻ ዓመታት ወቅት ነበር።

## በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1ኛ ጢሞ. 6፡12 «መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፤ የተጠራህለትንም በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለም ሕይወት ያዝ።»

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ 1ኛ ጢሞቴዎስን የጻፈበት ምክንያት ምንድነው?
2. ጳውሎስ ከጢሞቴዎስ ጋር ምን ግንኙነት ነበረው?
3. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ትምህርት አዘል መልእክቶችን ጥቀሱ።
4. ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ያወቀው መቼ ነበር?

## የቤት ሥራ

1ኛ ጢሞቴዎስ 4-6 አንብቡ።

# ትምህርት ስልሳ አንድ

## የ1ኛ ጢሞቴዎስ አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የጢሞቴዎስ መጠራት፤ ምዕ. 1።
2. በቤተ ክርስቲያን ለሚደረጉ ስብሰባዎች መመሪያ፤ ምዕ. 2።
3. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመዘኛ፤ ምዕ. 3።
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰጠ ትምህርት፤ ምዕ.4።
5. የቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ አገልግሎት፤ ምዕ. 5።
6. የጢሞቴዎስ ባሕርይ፤ ምዕ. 6።

## የ1ኛ ጢሞቴዎስ ንድፍ

**የ1ኛ ጢሞቴዎስ ንድፍ**




1ኛ ጢሞቴዎስ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ማኅበርና አስተዳደር በሚመለከት ተግባራዊ ምክር ያቀርባል። በተጨማሪ የራሱን የግል ኃላፊነት በሚመለከትና ከቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት መሥራት እንዳለበት ለጢሞቴዎስ ምክር ይሰጠዋል።

## የጢሞቴዎስ የግል ኃላፊነቶችና ምሳሌነት

1. በሐሰት ትምህርቶች ላይ ጠንካራ አቋም መውሰድ አለበት፤ 1፡3-4፤ 6-20 አንብቡ።
2. በንፁህ ልብና ሀሊና ማፍቀር ይኖርበታል፤ 1፡4-5 አንብቡ።
3. ሁብታም ለመሆን ከመመኘት መጠንቀቅ ይገባዋል፤ 6፡6-16 አንብቡ፤ ለሀብታሞች ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል።

## የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፥ ተቋምና አስተዳደር

1. የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፤ ምዕ. 2

   ሀ/ ጸሎት፡- በቅድሚያ ልመና፥ ጥያቄና ምስጋና ይገኛሉ። ስለሚድኑ ሰዎች ጸሎት ማድረግ ይገባል። ለመሪዎችና በሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ መጸለይ አለባቸው።

ለ/ ስብሰባዎች በሥነ ሥርዓት መደረግ ይኖርባቸዋል። ወንዶች ቁጡና ጨቅጫቃ መሆን የለባቸውም። ሴቶች ያለ አግባብ በወንዶች ላይ ሥልጣን መጠቀም የለባቸውም። ሴቶች በአግባብ መልበስ ይገባቸዋል።

2. የቤተ ክርስቲያን ተቋም፤ ምዕ. 3ና 4
   ሀ/ የሽማግሌዎች መመዘኛ፤ 3፡1-7።
   ለ/ የዲያቆናት መመዘኛ፤ 3፡8-13።
   ሐ/ የዲያቆናት ሚስቶች መመዘኛ፤ 3፡11።
3. የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፤ ምዕ. 5፡1-6፤ 10
   ሀ/ የሽማግሌዎችና የሴቶች ኃላፊነት፤ 5፡1-2።
   ለ/ የመበለቶች ኃላፊነትና የሚያደርግላቸው እንክብካቤ፤ 5፡3-16።
   ሐ/ የሽማግሌዎች ሥራ፤ 5፡17-25።
   መ/ የአሠሪዎችና የሠራተኞች ግንኙነት፤ 6፡1-2።
   ሠ/ የመምህራን ሥራ፤ 6፡3-10።

ክርስቶስ ብቸኛ አስታራቂ እንደሆነ በግልፅ የሚናገረውን 1ኛ ጢሞ. 2፡5ን በትኩረት ተመልከቱት።

## ጥያቄዎች

1. የጢሞቴዎስ መልእክት የእያንዳንዱን ምዕራፍ አጠቃላይ አቢይ ትምህርት ጻፉ።
2. የስብሰባዎች ልምድ መሆን የሚገባቸው ሁለት ነገሮች ጥቀሱ።
3. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ መመዘኛ ነጥቦችን ጥቀሱ።
4. የሽማግሌ ሚስት መመዘኛ ነጥቦች ምን ምንድናቸው?
5. ጢሞቴዎስ ጥንቃቄ እንዲያደርግባቸው የተሰጡትን ሦስት ነገሮች ዘርዝሩ።

## የቤት ሥራ

1ኛ ጢሞቴዎስ 1-6 አንብቡ።

# ትምህርት ሰላሳ ሁለት

## የ1ኛ ጢሞቴዎስ አጭር ማብራሪያ

### 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ አንድ

መልእክቱ የአሪትን ሕግ ያለአግባብ የተጠቀሙትን ሐሰተኛ መምህራን በማስጠንቀቅ ይጀምራል። ጳውሎስ የክርስትናን እምነት አጥብቆ እንዲይዝ ጢሞቴዎስን ይመክረዋል። ከቤተ ክርስቲያን የተባበሩ ሁለት ሰዎችን በማሳሰብ ያስጠነቅቀዋል።

### 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ሁለት

ለሰዎች ሁሉ ይልቁንም ለመንግሥት ባለሥልጣኖች ጸሎት እንዲደረግ በማሣሣት ይጀመራል። ከዚያም ክርስቲያን ሴቶች በሥርዓት እንዲለብሱና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከወንዶች የበለጠ ሥልጣን እንዳይዙ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ይገኛል። ሴቶች የባልትና ተግባራቸውን በሚገባ ሲያከናውኑ በክርስትና ሕይወታቸው የጌታን በረከት ይቀበላሉ፤ 2፡15።

## 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ሦስት

ቀጥሎ ጳውሎስ የሽማግሌዎችና የዲያቆናትን መመዘኛ ነጥቦች ያቀርባል። ሽማግሌ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነው። ዲያቆናት ደግሞ የሽማግሌዎቹ ረደቶች ናቸው። የሁለቱም መመዘኛ ነጥቦች በጣም የመሳሰላሉ። በተጨማሪ የሚስቶች መመዘኛ ነጥቦች ተሰጥተዋል፤ 3፡1-13 አንብቡ።

## 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ አራት

ለሐሰተኛ ትምህርት የተሰጠ ሌላ ማስጠንቀቂያ ይገኝበታል። አንዳንዶች የኢጋንንትን አምልኮ ሲያስተምሩ ሌሎች ደግሞ ማግባትና አንዳንድ ምግቦችን መመገብ ኃጢአት ነው ብለው ያስተምራሉ። ጢሞቴዎስ ራሱ የእግዚአብሔርን ቃል እየተመገበ በተግባርም ሆነ በአርያነት ከማስተማርና ከማስጠንቀቅ መቆጠብ የለበትም።

## 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ አምስት

ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ከሉ ሰዎች ጋር የሚኖረውን ግንኙነት በሚመለከት ለጢሞቴዎስ ትእዛዝ ይሰጠዋል። ወጣት እንደመሆኑ መጠን ሌሎች ወጣቶችን እንደ ወንድሞች፥ ሽማግሌዎችን እንደ አባቶች፥ አሮጊቶችን እንደ እናቶችና ወጣት ሴቶችን እንደ እህቶች ማስተናገድ ይገባዋል። ባልቴቶች በቤተሰቦቻቸው መረዳት ይኖርባቸዋል። ወጣት መበለቶች እንደገና ማግባት ሲኖርባቸው የሚረዳቸው ቤተሰብ የሌላቸው አሮጊት ባልቴቶች በቤተ ክርስቲያን መረዳት ይኖርባቸዋል።

ታማኝ ሽማግሌዎች በተለይም በማስተማርና በመስበክ የሚያገለግሉት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል። በ2 ወይም በ3 ምስክሮች ካልተደገፈ በስተቀር ጢሞቴዎስ ሽማግሌዎችን እንዳይከስ ጳውሎስ ያስጠነቅቀዋል።

## 1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ ስድስት

ጳውሎስ የክርስቲያን አሠሪዎችንና ሠራተኞችን ግንኙነት በሚመለከት ትእዛዝ ይሰጣል። ለሐሰተኛ መምህራንና የሀብት ምኞት በሚመጣባቸው ፈተና ተጠምደው የሚወድቁትን ሀብታሞች በሚመለከት ብዙ ማስጠንቀቂያዎች ይሰጣል። በመደምደሚያው ላይ ጳውሎስ ስለ ግሉ መንፈሳዊ ኃላፊነቶች ጢሞቴዎስን ያሳስበዋል።

## ጥያቄዎች

1. በ4፡1-5 ላይ የተጠቀሰው ሐሰተኛ ትምህርት ዛሬም በዓለም ውስጥ ይገኛል? ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ተወያዩበት።
2. ጳውሎስ የባርነት ሥርዓት እየደገፈ ነበር ወይስ በዘመኑ ስለነበረው ሁኔታ ማስተማሩ ነው?
3. በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገንዘብ ጥማት ለመሪዎች እንቅፋት የሚሆንበት ወቅት አለ?

## የቤት ሥራ

2ኛ ጢሞቴዎስ 1-2 አንብቡ።

# ትምህርት ስልሳ ሦስት

## የ2ኛ ጢሞቴዎስ ዓላማ

ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሲሆን መሞቱ የተቃረበ መሆኑ ተሰምቶታል፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡6። ጳውሎስ በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ ስደቶች መምጣታቸውን ተመልክቷል፤ ስለዚህ ለጢሞቴዎስ ሌላ ደብዳቤ እንዲፅፍ ሁለት ምክንያቶች ነበሩት።
1. ጢሞቴዎስ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ እንዲሆንና ይህንንም ለማስተማር እንዳይፈራ ለማሳሰብና ለማፅናናት ነበረ፤ 4፡2።
2. ለሚደርስበት መከራና ወደፊት ስለሚመጣው ክሕደት ጢሞቴዎስን ለማዘጋጀትና ለማበረታት ነበረ፤ 2፡1-4፤ 3፡1-5፤ 4፡3-4። የተጻፈው በ67 ዓ.ም. ገደማ ነው።

## በ2ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. ለቃሉ ታማኝ ሁን፤ 1፡13፤ 2፡15፤ 3፡16፤ 4፡2።
2. በፈተና ፅና፤ 1፡7፤12፤ 2፡3-4፤ 3፡12፤ 4፡7-8።

## ክሕደት

1. ክሕደት ምንድነው? አለማወቅ ወይም ከትምህርት የሚመጣ ጊዜያዊ ስሕተት አይደለም። እውነትን የሚያውቁና ክርስትናን ተቀብለው የነበሩ ሰዎች በእውነት ላይ ያደረጉት አመፅ ነው።
2. ክሕደት የሚመነጨው ከየት ነው? 3፡1-7 አንብቡ።
3. ከክሕደት አንፃር የእውነተኛ አማኝ ተስፋ ምንድነው? እግዚአብሔር ጤናማ አዕምሮዎችን ሰጥቶናል፤ 1፡7። እግዚአብሔር እንደሚጠብቀን ተስፋ ሰጥቶናል፤ 1፡12፤ 2፡13። እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤ ያትምማል፤ 2፡19። የእግዚአብሔር ቃል

ጥበብና የመለየት ችሎታን ይሰጣል፤ 3፡14-16። የሽልማት ቃል ኪዳን ... የጽድቅ አክሊል ነው፤ 4፡8።

4. ክርስቲያን ይህን ክሕደት የሚዋጋው እንዴት አድርጐ ነው? ጳውሎስ እንዲህ ይላቸዋል፡-
   ሀ/ በጌታ አትፈሩ፤ 1፡8።
   ለ/ በዚህ ዓለም ኑሮ ራሳችሁን አታጠላልፉ፤ 2፡4።
   ሐ/ የቃሉን እውነት ለሌሎች አስተምሩ፤ 2፡1-2።
   መ/ የእግዚአብሔርን ቃል አጥኑ፤ 2፡15፤ 3፡16።
   ሠ/ ከወጣትነት ምኞት ሽሹ፤ 2፡22።
   ረ/ በእግዚአብሔር ቃል ኑሩ፤ 3፡14።
   ሰ/ ትጉ፤ በመከራ ታገሡ፤ 4፡5።

## የጳውሎስ ስንብት

2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡6-8 አንብቡ።

1. የጳውሎስ መሞቻ ጊዜ በተቃረበበት ወቅት ብዙዎች ትተውት እንደሄዱ አስተውሉ፤ 4፡16 አንብቡ። ሆኖም ጳውሎስ ሁኔታዎች የማይመቹ በሚሆኑበት ወቅትም እንኳ ቢሆን በትጋት እንዲሰብክ ጢሞቴዎስን ያጽናናዋል፤ 4፡1-2።
2. ጳውሎስ ሞትን አይፈራም። የመሞቻው ጊዜ ስለተቃረበ ዝግጁ መሆኑን ተናግሯል። የእግዚአብሔር ቀጠሮ ዘወትር ትክክል ነው።
3. ጳውሎስ ሥራውን መልካም አድርጐ እንዲሠራና ለታማኝነቱ ሽልማት እንደሚቀበል አውቋል። ለጌታ ታማኝ የሆኑ ሁሉ ተመሳሳይ ተስፋ አላቸው።

## ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ የሚያስጠነቅቀው ከምን ዓይነት ክሕደት ነው?
2. ከክሕደት አንፃር ክርስቲያን ያለው ተስፋ ምንድነው?
3. ጳውሎስ ይህንን 2ኛ መልእክት ለጢሞቴዎስ የጻፈለት ከምን ዓላማ ተነሥቶ ነው?
4. ጳውሎስ ይህንን መልእክት ሲጽፍ በምን ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ነበር?
5. አማኝ ክሕደትን እንዴት መቋቋም ይችላል?

## የቤት ሥራ

2ኛ ጢሞቴዎስ 3-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሰላሳ አራት

## የ2ኛ ጢሞቴዎስ አጠቃላይ አስተዋፅዖ

የግል ኃላፊነት፤ ምዕ. 1
የመጋቢነት ኃላፊነት፤ ምዕ. 2

የተተነበዩ ፈተናዎች፤ ምዕ. 3
እየተቃረበ ያለው የጳውሎስ ሞት ምዕ. 4

የ2ኛ ጢሞቴዎስ መልእክት ትኩረት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ቃል አጥብቆ የመያዝን አስፈላጊነት ነው። ለምሳሌ፡-

ምዕራፍ 1፡- ጳውሎስ ያስተማረውን እውነተኛ ቃላት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አጥብቆ እንዲይዝ ጢሞቴዎስ ታዟል።

ምዕራፍ 2፡- ጢሞቴዎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለው አገልግሎቱ «እንዲያጠና ... ቃሉን በትክክል እንዲያስተምር» ተመክሯል፤ 2፡15

ምዕራፍ 3፡- የእግዚአብሔር ቃል ለሕይወት ችግሮችና ፈተናዎች፥ እውነትን ለማስተማር፥ ስሕተትን ለማረም፥ ጥፋትን ለማስተካከልና ለትክክለኛ ኑሮ ጠቃሚ ነው፤ 3፡16።

ምዕራፍ 4፡- ጊዜው ምቹ ቢሆንም ባይሆንም ለማሳመን፥ ለመገሰፅና ለማበረታታት የእግዚአብሔርን ቃል መስበክ አለብን፤ ጳውሎስ ይህንን መልዕክት ሲጽፍ በእስር ቤት ውስጥ ነበር።

የ2ኛ ጢሞቴዎስ ንድፍ



## በአካባቢው ስለሚገኝ ክሕደት የክርስቲያን ኃላፊነት

ማሳሰቢያ፡- ክሕደት ማለት እውነትን በሚያውቁትና በሚረዱት ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣት ማለት ነው። ኃላፊነቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. ቃሉን እንዲያስተምሩ ሌሎችን ማሰልጠን፤ 2፡2።
2. እንደ መልካም ወታደር መከራ መቀበል፤ 2፡3።
3. ከክፉ ሁሉ መራቅ፤ 2፡4፤22።
4. ቃሉን ማጥናት፤ 2፡15።
5. መትጋትና መከራን መታገስ፤ 4፡5።

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔርን ቃል ከማስተማርና ከመስበክ መቆጠብ የሚኖርብን ጊዜ ይኖራል?
2. የእግዚአብሔር ቃል በሕይወት ውስጥ ይሠራል?
3. የ2ኛ ጢሞቴዎስን አጠቃላይ አስተዋፅዖ ዘርዝሩ።
4. የግልና የመጋቢነት ኃላፊነቶችን ለመወጣት የሚያስችለን መመሪያን፤ ለፈተና ብርታትትንና ለሞት ፀጋን የሚሰጠን ምንድነው?

## የቤት ሥራ

ቲቶ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት ስልሳ አምስት

## የቲቶ መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈው በ65 ዓ.ም. ገደማ ነው።

## ቲቶ

1. ቲቶ ወደ ክርስቶስ የመጣው «ልጄ» ብሎ በሚጠራው በጳውሎስ አማካይነት ነው፤ 1፡4።
2. ቲቶ የግሪክ ተወላጅ ሲሆን ምናልባትም የሶሪያዋ አንጾኪያ ነዋሪ ሳይሆን አይቀርም። ጳውሎስና በርናባስ ስለ አገልግሎታቸው ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር ለመወያየት ከአንፆኪያ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄዱ ቲቶ አብሮአቸው ሄዷል፤ ገላ. 2፡1-2።
3. የቲቶ ስም በሐዋርያት ሥራ ውስጥ አልተጠቀሰም።
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቲቶ የነበረውን ችግር እንዲፈታ ወደ ቆሮንቶስ ተልኳል፤ 2ኛ ቆሮ. 7፡6-10፤13፤16።
5. ጳውሎስ የሥራ ባልደረባውን ቲቶን ነገሮችን በሥርዓት እንዲያደራጅና በያንዳንዱ ከተማ ሽማግሌዎችን እንዲሾም በቀርጤስ ደሴት ትቶት ነበር፤ ቲቶ 1፡5።

6. ቲቶ ሮምን ለቆ ወደ ድልማጥያ ሄዷል፤ የሄደው ምናልባት በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ለማገልገል ሳይሆን አይቀርም፤ 2ኛ ጢሞ. 4፡10።

## የቲቶ መልእክት ዓላማ

1. ቲቶ ከአይሁድ ወግ አጥባቂነት ችግር ጋር ወይም በቀርጤስ ደሴት ቤተ ክርስቲያናት መካከል ስለ አሪት ሕግ የተነሣውን ጠብ እንዴት አድርጐ መጋፈጥ እንደሚችል ለማስተማር ነው፤ በትምህርት 43 ውስጥ በሚገኘው ካርታ ላይ የቀርጤስን ደሴት አክሉበት።
2. የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ባሕርይ በሚመለከት ትእዛዝ ለመስጠት ነው።

## በቲቶ መልእክት ውስጥ የተሰጠ የክርስትና ትምህርት

1. ስለ እግዚአብሔር፦
   ሀ/ እግዚአብሔር አብ፤ ቲቶ 1፡1፤ 3-4፤ 2፡10፤ 3፡4።
   ለ/ እግዚአብሔር ወልድ፤ ቲቶ 1፡4፤ 2፡13፤ 3፡6።
   ሐ/ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፤ ቲቶ 3፡5።
2. ስለ ደኅንነት፤ ቲቶ 2፡11-14፤ 3፡4-7።
3. የክርስቶስ መመለስ የአማኞች ተስፋ ነው፤ ቲቶ 2፡13። የቲቶ መልዕክት አቢይ ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ባሕርይ ላይ ያተኩራል።

## ጥያቄዎች

1. ቲቶ ማን ነበር?
2. በቀርጤስ ደሴት ባሉት ቤተ ክርስቲያናት መካከል ጠብ የጫረው ምንድነው?
3. በቲቶ መልእክት ውስጥ የተሰጡት ትምህርቶች ምን ምንድናቸው?
4. የቲቶ መልእክት አቢይ ትምህርት ምንድነው?

# ትምህርት ስልሳ ስድስት

## የቲቶ መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መመዘኛ፤ ምዕ. 1።
2. የቤተ ክርስቲያን አባላት ኃላፊነት፤ ምዕ. 2።
3. የክርስቲያንን አኗኗር የሚመለከቱ ማበረታቻዎች፤ ምዕ. 3።

የቲቶ መልእክት ንድፍ




# የቲቶ መልእክት ማጠቃለያ

የቲቶን መልእክት 3 ምዕራፎች በምታነቡበት ጊዜ የመጽሐፉን አቢይ ትምህርት አስታውሱ፤ ይኸውም በትምህርት 65 ቁ. 6 ውስጥ ይገኛል።

## ቲቶ ምዕራፍ አንድ

ጳውሎስ ቀርጤስ ለሚገኘው ለቲቶ ሲጽፍለት ስለ ቤተ ክርስቲያናት ሥርዓትና ባሕርይ ምክር ሰጥቷል። በመጀመሪያ ቲቶ ለእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መምረጥ ነበረበት። የሚመረጡትም ሰዎች እንከን የሌለባቸው፣ የአንዲት ሚስት ባል የሆኑና የተመሰከረላቸው ያመኑ ልጆች ያሏቸው መሆን ነበረባቸው። እውነተኛ ትምህርት ማስተማር፣ በእውነተኛ ትምህርታቸው ሌሎችን ለማበረታታት የሚችሉና በተጨማሪ የሐሰት ትምህርት የሚያሰራጩትን ሰዎች ስሕተት ማጋለጥ ነበረባቸው።

## ቲቶ ምዕራፍ ሁለት

ቀጥሎ ቲቶ እንዴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልዩ ልዩ ቡድኖችን መምከር እንደሚገባው ጳውሎስ ያስተምረዋል። ቲቶ ሽማግሌዎች ልከኞች፣ ጭምቶችና ራሳቸውን የሚገዙ እንዲሆኑ መምከር ነበረበት። አሮጊቶች ሐሜተኞችና የወይን ጠጅ የሚጠጡ ሳይሆኑ ለወጣት ሴቶች ምሳሌ የሚሆን መልካም ኑሮ መኖር ነበረባቸው። እነዚህ አሮጊቶች ወጣት ሴቶች ራሳቸውን እንዲገዙና ንፁህ እንዲሆኑ፤ ለባሎቻቸው ታዛዦች በመሆን ለእግዚአብሔር ምስክር እንዲሆኑ

ማስተማር ነበረባቸው። ወጣት ወንዶች ራሳቸውን የሚገዙና የመልካም ባሕርይ ምሳሌ መሆን ይገባቸዋል። ትምህርታቸውን ማንም ሰው እንዳይነቅፈው ለእግዚአብሔር ቃል የታመነና እውነተኛ መሆን አለበት። ቲቶ ራሱ ወጣት እንደመሆኑ መጠን የእነዚህ ሰዎች ዓይነተኛ ምሳሌ መሆን ነበረበት። ሠራተኞች ታዛዦች፣ የሚያከብሩና ለአሠሪዎች ታማኞች በመሆን ለክርስቶስ የመቤዠት ሥራ ምስክር መሆን ነበረባቸው። ጥሩ ሚስቶችና እናቶች እንዲሆኑና ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲያፈቅሩ ታዝዘዋል። የደኅንነት ትምህርት፣ የእግዚአብሔር ፀጋና በክርስቶስ ያለን ተስፋ የክርስቲያን ባሕርይ መሠረት ናቸው፤ 2፡11-15። ቲቶ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በተደገፈ ሥልጣን ማበረታታትና መገሰፅ ነበረበት።

## ቲቶ ምዕራፍ ሦስት

ከዓለም ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ የክርስቲያን ምስክርነት በግልፅ መታየት አለበት። ክርስቲያን ለመንግሥትና ለቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ታዛዥ መሆን አለበት። የክርስቲያን ንግግር ክርስቶስን የሚያሳይና ጠባዩም ለሌሎች ሰላማዊና ተግባቢ ለማንኛውም ሰው መልካም አቋም የሚያሳይ መሆን ይገባዋል። ሁላችንም በተፈጥሮአችንና በሥራችን ኃጢአተኞች ነን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በቸርነቱና በምሕረቱ ስላስተናገደን እርስ በርሳችን አንዱ ለሌላው ቸርና ታጋሽ መሆን ይገባዋል።

ክርስቲያን የማይረባ ክርክርንና ስለ እሪት ሕግም መጣላትን ማስወገድ ይገባዋል። እንደዚህ የሚያደርጉትን ማስጠንቀቅ ነበረባቸው፤ እምቢ ብለው በዚያው ከቀጠሉ ከእነርሱ መለየት ይገባዋል። በመጨረሻም ቲቶ አማኞች እርስ በርሳቸው በችግሮቻቸው የመረዳዳት መልካም ሥራቸውን እንዲቀጥሉና ሰነፎች እንዳይሆኑ ማበረታታት ነበረበት። እውነትን አውቀው የሚቃወሙ አባሎች ድርብ ማስጠንቀቂያ ያስፈልጋቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. የቲቶን መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ በዝርዝር ጻፉ።
2. እውነትን ለሚቃወም ሰው ስንት ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት?
3. በአማኝ ላይ መታየት ያለባቸውን ባሕርያት ዘርዝሩ፤ ቲቶ 3፡2።
4. የክርስቲያን ሴቶች መለያ ምን መሆን አለበት?
5. የክርስቲያን መሪዎች መመዘኛዎች ምን ምንድናቸው?

## የቤት ሥራ

የፊልሞናን መልእክት አንብቡ።

# ትምህርት ስልሳ ሰባት

## የፊልሞና መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው። የተጻፈው በ60 ዓ.ም. ገደማ ነው። የተጻፈው ለፊልሞና፥ ለሚስቱና ምናልባትም ለልጆቹ ነው፤ ፊልሞና ቁ. 2ን ተመልከቱ።

## የፊልሞናና የአናሲሞስ ማንነት

ፊልሞና የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን አባል ነበር። አገልጋዩ አናሲሞስ ከድቶት ወደ ሮም በፈረጠጠበት ጊዜ በዚያ እስረኛ የነበረውን ጳውሎስን ተገናኘው። ጳውሎስም አናሲሞስ ጌታን እንዲቀበል ከረዳው በኋላ ወደ ፊልሞና እንዲመለስ አሳመነው። በሮም መንግሥት ሕግ መሠረት የከዳተኛ ባሪያ ቅጣት ሞት ነበር። አናሲሞስ ግን ፊልሞናን መክዳት ብቻ ሳይሆን ምናልባት ገንዘቡንም ሳይሰርቀው አይቀርም፤ ቁ. 18-19 አንብቡ።

አናሲሞስ ማለት «ጠቃሚ» ማለት ነው። ከዚህ ቀደም ግን አናሲሞስ ለፊልሞና ጠቃሚ አልነበረም። ሆኖም አሁን ክርስቶስን ስለተቀበለ «ለእኔም ለአንተም ይጠቅመናል» ብሎ ጳውሎስ ይናገራል። ጳውሎስ በእስር ቤት ሳለ አናሲሞስ በአንዳንድ መንገድ አገልግሎታል፤ ቁ. 11-13።

## የመልእክቱ ዓላማ

ይህ ጳውሎስ ለፊልሞና የጻፈለት ምክንያት አናሲሞስን መልሶ እንደ አገልጋዩ ብቻ ሳይሆን በክርስቶስ እንደ ወንድም አድርጐ እንዲቀበለው የሚጠይቅ የግል ደብዳቤ እንዲሆን ነው፤ ቁ. 16። ጳውሎስ «እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው» ብሎ ጽፎለታል፤ ቁ. 17።

## የመልእክቱ አቢይ ትምህርት ምሕረት ነው

ጳውሎስ «አናሲሞስ በአንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ወይም ብድር ያለበት እንደሆነ ይህንን በእኔ ላይ ቁጠር» ብሎ ተናግሯል፤ ቁ. 18። እማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ፍፁም ሆኖ ሊቆም የቻለው ክርስቶስ ኢየሱስ የኃጢአትን ሙሉ ዋጋ ስለከፈለ ነው። የእኛ ኃጢአት በእርሱ ላይ ተቆጥሯል፤ ኢሳ. 53፥6ና ሮሜ 6፥23 አንብቡ። ይህ ደብዳቤ አሠሪውን ከድቶ የኮበለለን ሰው ሕይወት የለወጠው ወንጌል ያለውን ኃይል ያሳያል።

## የፊልሞና መልእክት አስተዋፅዖ

1. ምስጋና ለፊልሞና፤ ቁ. 1-7።
2. ልመና ለአናሲሞስ፤ ቁ. 8-25።

## ጥያቄዎች

1. በቆላስይስ ከተማ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ የምታደርገው የት ነበር?
2. በሮም መንግሥት ሕግ የከዳተኛ ባሪያ ቅጣት ምንድነው?
3. ፊልሞና ኮብላዩ አናሲሞስን እንዲቀበለው ጳውሎስ የሚጠይቀው እንዴት ነው? ቁ. 16-17።
4. የአናሲሞስ ተስፋ መሠረት ምንድን ነበር?
5. አናሲሞስ ማለት ምን ማለት ነው?
6. የፊልሞና መልእክት አቢይ ትምህርት ምንድነው?

የፊልሞና መልእክት ንድፍ




## የቤት ሥራ

ዕብራውያን 1-4 አንብቡ።

# ትምህርት ሰላሳ ስምንት

## የዕብራውያን መልእክት መግቢያ

የጸሐፊው ስም በመጽሐፉ ውስጥ ተጠቅሶ አይገኝም። በ70 ዓ.ም. ስለሆነው የኢየሩሳሌም ውድቀት በመልእክቱ ውስጥ ስላልተጠቀሰ የተጻፈው ከዚህ ጊዜ በፊት ሳይሆን አይቀርም፤

ይኸውም በ68 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል። የተጻፈው በተለይ ለአይሁድ ክርስቲያኖች ሲሆን በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ጭምር ነው።

## የዕብራውያን መልእክት ዓላማ

1. የብሉይ ኪዳን ሕግ በክርስቶስ ፍጻሜ እንዳገኘ ለማረጋገጥ ነው።
2. ስደትን ለማምለጥ ወደ ምኩራብ ሥርዓት እንዳይመለሱ ከአይሁድ ወገን ያመኑትን ለማስጠንቀቅ ነው።
3. እርስ በርስ ለመደጋገፍ የሕብረትን አስፈላጊነት ለማተኮር ነበር።

## የዕብራውያን መልእክት አቢይ ትምህርት

የእግዚአብሔር ልጅ ታማኝ፥ አዳኝና ታላቅ ካህን ስለሆነ የበላይነት ያለው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

## በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. የተሻለ፤ 1፡4፤ 6፡9፤ 7፡7፤19፤22፤ 8፡6፤ 9፡23፤ 10፡34፤ 11፡16፤35፤40፤ 12፡24።
2. ሰማያት ወይም ሰማያዊ፤ 1፡10፤ 3፡1፤ 4፡14፤ 6፡4፤ 7፡26፤ 8፡1፤ 5፤ 9፡23-24፤ 10፡34፤ 11፡16፤ 12፡22፤25-26።

## በዕብራውያን መልእክት ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. 2፡18፤ ክርስቶስ ፈተናችንን ያውቃል።
2. 4፡15-16፤ ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ነው።
3. 7፡25፤ ክርስቶስ አስታራቂያችን ነው።
4. 11፡6፤ በክርስቶስ ላይ ያለን እምነት ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ብቸኛ መንገድ ነው።
5. 12፡1-2፤ ክርስቶስ ፍጹም የሆነ ምሳሌአችን ነው።

## የዕብራውያን መልእክት ልዩ ባሕርያት

1. አማኞች ከአሪት ሕግ አንፃር ያላቸውን ግንኙነት የዕብራውያን መልእክት ያብራራል። የሮሜ መልእክት ደግሞ አማኞች ከአሪት ሕግ ሥልጣን አንፃር ያላቸውን ግንኙነት ያብራራል።
2. በአሮጌው ማለት በድሮ ኪዳን ውስጥ ለውጥና መሻሻል እንደነበረ ለማሳየት መልእክቱ የብሉይ ኪዳን ጥቅሶችን ይጠቀማል፤ ኤር. 31-34ና ዕብ. 8 ተመልከቱ። ይኸውም በክርስቶስ የተሻለ ለሆነው ለአዲሱ ኪዳን መንገድ ለማዘጋጀት ነው።

## ጥያቄዎች

1. የዕብራውያን አቢይ ትምህርት ምንድነው?
2. የተጻፈው ለምንድነው?
3. ከብሉይ ኪዳን ሕግጋት ውስጥ የሚያብራራው የትኛውን ክፍል ነው?
4. የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው ለማን ነበር?

## የቤት ሥራ

ዕብራውያን 5-8 አንብቡ።

# ትምህርት ስልሳ ዘጠኝ

## የዕብራውያን መልእክት አጠቃላይ አስተዋፅዖ

1. የክርስቶስ በላጭነት ከመላእክት ጋር ሲነፃፀር፤ ምዕ. 1-2።
2. የክርስቶስ በላጭነት ከሙሴና ከኢያሱ ጋር ሲነፃፀር፤ ምዕ. 3-4።
3. የክርስቶስ በላጭነት ከአሮናዊው ክህነት ጋር ሲነፃፀር፤ ምዕ. 5-6።
4. ክርስቶስ አስታራቂያችን፤ ምዕ. 7።
5. ክርስቶስ ከቃል ኪዳኑ አንፃር፤ ምዕ. 8-9።
6. ክርስቶስ ከእምነት አንፃር፤ ምዕ. 10-11።
7. ክርስቶስ ከክርስትና ባሕርይ አንፃር፤ ምዕ. 12-13።

## የዕብራውያን መልእክት ንድፍ




በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ተከታታይ ንዕዐሮች በውስጡ እንደሚገኙበት አስተውሉ። ከእያንዳንዱ ንዕዐር በኋላ ማስጠንቀቂያ ይገኛል፤ ከእያንዳንዱ ማስጠንቀቂያ ጋር ደግሞ ማበረታቻ አለ።

1. ንፅፅሩ:- ክርስቶስ የተሻለ መልእክተኛ ነው። እርሱ ከመላእክት ይበልጣል፤ 1:4-14።
   ማስጠንቀቂያው:- ስለ ቸልተኝነት ችግር የተሰጠ ነው፤ 2:1-4።
   ምክሩ:- እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን? 2:3
2. ንፅፅሩ:- ክርስቶስ የተሻለ ሐዋርያ ነው። እርሱ ከሙሴ ይበልጣል፤ 3:1-6።
   ማስጠንቀቂያው:- ስላለማመን የተሰጠ ነው።
   ምክሩ:- ወንድሞች ሆይ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤ 3:12።
3. ንፅፅሩ:- ክርስቶስ የተሻለ ሊቀ ካህን ነው። እርሱ ከአሮን ይበልጣል፤ 4:14-5:4።
   ማስጠንቀቂያው:- ስለ መንፈሳዊ አለመብሰል የተሰጠ ነው፤ 5:11-6:12።
   ምክሩ:- «ከጊዜው የተነሣ አስተማሪዎች መሆን ሲገባችሁ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ ያስፈልጋችኋልና የሚያስፈልጋችሁ ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም» 5:12።

4. ንፅፅሩ፦ ክርስቶስ የተሻለ ኪዳን አጽቅቋል፤ 8፡1-13፤ 9፡1-28።
ማስጠንቀቂያው፦ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ፍርድ የተሰጠ ነው፤ 9፡27።
ምክሩ፦ ማበረታቻዎች ከሚቀጥለው ንፅፅር በኋላ ተሰጥተዋል፤ ስለዚህ ተራ ቁጥር 5 ተመልከቱ።
5. ንፅፅሩ፦ ክርስቶስ የተሻለ መስዋዕት ነው፤ 10፡1-31።
ማስጠንቀቂያው፦ እውነትን እያወቁ ስለሚቃወሙት የተሰጠ ነው፤ 10፡26-27።
ምክሩ፦
ሀ/ በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤ 10፡22።
ለ/ እንዳይነቃነቅ የእምነታችንን ምስክርነት እንጠብቅ፤ 10፡23።
ሐ/ ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንነቃቃ፤ እርስ በእርሳችን እንተያይ፤ 10፡24።
መ/ በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደሆነ መሰብሰባችንን አንተው፤ 10፡25።
6. ንፅፅሩ፦ ክርስቶስ በእምነት የተሻለ መንገድ ነው ... 10፡32-12፡29።
ማስጠንቀቂያው፦ በክርስቶስ ያለውን የእግዚአብሔርን መንገድ ስለ መቃወም የተሰጠ ነው፤ 12፡25-29።
ምክሩ፦ በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ፀጋ እንያዝ፤ 12፡28።

## ጥያቄዎች

1. ክርስቶስ የሚበልጣቸው 3 የቀድሞ ሥርዓቶችን ጥቀሱ።
2. በዕብ. 7 ውስጥ በቀረበው መሠረት የዚህ መልእክት አቢይ ትምህርት ምንድነው?
3. በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ጥንቃቄ እንድናደርግባቸው የተነገሩንን 6 ችግሮች ጥቀሱ።

## የቤት ሥራ

ዕብራውያን 9-11 አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ

ማሳሰቢያ፦ ይህንን የዕብራውያንን መልእክት ማጠቃለያ በአንድ ትምህርት ሥር ለማጠቃለል በጣም ስለሚረዝም ግማሹ ክፍል በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ ይገኛል።

## የዕብራውያን መልእክት አጭር ማብራሪያ

## የመልእክቱ ዓላማ

ከአይሁድ ወገን ላመኑት ክርስቲያኖች ክርስትና የመጨርሻ መለኮታዊ መገለጥ መሆኑን ለማብራራት ነው። የወንጌሉ ሥርዓት በኦሪት ውስጥ ከሚገኘው ውስብስብ ሥርዓት ሲነፃፀር በጣም ቀላል መሆኑ ስለመሰላቸው ብዙዎቹ ክርስቶስን ለቀው ወደ ጴሮ ሥርዓት ተመልሰው ለመሄድ ተፈትነዋል። በኦሪት ሥርዓት ውስጥ ቤተ መቅደስን፥ መሠዊያን፥ ካህናትንና

መሥዋዕቶችን ማየት ሲችሉ በክርስትናቸው ውስጥ ከእነዚህ መካከል አንዱም አልተገኘም፤ ስለዚህ የዕብራውያን ጸሐፊ ክርስትና የሚበልጥ መሆኑንና ክርስቶስ የእነዚህ ሁሉ የቀድሞ ምሳሌዎች ፍፃሜ እንደሆነ ይገልጽላቸዋል።

## ዕብራውያን 1-2

ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅና ከሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ያሳያል። እግዚአብሔር መላእክቱን፤ መልእክተኞቹና አገልጋዮቹ አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል፤ ነገር ግን ፈጣሪ የነበረውና አሁን በአብ ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ ይበልጣል። በክርስቶስ ያገኘነውን መዳን ቸል የሚሉ ሁሉ ማምለጫ የላቸውም፤ 2፡3። አሁን ሰዎች ከመላእክት ያነሱ ናቸው፤ ነገር ግን የደህንነት ወራሾች የሆኑት ከክርስቶስ ጋር ከመላእክት በላይ ይሆናሉ። መላእክት የደህንነት ወራሾች የሚሆኑትን አማኞች ያገለግሏቸዋል፤ 1፡14።

ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ሲል ለጥቂት ጊዜ ከመላእክት ያነሰ ሆኖ ነበር። እርሱ የሰውን እንጂ የመላእክትን አምሳል አልወሰደም። ይህንንም ያደረገው ሞቶ የሞትን ኃይል ለማጥፋት ነበር፤ 2፡14-15። እርሱ እንደ ሰው ተፈትኗል፤ ስለዚህ የእኛን ፈተናዎችና መከራዎች ይረዳል፤ 2፡18።

## ዕብራውያን 3-4

ታላቅ ሐዋርያችንና ሊቀ ካህናችን ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል። ቤት የሚሠራ ሰው ከሠራው ቤት ይልቅ ክብር ይቀበላል። ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት በአገልጋይነት ታማኝ ነበር፤ ነገር ግን ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በልጅነት ታማኝ ነው። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እስራኤላውያን በምድረበዳ ልባቸውን በእግዚአብሔር ላይ እንዳደነደኑ እነርሱም እንዳያደነድኑ ሰዎችን ያስጠነቅቃል። ካለማመንና ከኃጢአት ማታለል መጠንቀቅ አለብን፤ አለበለዚያ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ለመግባት አንችልም። ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት መግቢያው በእምነት ብቻ እንጂ በራስ ጥረት አይደለም። ስለዚህ ብቻውን ዕረፍት ሊሰጠን የሚችለውን በክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት አጥብቀን መያዝ ይኖርብናል።

## ዕብራውያን 5-6

አሮን የአሮጌው ኪዳን ሊቀ ካህንና የክርስቶስ ምሳሌ ነበር። ሆኖም ሌዋዊው ክህነት ዘወትር በሞት ይቋረጥ ነበር። የክርስቶስ ክህነት ግን እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ነው፤ ዘፍ. 14፡18፤ ዕብ. 7፡1-3 ተመልከቱ። የመልከጼዴቅ ክህነት ለየት ያለ ነበረ።

1. ሌላ ሊቀ ካህን ሁሉ ሰው ብቻ ነበር፤ ዕብ. 7፡4ን ከ1ኛ ጢሞ. 2፡5 ጋር አገናዝቡ።
2. እርሱ ንጉሥና ካህን ነበር፤ ዘፍ. 14፡18ን ከዘካ. 6፡12-13 ጋር አገናዝቡ።
3. የስሙ ትርጉም ንጉሤ ጻድቅ ነው የሚል ነው፤ ኢሳ. 11፡5።
4. ስለ ልደቱ የተጻፈ ታሪክ የለም፤ ዮሐ. 1፡1። ደግሞም ስለ ሕይወት መጨረሻ ምንም የተጻፈ ነገር የለም፤ ሮሜ 6፡9፤ ዕብ. 7፡23-25።
5. ሊቀ ክህነትን ያገኘው በሰው ሥርዓት አይደለም፤ መዝ. 109 /110/፡4።

መሥዋዕት ከማቅረብ አንፃር የክርስቶስ ክህነት የአሮንን ይመስላል። በክርስቶስ የተሰጠው አዲስ ኪዳንና አዲስ የክህነት ሥርዓት ከአሮጌው ሥርዓት እጅግ የበለጠ ነው። ስለዚህ

የዕብራውያን ጸሐፊ «ጊዜ ወጸለፈበት ወደ አሮጌው ሥርዓት አትመለሱ፤ የእግዚአብሔር ቃል መልካም እንደሆነ ታውቃላችሁ፤ ኃይሉንም ቀምሳችሁ ተረድታችኋል፤ ወደኋላችሁ ብትመለሱ ግን የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና ትሰቅሉታላችሁ፤ ወደ ኃፍረትም ትመለሱታላችሁ» ይላቸዋል።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ጠብቋል፤ እርሱ ሊዋሽ አይችልም። የፀና ቃል ኪዳን ስለተሰጠን በክርስቶስ ያገኘነውን ተስፋ አጥብቀን እንያዝ።

## ጥያቄዎች

1. የዕብራውያን መልእክት ዓላማ ምን ነበር?
2. አማኞች አሁን ከመላእክት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምንድነው?
3. ክርስቶስ ለጥቂት ጊዜ ከመላእክት ያነሰ ሥፍራ የወሰደው ለምንድነው? ሁለት ምክንያቶች ስጡ።
4. ክርስቶስ ከሙሴ የሚበልጠው እንዴት ነው?
5. ሰውን ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚያደርሰው መንገድ ምንድነው?
6. ወደ አሮጌው ኪዳን ሥርዓቶች ብንመለስ በክርስቶስ ላይ ምን ማድረጋችን ነው?

## የቤት ሥራ

ዕብራውያን 12-13 አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ አንድ

## ይህ ክፍል የትምህርት 70 ቀጥያ ነው

### ዕብራውያን 7 ክርስቶስ አስታራቂያችን

የአሮን ማለትም የሌዊ ክህነት ፍፁም ቢሆን ኖሮ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት የተሾመ ሌላ ካህን ለምን ያስፈልገናል? በኦሪት ሕግ የተሰጠው ክህነት በካህናት ሞት ተቋርጦ ነበር፤ የክርስቶስ ክህነት ግን ለዘላዓለም አይቋረጥም። ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ወገን እንጂ ከሌዊ ወገን አልነበረም፤ ነገር ግን የኦሪት ሕግ ምንም ነገር ፍፁም አላደረገም። «የተሻለው ተስፋ» የሆነው ክርስቶስ ፍፁም ሊያደርገን ይችላል። ክርስቶስ አስታራቂያችን ሲሆን እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ለማማለድ ለዘላለም ይኖራል። እርሱ እንደ ሌሎቹ ሊቀ ካህናት አይደለም፤ በየዕለቱ ስለ ኃጢአት መስዋዕት ማቅረብ አያስፈልገውም። ራሱን መስዋዕት አድርጐ ባቀረበበት ወቅት አንዴና ለዘላለም አንድ መስዋዕት ሰውቷል። ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ስለሆነ በሰማያዊ ሥፍራ በአብ ቀኝ ተቀምጧል፤ 8፡1።

### ዕብራውያን 8-9 ክርስቶስና አዲሱ ቃል ኪዳን

ክርስቶስ በኤርምያስ የተተነበየውን አዲስ ኪዳን አቋቋሟል፤ ኤር. 31:33። «ሕጌን በልቦናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ በደላቸውን እምራቸዋለሁና ኃጢአታቸውን ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።»

አሮጌው ቃል ኪዳን አልፏል። በአሮጌው ኪዳን የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ሥፍራዎቹ በጥብቅ የተወሰኑ ነበሩ፤ ካህኑ የሚያገለግልበት ቅዱስ ሥፍራ ነበረው። ሊቀ ካህን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ለራሱና ለሕዝቡ ኃጢአት መስዋዕት የሚሰዋበት ቅድስተ ቅዱሳን ነበረው። በየዓመቱ የመግባቱ ሥነ ሥርዓት የሚያመለክተን፤ ለእግዚአብሔር የቀረቡት የእንስሳት መስዋዕቶች የአማኞችን ልብ ፍፁም ሊያደርጉ እንደማይችሉ ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር አዲስ ሥርዓት እስከሚያቋቁም ድረስ ብቻ ጠቃሚ ነበሩ። ይህም አገልግሎት ጊዜያዊ ነበረ።

ክርስቶስ መጥቷል፤ አሁን የሚያገለግለውም በእጅ ባልተሠራ ድንኳን ውስጥ ነው። ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብቷል፤ ሉቃስ 23:45ን አንብቡ። ራሱን ፍፁም የሆነ መስዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አቅርቧል። ህያው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ደሙ ሕሊናችንን ከማይጠቅሙ ሥርዓቶች ያነፃል።

አዲስ ኪዳን የክርስቶስ የመጨረሻ ፈቃዱና ኑዛዜው ነው። እርሱ የአዲስ ኪዳን ደም የሆነውን ደሙን አፍስሷል። ክርስቶስ የእግዚአብሔር መኖሪያ ወደ ሆነው ሰማያዊ ሥፍራ ግብቶ ራሱን መስዋዕት በማድርግ ኃጢአትን አስወግዷል። «ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸውል» ዕብ. 9:28።

## ዕብራውያን 10-11 እምነት

አንዱ የአዲስ ኪዳን መስዋዕት ብዙዎች ከሆኑት የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ይበልጣል። እግዚአብሔር «ሕጌን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ፤ በሐሳባቸው ውስጥ እጽፈዋለሁ» ብሏል። አሁንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የመግቢያው መንገድ በእውነተኛ ልብ ያለ ጥርጥር በእምነት ነው። ክርስቶስ ለኃጢአታችን የተሠዋ መሆኑን እያወቅን ብንንቀው ማለትም በፈቃዳችን ኃጢአት ብናደርግ ኃጢአታችንን የሚያስወግድ ምን ሌላ መስዋዕት ይኖራል? እውነትን አውቀን ባንቀበለው የሚጠብቀን ፍርድ ብቻ ነው። ስለዚህ ጸሐፊው ትዕግሥትኞችና ተስፋ የማትቆርጡ ሁኑ ይላቸዋል። እርሱ በተስፋ ቃሉ መሠረት ይመጣል።

የእምነት ተቀዳሚነት በብዙ ምሳሌዎች ግልፅ ተደርጎ በምዕ. 11 ውስጥ ቀርበዋል። አቤል፤ ሄኖክ፤ ኖህ፤ አብርሃምና ሣራ፤ ይስሐቅ፤ ያዕቆብ፤ ዮሴፍ፤ ሙሴ፤ ኢያሱና ረዓብ እንደዚሁም ብዙ ሌሎች ሰዎች ሁሉም በእምነት ኖሩ። ሁሉም በእግዚአብሔር አመኑ፤ እምነታቸውም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረላቸው። አሮጌዎቹን ትእዛዞች ከመጠበቅ እንደዚህ ያለው እምነት የተሻለ ነው። ከመጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሔር እምነትን አክብሮታል።

## ዕብራውያን 12-13 የክርስቲያን ባሕርይ

እግዚአብሔር የሚወዳቸውን ሰዎች በመቅጣት ያስተምራቸዋል፤ ያሰለጥናቸዋል። ቅጣት ለእግዚአብሔር ልጆች ሲሆን ይኸውም ለጥቅማችን ነው። በወቅቱ ቅጣት አስደሳች አይመስልም፤ ነገር ግን የጽድቅን ፍሬ ያፈራል። የምንቀበለው ቅጣት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ይመሰክራል።

የሲና ተራራ የአሪት ሕግ የተሰጠበት ቦታ ሲሆን የፍርሃትና የመንቀጥቀጥ ሥፍራ ነው። የጽዮን ተራራ የሕያው እግዚአብሔር ከተማ፤ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም፤ ከብዙ ሺህ መላእክት ጋር ለአማኞች የተዘጋጀች የደስታ ሥፍራ ናት። በክርስቶስ አምነው ከእኛ ቀድመው ከሞቱት ሰዎች ጋር እንገናኛለን። አዲሱን ኪዳን ወዳደረገውና ከእንስሳት ሁሉ ደም የሚበልጠውን ደም ወዳፈሰሰው ወደ ክርስቶስ እንሄዳለን።

ስለዚህ፦

1. እርስ በርሳችሁ በመፋቀር፤
2. እንግዶችን በማስተናገድ፤
3. በእስር ቤት ያሉትን ባለመርሳት፤
4. በጋብቻ ውስጥ ታማኝ በመሆንና
5. ራሳችሁን ከገንዘብ ፍቅር ነፃ አድርጋችሁ ባላችሁ ነገር በመርካት እግዚአብሔርን አገልግሉት።

በእንግዳ ትምህርት ተስባችሁ እንዳትጠፉ የቀደሙትን መሪዎች ምሳሌ አትርሱ። የክርስቶስን ውርደት ለመካፈል ፈቃደኞች ሁኑ። የሚመሩአችሁን ታዘዙ። ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር የምስጋና መስዋዕት ሠዉለት፤ ጸልዩ። ደግሞም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው የሰላም አምላክ ፈቃዱን እንድታደርጉ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍፁማን ያደርጋችኋል።

## ጥያቄዎች

1. አሮጌው ኪዳን ወይም የአሪት ሕግ ሰውን ፍፁም ማድረግ ያልቻለው ለምንድነው?
2. የክርስቶስ ሊቀ ክህነት ከአሮን የሚበልጠው በምንድነው?
3. በአሁኑ ወቅት የክርስቶስ አዲስ ኪዳን የተጻፈው የት ነው?
4. የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የጸደቁት እንዴት ነው?
5. አማኝ ለእምነቱ መከራ ቢቀበል የሚያሳየው ምንድነው?
6. የሲናንና የጽዮንን ተራራ አወዳድሩ።
7. በዕብ. 13 በተጠቀሰው መሠረት አንዳንድ እግዚአብሔርን የምናገለግልባቸው መንገዶች ምን ምንድናቸው?
8. ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር መሠዋት የሚገባን መስዋዕት ምንድነው? 13፡15።

## የቤት ሥራ

ትምህርት 65-71 ማለት ቲቶ፤ ፊልሞናና ዕብራውያን ከልሱ።

# ትምህርት ሰባ ሁለት

## የቲቶ፥ ፊልሞናና ዕብራውያን ክለሳ

1. የቲቶ መልእክት አቢይ ትምህርት ምንድነው? የፊልሞናስ? የዕብራውያንስ?

2. በቲቶ መልእክት ውስጥ የተብራሩት ችግሮች ምን ምንድናቸው? በፊልሞናስ በዕብራውያንስ?
3. በዕብራውያን ውስጥ ክርስቶስ የሚበልጥ ወይም በርሱ በኩል ሆኖ የቀረበባቸው 3 ሹመቶች የትኞቹ ናቸው?
4. ጳውሎስ ፊልሞና ከዳተኛ ሠራተኛውን እንዲቀበል የጠየቀው እንዴት ነው?
5. ዕብራውያን የሚያብራራው የትኛውን የብሉይ ኪዳን ክፍል ነው?
6. የቲቶ መልእክት ዓላማ ምን ነበር? የፊልሞናስ? የዕብራውያንስ?
7. የዕብራውያን ጸሐፊ የአይሁድ አማኞችን የሚያስጠነቅቃቸው ከየትኞቹ 6 ችግሮች ነው?
8. የክርስቶስ ክህነት ከመልከ ጼዴቅ ክህነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
9. ለሚያምኑት የክርስቶስ ዋነኛው ተግባር ምንድነው? ለማያምኑትስ?
10. የፊልሞና መልእክት የሚሰጠን ምሳሌ ምንድነው?
11. ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ለሚስቶቻቸው የቀረቡትን መመዘኛ ነጥቦች ከልሷቸው?
12. ቲቶ የቤተ ክርስቲያንን ሥራ ይመራ የነበረው በየት ነው?
13. በቀርጤስ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ግጭት እንዲፈጠር ያደረገው ምንድነው?
14. የጥንቲቷን ቤተ ክርስቲያን ችግሮች የሚመስሉ ችግሮች በዛሬዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይገኛሉን
15. በቲቶ መልእክት ውስጥ የተሰጡት ትምህርቶች ምን ምንድናቸው?

## የቤት ሥራ

ለፈተና ተዘጋጁ።

# ትምህርት ሰባ ሦስት

## ምክር ለመምህሩ

ለተማሪዎችዎ ያዘጋጁትን ፈተና ይፈትኗቸው።

## የቤት ሥራ

ያዕቆብ 1-3 አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ አራት

## የያዕቆብ መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ያዕቆብ ነው። የተጻፈበት ዘመን የሚጠቅስ መረጃ በመልእክት ውስጥ ፈጽሞ ባይገኝም ያዕቆብ በ61 ዓ.ም. በአይሁዶች እንደተገደለ እናውቃለን። ስለዚህ ከዚያ ቀደም ተብሎ የተጻፈ ነው።

የተጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ወይም ተበትነው ለነበሩት ክርስቲያኖች ነበር፤ 1፡1።

## ጸሐፊው ያዕቆብ

ከትንሣኤ በፊት ያዕቆብና ሌሎች ወንድሞቹ በኢየሱስ አያምኑም ነበር፤ ዮሐ. 7፡3-5። ከትንሣኤ በኋላ የጌታ ወንድሞች ከሐዋርያት ጋር በጸሎት ላይ ነበሩ፤ የሐዋ. 1፡14። ጴጥሮስ ከእስር ቤት መውጣቱን ያዕቆብ እንዲያውቅ ይፈልግ ነበር፤ የሐዋ. 12፡7። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ለያዕቆብ ተገለጸለት፤ 1ኛ ቆሮ. 15፡7። ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር፤ የሐዋ. 15፡13፤ 21፤ 28፤ ገላ. 1፡19፤ 2፡9፤ 12።

## የያዕቆብ መልእክት ዓላማ

1. ይህ መልእክት የተጻፈው እስከ አሁን ድረስ በአሮጌው ኪዳን ላይ ሙጭጭ ብለው በተለጠፉት ሰዎች ማስፈራሪያ ምክንያት ትዕግሥትና ሰፊ ልብ የሚያስፈልጋቸውን ክርስቲያኖች ለማበረታታትና ለማጽናናት ነው።
2. ክርስቲያኖችን ለሚቃወሙት አይሁዶች የተጻፈ ነበር። መልእክቱ በክርስቶስ ያለንን የእምነት ውጤት ያብራራል።

## የመልእክቱ ባሕርያት

1. ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ ምኩራብ እንደመሰብሰቢያ ሥፍራ ሆኖ ተጠቅሷል፤ 2፡2። ይህ ነገር መልእክቱ በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ዘመናት መጻፉን ይጠቁመናል።
2. በዚያ ወቅት ቤተ ክርስቲያን የአይሁድን ሥርዓቶች በመፈጸም ላይ ነበረች፤ ይህም ደግሞ የተጻፈው በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ዘመናት አካባቢ መሆኑን ይጠቁመናል።
3. ያዕቆብ ከብሉይ ኪዳን ወይም ከገጠር አኗኗር ምሳሌዎችን በመጥቀስ ይጠቀማል፤ 3፡3-4፤ 7፤ 12፤ 4፡13፤ 5፡7።

በያዕቆብ መልእክት ውስጥ የሚገኝ ቁልፍ ጥቅስ፡- 2፡14 «ወንድሞች ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?

## ጥያቄዎች

1. ይህ መልእክት በሐዋርያት ዘመን ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን መጻፉን የሚጠቁመን ምንድነው?
2. ያዕቆብ ከገጠር ኑሮ ጠቅሶ የሚጠቀምባቸው ሁለት ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?
3. የያዕቆብ መልእክት ቁልፍ ጥቅስ ምን የሚል ነው? ጥቀሱት።
4. ያዕቆብ ማን ነበር? ስለ እርሱ አንዳንድ ነገሮች ጥቀሱ።

## የቤት ሥራ

ያዕቆብ 4-5 አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ አምስት

## የያዕቆብ መልእክት አስተዋፅዖ

1. ፈተና፤ ምዕ. 1 በመከራ ውስጥ ለነበሩ ክርስቲያኖች ነው።
2. ግብዝነት፤ ምዕ. 2 ተቃውሞ ለደረሰባቸው ክርስቲያኖች ነው።
3. አድልዎ፤ ምዕ. 3 ለተቃዋሚዎች የተጻፈ ነው።
4. ትዕቢት፤ ምዕ. 4 ለተቃዋሚዎች ነው።
5. የድል አድራጐት ሐሴት፤ ምዕ. 5 በመከራ ውስጥ ለነበሩ ክርስቲያኖች ነው።

ምዕራፍ 1ና 5 የተጻፉት በሌሎች ክርስቲያኖች ወይም ክርስቲያን ነን በሚሉ ሰዎች ዛቻና መከራ ይቀበሉ የነበሩትን አማኞች ለማበረታታት ነው።

ምዕራፍ 2-4 የተጻፉት ይዝቱ ለነበሩት ተገንጣይ ተቃዋሚዎች ነው።

የያዕቆብ መልእክት ንድፍ




# የያዕቆብ መልእክት ማጠቃለያ

ይህ ከአይሁድ ወገን ላመኑት ክርስቲያኖች የተጻፈው መልእክት ምናልባት አብዛኛዎቹ አማኞች አይሁዶች በነበሩበትና የአይሁድ ባሕል ልማዶችን በመለማመድ ላይ በነበሩበት ወቅት በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ዘመናት ሳይሆን አይቀርም።

ያዕቆብ አፋዊ በሆነውና መልካም ውጤት በሚያስገኘው እምነት መካከል ባለው ልዩነት ላይ ያተኩራል። የያዕቆብ መልእክት መዳን በእምነት ነው ብሎ ጳውሎስ ካስተማረው ትምህርት ጋር አይቃረንም፤ ነገር ግን እውነተኛ እምነት በመልካም ሥራ የተሞላ ሕይወትን ያስገኛል ብሎ በጥብቅ ይናገራል።

ክርስትናን ተቀብለናል በማለታቸው የሚደርስባቸውን መከራና ዛቻ ለመታገስ እንዲችሉ ለእውነተኛ አማኞች የተጻፈ የማበረታቻ መልእክት ነው።

በቤተ ክርስቲያን የነበሩ ችግሮች፤

1. ለሀብታም ማድላት፤
2. ሁብታም ድሀውን ይጨቁን ነበር፤ 2፡1-9፤ 14-16፤
3. አንደበት መቆጣጠር፤ 3፡1-18፤
4. ከዓለም ጋር መወዳጀት ነበሩ።

አንዳንድ ሰዎች መምህራን ለመሆን ሲጓጉ ጥቂቶች ንብረትንና ሀብትን ለመሰብሰብ ይመኙ ነበር። ሌሎች ደግሞ በተግባራቸው ትክክል አይሠሩም ነበር። ያዕቆብ

በመደምደሚያው ላይ እውነተኛው ፈራጅ ጌታ ስለሚመለስ በመከራቸው እንዲታገሡና ጸሎታቸውን እንዳያቋርጡ ክርስቲያኖችን ይመክራቸዋል።

በያዕቆብ መልእክት ውስጥ የተብራራው ችግር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ ሁለት የተነጣጠሉ ቡድኖች መካከል ያለ ነበር። ለእንደዚህ ዓይነት ችግር መፍትሔ ማግኘት ብዙ ጊዜ በጣም አዳጋች ሲሆን ደግሞም ከውጭ ከሚመጣ ተቃውሞ ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን እጅግ ያዳክማታል።

## ጥያቄዎች

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ችግሮች ምን ምንድናቸው? አራቱንም ጥቀሱ።
2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ይፈጥሩ የነበሩት ሰዎች አቋማቸው ምን ነበር?
3. ያዕቆብ በመከራ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች የሚሰጠው የመጨረሻ ማፅናኛ ምን ነበር?
4. የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ችግር ከውጭ ከሚመጣ ችግር የሚከብደው ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ጴጥሮስን አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ ስድስት

## የ1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ጴጥሮስ ነው። የተጻፈው በ65 ወይም በ66 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል። ምክንያቱም ጴጥሮስ በዚያ ዘመን አካባቢ እንደሞተ ስለምናውቅ ነው።

## የተጻፈው ለማን ነው?

1ኛ ጴጥሮስ በእስያ በተለይም በሰሜን ምዕራብ ክፍል በስደት ምክንያት ተበትነው ለነበሩት አይሁድ ክርስቲያኖች የተጻፈ ነው። 2ኛ ጴጥሮስ የተጻፈው ለጠቅላላው ክርስቲያን ነው።

## የመልእክቶቹ ዓላማ

1ኛ ጴጥሮስ የተላከው በመከራ ውስጥ ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን ማፅናኛና መመሪያ ለመስጠት ነበር። 2ኛ ጴጥሮስ የተላከው ስለ ሐሰተኛ መምህራን ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠንቀቅ፥ አማኞችን ስለ እግዚአብሔር ጥሪና ስለ ጌታ መመለስ ለማሳሰብ ነበር።

## የመልእክቶቹ አቢይ ትምህርት

የ1ኛ ጴጥሮስ ዋነኛው ትምህርት «መከራና ክብር ለክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን» የሚል ነው፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡20 አንብቡ። የ2ኛ ጴጥሮስ «ስለ ክርስቶስ ምፅዓት ማስጠንቀቂያና ማፅናኛ» የሚል ነው።

## የመልእክቶች ልዩ ባሕርያት

በ1ኛ ጴጥሮስ ውስጥ ብዙ ትእዛዞች ይገኙበታል፤ ለምሳሌ፡- «በመጠን ኑሩ» 1፡13። «ቅዱሳን ሁኑ» 1፡15። በተጨማሪ 1፡17፤22፤ 2፡3፤13፤17፤ 3፡7-8፤ 14-15፤ 4፡1፤13፤17፤ 19፤5፡6፤9ን ተመልከቱ።

1ኛ ጴጥሮስ ብዙ ጊዜ የኢየሱስን መከራ ይጠቅሳል። 2ኛ ጴጥሮስ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል። እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በይሁዳ መልእክት ውስጥ የሚገኙትን ይመስላሉ።

ጴጥሮስ በሚጽፍላቸው ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበሩ ችግሮች፡-

1. ብዙዎች ስለ እምነታቸው መከራ ይቀበሉ ነበር፤ ጴጥሮስ ግን መከራን በትዕግሥት እንዲቀበሉና በኑሮአቸው ውስጥ ፀጋ እንዲበዛላቸው ይመክራቸዋል፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡19-20፤ 5፡10።
2. መሪዎች ነን በሚሉት ሐሰተኛ መምህራን ምክንያት ስሕተትና ጥርጥር ተፈጥሮ ነበር፤ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡1፤10፤11።

## ጥያቄዎች

1. የጴጥሮስ የመጀመሪያ መልእክት ዓላማ ምን ነበር? የ2ኛውስ?
2. በ1ኛ ጴጥሮስ ውስጥ ለተጠቀሰችው ቤተ ክርስቲያን የተሰጣትን አንዳንድ መመሪያዎች ጥቀሱ።
3. 2ኛ ጴጥሮስ የሚመሳሰለው ከየትኛው መልእክት ጋር ነው?
4. ክርስቲያን በማንኛውም ምክንያት መከራ መቀበል ይገባዋል? መከራችን ተቀባይነት የሚያጠው መቼ ነው? 1ኛ ጴጥ.-2፡20።
5. የክርስቶስ መመለስ የሚዘገየው ለምንድነው?

## የቤት ሥራ

2ኛ ጴጥሮስን አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ ሰባት

## የ1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ ንድፍ




## የ1ኛ ጴጥሮስ አስተዋፅዖ

1. ተስፋና ቅድስና በክርስቶስ፤ ምዕ. 1።
2. መገዛትና መከራ፤ የአማኝ ኃላፊነት፤ ምዕ. 2።
3. ቤተሰቦችና ለክርስቶስ መመስከር፤ ምዕ. 3።
4. መከራና አገልግሎት በክፉው ዓለም ውስጥ፤ ምዕ. 4-5።

ይህ አቢይ ትምህርት 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስን ያቀራኛቸዋል።

## የ2ኛ ጴጥሮስ አስተዋፅዖ

1. በክርስቶስ መጠራታችን፤ ምዕ. 1።
2. ስለ ሐሰተኛ መምህራን የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤ ምዕ. 2።

3. የክርስቶስ ለፍርድ መምጣት፤ ምዕ. 3።

ቤተ ክርስቲያን መከራ እንደምትቀበል ኢየሱስ ራሱ አስገንዝቦ ነበር፤ ነገር ግን ለመቀበል የሚያስችል ፀጋና ሽልማት እንደምታገኝ ተስፋ ተሰጥቷታል፤ 1ኛ ጴጥ. 5:4፤ 10። ቤተ ክርስቲያንን በመከራ እንድትበረታ የሚያደርጋት የክርስቶስ መምጣት የተስፋ ቃል ነው።

የሁለቱ የጴጥሮስ መልእክቶች ማዕከላዊ አቢይ ትምህርት በመከራ ውስጥ ያለችው ቤተ ክርስቲያን የሚለው ነው።

1. በተለይ የመጀመሪያው መልእክት መከራ ስለመቀበል ያብራራል።
   ሀ/ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፤ 1ኛ ጴጥ. 1:6-7፤ 5:10።
   ለ/ እንዴት ልንቀበል እንደሚገባን፤ 1ኛ ጴጥ. 2:19-20፤ 3:17፤ 4:12-14፤
   ሐ/ መከራን በመቀበል ምሳሌአችን፤ 1ጴጥ. 2:21-24፤ 3:18፤ 4:1-2
2. የመጀመሪያው መልእክት ስለ ክርስቲያን አኗኗር መሠረታዊ መመሪያዎችን ይሰጣል።
   ሀ/ ቃሉን አጥኑ፤ 1ኛ ጴጥ. 2:2-3፤ 3:15።
   ለ/ ከክፉ ራቁ፤ 1ኛ ጴጥ. 2:1፤ 11፤ 1ኛ ተሰ. 5:22 አንብቡ።
   ሐ/ በሥልጣን ላይ ላሉ ሁሉ ተገዙ፤ 1ኛ ጴጥ. 2:13-18፤ 5:5-6።
   መ/ ባልና ሚስት ለአንድነታቸው መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፤ 1ኛ ጴጥ. 3:1-12።
   ሠ/ ትጉና ጸልዩ፤ 1ኛ ጴጥ. 4:7፤ 5:8-9።
   ረ/ በመካከላችሁ ፍቅርን ተለማመዱ፤ 1ኛ ጴጥ. 4:8።
   ሰ/ ሌሎችን በፈቃደኝነት አስተናግዱ፤ 1ኛ ጴጥ. 4:9።
   ሸ/ ከእግዚአብሔር ኃይል ክንድ ሥር ራሳችሁን አዋርዱ፤ 1ኛ ጴጥ. 5:6።
   ቀ/ ጭንቀታችሁን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ጣሉት፤ 1ኛ ጴጥ. 5:7።
3. ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስለመጠራታቸው እርግጠኞች እንዲሆኑ በ2ኛው መልእክት ያሳስባቸውል፤ 2ኛ ጴጥ. 1:10።
   ሀ/ እምነታቸውን እንዳይክዱ ይጠብቃቸዋል፤ 2ኛ ጴጥ. 1:1።
   ለ/ ወደ ዘላለማዊው መንግሥት የመግባት መብት ይሰጣቸዋል፤ 1ኛ ጴጥ. 1:11።
4. 2ኛው መልእክት በተጨማሪ የሐሰተኛ መምህራን በቤተ ክርስቲያን ስለሚሠሩትና ስለሚያስተምሩት ትምህርት ጭምር ያስጠነቅቃል።
   ሀ/ ሐሰተኛ ትምህርት ያስተምራሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:1።
   ለ/ የዋጃቸውን ጌታ ይክዳሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:1።
   ሐ/ ስለ እውነት ክፉ ይናገራሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:2።
   መ/ የራሳቸውን ውሸቶች በማውራት ጥቅም ያገኛሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:3።
   ሠ/ ደፋሮችና ዘላፊዎች ሲሆኑ ባለሥልጣኖችን አያከብሩም፤ ስለ እግዚአብሔርም ክፉ ነገር ይናገራሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:10።
   ረ/ የበለዓምን መንገድ ይከተላሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 2:15።
   ሰ/ «የመምጣቱ ተስፋ ቃል ወዴት ነው? ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራል» በማለት ይዘብታሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 3:3-4።
5. 2ኛው የጴጥሮስ መልእክት ከስደትና ከሐሰተኛ መምህራን ትምህርት የተነሣ በሥቃይና በጥርጥር ውስጥ ለሚገኙት ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ መምጣት ታላቅ ተስፋ ያቀርብላቸውል።
   ሀ/ 2ኛ ጴጥ. 1:21፤ ቃሉ እርግጠኛና እውነተኛ ነው።
   ለ/ 2ኛ ጴጥ. 2:9፤ ጌታ የተፈተኑትን ያድናቸውል።

ሐ/ 2ኛ ጴጥ. 3፡ 9፤ ጌታ ታጋሽ ነው። ነገር ግን ስለ ፍርድ የተናገረውን ቃል አያጥፍም።
መ/ 2ኛ ጴጥ. 3፡ 13፤ ስለ አዲስ ሰማይና ምድር የተሰጠ ተስፋ።

6. 2ኛው የጴጥሮስ መልእክት ለማያምኑና ለከሐዲዎች የፍርድ ማስጠንቀቂያዎች ይሰጣል።
   ሀ/ የጽድቅን መንገድ ካወቁ በኋላ ወደ ክሕደት ከመሄድ ጨርሶ ባላወቁት ይሻላቸው ነበር፤ 2ኛ ጴጥ. 2፡ 22።
   ለ/ የጌታ ቀን እንደ ሌባ ሆኖ በሌሊት ይመጣል፤ ምድርና በርሷ ላይ የተደረገው ነገር ሁሉ ይቃጠላሉ፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡ 10።

ጴጥሮስ ለቀደመችው ቤተ ክርስቲያን የሰጠው መልእክት በዘመናችን በመከራ ውስጥ ለምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ያገለግላል።

## ጥያቄዎች

1. የጴጥሮስ 2 መልእክቶች ማዕከላዊ አቢይ ትምህርት ምንድነው?
2. በ1ኛ ጴጥሮስ የተሰጡትን የክርስቲያን አኗኗር መሠረታዊ መመሪያዎች ዘርዝሩ።
3. የሐሰተኛ መምህራንን ትምህርት ከተመለከታችሁ በኋላ ዛሬ ካላችሁ ልምምድ ጋር አወዳድሩት።
4. እውነትን አውቀው ለሚቃወሙ ወይም ፊታቸውን ለሚመልሱ ሰዎች የተሰጠው ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ምንድነው?
5. ቤተ ክርስቲያን ለዓለም የምትመሰክርባቸው 2 መንገዶች ምን ምንድናቸው?

## የቤት ሥራ

1ኛ ዮሐንስን አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ ስምንት

## 1ኛ፤ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። በመልእክቶቹ ውስጥ ስሙ ባይጠቀስም የአጻጻፍ ዘይቤውና ይዘቱ ከዮሐንስ ወንጌል ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ እነዚህ ሦስት መልእክቶች እርሱ የጻፋቸው መሆናቸው ግልፅ ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡ 1-7። የተጻፉት ምናልባት ከ70 ዓ.ም. በኋላ ሳይሆን አይቀርም። የተጻፉት ለማን ነው? እነዚህ መልእክቶች የተጻፉት ለአማኞች ሁሉ ሊሆን ምናልባት በኤፌሶን ለነበሩ ቀድሞ ለሚያውቃቸው ጥቂት ሰዎች ሳይሆን አይቀርም፤ 1. 1ኛ ዮሐንስ፤ «ልጆቼ ሆይ» 1ኛ ዮሐ. 2፡ 1፤ 7፤ 18፤ 28። «ወዳጆቼ ሆይ» 1ኛ ዮሐ. 4፡ 1፤ 7፤ 11 ወዘተ። 2. 2ኛ ዮሐንስ «ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆችዋ» ሲል ምናልባትም ዮሐንስ የሚያውቀው አንድ ያልተገለጸ ቤተሰብ ሊሆን ይችላል፤ 2ኛ ዮሐ. ቁ. 1። 3. 3ኛ ዮሐንስ፤ «ለጋይዮስ» 3ኛ ዮሐ. ቁ. 1።

## የመልእክቶቹ ዓላማ

አንባቢያን በክርስቶስ እምነት ያላቸውን ዕውቀት፣ ደስታና ዋስትና ለማጠንከር ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡3-4፤ 5፡13። ከሐሰት ትምህርት እንዲጠበቁ ለማድረግ ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡1፤ 4፡1።

የመልእክቶቹ አቢይ ትምህርት የእውነተኛ የወንጌል አገልጋይና የእርሱን መልእክት መፈተኛ ለመስጠት ነው።

## የመልእክቶቹ ባሕርያት

1. የዮሐንስ ጽሑፎች ስለ ብርሃን፣ ሕይወትና ፍቅር በተደጋጋሚ ይናገራሉ። ይህንን ሁኔታ በዮሐንስ ወንጌልም ውስጥ ተመልክተናል።
2. ዮሐንስ ስለ መልካምና ክፉ፤ ስለ ብርሃንና ጨለማ እንዲሁም ስለ እውነተኛና ሐሰተኛ ሲናገር እርግጠኛ ሆኖ ነው።

## በመልእክቶቹ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1/ ብርሃን፤
2/ ሕይወት፤
3/ ፍቅር፤
4/ «እናውቃለን» 1ኛ ዮሐ.2፡3፤ 5፤ 29፤ 3፡14፤ 16፤ 19፤ 24፤ 4፡13፤ 16፤ 5፡15፤ 18-20።

## በመልእክቶቹ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

እነዚህን ምዕራፎች በምታነቡበት ወቅት ምዕራፎቹ በጠቅላላ በነዚህ አቢይ ትምህርቶች ላይ እንዴት እንደሚያተኩሩ ተመልከቱ፡-

1/ 1ኛ ዮሐ. 1፡7፤ በብርሃን ተመላለሱ፤
2/ 1ኛ ዮሐ. 1፡9፤ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ፤
3/ 1ኛ ዮሐ. 3፡18፤ በሥራና በእውነት ተዋደዱ፤
4/ 1ኛ ዮሐ. 4፡1፤ መናፍስትን መርምሩ፤
5/ 1ኛ ዮሐ. 4፡10፤ የእውነተኛ ፍቅር ምሳሌ፤
6/ 1ኛ ዮሐ. 5፡12፤ ልጁ ያለው ሕይወት አለው።

## ጥያቄዎች

1. በዮሐንስ ጽሑፎች ውስጥ በተደጋጋሚ የሚገኙት ሦስት ቃላት ምን ምንድናቸው?
2. የእውነተኛ ፍቅር ምሳሌ ምንድነው?
3. የዮሐንስ መልእክቶቹ አቢይ ትምህርት ምንድነው?

4. መልእክቶቹን ሲጽፍ የዮሐንስ ዓላማ ምን ነበር?

## የቤት ሥራ

1ኛና 2ኛ ዮሐንስን አንብቡ።

# ትምህርት ሰባ ዘጠኝ

## የ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ መልእክቶች ንድፍ

## የእውነተኛ የወንጌል አገልጋይና የመልእክቱ መፈተኛ



# የ1ኛ፤ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ አስተዋፅዖ

የእውነተኛ መልእክተኛና የመልእክቱ መፈተኛ ቀርበዋል። እነዚህ ነገሮች የቀረቡት እውነተኛ ክርስቲያኖች እነ እገሌ ናቸው፤ እነ እገሌ ግን አይደሉም ብለን እንድንፈርድ አይደለም። ይህንን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

## የቀረቡት መመዘኛዎች

1. በብርሃን ይመላለሳል፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡7፤
2. ወንድሞችን ይወዳል፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡9-11፤
3. መልካም ሥራዎችን ይሠራል፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡18፤
4. መንፈስ ቅዱ መልእክቱን ይፈትናል፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡1-3፤
5. እምነትን ይለማመዳል፤ 1ኛ ዮሐ. 5፡4-5፤
6. እግዚአብሔርን ይታዘዛል፤ 2ኛ ዮሐንስ፤
7. በእውነት ይመላለሳል፤ 3ኛ ዮሐ. ቁ. 4፡8።

የዮሐንስ መልእክቶች ማዕከላዊ ምንባብ 1ኛ ዮሐንስ 4፡1-6 ነው። አማኞች እውነትን ለይተው እንዲያውቁና እንዲያስተምሩ የሚረዳቸው መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ዮሐ. 16፡13 አንብቡ። በማታለልና በሐሰት ትምህርት በተሞላ ዓለምና ዘመን ውስጥ የሚሰጡት ትምህርቶች ከእግዚአብሔር መሆናቸውን ለመመርመርና ለማረጋገጥ የምንችልበት የመለየት ስጦታ ያስፈልገናል።

የክሕደት መንፈስ ማለት ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነና ሰው ሆኖ መምጣቱን መካድ ማለት ነው። ክርስቶስ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ መምጣቱን የሚክድ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ የለውም፤ ነገር ግን ጠላት የሆነው የሰይጣን መንፈስ አለው።

የክርስቶስ የሆኑ ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ አላቸው፤ ይህ መንፈስ የዓለም የሆኑት ካላቸው የበለጠ ብርታት አለው። አንድ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር መሆኑንና አለመሆኑን ሌሎች መፈተኛዎች አሉን፤ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት የመልእክቱን መፈተኛና ከአማኝ ልብ ውስጥ ማረጋገጫዎችን ያዘጋጃል።

የእውነተኛ አማኝ የመሆኑና በተለይም ከእግዚአብሔር የተላከ መምህር የመሆኑ ሌሎች ማረጋገጫዎች፡-

1. የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ይጠብቃል፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡3።
2. ለክርስቲያን ወንድሞች ፍቅር ይኖረዋል፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡9፤ 3፡14፤ 4፡7-8፤ 20-21፤ በተጨማሪ ዮሐ. 13፡35 አንብቡ። ይህ እውነተኛ የክርስቶስ ፍቅር ለአማኝ ምን ያደርግለታል? 1ኛ ዮሐ. 4፡17-18 አንብቡ።
3. ዓለምንና የእርሷ የሆኑትን ነገሮች አይወድም፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡15።
4. ክርስቶስ ጻድቅ መሆኑን ያውቃል፤ ያምናልም፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡29።
5. ኃጢአትን መለማመድ ያቋርጣል፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡9፤ 5፡18።
6. በውስጡ የመንፈስ ቅዱስ ምስክር አለው፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ 5፡10።

# በዮሐንስ መልእክቶች ውስጥ የሚገኙ 3 ልዩ ትምህርቶች

1. እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 1፡5 በተጨማሪ ዮሐ. 8፡20 አንብቡ።

እግዚአብሔር ራሱን ይገልጻል፤ ስለዚህ ታላቅነቱንም ያሳያል።
የብርሃን ልጆች ከሆንን፡-

ሀ/ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት መሲህ መሆኑና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እናምናለን፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡15-24።

ለ/ በዓለም ውስጥ የሚያገኙትን ነገሮች ሳይሆን ወንድሞቻችንን እንወዳለን።

2. እግዚአብሔር ሕይወት ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 2፡25፤ 5፡12፤ በተጨማሪ ዮሐ. 14፡6 አንብቡ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጥ ስለ ሆነ ልጁ ያለው ሕይወት አለው። የእግዚአብሔር ሕይወት በውስጣችን ካለን ይህንን ለወንድሞቻችን በምናሳየው በፍቅርና በተግባራችን እንገልጸዋለን፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡18። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደተገለጠ እንመሰክራለን፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡2።
3. እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡16፤ በተጨማሪ ዮሐ. 3፡16 አንብቡ። የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ ውስጥ ተገልጧል። እግዚአብሔር በኃጢአት የተሞላውን ሰው ለመዋጀት ሕይወቱን የሰዋውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጥቷል። የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችን ካለን ትእዛዛቱን እንፈጽማለን፤ 1ኛ ዮሐ. 3፡24፤ በተጨማሪ ዮሐ. 14፡15፤ 24 አንብቡ። እግዚአብሔርን የምንወደው ከሆነ በእርሱ ውስጥ እንኖራለን፤ 1ኛ ዮሐ. 4፡12-13፤ በተጨማሪ ዮሐ. 15፡5 አንብቡ።

## ጥያቄዎች

1. የመልእክተኛውና የመልእክቱ መፈተኛ የሆኑት የዮሐንስ መልእክቶች ማዕከላዊ ጥቆሶች ምን ምንድናቸው?
2. ዮሐንስ በጽሑፎቹ ውስጥ እግዚአብሔርን በማስመልከት የሚያቀርባቸው 3 ትምህርቶች ምን ምንድናቸው?
3. እውነተኛ የክርስቶስ ፍቅር ለአማኞች ምን ያደርግላቸዋል? 1ኛ ዮሐ. 4፡17-18።
4. ባለንበት ዘመን የቀረበውን መልእክት መፈተን አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
5. የእውነተኛ አማኝ ማረጋገጫዎችን ዘርዝሩ።
6. አንድ ሰው አማኝ ነው ብለን አስረግጠን መፍረድ እንችላለን?

## የቤት ሥራ

ያዕቆብ፤ 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስና 1ኛ፥ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስን ከልሱ።

# ትምህርት ሰማንያ

## የያዕቆብ፣ የ1ኛና 2ኛ ጴጥሮስና የ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ ክለሳ

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የያዕቆብ መልእክት ከ61 ዓ.ም. በፊት መጻፉን እንዴት እናውቃለን? ያዕቆብ የተገደለው በ61 ዓ.ም. ነበር።
2. በመጀመሪያዎቹ የቤተ ክርስቲያን ዘመናት አማኞች ዘወትር የሚሰበሰቡት የት ነበር? በምኩራብ ነበር።
3. ያዕቆብ በሐዋርያት ዘመን መጻፉን የሚጠቁመን ሌላው ማስረጃ ምንድነው? አሁንም ክርስቲያኖች የአይሁድን ሥራዓቶች ይፈጽሙ ነበር።
4. የአንድ ሰው የእምነት ማረጋገጫ ምንድነው? ተግባሩ።
5. ያዕቆብ በጻፈላቸው ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ችግርን የሚፈጥሩት እነማን ነበሩ? ራሳቸውን እንደ ጻድቅ የሚቆጥሩ ትዕቢተኛ የአይሁድ እምነት አጥባቂዎችና ብዙ ሀብታሞች ነበሩ።
6. በተለይ በመከራ ላይ ለምትገኘው ቤተ ክርስቲያን የተጻፈው መልእክት የቱ ነው? 1ኛ ጴጥሮስ ነው።
7. ከነዚህ ከሦስቱ ጸሐፊዎች ማለት ከያዕቆብ፥ ከጴጥሮስ ወይም ከዮሐንስ በተለይ ስለ ኢየሱስ ዳግም ምፅዓትና ስለ መጨረሻዎቹ ዘመናት ክሕደት የሚያስተምር ማን ነው? ጴጥሮስ በ2ኛው መልእክቱ ነው።
8. ሥቃያችንና መከራችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኘው መቼ ነው? በጥፋታችንና በኃጢአታችን ምክንያት ስንሰቃይ ነው፤ 1ኛ ጴጥ. 2፥20።
9. ጌታ ከመመለስ የሚዘገይ የሚመስለን ለምንድነው? ማንም እንዲጠፋ ስለማይፈልግ ነው።
10. ኢየሱስን እንደ ብርሃን፥ ሕይወትና ፍቅር የሚያቀርበው የትኛው መልእክት ነው? 1ኛ ዮሐንስ ነው።
11. በ1ኛ ዮሐንስ ውስጥ አማኞች ምን ምን እንዲፈትኑ ታዝዘዋል? የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩትን ሰዎች መናፍስት።
12. አንድ መልእክተኛ እውነተኛ መሆኑን እንዴት እናውቃለን? 1ኛ ዮሐ. 4፥1-3 ተመልከቱ።
13. የእውነተኛ መልእክተኛን 3 ባሕርያት ጥቀሱ። የ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ አስተዋፅዖ ትምህርት 79 ተመልከቱ።
14. እውነትን ሳያዳላ ሊፈትን የሚችል ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው።
15. ጴጥሮስ በ2ኛ መልእክቱ ውስጥ የሚሰጠው ትንቢታዊ እውነት ምንድነው? አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚመጣ ነው።

# ትምህርት ሰማንያ አንድ

## ከያዕቆብ፤ 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስና 1ኛ፤ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ

**ዮሐንስ ማለት ከትምህርት 74-79 ተውጣጥቶ የተዘጋጀ ፈተና**

## ምክር ለመምህሩ

**ፈተናዎን ካዘጋጁ በኋላ ተማሪዎችዎን ይፈትኑ።**

## የቤት ሥራ

**የይሁዳን መልእክት አንብቡ።**

# ትምህርት ሰማንያ ሁለት

## የይሁዳ መልእክት መግቢያ

ጸሐፊው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ይሁዳ ነው። የተጻፈበት ዘመን ምናልባት 66 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል። የተጻፈው ለቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ነው።

## የመልእክቱ ዓላማ

1. የቀደመችውን ቤተ ክርስቲያን ከክሕደትና ከአመፅ እንድትጠብቅ ለማስጠንቀቅ፤
2. አማኞች ለእምነታቸው እንዲታገሉ ለማደፋፈርና
3. የተማሩትን ወንጌል ማስተማር እንዲቀጥሉ ለማሳሰብ ነው። የመልእክቱ አቢይ ትምህርት ስለ እምነት መታገል ነው፤ ቁ. 3።

## የመልእክቱ ልዩ ባሕርያት

1. በ2ኛ ጴጥሮስ ውስጥ ከሚገኙት ማስጠንቀቂያዎች ጋር ይመሳሰላል።
2. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተሰጡት ከባድ መልእክቶች መካከል አንዱ ነው።
3. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ግሩም ምርቃቶች መካከል አንዱን ይዟል፤ ቁ. 24-25።

## የይሁዳ መልእክት አስተዋፅዖ

1. ለአመፅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤ ቁ. 1-4።

2. የአመፅ ምሳሌዎች፤ ቁ. 5-7።
3. ስለ አመፅ የተሰጠ መግለጫ፤ ቁ. 8-19።
4. የአመፅ መቋቋሚያ፤ ቁ. 20-23።

የይሁዳ መልእክት ንድፍ




## የይሁዳ መልእክት ማጠቃለያ

የይሁዳ መልእክት እውነትን አውቆ ስለመቃወም ወይም ስለ ክሕደት ያስጠነቅቃል። ይሁዳ ክሕደት እንዴት እንደተቀጣ ለማሳየት 3 ሁኔታዎችን ይጠቅሳል። እነርሱም፡-

1. ወደኋላቸው የተመለሱትን እስራኤላውያንን፥
2. የወደቁትን መላእክትና
3. የሰዶምና የገሞራ ከተሞች ናቸው።

ከዚህ በኋላ ከብሉይ ኪዳን 3 የክሕደት ባህርያት ምሳሌዎችን ይጠቅሳል።

1. ቃየል የሰብዓዊ ሃይማኖትና የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመጥላት ምሳሌ ነው።
2. በለዓም መንፈሳዊ ነገሮችን ለገንዘብ ማግኚያ የመጠቀም ምሳሌ ነው።
3. ቆሬ በእግዚአብሔር መመሪያ ላይ የማመፅ ምሳሌ ነው።

በእነዚህ ነገሮች ሁሉ ላይ ፍርድ እንደሚሰጥ የተረጋገጠ ነው። ክርስቲያኖች የጌታን መምጣት እየተጠባበቁ ራሳቸውን በእምነት፤ በጸሎትና በፍቅር ማነፅ ይኖርባቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር በእስራኤላውያን መካከል ክሕደትን እንዴት ቀጣ? የወደቁትንስ መላእክት? የሰዶምና የገሞራ ከተሞችንስ?
2. በለዓም የገንዘብ ወይም የቁስ ጥቅም ለማግኘት ወይም ዝናን ለማትረፍ ምን ለማድረግ ሞከረ? 2ኛ ጴጥ. 2፡15፤ ዘኁ. 22፡1-41።
3. አማኞች ለእምነት እንዲታገሉ ይሁዳ ለምን ይመክራቸዋል?
4. ይሁዳ የሚመሳሰለው ከየትኛው መልእክት ጋር ነው?

## የቤት ሥራ

የዮሐንስ ራዕይ 1-7 አንብቡ።

# ትምህርት ሰማንያ ሦስት

## የዮሐንስ ራዕይ መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ሲሆን የጻፈው በጌታ ስላለው እምነት በፍጥሞ ደሴት በግዞት ላይ በነበረበት ወቅት ነው፤ 1፡9። የተጻፈበት ዘመን ምናልባት በ96 ዓ.ም. ገደማ ይሆናል። የተጻፈው ለሚያነቡና ለሚያዳምጡ ሁሉና በእስያ ለሚገኙ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ነው፤ 1፡3-4። ከእግዚአብሔር የተሰጠ ራዕይ ወይም ተከታታይ ራዕዮች ናቸው። ይህ ዮሐንስ ያየውና የሰማው እግዚአብሔር እንዲጽፍ የነገረው ነው።

## የመጽሐፉ ዓላማ

1. ያለፉ ነገሮችን /1፡1-20/ የአሁን ጊዜ ነገሮችንና /2፡1-3፡2/ ከዚህ በኋላ የሚፈፀሙትን ነገሮች /4፡1-22፡5/ ራዕይ ያቀርባል፤ በተጨማሪ ራዕይ 1፡19 ተመልከቱ።
2. ክርስቶስ በክብር ላይ እንዳለ የሚያሳይ ራዕይ ነው፤ 1፡5-7፤4፡4-5፤ 19፡7-16።
3. የተጻፈው በተሰደዱትና ወደፊት በሚመጣው ዘመን ስደት በሚጠብቃቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙትን ክርስቲያኖች ለማጽናናት ነበር፤ 1፡3፤ 9።

## በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ኢየሱስ በሚከተሉት ምሳሌዎች ቀርቦአል

1. እንደ የምድር ነገሥታት መሪ፤ 1፡5።
2. እንደ ሙሽራና የቤተ ክርስቲያን ራስ፤ 2፡1-3፡22፤ 19፡7-9።
3. እንደ የይሁዳ ነገድ አንበሳ፤ 5፡5።
4. እንደ ታረደው በግ፤ 5፡6፤ 12።
5. እንደ ሊቀ ካህን፤ 8፡3-6።
6. እንደ ንጉሥና ዳኛ፤ 19፡11-20፡15።

የዮሐንስ ራዕይ አቢይ ትምህርት «ክርስቶስ ይመጣል» ወይም «የክርስቶስ መንግሥት በሙላት መገለጥ» ነው።

## በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላት

1. ሰባት፤ 1፡4፤13፤16፤5፡1፤8፡2፤15፡1፤7፤
2. እውነት፤ 5፡3፤19፡2፤11፤21፡5፤22፡6።

## በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ጥቅሶች

1. 1፡19 «እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህ በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።»
2. 11፡17 «ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ትልቁን ኃይልህን ስለያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን።»
3. 21፡4 «እንግዲህ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ሐዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀድሞው ሥርዓት አልፎአልና።»

## ጥያቄዎች

1. በራዕይ የተገለጠው ነገር ምንድነው? 1፡9።
2. በራዕይ የተገለጠው ማን ነው? 1፡1።
3. ባለንበት ዘመን ለሚገኙት ክርስቲያኖች የዮሐንስ ራዕይ ምን ይጠቅማቸዋል?
4. የተጻፈው ለማን ነበር?
5. የዮሐንስ ራዕይ አቢይ ትምህርት ምንድነው?

## የቤት ሥራ

ራዕይ 8-15 አንብቡ።

# ትምህርት ሰማንያ አራት

**የዮሐንስ ራእይ አጠቃላይ አስተዋፅዖ ንድፍ**



# የዮሐንስ ራዕይ አስተዋፅዖ

## 1. ሰባቱ የአብያተ ክርስቲያናት ደብዳቤዎች፤ 1-3

ሀ/ ኤፌሶን መልካም ታሪክ ሲኖራት ፍቅሯን አጥታ ነበር፤ 2፡1-7።
ለ/ ሰምርኔስ በሰይጣን ልዩ ፈተና ውስጥ ስትሆን ታማኝ ለሆኑት ሽልማት እንደሚሰጣቸው ቃል ኪዳን ተሰጥቷታል፤ 2፡8-11።
ሐ/ ጴርጋሞን ይህችም ቤተ ክርስቲያን በሰይጣን ልዩ ፈተና ውስጥ ስትሆን በሐሰት ትምህርት ተሳስተው የጠፉት ለንስሐ ተጠርተዋል፤ 2፡12-17።
መ/ ትያጥሮን በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥነ ምግባር ጉድለት ሲኖር እንዳይታለሉ ወደፊት መጓዛቸውን በመቀጠል በክርስቶስ ያለውን ሕይወት እንዲወርሱ ተነግሯቸዋል፤ 2፡18-29።
ሠ/ ሰርዴስ የሞተች ቤተ ክርስቲያን ነበረች፤ ስለዚህ እንድትነቃ ተመክራለች፤ 3፡1-6።
ረ/ ፊልደልፍያ ስለ ታማኝነቷ ስትመሰገን በሚመጣው መከራ ደግሞ ልዩ ጥበቃ እንደሚደረግላት የተስፋ ቃል ተሰጥቷታል፤ 3፡7-13።
ሰ/ ሎዶቅያ ስላሳየችው ለዘብተኛነት የተወገዘች ሲሆን አሁንም ንስሐ መግባት ትችላለች፤ 3፡14-22።

መኅተሞች ከመፈታታቸው በፊት ሁለት ልዩ ራዕዮች ቀርበዋል፡-

1. ስለ እግዚአብሔር፤ ምዕ. 4፡1-11።
2. ስለ ክርስቶስ ናቸው፤ ምዕ. 5፡1-14።

## 2. ሰባቱ ማኅተሞች፤ ምዕ. 6-8፡1

ማኅተሞቹም፡-

1. ሐሰተኛው ክርስቶስ
2. ጦርነት
3. ረሃብ
4. ሞት
5. የሰማዕታት ጥያቄና
6. ትርምስ ናቸው።

ቀጥሎም የእግዚአብሔር ቁጣና የ144000ዎቹ አይሁድ አማኞች መታተም ተገልጧል። 7ኛው ማኅተም ሰባቱን መለከቶች ይገልጣል፤ 8፡1።

## 3. ሰባቱ መለከቶች፤ ምዕ. 8፡2-9፡21፤ 11፤ 15-19

ሀ/ የመጀመሪያው መለከት ከደም ጋር የተቀላቀሉ በረዶና እሳት፤ 8፡7።
ለ/ 2ኛው መለከት የባሕር ሲሶ ወደ ደም ይለወጣል፤ 8፡8-9።
ሐ/ 3ኛው መለከት የውሃዎች ሲሶ መራራ ይሆናል፤ 8፡10-11።
መ/ 4ኛው መለከት የፀሐይ፣ የጨረቃና ከዋክብት ሲሶ ጨለመ፤ 8፡12-13።
ሠ/ 5ኛው መለከት የሚናደፉ የጊንጥ ጅራት ያላቸው አንበጦች የሚያደርሱትም ስቃይ 5 ወር ይቆያል፤ 9፡1-12።

ረ/ 6ኛው መለከት አራት መላእክት ከኤፍራጥስ ወንዝ ተፈትተው የምድርን ሰዎች ሲሶ ይገድላሉ፤ 9፡13-21።

ሰ/ 7ኛው መለከት ሰማያዊው ቤተ መቅደስ ተከፍቶ መብረቅ፥ ነጐድጓድ፥ የምድር መንቀጥቀጥና ታላቅ በረዶ ይሆናል።

ማሳሰቢያ፡- ሰባተኛው መለከት ከመነፋቱ በፊት አንድ መልአክ ዮሐንስን ይጐበኘውና ሦስት ነገሮች ያሳየዋል።

1. ትንሹን መጽሐፍ፤ 10፡1-11፤
2. የቤተ መቅደስን መለኪት፤ 11፡1-2፤
3. ሁለቱን ምስክሮች፤ 11፡3-14።

## 4. ምልክቶች በምዕ. 12-14 ውስጥ የተገለጡት ሰባት ሰዎች የወደፊት ምልክቶችንና ሥልጣኖችን የሚያስተጋቡ ናቸው።

ሀ/ ሴቲቱ 12፡1-2፤ 13-17። የእስራኤል ምሳሌ ናት።
ለ/ ዘንዶው 12፡3-4፤ 13፤ 17። የሰይጣን ምሳሌ ነው።
ሐ/ ወንድ ልጅ 12፡5-6። የክርስቶስ ምሳሌ ነው።
መ/ ሚካኤል ሊቀ መልአኩ 12፡7-12።
ሠ/ ከባሕር የወጣው አውሬ 13፡1-10። ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ምሳሌ ነው።
ረ/ ከምድር የሚወጣው አውሬ 13፡11-18። የሐሰተኛው ነቢይ ምሳሌ ነው፤ 16፡13።
ሰ/ በጉና 144000ዎቹ በጽዮን ተራራ ላይ የሚያምኑት አይሁዶች ከክርስቶስ ጋር መሆናቸውን ያሳያል።

## <u>ከመጨረሻው ፍርድ በፊት እነዚህ 7 ሁኔታዎች ይገለጻሉ</u>

1. መልአካዊ መልእክቶች፤ 14፡6።
2. የፍርድ ጥሪ፤ 14፡7።
3. የባቢሎን ውድቀት፤ 14፡8።
4. የቁጣ ማስጠንቀቂያ፤ 14፡9-11።
5. የሙታን መባረክ፤ 14፡12-13።
6. የምከር ጥሪ፤ 14፡14-15።
7. የቁጣ ወይን ማጨድ፤ 14፡16-20፤ 15፡1-8።

## 5. ሰባቱ የእግዚአብሔር ቁጣ ጽዋዎች 16፡1-21

ሀ/ የመጀመሪያው ጽዋ ቁስሎች፤ 16፡1-2።
ለ/ 2ኛው ጽዋ ባሕርን ወደ ደም መለውጥና በውስጥዋ የሚገኙት ነገሮች መሞት፤ 16፡3።
ሐ/ 3ኛው ጽዋ ወንዞችና ጅረቶችን ወደ ደም መለወጡ፤ 16፡4-7።
መ/ 4ኛው ጽዋ የሚገሸልጥ ሙቀት፤ 16፡8-9።
ሠ/ 5ኛው ጽዋ ጨለማና ሥቃይ፤ 16፡10-11።
ረ/ 6ኛው ጽዋ የምሥራቅ ኃይላት ለአርማጌዶን ጦርነት መሰብሰብ፤ 16፡12-16።

ሰ/ 7ኛው ጽዋ የምድር መንቀጥቀጥ፣ ነጐድጓድ፣ መብረቅና የአህዛብ ሥልጣናት ፍፃሜ፣ 16፡17-21።

ምዕ. 17-19 የስድስተኛውንና የሰባተኛውን ጽዋዎች ራዕይ በይበልጥ ያብራራሉ።
ራዕይ 17፡1-19፡10 የባቢሎንን ፍርድ ያብራራሉ።
ራዕይ 19፡11-21፡21 የበጉ ሠርግ፥ የክርስቶስ በክብር መመለስ፣
የአርማጌዶን ጦርነት፣ 19፡17-19ን ከ16፡14-16 ጋር አገናዝቡ።
የአውሬውና የሐሰተኛው ነቢይ መደምሰስ ተገልጠዋል።

## 6. የክርስቶስ መንግሥት በሙላት መገለጥ፣ 20-22

ሀ/ ሰይጣን ለ1000 ዓመታት ይታሠራል፣ 20፡1-3።
ለ/ የሰማዕታት ትንሣኤ፣ 20፡4-6።
ሐ/ የሰይጣን የመጨረሻ መነሣትና ፍርድ፣ 20፡7-10።
መ/ ባላመኑት ሰዎች ላይ የሚፈጸመው የነጭ ዙፋን ፍርድ፣ 20፡11-15።
ሠ/ አዲሱ ሰማይና አዲሱ ምድር፣ 21፡1-8።
ረ/ የሕይወት ወንዝና የሕይወት ውኃ፣ 22፡1-5።

ማሳሰቢያ፡- ምዕ. 22፡6-21 የመጨረሻ መልእክትና የእግዚአብሔር ቃል ተስፋ ነው።

## ጥያቄዎች

1. ለቤተ ክርስቲያናት የተሰጡት መልእክቶች በዮሐንስ ዘመን ለነበሩት ብቻ ነበር?
2. ሰባቱ ማኅተሞች ሲፈቱ የተገለጠው ምን ነበር?
3. ሰባቱ መለከቶች የሚያውጁት ምንድነው?
4. ሰባቱ ምስሎች የምን ምሳሌዎች ናቸው?
5. ሰባቱ ጽዋዎች የምን ምሳሌዎች ናቸው?
6. በታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ ፊት የሚፈረድባቸው እነማን ናቸው?

## 7. ራዕይ 22፡6-19 አንብባችሁ ከዚህ በታች ለሚገኙት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ሀ/ ይህ ራዕይ የተሰጠው ለምንድነው? ቁ. 6።
ለ/ አማኞች ይህንን ትንቢት ማንበብና መታዘዝ የሚገባቸው ለምንድነው? ቁ. 7።
ሐ/ እነዚህን ራዕዮች እንድንረዳ እግዚአብሔር ይፈልጋል? ቁ. 10።
መ/ የሰውን ሽልማት የሚወስነው ምንድነው? ቁ. 12።
ሠ/ እንዲመጣ የተጋበዘው ማን ነው? ቁ. 17።
ረ/ በማንኛውም መንገድ ይህንን ራዕይ ለሚለውጡ ሰዎች የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድነው ቁ. 18-19።

## የቤት ሥራ

ራዕይ 16-19 አንብቡ።

# ትምህርት ሰማንያ አምስት

ማሳሰቢያ፦ ማጠቃለያው በአንድ ትምህርት ሥር ለማቅረብ በጣም ስለሚረዝም ቀሪው ክፍል በሚቀጥለው ትምህርት ውስጥ ይቀጥላል።

## የዮሐንስ ራዕይ አጭር ማብራሪያ

### የዮሐንስ ራዕይ 1-3

በቤተ ክርስቲያን ላይ በደረሰው ስደት ምክንያት ዮሐንስ ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት ይወሰዳል። እዚያ በነበረበትም ወቅት ጽፎ ለአብያተ ክርስቲያናት እንዲያስተላልፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ያዘዘውን ተከታታይ ራዕዮች ይቀበላል። እነዚህ ደብዳቤዎች የተጻፉት ምንም እንኳ በዮሐንስ ዘመን ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ቢሆንም በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ መድረኮች ላይ ስለነበራት ሁኔታ ትክክለኛ ገላፃ ያቀርባሉ። ጌታ በሚመለስበት ወቅት የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ምን እንደሚመስል ያሳዩ ይሆናል፤ ራዕይ 3፡14-19 አንብቡ።

### የዮሐንስ ራዕይ 4-7

ምዕ. 4-5 ቅዱሳን በሰማይ በዙፋኑ ዙሪያ ተሰብስበው በጉን ማለት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ሲያመልኩ ያሳዩናል። ምዕ. 6 ኢየሱስ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት የሚሆኑትን ድርጊቶች በሰባት ማኅተሞች መፈታት ያቀርብልናል፤ በትምህርት 84 ውስጥ የሚገኘው አስተዋፅዖ ተመልከቱ። በማንኛውም ዘመን እግዚአብሔር ሰውን ያለ ምስክር እንደማይተው ምዕ. 7 ያሳየናል። እግዚአብሔር በምድር ላይ ታላቅ ምስክሮች የሚሆኑ 144 000 ሰዎች የእስራኤል ነገዶች ያስነሣና በታላቁ መከራ ወቅትም ብዙዎች ጌታን ወደ ማወቅ ይመጣሉ።

### የዮሐንስ ራዕይ 8-10

ምዕ. 8፡1 የሰባተኛው ማኅተም መከፈቻ ነው። ይህ ማኅተም ሰባቱን መለከቶች ይገልጣቸዋል። ምዕ. 8-9 ስድስት ፍርዶችን የሚያቀርብልንን ስድስት መለከቶች ይዘዋል። እነዚህ ስድስት ፍርዶች በትምህርት 84 ውስጥ ተዘርዝረዋል። ሰባተኛው መለከት ከመነፋቱ በፊት በእጁ ትንሽ መጽሐፍና የሰባት ነጐድጓዶች ንግግር የያዘ ብርቱ መልአክ ይገለፃል፤ 11፡5። ሆኖም ዮሐንስ የሰባቱን ነጐድጓዶች ድምፅ እንዳይመዘግብ ትእዛዝ ይሰጠዋል። ከዚያም ዮሐንስ ትንሿን መጽሐፍ ከመልአኩ ተቀብሎ እንዲበላ ይታዘዛል። ዮሐንስም ሲበላው ለአፉ ጣፋጭ ለሆዱ ግን መራራ ሆነበት። ከዚህ በኋላ መልአኩ ዮሐንስን እንደገና በብዙ አሕዛብ፥ ቋንቋዎችና መንግሥታት መካከል የእግዚአብሔርን መልእክት እንዲያውጅ ይነግረዋል።

### የዮሐንስ ራዕይ 11

በመጀመሪያ ዮሐንስ ቤተ መቅደሱንና መሠዊያውን እንዲለካና በዚያም ያመልኩ የነበሩትን ሰዎች እንዲቆጥራቸው ይነግራቸዋል። የግቢው ውጫዊ ክፍሎች ለ42 ወራት ለአህዛብ እንደተሰጣቸው ለዮሐንስ ተነግሮት ነበር።

ከዚያም መልአኩ ምስክርነታቸውን እስከሚፈፅሙ ድረስ በታላቅ ኃይል ስለሚመሰክሩት ስለ ሁለቱ ምስክሮች ይናገራል። ከዚህ በኋላ ከባሕር የሚወጣ አውሬ እሸንፏቸው ይገድላቸውል፤ ሬሳቸውንም በኢየሩሳሌም ከተማ በጐዳና ላይ ይተዋል። ሆኖም ከሦስት ቀን ተኩል በኋላ ተመልሰው ከሞት ይነሡና በሕይወት ይመላለሳሉ፤ ጠላቶቻቸውም ደግሞ ይህንን ተመልክተው ይፈራሉ። ነገር ግን ሁለቱ ምስክሮች ጠላቶቻቸው እያዩአቸው ተጠርተው በደመና መካከል ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ።

ታላቅ የምድር መናወጥ የምድራቱን አንድ እስረኛና 7000 ሰዎች ይደመሰሳል። ከዚህ ጥፋት የዳኑት በፍርሃት ተውጠው ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጣሉ። አሁን ሰባተኛው መለከት ይነፋል፤ ክርስቶስም በሰማይ ላይ ይገለፃል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይከፈታል፤ ይህ ታሪክ በ15፡5 ላይ ይቀጥላል።

## የዮሐንስ ራዕይ 12-14

የሰባት ሰዎች ሁኔታዎች ተገልጿል፤ ቀጥሎም ሰባት ማስጠንቀቂያዎች ተሰጥተዋል፤ እነዚህም ነገሮች በ84ኛው ትምህርት ውስጥ ተብራርተዋል። ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ከመመለሱ በፊት የመጨረሻዎቹ ዘመናት ምልክቶች ናቸው። የወደፊት በምድር ላይ ሥልጣናትን ይወክላሉ። ዘንዶው ማለት ሰይጣን ከሰማይ ተወርውሮ ወደ ምድር ተጣለ፤ ኤፌ. 6፡12። ዲያብሎስ ጊዜው ወደ ማብቂያው እንደተቃረበ ስለሚያውቅ በጣም ተቆጣ። የክርስቶስ ተቃዋሚና ሐሰተኛው ነቢይ በሰይጣን ኃይል ምድርን ይመራሉ፤ የሚያምኑትም አይሁዶች ከባድ ስደት ይደርስባቸዋል። ስለ ባቢሎን ውድቀትና የአርማጌዶን ጦርነት ራዕይ ቀርቧል። በምዕ. 18-19 ውስጥ የነዚህ ነገሮች ፍፃሜ ተብራርቷል።

# ጥያቄዎች

1. ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት በግዞት ላይ የነበረው ለምንድነው?
2. በየትኛውም ዘመን እግዚአብሔር ለዓለም ምስክር ሰጥቷል፤ ታዲያ በታላቁ የመከራ ዘመን ምስክር የሚሆነው ማነው?
3. የወደፊት የምድር ክፉ መሪዎችን የሚወክሉት እነማን ናቸው?
4. ሰይጣን ከሰማይ ሲጣል ያስቆጣው ምንድነው?
5. ሁለቱ ምስክሮች በኢየሩሳሌም ምን ይደርስባቸዋል?

# የቤት ሥራ

ራዕይ 20-22 አንብቡ።

# ትምህርት ሰማንያ ስድስት

## ካለፈው የቀጠለ የዮሐንስ ራዕይ አጭር ማብራሪያ

### የዮሐንስ ራዕይ 15-19

በምዕራፍ 15 የሚታየው ሌላው ምልክት በክፉው ዓለም ላይ የሚደርሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ሰባት መቅሰፍቶች የያዙ ሰባት መላእክት መገለፅ ነው።

ቅዱሳን በአውሬውና በምስሉ ላይ ካገኙት ድል የተነሣ በሰማይ ይደሰታሉ፤ 12፡11። ኃያሉን ጌታ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ። ከዚያም የምስክሩ ድንኳን ተከፈተ፤ ሰባቱን መቅሰፍቶች የያዙት ሰባቱ መላእክት ወጡ እነዚህም በእግዚአብሔር ቁጣ የተሞሉ ሰባት ጽዋዎች ነበሩ። ሰባቱ የእግዚአብሔርን ቁጣ የያዙት ጽዋዎች በመላእክቱ በምድር ላይ ፈሰሱ፤ ምዕ. 16። እነዚህ ነገሮች በትምህርት 84 ውስጥ በሚገኘው አስተዋፅዖ ውስጥ ሰፍረዋል።

ምዕ. 17-19 ስድስተኛውንና ሰባተኛውን ጽዋዎች በሰፊው ያብራራሉ። ታላቂቱ ጋለሞታ ተደምስሳለች፤ ታላቂቱም ከተማ ባቢሎን ተገልብጣለች። በእርሷ ውስጥ ይነግዱና በቅንጦት ይኖሩ የነበሩ የምድር ነገሥታት በደረሰው ጥፋት ምክንያት ያለቅሳሉ፤ ያዝናሉም። ዋና ኃጢአተኛ የሆነችው ባቢሎን በመበላሸትዋ ምክንያት ስለተገለበጠች መላእክት ይደሰታሉ።

ምዕ. 19 ስለ በጉ የጋብቻ እራት ግብዣ ይናገራል። ክርስቶስ ከሙሽራይቱ ከቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ የሚቀመጥበት ቀን ደረሰ። ከዚያም የክርስቶስ በክብር መመለስ ይሆናል። ክርስቶስ ተመልሶ ወደዚህ ምድር ሲመጣ አመጣጡ ለፍርድ ነው፤ የዓለምን መንግሥታት በሙሉ በብረት በትር ይመራቸዋል። ቀደም ብሎ በምዕ. 14፡14-20ና 16፡13-16 ውስጥ የተጠቀሰው የመጨረሻ ታላቅ ጦርነት በምዕ. 19፡17-21 ውስጥ ፍፃሜ ያገኛል። አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ በእሳት ባሕር ውስጥ ይጣላሉ። በመጨረሻውና በታላቁ የአርማጌዶን ጦርነት ወቅት የሚሞቱትን ሰዎች ሥጋ ለመብላት የዓለም አዕዋፍ ሁሉ ይሰበሰባሉ።

### የዮሐንስ ራዕይ 20-22

ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ ለ1000 ዓመታት ይነግሣል። በነዚህ ዘመናት ወቅት ሰይጣን በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይታሠራል። በክርስቶስ መንግሥት ፍፃሜ ላይ በነጭ ዙፋን ተቀምጦ ዓለም ከተፈጠረች አንሥቶ እስከዚያ ጊዜ ባሉት ዘመናት ውስጥ የነበሩትን ኃጢአተኞች ይፈረድባቸዋል። እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያደረገውን የመቤዠትና የጽድቅ መንገድ ያልተቀበሉትንም ሁሉ ይፈርድባቸዋል።

ከዚያም እግዚአብሔር አሁን በኃጢአት ተበክለው የሚገኙትን ሰማይና ምድር ይደመስሳል፤ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን ይፈጥራል። የእግዚአብሔርም ሰዎች ፍጹማንና ያለኃጢአት ይሆኑና ከክርስቶስ ጋር በሰላምና በደስታ ለዘላለም ይኖራሉ።

የዚህ ራዕይ የመጨረሻ መልእክት አማኞች ትንቢቱን ሲያጠኑ ምንም እንዳይጨምሩም እንዳይቀንሱም ነው። እነዚህን ነገሮች የሚመሰክረው «አዎን በቶሎ እመጣለሁ!» ይላል።

## ምክር ለመምህሩ

የዮሐንስን ራዕይ በይበልጥ ለመተርጐም ከፈለጉ የዮሐንስ ራዕይ ማብራሪያ የተሰኘውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

## ጥያቄዎች

1. በክርስቶስ የ1000 ዓመታት መንግሥት ወቅት ሰይጣን የት ይሆናል?
2. የሰይጣን የመጨረሻና ዘላለማዊ ፍርድ ምንድነው?
3. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚኖር ማን ነው?
4. የዚህን ትንቢት ቃላት የሚጠብቁት ሰዎች የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ምንድነው? 22:14።
5. የዚህ በእግዚአብሔር ቃል መጨረሻ ላይ የሚገኘው መጽሐፍ የመዝጊያ ቃል ኪዳን ምንድነው? 22:20።

# ትምህርት ሰማንያ ሰባት

ለዓመቱ 2ኛ አጋማሽ ፈተና ክለሳ

| የጳውሎስ መልእክቶች | አቢይ ትምህርታቸው |
| --- | --- |
| 1. ሮሜ | ይህ የክርስትና እምነትና በአሮጌውና በአዲሱ ሕይወት መካከል ለተፈጠረው ግጭት የተሟላና ግልፅ ማብራሪያ ነው ። |
| 2. 1ኛ ቆሮንቶስ | ይህ የአዲስ ቤተ ክርስቲያን ችግሮችንና የክርስቲያን ባሕርይ መመሪያ ያቀርባል ። |
| 3. 2ኛ ቆሮንቶስ | ኢየሱስ ክርስቶስ ብቃት ያለው ተደርጎ ቀርቧል ። ጳውሎስ ስለ ሐዋርያነቱ መከላከያ ያቀርባል ። ስለ አስራትና ምፅዋት ትምህርት ይሰጣል ። |
| 4. ገላትያ | ጽድቅ የኦሪትን ሕግ በመጠበቅ ሳይሆን በእምነት ብቻ ነው ። |
| 5. ኤፌሶን | የአካሉን ማለት የቤተ ክርስቲያንን ራስ ክርስቶስን አድርጎ ያቀርባል ። በአካል ውስጥ አንድነት አስፈላጊ መሆኑን አጥብቆ ይናገራል ። |

| የጳውሎስ መልእክቶች | አቢይ ትምህርታቸው |
|---|---|
| 6. ፊልጵስዩስ | አማኝ ዘወትር በመከራ ጊዜም እንኳ ቢሆን መደሰትና ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ እንደሚችል ይገልፃል ። |
| 7. ቆላስይስ | ክርስቶስን የተፈጥሮ ሁሉና የቤተ ክርስቲያን ራስ አድርጐ ያቀርበዋል ። ስለ ሰብዓዊ ፍልስፍናዎች ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ። |
| 8. 1ኛና 2ኛ ተሰሎንቄ | 1ኛ ተሰሎንቄ ስለ ክርስቶስ መመለስ ማብራሪያ ይሰጣል ።<br>2ኛ ተሰሎንቄ ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት ስለሚሆነው ክህደት ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ። |
| 9. 1ኛ ጢሞቴዎስ | የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና አገልግሎት በሚመለከት መመሪያዎችን ይሰጣል ። |
| 10. 2ኛ ጢሞቴዎስ | ክህደት በመስፋፋት ላይ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት የመያዝ አስፈላጊነትን ያስተምራል ። |
| 11. ቲቶ | የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና የክርስቲያንን አኗኗር በመመልከት መመሪያ ይሰጣል ። |
| 12. ፊልሞና | ክርስቶስ ለኃጢአተኞች የሚያደርገው ምህረት ምሳሌ ነው ። |
| ሌሎች መልእክቶች | |
| 13. ዕብራውያን | ክርስቶስ ከለፉት ሥርዓቶች ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን ያሳያል ። ክርስቶስን አስታራቂያችን ወይም ሊቀ ካህናችን አድርጐ ያቀርበዋል ። |
| 14. ያዕቆብ | መልእክቱ በራሳቸው ጽድቅ የሚመኩትን ትዕቢተኞች ክርስቲያኖችን ሲገስጽ እውነተኞቹ ክርስቲያኖች ትዕቢተኞቹ የሰነዘሩባቸውን ዛቻዎችና ማስፈራሪያዎች እንዲችሉና በሰላም ከነርሱ ጋር ለመኖር እንዲሞክሩ ይመክራቸዋል ። |

| | |
|---|---|
| 15. 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ | በመከራ ላይ ላሉቸው ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ መመለስ አንፃር ትምህርት ይሰጣል ። |
| 16. 1ኛ ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ | ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ሕብረት እንዴት እንደሚጠብቁና የመልእክተኛውን መልእክት እንዴት እንደሚፈትኑ ያስተምራል ። |
| 17. ይሁዳ | ስለ መጨረሻው ዘመን ክህደትና ፀመፅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ። |
| 18. የዮሐንስ ራእይ | ይህ መጽሐፍ ያለፉ ፤ የአሁንና የወደፊት ሁኔታዎችን ይገልፃል ። |

የጳውሎስ የጉዞ መልእክቶች

| መልእክቱ | ችግሩ | መፍትሄው |
|---|---|---|
| 1. 1ኛ ተሰሎንቄ | ስለ ክርስቶስ መመለስ በትክክል አለመረዳት በሌሎች ሰዎች ጉዳይ እንዲገቡ የሚያደርጋቸውን ሥራ ፈትነትን አስከተለ ። | 1ኛ ተሰ. 4፣13—18 የክርስቶስን መመለስ ይገልፃል ። 1ኛ ተሰ. 4፣11፤ 2ኛ ተሰ. 3፣11—13 አጥኑ፤ በፀጥታ ኑሩ፤ የራሳችሁን ጉዳይ ተከታተሉ ። |
| 2 2ኛ ተሰሎንቄ | አንዳንዶች የመጨረሻው ታላቅ ስደት መጥቷል ብለው ስላመኑ ስለ ጌታ መምጣት በጥርጥር ውስጥ ነበሩ ። | ክርስቶስ ከመመለሱ በፊት «የአመፅ ሰው» ይገለፃል፤ ክህደትም ይበዛል፣ 2ኛ ተሰ. 2፣1—10 ። |

<u>የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ትምህርት አዘል መልእክቶች</u>

| መልእክቱ | ችግሩ | መፍትሄው |
|---|---|---|
| 3. 1ኛ ጢሞቴዎስ | የቤተ ክርስቲያን እድገት ስለ ሥርዓት፣ ተቋምና አስተዳደር ጥያቄ ፈጠረ። | 1ኛ ጢሞ. 2፥1—8 በመጀመሪያ ፀሎት። 1ኛ ጢሞ. 2፥9—15፤ 3፥11 የሴቶች ሚና። 1ኛ ጢሞ. 2፥1—13 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምርጫ። 1ኛ ጢሞ. 4፥1—11 አገልግሎታቸው። 1ኛ ጢሞ. 5፥6 አገልጋዮች። |
| 4. 2ኛ ጢሞቴዎስ | ክህደት ቤተ ክርስቲያንን ያሰጋት ነበር። | 2ኛ ጢሞ. 2፥22—26. ንፁሕ አኗኗር በመያዝ የማይረቡ ጥያቄዎችን አስወግዱ። 2ኛ ጢሞ. 3፥14፥15፤ 4፥2፥5 በተማራችሁት ትምህርት ፅኑ። |
| 5. ቲቶ | እሪትን ጠብቁ የሚለው ከይሁድ ወገን ያመኑት ሰዎች ያስተማሩት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መለያየትን ፈጠረ። | ቲቶ 1፥5፥13፥14 ሁሉን በሥርዓት አደራጅ፣ ደግሞም አጥፊውን ውቀስ። ቲቶ 2፥1፤ 3፥1—7 ጠንካራ ትምህርት አስተምር፣ ለሥልጣን ተገዙ፣ እርስ በርሳችሁም አንዱ ለሌላው ቸር ይሁን። |

ማሰቢያ፦ ጳውሎስ ከእስር ቤት የፃፉቸውን መልእክቶች ለመከለስ ወደ ትምህርት 53 ተመልከት

እነርሱም፦ ኤፌሶን፣ ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስና ፊልሞና ናቸው።

| ሌሎቹ መልእክቶች | የተፃፉ ምክንያቶች | አቢይ ትምህርት |
|---|---|---|
| 6. ዕብራውያን | የአይሁድ እምነት ወግ አጥባቂዎች በስነሱት ስደት ምክንያት አንዳንዶች ስደትን ለማምለጥ ወደ ኦሪት ሕግ መጠበቅ ሥርዓት ተመልሰው ነበር። | ማስጠንቀቂያዎች ዕብ. 2፥1—4፤ 3፥12፤ 5፥12፤ 9፥27፤ 10፥26፥27፤ 12፥29። አማኝ ስደት እንደሚደርስበት የታወቀ ነው፣ ዕብ. 2፥18። በእምነታችን፣ በትዕግሥታችንና በተስፋችን ያለን ብርታት ዕብ. 10፥16፥35—37። ክርስቶስ አስታራቂያችን ዕብ. 7፥25። |
| 7. ያዕቆብ | በትዕቢተኞች፤ ሀብታሞችና እኛ ጻድቅ ነን ባዮች ምክንያት ብዙ ትሑታን ክርስቲያኖች ይሠቃዩ ነበር። | እምነት በሥራ መታየት አለበት ያዕ. 1፥22። ለእግዚአብሔር ተገዙ ያዕ. 4፥7። ታገሡ ያዕ. 5፥7። እርስ በርሳችሁ ኃጢአታችሁን በመናዘዝ ፀልዩ ያዕ. 5፥16። |

| ሌሎቹ መልእክቶች | የተፃፉ ምክንያቶች | አቢይ ትምህርት |
|---|---|---|
| 8. 1ኛና 2ኛ ጴጥሮስ | ከአይሁድ ወገን ያመኑት ሰዎች መከራ። ጌታን እንኳ ሳይቀር እንዲክዱ የሚያስተምሩአቸው የሐሰተኛ መምህራን ግፊት። | ከፉውን አስወግዱ የእግዚአብሔርን ቃል ተመኙ 1ኛ ጴጥ. 2፣1፣2። ጭንቀታችሁንና ፍርሃታችሁን በክርስቶስ ላይ ጣሉት 1ኛ ጴጥ. 5፣7። ከመከራ እንዲያድናችሁ በጌታ ታመኑ 2ኛ ጴጥ. 2፣9። የክርስቶስን መመለስ የተስፋ ቃል እመኑ 2ኛ ጴጥ. 3፣10። |
| 9. 1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ | ሕብረትን ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት አድርጉ ስለ መጠበቅና የሐሰት ትምህርትን ለይቶ ስለማወቅ ነው። | በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ተመላለሱ፣ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ 1ኛ ዮሐ. 1፣7፣9። በሥራና በእውነት ተፋቀሩ 1ኛ ዮሐ. 3፣18። መናፍስትን መርምሩ 1ኛ ዮሐ. 4፣1—4። እመኑ 1ኛ ዮሐ. 5፣4፣5። ታዘዙ 2ኛ ዮሐ. ቁ. 6። በእውነት ተመላለሱ 3ኛ ዮሐ. ቁ. 3፣4። |
| 10. ይሁዳ | በኃጢአት ወደ ተሞላ ኑሮ ስለሚመራ ክህደት ነው። | ለእምነት ታገሉ ይሁዳ ቁ. 3። እምነታችሁን አንፁ ፀልዩ ትጉ ይሁዳ ቁ. 20፣21። |
| 11. የዮሐንስ ራእይ | በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኙ ብዙ የተለያዩ ችግሮች፤ መንፈሳዊ ቅዝቃዜ፤ የፍቅር ማነስ፤ የገንዘብ ፍቅር፤ ግድየለሽነትና ክህደት ነበሩ። | ክርስቶስ እንደየሥራችን ሽልማት ሊሰጠን በቶሎ ይመጣል፣ ስለዚህ ትጉና ፀልዩ! ንስሐ ግቡ ራእ. 22፣12፤ 2፣5፣25፤ 3፣11፣19። |

# ትምህርት ሰማንያ ስምንት

ከትምህርት 48-87 ካሉት ትምህርቶች የተውጣጣ ለዓመቱ የመጨረሻ አጋማሽ ለምሳሌ ያህል የቀረበ ፈተና።

## በባዶ ሥፍራዎች ሙሉ

1. ____________ ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መልእክት ይልቅ ቤተ ክርስቲያንን አብራርቶ ይገልፃታል።
2. ኤፌሶን __________ ተብላ የምትጠራው የግሪክ ጣዖት አምልኮ ማዕከላዊ ሥፍራ ነበረች።

3. ____________ በምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ሴቶች ነበሩ።

4. ቆላስይስ ክርስቶስን የፍጥረት ሁሉ ራስ አድርጐ ያቀርበዋል፤ ኤፌሶን ደግሞ ክርስቶስን በ ____________ ላይ ራስ አድርጐ ያቀርበዋል።

5. ____________ የአማኝ የክብር ተስፋ ነው።

6. በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የነበረው ችግር የ ____________ ፍላጐት ነበር።

7. በፊልጵስዩስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ችግር ____________ ነበር።

8. በቆላስይስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ችግር ____________ ነበር።

9. በተሰሎንቄ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ችግር ስለ ____________ በትክክል አለመረዳት ነበር።

10. በ1ኛና 2ኛ ጢሞቴዎስ እንዲሁም ቲቶ ሦስቱም በ ____________ ላይ ያተኩራሉ።

## አዛምድ

____________ ሀ/ ጢሞቴዎስ በምሳሌነትና በአገልግሎት ላይ ያሉት የግል ኃላፊነቶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል። — 1. ክሕደት

____________ ለ/ እውነትን በሚያውቁትና በተረዱት ሰዎች ሆን ተብሎ መካድ። አስታራቂያችን — 2. ክርስቶስ

____________ ሐ/ አቢይ ትምህርቱ ይቅርታ የሆነ መጽሐፍ። — 3. ፊልሞና

____________ መ/ የጸሐፊው ስም ያልተጠቀሰበት መጽሐፍ። — 4. ኤፌሶን

____________ ሠ/ የዕብራውያን መልእክት ማዕከላዊ አቢይ ትምህርት። — 5. 1ኛ ጢሞቴዎስ

____________ ረ/ በክርስቶስ ያለን እምነት ተግባራዊ ውጤት ያሳየናል። — 6. ይሁዳና 2ኛ ጴጥ.

____________ ሰ/ የክርስቶስን መመለስ በሚመለከት መልእክታቸው ማስጠንቀቂያና ጢሞቴዎስ ማጽናናት የሆነ ሁለት መልእክቶች። — 7. ቲቶና

____________ ሸ/ መልእክታቸው የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የሚመለከት ሁለት ቆላስይስ መልእክቶች። — 8. ኤፌሶንና

____________ ቀ/ በቤተሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት በሚመለከት ትምህርት የሚሰጡ 2 መልዕክቶች። — 9. ያዕቆብ

____________ በ/ «የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ ብሎ የሚመክረን መልእክት። — 10. ዕብራውያን

## እውነት ወይም ሐሰት

__________1/ ራዕይ የተጻፈው በጳውሎስ ነው።

__________2/ ኤፌሶን የትንቢት መልእክት ነው።

__________3/ ፊልሞና የኮበለለው አገልጋይ ነበረ።

__________4/ ኤፌሶን በጳውሎስ ዘመን በእስያ እጅግ ጠቃሚ የሆነች የንግድ ከተማ ነበረች።

__________5/ ፊልጵስዩስ ለጳውሎስ ስለተላኩለት ስጦታዎች የተጻፈ የምስጋና መልእክት ነው።

__________6/ ጳውሎስ አማኞች በመከራቸው እንዲደሰቱ ይመክራቸዋል።

__________7/ 2ኛ ተሰሎንቄ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ያስተምረናል።

__________8/ ብዙ መልእክቶች ስለ ክርስቲያን ባሕርይ ያስተምራሉ።

__________9/ የፊልሞና አቢይ ትምህርት ይቅርታ ነው።

## ምርጫ

1/ የዕብራውያን መልእክት ዓላማ

ሀ. በመከራ ውስጥ የነበሩትን ክርስቲያኖች ማበረታታት ነው።

ለ. ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን እንደተፈጸመ ለማረጋገጥ ነበር።

ሐ. የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በሚመለከት መመሪያ መስጠት ነበር።

2/ ክሕደት ማለት

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል አለማወቅ ነው።

ለ. የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት ወቅታዊነት አለመረዳት ነው።

ሐ. በሚያውቁትና በተረዱት ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል መወገዝ ነው።

3/ ዕብራውያን 7

ሀ. ጽድቅ የሚገኘ በክርስቶስ በማመን ነው ብሎ ያስተምራል።

ለ. ክርስቶስ መንግሥቱን ለማቋቋም ይመለሳል ብሎ ያስተምራል።

ሐ. ክርስቶስ እስታራቂያችን ነው ብሎ ያስተምራል።

4/ ያለፉ፣ የአሁንና የወደፊት ሁኔታዎችን የሚገልፅ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ

ሀ. የዮሐንስ ራዕይ ነው።

ለ. የያዕቆብ መልእክት ነው።

ሐ. 1ኛ ዮሐንስ መልእክት ነው።

5/ ስለ ክርስቶስ መመለስ ክርስቲያኖችን በተለይ የሚያበረታቱና የሚያስጠነቅቁ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

ሀ. ኤፌሶን፤ ቆላስይስና ፊልጵስዩስ ናቸው።

ለ. ዕብራውያን፤ ያዕቆብና ፊልሞና ናቸው።

ሐ. 2ኛ ጴጥሮስ፤ ይሁዳና 1ኛ ተሰሎንቄ ናቸው።

6/ በቆላስይስ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ችግር

ሀ. ሰብዓዊ ፍልስፍናን ከክርስቶስ ማስቀደም ነበር።

ለ. በቤተ ክርስቲያን የነበሩት ሴቶች ሥርዓት አልባ ነበሩ።

ሐ. የግሪክ ጣዖት የነበረችው የዲያና አምልኮ ነበር።

## በይበልጥ ተስማሚ ነው የምትሉትን ምረጡ፤ ሆኖም ሁለቱም ትክክል ናቸው።

1/ ሀ. እግዚአብሔር ለአማኞች መንፈሳዊ ትጥቅ ሰጥቷቸዋል፤ ስለዚህ ሰይጣንን መፍራት አያስፈልጋቸውም።
   ለ. እግዚአብሔር የሰጠውን መንፈሳዊ ትጥቅ በሚጠቀምበት ጊዜ አማኝ የይጣንን ድል ያደርገዋል።
2/ ሀ. ዮሐንስ በራዕይ ስለ ወደፊት የዓለም ሁኔታዎች እንዲፅፍ ተነግሮት ነበር።
   ለ. የዮሐንስ ራዕይ ያለፉትን፥ የአሁኑንና ወደፊት የሚመጡትን ነገሮች ይገልፃል።
3/ ሀ. ክርስቲያን ሀብታም ለመሆን ከመመኘት መጠንቀቅ ይኖርበታል።
   ለ. ሀብት ወይም ገንዘብ ኃጢአት አይደለም፤ ነገር ግን ሀብት ወይም እርሱን መመኘት እዕምሮአችንን የራሱ ምርኮኛ ሲያደርግ ያን ጊዜ ኃጢአት ይሆናል።
4/ ሀ. ክርስቲያኖች ማገልገላቸውን ሳያቋርጡ የክርስቶስን መመለስ በደስታ መጠበቅ አለባቸው።
   ለ. ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ መመለስ መደሰትና ትጉህ መሆን ይኖርባቸዋል።
5/ ሀ. መንፈሳዊ ስጦታዎች ለአማኞች የተሰጡት ለቤተ ክርስቲያን ጥቅምና ለእግዚአብሔር ክብር ነው።
   ለ. እግዚአብሕር አማኞች ማገልገል እንዲችሉ ብዙ መንፈሳዊ ስጦታዎች ይሰጣል።

## አጫጭር መልስ ስጡ

1/ በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ ለክርስቶስ የተሰጡት 3 ስሞች ወይም የተጠቀሱት 3 ሥልጣኖች ምን ምንድናቸው?
2/ ከብሉይ ኪዳን 2 የክሕደት ምሳሌዎችና ከሃዲዎቹ እንዴት እንደ ተቀጡ ጻፉ።
3/ እምነትንና ሥራን በሚመለከት የያዕቆብ መልእክት ቁልፍ ሐሳብ ምንድነው?
4/ አሮጌው ኪዳን ወይም ሕግ ሰውን ፍጹም ማድረግ የማይችለው ለምንድነው?